**DSpace Institution**

**DSpace Repository** **http://dspace.org**

Folklore/Cultural Studies Thesis and Dissertations

2014-03

# þÿ 5 & s … ` + Ê ï • e ¥ • ï s × Ü + •
# þÿ ` ï e ( ¤ ë 5 ¨ p p p ± * • u

þÿ L E - p , 5

http://ir.bdu.edu.et/handle/123456789/13284

*Downloaded from DSpace Repository, DSpace Institution's institutional repository*

ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ ፋኩሊቲ

የፎክሎር (የባህል ጥናት) ትምህርት ክፍል

የድኅረ ምረቃ መርሀ ግብር

# “ስጦታ ለማኅበራዊ ደንብ እንደ መታዘዝ መገለጫነት በደብረ ኤልያስ ከተማ ተተኳሪነት”

በፎክሎር ትምህርት ክፍል የድኅረ ምረቃ መርሃ ግብር ለሁለተኛ ዲግሪ ከፊል ማሟያ የቀረበ ጥናት

በ

ፍቅርተ አግማስ

የካቲት 2014 ዓ.ም

ባሕር ዳር
ዩኒቨርሲቲ

# ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ

## የሂዩማኒቲስ ፋኩሊቲ

## የፎክሎር (ባህል ጥናት) ትምህርት ክፍል

## የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

"ስጦታ ለማኅበራዊ ደንብ እንደመታዘዝ መገለጫነት በደብረኤልያስ ከተማ ተተኳሪነት"

ለፎክሎር የሁለተኛ ዲግሪ ለማግኘት በከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት

በ

ፍቅርተ አግማስ

አማካሪዎች

ዋልተንጉሥ መኰንን (ዶ/ር)

ዐብዩ አስማማው (ዶ/ር)

የካቲት 2014 ዓ.ም

ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ

**ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ**

**ሂዩማኒቲስ ፋኩልቲ**

**የፎክሎር (ባህል ጥናት) ትምህርት ክፍል ድኅረ ምረቃ መርሃ ግብር**

ስጦታ ለማኅበራዊ ደንብ እንደ መታዘዝ መገለጫነት በደብረ ኤልያስ ከተማ ተተኳሪነት በሚል ርዕስ በፎክሎር (ባህል ጥናት) ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ በፍቅርተ አግማስ አስማረ የካቲት 2014 የቀረበው ይህ ጥናት የዩኒቨርስቲው የጥራትና የወጥነት መስፈርት ስለማሟላቱ በፈታኞች ተረጋግጦ ተፈርሟል፡፡

አማካሪዎች

ዋልተንጉሥ መኰንን (ዶ/ር) ፊርማ-------------------

ዐቢዩ አስማማው (ዶ/ር) ፊርማ ------------------

ፈታኞች

የውጭ ፈታኝ፡- -------------------------- ፊርማ------------------

የውስጥ ፈታኝ፡- -------------------------- ፊርማ------------------

## ማረጋገጫ

ስጦታ ለማኀበራዊ ደንብ እንደ መታዘዝ መገለጫነት በደብረ ኤልያስ ከተማ ተተኳሪነት በሚል ርዕስ በፎክሎር (ባህል ጥናት) ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ፣ በሂዩማኒቲስ የፎክሎር (ባህል ጥናት) ትምህርት ክፍል፣ በፎክሎር የድኅረ ምረቃ ፕሮግራም፣ በፎክሎር የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ያቀረብኩት ይህ ጥናት ካሁን በፊት በማንኛውም አካል ያልተሰራ፣ ለማንኛውም ተቋም ያልቀረበና የራሴ ወጥ ስራ መሆኑን፤ የጠቀስኳቸው ድርሳናትም በትክክል በዋቢነት ያገለገሉና የተጠቀሱ መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም፡- ፍቅርተ አግማስ ፊርማ ______________________ ቀን ____________________

# ምስጋና

በመጀመሪያ ነጻ የትምህርት እድልን ሰጥቶ እንድማር ስላመቻቸልኝ ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲን አመሰግናለሁ፡፡ ይህ ጥናት እንዲህ ያለ ቅርጽ እና ይዘት ይዞ እንዲቀርብ ምክራቸውን በመለገስ፣ አስፈላጊ ማቴሪያሎችን በመስጠት በአጠቃላይ ውድ ጊዜአቸውን ሰውተው ያማከሩኝን ዶ/ር ዋልተንጉሥ መኰንን እና ዶ/ር ዐብዩ አስማማውን  ከልብ አመሰግናለሁ፡፡  በተጨማሪም ጽሑፉን በማረም እና ፎርማት በማስተካከል እንዲሁም ምክረሀሳቦችን በመስጠት ያገዘኝን ዶ/ር ሞገስ ሚካኤልን አመሰግናለሁ፡፡ ይህን ጥናት ለማካሄድ መረጃ በመስጠት ከዚያም አልፎ ስጦታ ተብሎ የተሰጣችሁን ዕቃ በማሳየት ለተባበራችሁኝ መረጃ ሰጪዎቼ በሙሉ ይህ ጥናት ካለ እናንተ ትብብር የሆነውን አይሆንም ነበርና በጣም አመሰግናችኋለሁ፡፡ የተጠኝውን ማህበረሰብ ባህል እና አኗኗር እንድረዳ የተለያዩ ብሮሸሮችን በመስጠት ከዚያም አልፎ ከተጠኝው ማኅበረሰብ ውስጥ ስለ ስጦታ ባህሉ መረጃ የሚያቀብሉኝን ሰዎች ጥቁምታ በመስጠት ለተባበራችሁኝ የደብረ ኤልያስ ባህልና ቱሪዝም ሰራተኞች አቶ ዮሐንስ እና ወይዘሮ ሃይማኖት ደሳለኝ በጣም አመሰግናለሁ፡፡

## *አጠቃሎ*

*የዚህ ጥናት ትኩረት ስጦታ ነው። ዋና ዓላማውም ስጦታ በደብረ ኤልያስ ከተማ ማኅበረሰብ ልማድ (ማኅበራዊ ደንብ) ውስጥ ለማኅበራዊ ደንብ ለመታዘዝ ያለውን ገጽታ መመርመር ነው። ከዋናው ዓላማ በተጨማሪ በአካባቢው ማኅበረሰብ ዘንድ ስጦታ ለመስጠት አነሳሽ የሆነውን ነገር መለየት፣ ስጦታው የተሸከመውን ትዕምርት መመርመር እና ያለውን ፋይዳ መንተንተን የሚሉ ንዑስ ዓላማዎችን አካቷል። የጥናቱን ዓላማ ለማሳካት በዋናነት ቃለመጠይቅን፤ እንዲሁም ምልከታን እና ቡድን ተኮር ውይይትን በመጠቀም መረጃውን ለመሰብሰብ ተችሏል። የተሰበሰቡትን መረጃዎች ደግሞ በገላጭ ስልት፣ አልተሪዝም፣ “ሪስፐሮሲቲ”፣ ሥነ ትእምርት/ውክልና እንዲሁም ተግባራዊ ንድፈ ሀሳቦችን በመጠቀም ተተንትነዋል። በውጤቱም ማኅበረሰቡ የወቅቶችን መፈራረቅ፣ የተለያዩ የህይወት አጋጣሚዎችን ክስተቶች እንዲሁም የልዩ ልዩ ክብረ በዓላትን መምጣት ተከትሎ እርስ በእርስ ያለውን መተሳሰብ ለመግለጽ፣ ቀረቤታን ለማሳየት፣ ደስታን ለመፍጠር እና የሌሎችን ደስታ ለመካፈል፣ ሀዘንን ለመግለጽ፣ ምርጫን እና ውዴታን ለመጠቆም፣ ለወዳጅ ያለን አክብሮት ለማሳየት፣ መልካም ምኞትን ለመግለጽ፣ ዕንግዳ ለማላመድ፣ ይቅርታን ለማግኘት፣ ምስራችን ለማብሰር፣ ውለታን ለመመለስ፣ ከአደጋ ለመጠበቅ ወዘተ. በሚሉ አነሳሽ ምክንያቶች ስጦታ የመለዋወጥ ልማድ እንዳለው ያሳያል። በዚህ ጥናት ውስጥ ማኅበረሰቡ የሚያደርገው የስጦታ ልውውጥ ወይም ልውውጡን የሚያደርግበት መንገድ ያለውን ባህል እና አስተሳሰብ፣ ሃይማኖቱን፣ መተዳደሪያ ስራውን ሲያንጸባርቅበት ተስተውሏል። በተጨማሪም ከስጦታ ደንቡ ሳያፈነግጥ ለሰዎች፣ ለፈጣሪ እንዲሁም ለረቂቅ መናፍስት የሚከውናቸው ስጦታዎች በሰጪ እና ተቀባይ መካከል አዲስ ግንኙነትን ለመፍጠር፣ ያለውን ግንኙነት ለማጠንከር፣ ለማለሳለስ እንዲሁም ለማስቀጠል ያለው ሚና ከፍተኛ እንደሆነ የጥናቱ ውጤት አሳይቷል።*

# የይዘት ማውጫ

<u>ርዕስ</u> <u>ገጽ</u>

ምእራፍ አንድ፡- መግቢያ ........ 1
1.1 የጥናቱ ዳራ ........ 1
1.3. የጥናቱ ዓላማዎች ........ 8
1.3.2. ዝርዝር ዓላማዎች ........ 8
1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ ወይም አስፈላጊነት ........ 9
1.5 የጥናቱ ወሰን ........ 9
1.6 የመስክ ስነ-ምግባር ........ 10
1.7 ያጋጠሙ ችግሮች እና የተወሰዱ መፍትሄዎች ........ 12
ምዕራፍ ሁለት፡- ክለሳ ድርሳናት ........ 13
2.1 የቀደምት ጥናቶች ቅኝት ........ 13
2.1.1 የውጪ ሀገር ጥናቶች ........ 13
2.1.2 የሀገር ውስጥ ጥናቶች ........ 16
2.2 ንድፈ ሐሳባዊ ዳራ ........ 19
2.2.1 አልተሪዝም (Alturism) ቲዮሪ ........ 19
2.2.2 መመላለስ (Reciprocity) ንድፈ ሀሳብ ........ 21
2.2.3 ሥነ ፍቺ (semiotics) ........ 24
2.2.4 ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ ---------- 25
2.3 ጽንሰ ሐሳባዊ ማዕቀፍ ........ 29
2.3.1 ማኅበራዊ ደንብ (social norms) ........ 29
2.3.2 ሀገረ ሰባዊ ልማድ ........ 31
2.3.3 ስርዓተ ከበራዎች ........ 34
2.3.4 የ ስጦታ ልማድ ........ 38
2.3.5 የስጦታ ዓይነቶች ........ 39
2.3.6 ስጦታ ለመስጠት አነሳሽ የሆኑ ምክንያቶች ........ 42
2.3.7 የስጦታ ተግባራት ........ 49
ምዕራፍ ሶስት፡- የአጠናን ስነ ዘዴ ........ 51
3.1 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ........ 51
3.1.1 ምልከታ ........ 51
3.1.2 ቃለ መጠይቅ ........ 52

3.1.3 ተተኳሪ የቡድን ውይይት ..... 53

3.2 የናሙና አመራረጥ ዘዴ ..... 54

3.3 የመረጃ መተንተኛ ዘዴ ..... 54

ምዕራፍ አራት፡- አካባቢያዊ ዳራ ..... 56

4.1 የደብረ ኤልያስ አመሰራረት ታሪክ ..... 56

4.2 የደብረ ኤልያስ መልክአምድራዊ ገጽታ እና መስህቦች ..... 57

4.3 የደብረ ኤልያስ ማህበረሰብ ዝምድ መመስረቻ መንገዶች ..... 58

ምዕራፍ አምስት፡- የመረጃ አቅርቦትና ትንተና ..... 61

5.1 በህይዎት አውራ ጎዳና ስርዓተ ከበራዎች ስር የሚገኙ ስጦታዎች ..... 61

5.1.1 በመወለድ ጊዜ ያሉ ስጦታዎች ..... 61

5.1.3 ማደግን ተከትሎ የሚሰጡ ስጦታዎች ..... 67

5.2 በጊዜ ሰሌዳዊ እና የመታሰቢያ ስርዓተ ከበራዎች ስር የሚገኙ ስጦታዎች ..... 85

5.3 በመከራ ስርዓተ ከበራ ውስጥ የሚገኙ ስጦታዎች ..... 96

5.4 የቁርባን እና ልውውጥ ስጦታዎች ..... 101

5.5 በጾም እና ፍስክ ወቅት ያሉ ስጦታዎች ..... 104

5.6 የስጦታ ፋይዳ ..... 109

5.6.1 ማህበራዊ ፋይዳ ..... 109

5.6.2 ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ..... 110

5.6.3 ባህላዊ ፋይዳ ..... 112

5.6.4 ሃይማኖታዊ ፋይዳ ..... 113

5.6.5 ስነ ልቡናዊ ፋይዳ ..... 114

ምዕራፍ ስድስት፡- ማጠቃለያ እና የይሁንታ ሀሳብ ..... 116

6.1. ማጠቃለያ ..... 116

6.2 የይሁንታ ሀሳብ ..... 118

ዋቢዎች ..... 120

አባሪ 1 ..... i

አባሪ 2 ..... iii

አባሪ 3 ..... x

## ምእራፍ አንድ፡- መግቢያ

ይህ ጥናት ትኩረቱ በደብረ ኤልያስ ከተማና አካባቢው በሚኖረው ማኅበረሰብ በሚተገበሩ ስጦታ የመስጠትና የመቀበል ልማዶች ላይ ሲሆን በይበልጥ ደግሞ ስጦታ መስጠትም ሆነ መቀበል ለማኅበራዊ ደንቦች፣ ስምምነቶችና ሥርዓቶች ከመታዘዝ አንጻር ያላቸው ገጽታ ላይ ያተኩራል፡፡

ይህ ምእራፍ የጥናቱን የመጀመሪያ ክፍል አጠቃላይ ይዘትና መዋቅር ያስተዋውቃል፡፡ በስሩ የጥናቱ ዳራ፣ አነሳሽ ምክንያቶች፣ የጥናቱ ዐቢይና ዝርዝር ዓላማዎች፣ የጥናቱ ውጤት ጠቀሜታዎች፣ የጥናቱ ወሰንና ሥነ ምግባራዊ ጉዳዮች ቀርበውበታል፡፡

### 1.1 የጥናቱ ዳራ

ስጦታ (gift) የሚለው ሐሳብ በውስጡ በጣም ሰፊ ጉዳዮችን ያካትታል፡፡ ሰዎች "ስጦታ" ለሚለው ጽንሰ ሐሳብ ያላቸው አመለካከትም ጉዳዩን እንደተረዱበት መጠን እና እንደኖሩበት ማኅበረሰብ ባህል የተለያየ አተያይ ስለሚኖራቸው ለጉዳዩ አንድ ወጥ ብያኔ ለማስቀመጥ አዳጋች ነው፡፡ የቃሉን ፍቺ በተመለከተ "ስጦታ" ማለት "መስጠት፣ ዕንካ ውሰድ ማለት፣ እጅን መዘርጋት" እንደሆነ ኪዳነወልድ (1948፣859) ይገልጻሉ፡፡ እንዲሁም ስጦታ ያለምንም ምላሽ እና ክፍያ የራስ የነበረን ነገር ለሌላ አካል ንብረት እንዲሆን ወዶና ፈቅዶ ያለምንም ካሳ ወይም ጥበቃ መስጠት እንደሆነ "something acquired without compensation." በማለት Wordweb international Dictionary (wwdictionary.com) ይገልጻል፡፡ ከዚህም የምንረዳው ስጦታ፣ የግል የሆነ ማንኛውንም ጠቃሚ ነገር ከራስ በመጣ ተነሳሽነት ለሌላ እንዲሆን መፍቀድ ወይም መስጠት እንደሆነ ነው፡፡ በተጨማሪም ስጦታ በሰጪ፣ በተቀባይ እና ለስጦታ በሚቀርበው ጉዳይ መካከል የሚከወን ስምሙ የሆነ ግንኙነት ነው በማለት Oxford Dictionary ይተረጉመዋል፡፡ "Gift is a meaningful connection between two parties has been established through the giving and receiving of something significant." ይህም የሚያስረዳው ከሰጪው ጋር አያይዞ ስጦታ አንድ ጠቃሚ ነገር በመስጠት እና በመቀበል በኩል በሁለት ወገኖች (በሰጪ እና በተቀባይ) መካከል ትርጉም ያለው ትስስር የሚፈጥር ነገር እንደሆነ ነው፡፡

ስጦታ የመስጠትና የመቀበል ባህል ብዙ መነሻ ምክንያቶች እና ዓላማዎች ያሉት ሲሆን፣ የሰው ልጅ ቀድሞ ከያዛቸው ጥንታዊ የሥልጣኔ ተግባራት መካከል አንዱ ሊሆን እንደሚችልም ይገመታል፡፡ ከጥንት ሰዎች በዋሻ ውስጥ ይኖሩ ከነበረበት ዘመን ጀምሮ

ስጦታዎች የእርስ በርስ መፈቃቀድንና አንዱ ለሌላው ያለውን በጎ ስሜትና ፍቅር ለማሳየት ያገለገሉ እንደነበር ጥናቶች ይነግሩናል፡፡ በመደብ በተከፋፈለ ሥርዓት ውስጥም የጎሳዎች ወይም የጎሳ መሪዎች የአንድ ወሳኝ ስኬት አካል ሲሆኑ ለሰሩት መልካም ሥራ እና ገድል ማስታዎሻ ይሆን ዘንድ አባላቱ አድናቆታቸውን ስጦታዎችን በማቅረብ ይገልጹ እንደነበር ይነገራል፡፡ ይኸ ገጸ በረከትም ለክስተቱ ምልክት ሆኖ ይቀመጥ ነበር (Whitingham; 2020, 2)፡፡

ያልተለመደ ቅርፅ ያላቸውን እንደ ዐለት ያሉ ቅርጻ ቅርጾችን፣ የእንስሳት ጥርሶችን፣ ከዛፍ ላይ የሚላጡ ቅርፊቶችን ወይም ከሌላው በተፈጥሮ ከሚገኝ ነገር የተሰበሰቡ ነገሮችን በስጦታ መልክ እያዘጋጁ ይሸልሙ እንደነበር የታሪክ ድርሳናት ይመሰክራሉ፡፡ የስጦታ መስጠትና መቀበል ወደ ተራቀቀ ስልጣኔ ቢያድግም፣ በአመጣጡ ግን ከረጅም ጊዜ በፊት ጀምሮ ይደረግ የነበረ የተለመደ ባህርይ ነው፡፡ የሰው ልጅ ሥልጣኔ እያበበ የእጅ መሥሪያ መሳሪያዎች መፈጠር ከጀመሩ በኋላ ደግሞ ስጦታዎች የበለጠ ግልፅ እየሆኑና ከሥልጣኔው ጋር እኩል እየዘመኑ መጥተዋል፡፡ ለምሳሌ፦ በእንስሳት ጥርስ ላይ ቀዳዳዎችን በመብሳት እና ልዩ ልዩ ድንጋዮችን በተለያዩ ቅርጻቅርጾች በማስዋብ በአንገት ላይ እና በእግር እንዲሁም በፀጉር ላይ በማስቀመጥ እንዲታዩ እና ሌሎች ብዙ ነገሮችም እንዲፈጠሩ ሆኗል፡፡

በኋላም በግብፃውያን ዘመን ስጦታዎች በተለይም ለፈርዖኖች የተበረከቱት ግዙፍ ፒራሚዶች ለቋሚ ሀብቶቻቸው ማከማቻና መጠበቂያ እንዲሆኑ ታስበው የተዘጋጁ ነበሩ፡፡ ለአምልኮ ጣዖት መፈጸሚያ፣ ለተለያዩ የእምነት ተግባራት ማከናወኛ ይሆኑ ዘንድ በዚህ መልክ እየተሰሩ መቅረብ ጀምረው ነበር፡፡ በሮማውያን ዘመንም ሰዎች እርስ በርሳቸው መልካም ዕድልና ምኞት ለመገላለጽ ሥጦታዎችን ምልክት አድርገው ይለዋወጡ ነበር፡፡ ይህም ለዘመናት የዘለቀ እና በኋላም በሁሉም የምዕራባውያን ሥልጣኔ ላይ ተጽዕኖ የአሳደረ ነገር ሆኗል፡፡ እንደነዚህ ያሉት የመልካም ዕድሎች ምልክቶች ውለታዎችን ለመሸከም እና ታማኝነትን ለማሳየት እንዳገለገሉ ታሪክ ይነግረናል (Ibid)፡፡

በመካከለኛው ዘመንም፣ ስጦታዎች የነገስታትን የግል ሞገስ ለማስጠበቅ ወይም በጦርነት ጊዜ ታማኝነትን ለማሳየት ያገለግሉ ነበር፡፡ በተጨማሪም፣ የጋብቻ እጮኞች የግል ስጦታዎች ከሳንቲሞች እስከ ውድ ማዕድናት ድረስ፣ መንጋ ከብቶች፣ ፍየሎች ወይም በጎች የመሳሰሉ ጥሎሾችን ያቀርቡ ነበር፡፡ ይህም በእኛ ሀገር እና በብዙ ባህሎች ውስጥ እንደዚህ ያሉ ጥሎሽ እና ሌሎች ተመሳሳይ የስጦታ ዕቃዎች ዛሬም አሉ (Ibid)፡፡

የሰው ልጅ ማኅበራዊ ግንኙነትና ትስስር እያደገ፣ የመገናኛና የመጠያየቂያ አውዶች እየሰፉ በመምጣታቸው፣ የስጦታ መልኩም በዚያው ልክ እየሰፋና እያደገ መጥቷል፡፡ የልደት ቀናትን እና ዓመታዊ በዓላትን በማስመልከት የመልካም ምኞት መግለጫ ሆነው የሚያገለግል ብዙ ስጦታዎች አሉ፡፡ ስጦታ ፍቅር ገላጭነቱ በሁሉም ማኅበረሰብ ዘንድ እንደመልካም እሴት አስቆጥሮት ዛሬ ስጦታ በዓለም ዙሪያ በሁሉም ባህሎች ለቤተሰብ አባላት፣ ለጓደኞች፣ ለሥራ ባልደረቦች እና ለጎረቤቶች በመስጠት የልብ መሻቶች እና መቀራረቦችን አትርፏል፡፡ በጣም በተጨናነቀ ጊዜ ውስጥ እንኳን ሰዎች በተለያዩ ምክንያቶች እና አጋጣሚዎች ለአንድ ሰው የሚሰጡትን የአሁኑን ጊዜ እንዲያገኙ የሚያስችሏቸውን ስጦታዎች በመፍጠር እና በመሸጥ ላይ ያተኮሩ ትልልቅ ኢንዱስትሪዎች ተከፍተዋል፡፡ ዛሬ የስጦታ መስጠት ባህል አሁንም በዕለት ተዕለት ክንውናችን ውስጥ ልማድ ስለሆነ በስጦታው ውስጥ ማን እንደሆንን እና በስጦታ መልክ ማስተላለፍ የምንፈልገውን መልእክት ምን እንደሆነ ለማወቅ የሚካሄዱ ምርምሮች ተደርገዋል፡፡

የስጦታ ልማድ የዳበረውና የተፈጠረው በሰው ልጅ ባህል ውስጥ ነው የሚለውን ጉዳይ የማይቀበሉና አስረጅ በመምዘዝ የሚከራከሩ ተመራማሪዎች አሉ፡፡ ከእነዚህም ውስጥ Kat (2011, 3) ስጦታ የመስጠት ሂደት ሰዎች ከመፈጠራቸው በፊት በእንስሳት ዓለም እንደነበረ እንዲህ ታስረዳለች "Even before the existence of humans, gift giving was present in the animal kingdom! Our chimpanzee ancestors have been known to give food to females in exchange for potential mating or receiving favours from others, meaning gift giving is definitely in our nature." ስጦታ የመስጠት ሂደት በሰዎች መካከል የተጀመረ ሳይሆን በእንስሳት ዓለምም ጥንት ቺምፓዚዎች ለሴቶቻቸው ምግብ ይሰጡ ነበር፡፡ በተፈጥሮ ውስጥ አብሮ ያለ ጉዳይ ነው፤ በማለት ታስረዳለች፡፡ ዛሬም በአካባቢያችን የምናገኛቸው እንስሳቶች በተለይ ዘር ለመተካት በሚያደርጉት ሂደት ውስጥ የሚያደርጋቸው ነገሮች የካትን ሃሳብ የሚያጎሉ ተግባሮች ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ ወንድ ሴቷ የምትወደውን ነገር በመስጠት ሲያሳምናት፣ ደጅ በመጥናትና ስጦታ በማቅረብ የፈለገውን ለማግኘት ሲሞክር እንመለከታለን፡፡ ለምሳሌ፦ አውራ ዶሮ እንስቷን የሚስብበት መንገድ ምግብ ጭሮ መጥራትና መጋበዝ ነው፡፡ ይህም ሀሳብ ስጦታ፣ በሰዎች ዘንድ ያለ ማኅበራዊ ስሪት ብቻ ሳይሆን ተፈጥሯዊም ያደርገዋል፡፡

በተጨማሪም፣ ስጦታን ሰዎች ለሰዎች ወይም እንስሳት የሚፈጽሙት ተግባር ብቻ ሳይሆን በሰው እና በአምላክ መካከልም የሚከወን ድርጊት ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ለዚህም ምሳሌ የሚሆነው

በክርስትና ሃይማኖት ውስጥ ትልቅ ቦታ የሚሰጠው አምላክ ሰውን ለማዳን ወደዚህ ምድር በመጣ ጊዜ ወይም እግዚአብሔር አብ አንድያ ልጁን ወልድን (ኢየሱስ ክርስቶስን) ለዓለም መዳን ሰጠ፣ በዚያን ጊዜ በቤተልሔም ሲወለድ ሰብዓሰገል (የጥበብ ሰዎች) ወርቅ፣እጣን እንዲሁም ከርቤ ስጦታ እንደሰጡት ይነገራል። እነዚህ ሶስት የጥበብ ሰዎች ኢትዮጵያውያን እንደነበሩ ስማቸውም አቦል፣ ቶና፣ በረካ ይባሉ እንደነበር ዝርዝር ታሪካቸውን (አማን፣ 2012 ዓ.ም) ላይ በስፋት ገልጸዋል። ይህም የሆነው ክርስቶስ ከመወለዱ ከብዙ ዓመታት በፊት "መኳንንት ከግብፅ ይመጣሉ፤ ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች።" መዝ 67፣31 እና "በፊቱ ኢትዮጵያ ይሰግዳሉ ጠላቶች አፈር ይልሳሉ የተርሴስ ነገስታት ስጦታን ያመጣሉ።" መዝ 71፣9 ተብሎ በቅዱስ ዳዊት የተነገረው ትንቢት በእነዚህ የጥበብ ሰዎች እንደተፈጸመ ይገልጻሉ። እንዲሁም (ኢት፦ስጦታ) (ዮጵ፦ወርቅ) ኢትዮጵያ ማለት "የወርቅ ስጦታ"፤ እጆች የተባሉት ለክርስቶስ ስጦታ ያቀረቡት ኢትዮጵውያን ጠበብት ሲሆኑ፤"ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች" የተባለው አንደኛው ምስጢሩ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ለእግዚአብሔር በየጊዜው የሚያቀርቡት ስእለት እና መባ እንደሆነ ይገልጻሉ። አማን (2012፣82) ከዚህም የምንረዳው ኢትዮጵያውያን ከጥንት ጀምሮ የስጦታ ባህል እንዳላቸው እና ስጦታቸውም በአምላክ የተወደደ እንደሆነ ነው። በአጠቃላይ ስጦታ ሰው ከሰው፣ ሰው ከአምላክ እና ሰው ከተፈጥሮ ጋር ሊለዋወጠው የሚችል ጉዳይ ነው።

አንዳንድ አጥኝዎች ከሚመራመሩበት ዘርፍ አንጻር ስጦታን የተለያየ ፍቺ ሰጥተውት እናገኛለን። ለምሳሌ፣ የስነልቦና አጥኝዎች የሰዎችን ግላዊ ማንነት ከመግለጽ አንጻር መረምሩታል። Schwartz (1967) የማኅበራዊ ጉዳይ ባለሙያዎች ደግሞ፣ ማኅበረሰቦችን ከማቀራረብ አኳያ ለሚኖረው ፋይዳ ትኩረት ሰጥተው ይመረምሩታል (Mathews 2017)። የምጣኔ ሃብት ባለሙያዎች፣ ከሚያስገኘው ኢኮኖሚያዊ ጥቅምና ቁሳዊ ፋይዳ አንጻር ይረዱታል። Camerer (1988) የህግ ባለሙያዎች፣ ስጦታን ከጉቦ ጋር አስተሳስረው ከመልካም ይልቅ የሚኖረውን አሉታዊ ጎን ትኩረት ሰጥተው ያብራሩታል። Graycar (2016) ይህም ሆኖ በስጦታ ላይ የሚደረጉ ምርምሮች በየጊዜው እየሰፉ እና እያደጉ፣ አዳዲስ እይታዎችን እያቀፉ በመሄድ ላይ ናቸው። የተለያዩ ጥናቶችም የስጦታ አገልግሎቱና ተግባሩ ብዙ እንደሆነ ያስገነዝባሉ። የመጀመሪያ ጥቅሙ በተቀባዩና በሰጪው መካከል ትስስርን ለመፍጠር ይረዳል የሚለው ነው። ሌላኛው ደግሞ፣ ስጦታ ለማህበራዊ ደንብ መታዘዝን ማሳያ፣ ወዳጅነትን ማጠናከሪያ እና ለሰው ያለን ፍቅር ማሳወቂያ Carrier (1990)፣ ውዴታን ወይም ፈቃድን

መግለጫ እና ምርጫን መጠቆሚያ Schwartz (1967)፣ ማኅበራዊ ግንኙነትን ማደሻ፣ የልብ መሻቶች፣ ራስን በሌላው ሰው አስተሳሰብ ውስጥ ማግኘትን እና አድናቆት መጠቆሚያ Belk (1993) አድርገው የሚረዱት በርካቶች ናቸው፡፡

ጉዳዩ ሰዎች አብሮ በመኖር ሂደት ውስጥ የፈጠሩት እና ቡድናዊ አከዋወን ያለው በመሆኑ፤ ከፎክሎር እይታ አንጻርም ሊመረመር እንደሚችል ማሳየት የዚህ ጥናት አንዱ ዓላማ ነው፡፡ ፎክሎር ቡድንን እና የቡድኑን የጋራ ሃሳብና ጥበብ እንደሚያካትት ሁሉ ስጦታም በሰጪ እና በተቀባይ እንዲሁም ለስጦታ በሚቀርበው ነገር መካከል የሚኖርን የጋራ ገጽታ የሚመረምርና ለክዋኔው ሁለትና ከዚያ በላይ መሆንን የሚጠይቅ ነገር ነው፡፡ በዚህ ግንኙነት ውስጥ የስጦታ ምርጫ፣ ደንብ፣ የጋራ ፍላጎት ወዘተ. እንደ የጋራ ጥበብ (lore) አብሮ የሚጠና፣ የማኅበረሰቡ ባህል እና ማንነት በስጦታው አማካኝነት የሚታይበት የጋራ ጥበብ ነው፡፡

የስጦታው አከዋወን  በግል ወይም በቡድን ሊሆን ይችላል፡፡ በስጦታ እሳቤ  ውስጥ የሰጪው እና የተቀባይ መኖር ብቻ ጉዳዩን ምሉዕ አያደርገውም፡፡ ስጦታ ያለውን ቅርጽ ለማግኘት አንዱን ሰጪ ሌላውን ተቀባይ የሚሆንበት ጠቃሚ ነገር  ያስፈልገዋል፤ ይህ ጠቃሚ ነገር አብዛኛውን ጊዜ ሁለት አይነት አቀራረብ ይኖረዋል፡፡ ወይም ሰጪው አካል ስጦታውን  በሁለት መንገዶች ለተቀባይው ሊያቀርብ ይችላል፡፡ የመጀመሪያው በሚታይ መልኩ፣ ሊጨበጡ፣ ሊቀመሱ ፣ ሊሸተቱ የሚችሉ ቁሶችን ሲሆን ሁለተኛው በቁስ የማይገለጹትን ያካትታል፡፡ ለምሳሌ፦ሃሳብን፣ መልካም ፈቃድን (ልብን)፣ ነጻ ጉልበትን ወዘተ. እንደ ስጦታ ሊያቀርብ ይችላል፡፡ ከስጦታ ጋር አብሮ ሊነሳ የሚገባው ሌላ ጉዳይ የስጦታው ዓላማ ነው፡፡ ስጦታ ስምሙ የሆነ ግንኙነት እና ግንኙነቱን የሚያስቀጥልበት መንገድ ነው፡፡ ነገር ግን ማንኛውንም ጠቃሚ ነገር በመስጠት እና በመቀበል መካከል ያለ ግንኙነት ሁሉ ስጦታ ነው ለማለት አይቻልም፡፡ ምክንያቱም ስጦታ ከራስ በተገኘ ንብረት እና ከራስ በመጣ ተነሳሽነት ከተቀባይ አዳች ነገር ሳይጠብቁ፤ ያለምንም ምላሽ (return) መስጠት ላይ የሚተኩር መሆኑ ነው፡፡ ለዚህም ምሳሌ ሊሆነን የሚችለው በሙስና ወይም ጉቦ (corruption or bribe) እና በስጦታ መካከል ያለውን ተመሳስሎ እና ልዩነት ነው፡፡ ተመሳስሏቸው ሁለቱም በሰጪና በተቀባይ መካከል ትስስር ሊፈጥር የሚችል አንዳች ጥቅም ያለው ነገር የመስጠትና የመቀበል ሂደት ነው፡፡ በጉቦ እና በስጦታ መካከል ስላለው ልዩነት ግን አንድ የአንትሮፖሎጂ ጥናት ግለሰቦች ስጦታን በሚለዋወጡበት ጊዜ ማኅበራዊ ትስስር ይጠናከራል እንዲሁም ተደጋጋፊነት ይፈጠራል፡፡ ስጦታውም ከግል ሀብት የመጣ ከሆነ በግልጽ ስጦታ ነው፡፡ ስጦታ ከተሰጠ በኋላ ምላሽ ግድ ከሆነ፤ የሚመለሰው ነገርም ከድርጅት

ከሆነ ወይም "ከራስ ኪስ" ይልቅ የመንግሥት ሀብት ከሆነ ምናልባት ጉቦ ሊሆን ይችላል:: በማለት ያስረዳል "When individuals exchange gifts social bonds are strengthened and reciprocity is created. If the gift and the reciprocation both come from private resources it is clearly a gift. If what is reciprocated after a gift is given comes from an organization, or is a government resource rather than from ones own pocket then it is most likely a bribe." Graycar (2016) ከዚህም የምንረዳው ስጦታ የግል ከሆነ ንብረት መነሻ ያለው ነው፣ ግልጽ ነው፣ ስጦታ ለሚበረከትለት ሰው ምላሽ (return) ብዙ ጊዜ አይጠበቅም ሊቀርም ይችላል::

ስጦታዎች እንደ አካባቢው ባህል እና ልማድ ሲተገበሩ ትርጉማቸው ይበልጥ ይጠነክራል:: እንደ ፎክሎርም የተመረመረው ጉዳይ ስጦታ እንደ መታዘዝ ያለው ደንብ እና ከስጦታው ጀርባ ያለው የማህበረሰብ አስተሳሰብ ነው:: ማህበረሰቡ የስጦታ ልማዶቹን በአዎንታዊ ጎናቸው ብቻ አይረዷቸውም:: አንዳንድ ጊዜም ከማታለል፣ ከሹፈት፣ ከጉቦ፣ ከውርደት፣ የበላይ ከመሆን፣ ከማሰናከል፣ ለመጎዳት ወዘተ. ሊወስዳቸው እንደሚችል Komter (2007) እንዲህ ሲል ይገልጻል:: "Gifts can be used to manipulate, flatter, bribe, deceive, humiliate, dominate, offend, hurt and even kill." ስለዚህ ስጦታ ስምሙ የሆነውን ትርጉም የሚያመጣው የሰዎችን አብሮነት፣ ማህበራዊነት እና መልካም የሆነ ግንኙነትን መመስረት ላይ አላማውን ሲያደርግ ነው::

ስጦታ መቀያየር በብዙ ማህበረሰቦች ዘንድ የተለመደ ተግባር እንደሆነ በዝግመተ ለውጥ ሞዴል ውስጥ በግንኙነት መጀመሪያ ስጦታዎች የመስጠት ማህበራዊ ልማድ ወደ መተማመን እና መተባበር ሊመራ እንደሚችል H. Lorne (1997) እንዲህ ይገልጻሉ::"Gift giving is a practice common to many societies. In an evolutionary model the social custom of giving gifts at the beginning of a relationship can lead to trust and cooperation." በዚህ ጥናትም በተጠኘው ማኅበረሰብ ዘንድ ያለውን የስጦታ ልውውጥ አነሳሽ ምክንያቶች በመዘርዘር ፣ እንደ ማህበረሰቡ ደንብ ስጦታ ምንድን ነው? ከስጦታው ጀርባ ያለው ትርጉም ምን ይመስላል? እንዴትስ ይቀበለዋል? የሚለውን ጉዳይ በስፋት ተዳሷል:: በዚህም ውስጥ ስጦታ ማኅበራዊ ደንቦችን ጠብቆ በመፈጸም በኩል ወይም የአካባቢውን ባህል ጠብቆ እንዴት እንደሚከወን የደብረ ኤልያስ ከተማ ማኅበረሰቦች ላይ በማተኮር ማን ለማን ይሰጣል፣ የትኛው ስጦታ ያስመሰግናል፣ የትኛውስ ያስነቅፋል፣ ስጦታው ለምን ተመረጠ፣ በስጦታው አማካኝነት የሚገኘው ውጤት እስከምን ይደርሳል ወዘተ. የሚሉ ጥያቄዎች በማንሳት ስጦታን ለማህበራዊ ደንቦች የሚኖርን

ፋይዳ ተመርምሯል። ማህበረሰቡ ስጦታን መቼ፣ የት፣ እንዴት፣ ማን፣ ለማን፣ በምን አይነት ሁኔታ እና ለምን ይሰጣል? የሚለውን የስጦታ ልምድ ስንመለከት በማኅበራዊ ህይወት ውስጥ የሚያደርጋቸው የስጦታ ልውውጦች የማኅበረሰቡን ባህል እና የአኗኗር ዘይቤ ለማሳየት ተሞክሯል።

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች

ከስልጣኔ እና ዘመናዊነት ጋር በተያያዘ ትውልዱ የራሱን ትቶ የፈረንጆቹን በዓል በተለይም በገና በዓል ወቅት የሚያከብሩትን የስጦታ ልውውጥ በየሚዲያውና ባገኘው አጋጣሚ ሲያገዝፍ የሃገሩን ነባር እሴት ከመዘንጋቱም ባለፈ "እኛ የስጦታ በዓል የለንም!" ከሚል መደምደሚያ የደረሰ ይመስላል። ከዚህ አንፃር በተለይ በወጣቱ ዘንድ በተጨባጭ ያለውን የዕውቀት ክፍተት ለመሙላት  እንደ አንድ ማሳያ ይሆናል የሚል  ሀሳብ ጥናቱን ለማድረግ አነሳስቶኛል።

በአሰሳ ንባብ ወቅት እንደተገነዘብኩት ከዚህ በፊት ስጦታ እንደ ፎክሎር የተለያዩ ማኅበረሰቦች ልዩ ልዩ ክዋኔዎች በሚጠኑበት ጊዜ አብሮ ይነሳል እንጂ ዋና ርዕሰ ጉዳይ ሆኖ፤ ለብቻው ተነጥሎ ብዙ አልተመረመረም። ስጦታ የከዋኞቹን ማንነት በመግለጽ በኩል ያለው ሚና ብዙ ትኩረት አልተሰጠውም። ጥናቱ በሚደረግበት ደብረ ኤልያስ አካባቢ በሚኖረው ማኅበረሰብ ልማድ ውስጥ ደግሞ ማኅበረሰቡ የተለያዩ ባህላዊ፣ ማኅበራዊ፣ ሃይማኖታዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ወዘተ. ጉዳዮቹ ውስጥ ስጦታ የመለዋወጥ ልማድ ያለና ከፍ ያለ ማኅበራዊ ዋጋ ይሰጠዋል። ይህ ልማድ እንደ ጥናት ዘርፍ በሌሎች ሀገሮች እና ትምህርት ክፍሎች ለምሳሌ፡ በማኅበረሰብ ጥናት፣ በስነ ሰብዕ፣ በቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ወዘተ. ትልቅ ትኩረት የተሰጠው እና በሰፊው የተዳሰሰ ርእስ ቢሆንም፣ ይህንን የተመለከተ ብዙ ባህል እና ስጦታ የመስጠትና የመቀበል ምክንያቶች እያሉን በእኛ ሀገር ትኩረት ሲደረግበት አይታይም። ከዚህም የጥናት ክፍተት በመነሳት በአካቢውም በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ ጥናት ስላልተደረገ፣ ጉዳዩን ለመመርመር ፍላጎት አድሮብኛል። ስጦታ ካሉት በርካታ ፋይዳዎች መካከል የእርስ በእርስ ግንኙነትን መፍጠር፣ ማጠናከር እና ከዚያም አልፎ የሻከረ ግንኙነትን ማለሳለስ፣ በግጭት ሰበብ ላልቶ ወይም ተቋርጦ የነበረን ግንኙነት ሰላማዊ ማድረግና ተቋርጦ ወደነበረው ግንኙነት መመለስ፣ ጠንካራውን ማበረታታት ወዘተ. ናቸው። በአሁኑ ጊዜ ከዘመናዊነት ጋር ተያይዞ የሚመጡ የማኅበረሰብ ባህል መበረዞች አሉ። ስለዚህም፣ የጉዳዩን መልካም ጎኖች በማውጣት የሚመለከተው የማኅበረሰብ ክፍል ባህሉን እንዲያስቀጥል እና ትኩረት እንዲያደርግበት ለማመላከት እንዲሁም ከዚህ አንጻር ጠቀሜታዎቹን አጉልቶ በማውጣት የማኅበረሰቡን ሰላም

እና ዘላቂ አብሮነት ለማስቀጠል አስተዋጽኦ እንዳለው በባህሉ ውስጥ ያለውን ሚና ማስገንዘቡ አስፈላጊ ሆኖ ስለታየኝ ጥናቱን ለማድረግ ሌላ ምክንያት ሆኖኛል፡፡

በሌሎች ሀገሮች ስጦታን በተመለከተ ከተጠኑ ጥናቶች ለምሳሌ፦ ምዕራባውያን ስጦታ ለመለዋወጥ በሰፊው የሚያተኩሩበት ቀን አለ፡፡ እርሱም አዲስ ዓመት ወይም ገና ሲሆን በዚህ ዙሪያ ብቻ በርካታ ጥናቶችን ከተለያየ እይታ አንጻር ተመርምረው ለማንበብ ችያለሁ፤ ስጦታ በመስጠት የሚገኙትን ጥቅሞች እና ከስጦታ ጀርባ ያለውን ስነልቡና በተመለከተ Schwartz (1967፣ 69) በተለያዩ አተያዮች ጥናት አድርገዋል፡፡ በርግጥ ጉዳዩ ጥናት የሚፈልግ ቢሆንም ስጦታ ማለት በብልጭልጭ ወረቀት ተጠቅልሎ የሚሰጥ ነገር እንደሆነ ብቻ የምናስብ እንኖራለን፡፡ ነገር ግን በኢትዮጵያውያን ባህል ዘመን ሲለወጥ (በአዲስ ዓመት) እንቁጣጣሽ/አደይ አበባ/ በህጻናት እና በልጃገረዶች የአበባ እና እንግጫ ስጦታ የሚጀመር ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ሌሎች ማህበራዊ፣ ሃይማኖታዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ ወዘተ. ጉዳዮች ውስጥ ሁሉ ስጦታ የመለዋወጥ ልምዶችን በስፋት እናገኛለን፡፡ ኢትዮጵያውያን ከሚታወቁባቸው በርካታ እሴቶች መካከልም አንዱ ለአንዱ የሚያደርገው በጎነት እና የመረዳዳት የመተጋገዝ ተግባር እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ይህ ሁሉ እንዳለ ሆኖ ጉዳዩ (የመስጠት ልማዱ) እንደ ጥናት ከዚህ በፊት ትኩረት ተሰጥቶት አልተዳሰሰም፡፡ በዚህም ጥናት ደብረ ኤልያስ ላይ ጥናት በማድረግ በአካባቢው የሚገኘውን ስጦታ የመለዋወጥ ልማድ በማሳየት፣ ስጦታን ከግለሰብ አልፎ በማኅበረሰብ ባህልም ውስጥ እንዳለ እና ስጦታ ለማኅበረሰቡ ደንብ ያለውን ሁለንተናዊ ገጽታ በማሳየት ጉዳዩ እንደ ፎክሎርም ትኩረት ተሰጥቶት ሊጠና እንደሚችል የመጠቆም ሀሳብ ስላለኝ ይህን ጥናት ለማድረግ ተጨማሪ ምክንያት ሆኖኛል፡፡

## 1.3. የጥናቱ ዓላማዎች

### 1.3.1. ዋና ዓላማ

በምስራቅ ጎጃም ዞን ደብረ ኤልያስ ከተማ የሚገኙ ማኅበረሰቦችን ስጦታ የመለዋወጥ ልማድን በመመርመር ለማኅበራዊ ደንቦች መታዘዝን በማጠንከር በኩል ያለውን ሚና ማሳየት የዚህ ጥናት ዋነኛ ዓላማ ነው፡፡ ጥናቱ የሚከተሉት ንኡሳን ዓላማዎች አሉት፡፡

### 1.3.2. ዝርዝር ዓላማዎች

- ስጦታ ለመስጠት አነሳሽ የሆኑትን ነገሮች መለየት፤
- ስጦታዎች የተሸከሙትን ትዕምርት መመርመር፤

- ስጦታዎች ያላቸውን ሁለንተናዊ ፋይዳ ማብራራት ናቸው፡፡

## 1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ ወይም አስፈላጊነት

ይህ ጥናት በታለመው መልክ መጠናቱ ያስገኛቸዋል ተብለው የሚታሰቡ በርካታ ጥቅሞች አሉት፡፡

- በደብረ ኤልያስ አካባቢ የሚኖሩ ማኅበረሰቦች የተለያዩ ጉዳዮች ተከትሎ የሚያደርጉትን ስጦታ የመለዋወጥ ልማድ፣ አነሳሽ ምክንያቶች፣ የስጦታ ፋይዳዎች እና የስጦታዎችን አካባቢያዊ ትርጉም ሊያሳዉቅ ይችላል፡፡
- በስጦታ እና በዚህ ጥናት ስር ከሚጠቀሱ ተዛማጅ ሀሳቦች ጋር በተያያዘ ጥናት ለማድረግ ለሚነሱ ሌሎች አጥኚዎች ለንጽጽር ጥናት ሊጠቀሙበት እንዲሁም እንደ መነሻ ሀሳብ ሊጠቀሙበት ይችላሉ፡፡
- በዚህ ርዕሰጉዳይ ዙሪያ በሚነሱ ሀሳቦች አማካኝነት አብዛኛው ሰው ለስጦታ ያለውን እይታ ከፍ እንዲል መንገድ ሊጠቁም ይችላል፡፡ ይህም ሲባል ሰዎች እርስ በእርስ ከሚሰጣጡት ስጦታ በተጨማሪ በማኅበረሰብ ወይም በቡድን የሚታወቅና የሚተገበር የስጦታ ልማድ እንዳለ ያስገነዝባል፡፡
- በስጦታ አማካኝነት የተለያዩ ማኅበራዊ፣ ሃይማኖታዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ጉዳዮችን ተከትሎ የሚደረጉ ማኅበራዊ ክንውኖች እንዴት እንደሚገለጹ እና በስጦታው በኩል ያለውን የማኅበረሰብ ምንነት ሊያሳይ ይችላል፡፡

## 1.5 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በደብረ ኤልያስ ወረዳ ውስጥ ከሚገኙ 16 የገጠር ቀበሌዎች እና 4 ታዳጊ ከተማዎች ውስጥ አንዱ በሆነው በደብረ ኤልያስ ከተማ ላይ አተኩሯል፡፡ ይህም የተመረጠበት ምክንያት በወረዳው ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ የገጠር ቀበሌዎች መገናኛ ከተማ ስለሆነ መረጃው ሁሉን ያካተተ እንዲሆን እና የአካባቢው ማኅበረሰቦች በተሻለ ለማግኘት ስለሚረዳ ነው፡፡ ከርዕሰ ጉዳይ አንጻርም ሃገረሰባዊ ልማድ ስር ከሚካተቱ የወቅታዊ ወይም ካላንደሪካል እና የህይወት ምዕራፍ ሽግግር ክዋኔዎች ውስጥ የሚሰጡ ስጦታዎች ላይ የሚያተኩር ይሆናል፡፡ ይህም የተመረጠበት ምክንያስ ከሌላው በተሻለ በእነዚህ ክዋኔዎች ውስጥ ስጦታ ለማኅበራዊ ደንቦች ያለው መታዘዝ ወይም የስጦታ ህግ ጎልቶ ስለሚታይ ነው፡፡ ማኅበረሰቡ ስጦታን እንዴት ይረዳዋል፣ እንዴትስ ያስተናግደዋል ወይም ለምን ይጠቀምበታል፣ ስጦታ ብሎ የሚያቀርበው

ነገርስ በዓይነት እና በመጠን እንዴት ያስቀምጠዋል፣ የስጦታ ጠቀሜታውስ እስከምን ድረስ ነው ወይም ምን ይመስላል፣ በስጦታው ውስጥ የሚያስተላልፋቸው መልዕክቶችስ ምን ይመስላሉ ወዘተ. የሚሉትን ጉዳዮች አካቷል። ተጠኚው ማኅበረሰብ ስጦታ የሚለዋወጥበት የራሱ የሆነ መቼት እና ምክንያት ያለው ሲሆን፣ ይኸውም ጊዜን፣ ሁኔታን እና ቦታን የሚያካትት ነው። ጊዜ ሲባል የወቅቶች መፈራረቅን፣ ከዘመን ዘመን መሸጋገርን፣ የምርት መድረስን የተለያዩ በዓላትን ወዘተ. ተከትሎ የሚለዋወጧቸው ስጦታዎችን ይመለከታል፤ በተጨማሪም ከስጦታ መለዋወጫ ምክንያቶች ውስጥ በጊዜው የነበረን የህይወት ክስተቶችን ተከትሎ የሚከወነውንም ያካትታል።

ከእነዚህ ውስጥ መወለድ፣ ማደግን እና መሞትን ተከትሎ ሰዎች ለሰዎች፣ ለአምላካቸው እና በቡድንም የሚያደርጉት ስጦታ አለ ይህን አስመልክቶ "የሰው ልጅ በሚኖርበት ዘመኑ የሚያልፋቸውን ተፈጥሮአዊ ሁነቶች መነሻ በማድረግ ለምሳሌ ከመረገዝ፣ ከመወለድ፣ ወጣት ከመሆን ጋር ተያይዞ ማግባት፣ ማርጀት፣ በመሞት ጊዜ እና በተወሰኑ የእድሜ ደረጃዎች ሲደርስ፣ ወዘተ የሚከወኑ ስርዓቶች ከህይወት አውራ ጎዳና ስርዓቶች የሚመደቡ" እንደሆኑ ካትሪን (1977፣95) ትገልጻለች። ይህ ጥናትም ከህይወት አውራ ጎዳና ስርዓቶች እና ወቅቱን ተከትለው ከሚከወኑ በዓላትን ወይም ሌሎች ከበራዎች ጋር ተያይዞ የሚደረጉ ስጦታዎች ላይ በማተኮር ማህበረሰቡ ያለውን የስጦታ ልማድ፣ ትዕምርት በዚያም ውስጥ ያለውን የማህበረሰብ የጋራ አስተሳሰብ መርምሯል። በተጨማሪም ስጦታዎቹ ግንኙነትን በመፍጠር፣ በማጠናከር፣ በማስቀጠል እና በማለሳለስ በኩል ያላቸው ሚና ምን እንደሚመስል ተመልክቷል።

## 1.6 የመስክ ስነ-ምግባር

የመስክ ስነምግባር ማለት በምርምር ወቅት አጥኚው ለመረጃ ሰጪዎች እና ለራሱ ምቹ የሆኑ መንገዶችን የሚፈጥሩ አካሄዶችን የመከተል እና አላስፈላጊ ነገሮች ደግሞ የመተው ሁኔታ ነው። "Research ethics deals with how we treat those who participate in our studies and how we handle the data after we collect them." (Vanderstop & Johnston, 2009;12) "የምርምር ስነ-ምግባር በጥናቶቻችን ውስጥ የሚሳተፉትን እንዴት እንደምንይዝ እና እንዴት መረጃ እንደምንሰበስብ ይመለከታል" በማለት ይገልጻሉ። በጥናት ወቅት አጥኚው የጥናት እና ምርምር ስነምግባሮችን አክብሮ በሚጓዝበት ሁኔታ ችግሮችን ቀድሞ መከላከል አሊያም መቀነስ ያስችለዋል።

አካሄዶቹም የተጠኝውን ማህበረሰብ ባህል የጠበቁ መሆን አለባቸው፡፡ ይህን በተመለከተ አባንዶ (2019) "ምርምር እውቀትን ለመፍጠር በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ወደ አዳዲስ ግንዛቤዎች፣ ግኝቶችና ፈጠራዎች ይመራል፡፡ በዚህም ለህብረተሰብ ልማት አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡ ይህ እንዲሆን እሴትን በጠበቀ መልኩ ጥራት ያለው እንዲሆን በታማኝነትና በስነ ምግባር ሊሰራ ይገባል፡፡"በማለት ይገልጻል፡፡ የባህል አጥኝ ደግሞ ከሌላው ተመራማሪ በተለየ መልኩ የተጠኝውን ማህበረሰብ ባህል ጠንቅቆ መረዳት እና ማክበር በተቻለ መጠንም ማህበረሰቡን መስሎ መረጃ መሰብሰብ ይጠበቅበታል፡፡ ይህ ጥናት በሚደረግበት ወቅት በሚቻለው ሁሉ የመስክ ስነምግባሮችን እና የአካባቢውን ባህል በጠበቀ መልኩ አስፈላጊውን መረጃ ለመሰብሰብ የሚከተሉትን ጉዳዮች በአትኩሮት ተግብሬአለሁ፡፡

- ✓ መረጃ ለመሰብሰብ በምገኝበት ቀን የሚያስፈልጉኝን የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ደህንነት አረጋግጬ ይዤ በቀጠሮ ቀን ተገኝቻለሁ፡፡
- ✓ በመረጃ ስብሰባ ወቅት የመረጃ ሰጪዎችን ፈቃድ ቀድሜ ጠይቄ ስምምነታቸውን በቃል አረጋግጫለሁ፡፡
- ✓ ተጠኝዎች አስፈላጊውን መረጃ እንዲሰጡኝ የጥናቴን አላማ እና ውጤት በማብራራት አስረድቼአቸዋለሁ፡፡
- ✓ የፎቶ፣ የድምጽ እና የቪድዮ መረጃወችን ቀረጻ ያደረግሁትም ለጥናቴ አስፈላጊነታቸውን በማስረዳት እና ፈቃደኝነታቸውን በማረጋገጥ ነው፡፡
- ✓ መረጃ በምሰበስብበት ወቅት በንግግር በአለባበስ እና የማህበረሰቡን ልማድ በማክበር ከተጠኝዎች ጋር ለመስማማት ወይም ለመቀራረብ ሞክሬአለሁ፡፡
- ✓ መረጃ ሰጪዎችን በምጠይቅበት ወቅት የግል ፍላጎታቸውንም ለማክበር ሞክሬአለሁ፡፡ ለምሳሌ፦ ከምርምር ጥያቄዎቼ ውስጥ እንደ ማጠቃለያ ጥያቄ "እርስዎ ምን አይነት ስጦታ ሰጥተው ያውቃሉ?" የሚል ጥያቄ አንስቼ ነበር፡፡ ሆኖም አንዳንድ ተጠኝዎች እንደ ባህሉ የሚደረገውን እንጂ የግል ስጦታውን ድብቅ አድርገው "የሰጡትን መናገር አይገባም" የሚል ምላሽ ሰጥተውኛል፡፡ በዚህ ምላሽም የስጦታን ሚስጢራዊ ጎን ተረድቼበታለሁ እንጂ ተጠያቂዎቼ እንዲመልሱልኝ አላስገደድሁም፡፡
- ✓ የቡድን ተኮር ውይይት በማደርግበት ወቅት ተጠኝዎቼን በማመስገን እና እንደ አካባቢው ባህል ፈቃዳቸውን ጠይቄ የተለመደውን ባህላዊ መጠጥ "ጠላ" በመጋበዝ ለመወያየት ችያለሁ፡፡ ይኸውም ተሰብስቦ መወያየት ከቃለ መጠይቅ ረዘም ያለ ጊዜ

ሊወስድ ስለሚችል  መሰልቸትን ለመቀነስ ጥሩ ይሆናል ብዬ በማሰብ ሲሆን ውጤቱም የተሳካ ሆኖልኛል፡፡

## 1.7 ያጋጠሙ ችግሮች እና የተወሰዱ መፍትሄዎች

በመረጃ ስብሰባ ወቅት አብዛኛው ተጠኝዎች ስጦታን ድብቅ የማድረግ እና "የሰጡት አይነገርም" የሚል ልማድ ያላቸው ሆነው በማግኘቴ ስለ ስጦታ በቀላሉ ቃለመጠይቅ ለማድረግ ችግር ሆኖብኝ ነበር፡፡ ነገር ግን የጥናቱን ጥያቄዎች ለስጦታው አነሳሽ የሆኑ ምክንያቶችን በማንሳት ለምሳሌ፦ ክብረ በዓላትን በማንሳት በዚህ ክብረ በዓል ምን ይሰጣል? የዘመድ እና የባዕድ ስጦታ መሰረታዊ ልዩነቶች ምንድን ናቸው? ወዘተ. እያልሁ በማስረዳት በምልከታ ወቅት ያየኋቸውን ስጦታዎችንም በማንሳት ምክንያታቸውን በመጠየቅ እና ጥያቄውም ግላዊ ሳይሆን እንደ ማኅበረሰቡ ወግ ያለውን የአካባቢውን የስጦታ ደንብ  ለማወቅ እንደሆነ አስረድቼ መረጃውን በዝርዝር እንዲነግሩኝ ለማድረግ ሞክሪያለሁ፡፡

## ምዕራፍ ሁለት፡- ክለሳ ድርሳናት

በዚህ ክፍል የቀደምት ጥናቶች ቅኝት፣ ንድፈ ሐሳባዊ እና ጽንሰ ሐሳባዊ ዳራ ቀርበዋል፡፡ በቀደምት ጥናቶች ቅኝት ውስጥ ከስጦታ ጋር በይዘት ተቀራራቢ የሆኑ ሦስት የውጭ ሀገር እና ስጦታን በንዑስ ርዕስነት ያነሱ ሁለት የሀገር ውስጥ የቀደምት ጥናቶች፣ ንድፈ ሐሳባዊ ዳራ ውስጥ ደግሞ ከጥናቱ መረጃዎች እና ከጥናቱ ዓላማ አንጻር የተመረጡ ስምሙ የሆኑ አራት መተንተኛ ቲዎሪዎች አተያይ ተዳስዋል እንዲሁም በጽንሰ ሐሳባዊ ማዕቀፍ ውስጥ ስለ ማህበራዊ ደንብ፣ ስለ ልማድ፣ በልማድ ውስጥ ስለ ስርዓተ ከበራ፣ ፌስቲቫል እና የህይወት አውራ ጎዳና ስርዓቶች፣ ስለ ስጦታ አቀራረብ እና ዓይነቶች እንዲሁም ከስጦታ ጋር ተቀራራቢነት ያላቸው ሀሳቦች የተለያዩ ምሁራንን አተያዮችን በማስረዳት ቀርቧል፡፡ በምንነት እና ባህርይ ተካቷል፡፡

### 2.1 የቀደምት ጥናቶች ቅኝት

በዚህ ንዑስ ክፍል ውስጥ ከሚጠናው ርዕሰ ጉዳይ ጋር በይዘት ተቀራራቢ የሆኑ ስጦታን በተመለከተ በተለያዩ ትምህርት ዘርፎች የተካሄዱ ሶስት የውጭ ሀገር ምርምሮች እና ከሀገር ውስጥ ደግሞ ስጦታን በንዑስ ርዕስነት አቅፈው የያዙ ሁለት ጥናቶች በተዛማጅነት ቀርበዋል፡፡ እነርሱም፦ ከውጪ በMauss 1924 G.C, Social Anthropology ጥናት "The gift Forms and Functions of Exchange in Archaic Societies."፣ በSchwartz, 1967 G.C "The Social Psychology of the Gift" እና Aafke Komter and Wilma Vollebergh 1997 G.C "Gift giving and the Emotional Significance of Family and Friends." እና ከሀገር ውስጥ ሙሉቀን የኔሰው 2010 ዓ.ም "የለውጥ ሽግግር በባሶሊበን ማህበረሰብ ባህላዊ የሠርግ ስርዓት" እንዳሁም ሉባባ አህመድ 2012 ዓ.ም "በኢሉ አባቦር ዞን በዶረኒ ወረዳ ድንግልናቸውን ጠብቀው ለትዳር ለበቁ ሴቶች የሚደረግ ሥርዓት ትንተና" የሚሉ ናቸው፡፡ በዚህ የጥናት ክፍልም በተዛማጅነት የቀረቡት ጥናቶች በዋናነት ስጦታን ከምን አንጻር መርምረውታል፣ ስጦታ በስነልቡና አጥኝዎች፣ በማህበራዊ ሳይንስ፣ በባህል አጥኝዎች፣ በንግድ ሰዎች ምን መልክ እንዳለው፤ ከዚህ ጥናት ጋር ያላቸው ተመሳስሎ እና ልዩነት ምን ይመስላል የሚሉ ጉዳዮች ተዳሰውበታል፡፡

#### 2.1.1 የውጪ ሀገር ጥናቶች

በተዛማጅነት የቀረበው የመጀመሪያው ጽሑፍ እ.ኤ.አ በ1924 በፈረንሳዊው አንትሮፖሎጂስት እና ሶሺዮሎጂስት ማርሴል ማውስ የተደረገ በጥንታዊ ማኅበራት ውስጥ የልውውጥ ቅጾች እና ተግባራቸው ላይ ያተኮረ የሶሻል አንትሮፖሎጂ ጥናት ነው፡፡ ማውስ ብዙውን ጊዜ ዘመናዊ

የፈረንሳይ አንትሮፖሎጂ አባት ተደርጎ ይወሰዳል። ይህ ጥናት በፈረንሳይ ቋንቋ የተሰራ ሲሆን ለተዛማጅነት የተጠቀምሁት Gunnison በ1966 ወደ እንግሊዝኛ የተረጎመውን ነው። ማውስ በጥንታዊ ማኅበራት ውስጥ የልውውጥ ቅጾች እና ተግባራት በሚል "በጥንት" ማኅበረሰቦች ውስጥ የሚያተኩረው በቡድኖች መካከል ያለ የስጦታ ልውውጥ በሰዎች መካከል ግንኙነቶችን በሚገነባበት መንገድ ላይ ነው።

ማውስ በጥናቱ  ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች በተገኙ ተጨባጭ ምሳሌዎች መሠረት በስጦታ ላይ የተሰብሳቢዎችን ግዴታዎች ሲገልፅ ስጦታዎች የመስጠት ግዴታ ወይም ስጦታ በመስጠት አንድ ሰው እራሱን እንደ ለጋስ የማየት ሁኔታ እና በዚህም አክብሮት እንደሚገባው የመሰማት ሁኔታዎችን ይዳስሳል። እንዲሁም ስጦታ የመቀበል ግዴታን ሲገልጽ ስጦታን በመቀበል አንድ ሰው ለሰጪው አክብሮት ያሳያል እናም በአንድ ጊዜ የራሱን ልግስና ያረጋግጣል። በማለት የጥናቱን ውጤት ያስቀምጣል። አንድ ሰው ስጦታ ከተቀበለ በኋላ የሆነ ጊዜ ስጦታውን የመመለስ ግዴታ ውስጥ እንደሚገባ በመግለጽ ፤ በዚህም የአንድ ሰው ክብር ከዋናው ሰጭው ጋር የሚመጣጠን መሆኑን ለማሳየት ይጥራል ይለናል።

ስለዚህ ስጦታ መስጠት በሥነ ምግባር የታነፀ ወይም በማህበረሰብ ደንብ ውስጥ የተደገፈ ሲሆን ስጦታዎችን በሚለዋወጡ ሰዎች መካከል የሞራል ትስስር በመስጠት ፣ በመቀበል እና በመመለስ ላይ ከፍተኛ ሚና እንዳለው ይገልጻል። በተመሳሳይ ጊዜ ማውስ በስጦታ ተወዳዳሪ መሆን እና ስልታዊ ገጽታን አፅንዖት ይሰጣል። ይህም ማለት ሰዎች በስጦታ ልውውጥ ወቅት ከተቀበሉት የበለጠ መስጠት ላይ በማተኮራቸው በጥንታዊ ማህበራት ላይ ያደረገው ጥናት ማውስን  "no free gift" የሚል መደምደሚያ ላይ እንዲደርስ አድርጎታል። በዚህ ሥራ ውስጥ ማውስ ስለ ማህበራዊ ግንኙነቶች ስጦታ ያለውን አስተዋጽኦ አጉልቶ አሳይቶበታል። ስጦታዎች የሚከሰቱት በግለሰቦች ብቻ ሳይሆን በቡድኖች መካከል ነው እናም ሀብትን እና ንብረቶችን ብቻ ሳይሆን ማህበራዊ አብሮነትን ለመገንባት የሚሰሩ አጠቃላይ ክስተቶች እና የህብረተሰብ ክፍሎችን የንፅፅር ዘዴን በመጠቀም የእያንዳንዳቸውን ተደጋጋፊ የስጦታ ልምዶችን ከመረመረ በኋላ የተወሰነ ልዩነት ቢኖርም በውስጣቸው የተለመዱ ባህሪያት እንዳላቸው ይገልጻል።

የስጦታ ዓላማዎች ተቀራራቢ ቢሆኑም ከዘመናዊ ስጦታዎች ይልቅ  በባህላዊ  ማህበረሰቦች ውስጥ ያሉ ስጦታዎች  ከምናውቃቸው ከማንኛውም የበለጠ ውስብስብ እና የማህበረሰቡን

ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ዘመድ-ተኮር፣ ህጋዊ፣ አፈ ታሪካዊ፣ ሃይማኖታዊ፣ አስማታዊ፣ ተግባራዊ፣ ግላዊ እና ማህበራዊ ጉዳዮች ያቀፉ እንደሆኑ ይገልጻል። እናም ማውስ ስለ ልውውጥ ታሪክ እና ተፈጥሮ ስለ ዘመናዊ ምዕራባዊ ማኅበራት ግምቶች የሚቃረን ማስረጃ በመጥቀስ ቀደምት የልውውጥ ሥርዓቶች የመስጠት ፣ የመቀበል እና ከሁሉም በላይ ደግሞ መልሶ የመስጠት ግዴታዎች ዙሪያ ያተኮረ መሆኑን በጥናቱ አሳይቷል ።

ጥናቱ ከዘመናዊው ስጦታ ይልቅ በማህበረሰቡ ዘንድ ያለውን ባህላዊ የስጦታ ልውውጥ እና ተግባር በስፋት ዳሶ የጥናቱን ውጤት ማህበራዊ ትስስር ከመፍጠር ጋር አሰናስሎ ማቅረቡ አላማውን ከማሳካት አንጻር የጥናቱ ጠንካራ ጎን ነው። የማውስ (1924) ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ነገር ሁለቱም ስጦታ ላይ በማተኮር ለማህበረሰቡ ያላቸውን ጠቀሜታ መመርመራቸው ሲሆን ሁለቱም በስጦታ ዙሪያ መጠናታቸው ነው። ነገር ግን በጥናት አውድ እና መቼት እንዲሁም በይዘት ይለያያሉ። የማውስ ጥናት በምዕራቡ ዓለም ፈረንሳይ ትኩረት በማድረግ በማህበረሰቡ ውስጥ ያለውን የስጦታ ልውውጥ እና ጠቀሜታ በመጥቀስ ስለ ስጦታ በማህበረሰቡ ባህል አማካኝነት የተቀረጸውን የሰው አስተሳሰብ የመረመረ ነው። ይህ ጥናት ደግሞ ከኢትዮጵያውያን የስጦታ ባህል  የደብረ ኤልያስ ወረዳ ላይ በማተኮር እና ስጦታ በሚዘወተሩባቸው የተለያዩ አውዶች ላይ በሚቀርቡ ስጦታዎች በመወሰን ለማህበረሰቡ ደንብ ያላቸው መታዘዝ መርምሯል። በዚህም የእርስ በእርስ ግንኙነትን፣ መፈቃቀድን፣ የጋራ ፍላጎት መኖርን፣ ዝምድናን መፍጠርና ማጠንከርን፣ ግንኙነትን ማለሳለስን፣ ለሃይማኖት መታመንን፣ ለማህበራዊና ባህላዊ ደንቦች መታዘዝን ወዘተ. ያሉ የስጦታ ጠቀሜታዎች የሚመረምር ነው።

በሁለተኛነት የቀረበው  ጥናት ደግሞ እ.ኤ.አ በ1967 በSchwartz  "The Social Psychology of the Gift" በሚል የቀረበ  የስነ ልቡና ምርምር ነው። በዚህ ጽሑፍ  ውስጥ የስጦታ ልውውጥ ለማንነት ግንባታ ወይም ለማንነት ልማት እንዲሁም ያልተስተካከለን ማንነት ለመጠገን ያለው ጠቀሜታ  ምን እንደሚመስል ተብራርቶ ቀርቧል። በጥናቱ ውስጥ ስጦታን በመቀበል እና በመስጠት በኩል ያሉ የእርስ በእርስ ፍላጎቶች  ምን እንደሆኑ ማወቅ እንደሚቻል ይገልጻል። በተጨማሪም ስጦታ በሰዎች ዘንድ ያለውን ቅርርብ  በመቆጣጠር እንደ ማህበራዊ ቁጥጥር መሳሪያ እና የወዳጅነት መግለጫ ተደርጎ ያገለግላል፤ በማለት ስጦታ የማህበረሰቡን ስነ ልቡና ከመገንባት አንጻር ያለውን ሚና በዝርዝር ያስረዳል። በአጠቃላይ በጥናቱ ውስጥ ስጦታን እንደ መድሀኒት በመጠቀም የማህበረሰብ ልማት ወይም አዎንታዊ የሆኑ የማህበረሰብ  እድገቶች በስጦታ ልውውጥ ሊመጣ እንደሚችል ጠቀሜታውን ያስረዳል። የስኳርትዝ (1967) ጥናት

ስጦታ የማህበረሰብ ሰብዕናን ከመገንባት አንጻር ያለውን ሚና ብቻ የሚያስስ ሲሆን ይህ ጥናት ግን ስጦታ ለማህበረሰብ ደንብ ያለው መታዘዝ፣ የሚቀርበው ስጦታ ከባህል አንጻር የሚሰጠው ትርጉም እንዲሁም ለማህበረሰቡ የሚሰጠው ሁለንተናዊ ጥቅም ተገልጾበታል፡፡

በመጨረሻም የቀረበው ጥናት እ.ኤ.አ በ1997 ኮምትር እና ዊልያም ቮልበርግ "Gift giving and the Emotional Significance of Family and Friends." በሚል ስጦታ መስጠት ለቤተሰብ እና ለጓደኛ ያለውን ከስሜት ጋር የተያያዘ ጠቀሜታ የሚዳስስ ጥናት ነው፡፡ በዚህ ጥናት ውስጥ ስጦታ ለተለያዩ ቡድኖች በሚሰጥበት ጊዜ ብዙ ስጦታዎችን እነ ማን እንደሚቀበሉ እና ምን ዓይነት ስሜቶች እንደሚታይባቸው ተተንትኗል፡፡ ጥናቱ የኳንቲታቲቭ ወይም መጠናዊ የምርምር ዘዴን በመጠቀም መረጃዎችን የሰበሰበ ሲሆን የስጦታ ተቀባዮችን ስሜት ለመረዳት ስጦታዎች ከተዘጋጁ በኋላ በሰጪዎች የተሰጡትን አጠቃላይ የስጦታዎች ብዛት እና ለእያንዳንዱ ተቀባዮች ምድብ የጥናቱን ቁጥር መቶኛ ወስኖ የተቀበሉትን የስጦታ መጠን እና የትኛው በብዛት ይሰጣል የትኛውስ ይቀበላል የሚለውን መርምሯል፡፡ በመቀጠልም ከስጦታዎቹ ጋር አብሮ ለመሄድ ምን ዓይነት ስሜት እንደነበር በመወሰን የጥናቱን ውጤቶች በመስራት ልጆች እና ወላጆች ወይም አማች እያንዳንዳቸው ከሁሉም ስጦታዎች ውስጥ በግምት አስራ ሶስት በመቶ ይቀበላሉ፡፡ ይህ ለሌሎች የቤተሰብ አባላት ወይም ጓደኞች ከሚሰጡት ስጦታዎች መቶኛ ያነሰ ነው፣ በተጨማሪም ዘመዶች እና ጓደኞች እያንዳንዳቸው ከሁሉም ስጦታዎች ከአንድ አራተኛ በላይ ይቀበላሉ፡፡ የሚተዋወቁ ሰዎች እና ጎረቤቶች ከሁሉም በጣም ጥቂቱን ይቀበላሉ በማለት የጥናቱን ውጤት ያስቀምጣል። ይህ ጥናት ሰዎች በተለይም ቤተሰብ እና ጓደኛ የሆኑ ሰዎች ስጦታ በሚለዋወጡበት ጊዜ ያላቸውን ስሜት መጠናዊ የምርምር ዘዴን በመጠቀም የመረመረ ሲሆን ከጥናቱ አላማ አንጻር የጥናቱን ውጤት በማየት አላማውን እንዳሳካ መረዳት ይቻላል። ይህ ጥናት በስጦታ ዙሪያ መደረጉ የሚያመሳስላቸው ነገር ቢሆንም በምርምር ዘዴ እና በዓላማ ይለያያሉ፡፡

### 2.1.2 የሀገር ውስጥ ጥናቶች

ስጦታን በተመለከተ በይዘት ከዚህ ጥናት ጋር የተመሳሰሉ የሀገር ውስጥ ምርምሮች ለማግኘት አልቻልሁም፡፡ ነገር ግን ከጥናቱ ውስጥ በንዑስ ርዕስነት የተነሱባቸውን ሁለት ጥናቶች በተዛማጅነት ቀርበዋል፡፡

የመጀመሪያው ጥናት በሙሉቀን የኔሰው 2010 ዓ.ም "የለውጥ ሽግግር በባሶሊበን ማህበረሰብ ባህላዊ የሠርግ ስርዓት" በሚል በባሕርዳር ዩኒቨርስቲ የፎክሎር ዲፓርትመንት ለየሁለተኛ

ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናት ነው። የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ "የባሶሊበን ማህበረሰብን የሰርግ ስርዓተ ክዋኔን በማሳየት የለውጥ ሽግግር ሂደቱን መመርመር ላይ ያተኮረ ሲሆን፣ በተጋቢዎች ላይ የሚከሰቱ ችግሮችና መንስኤዎችን፣ ማከሚያ/ማላመጃ መንገዶችና ፋይዳቸውን በማሳየት፤ ሰርግ ለማህበረሰቡ ያለውን ማህበረ-ባህላዊ ፋይዳ የተመረመረበት ጥናት ነው። የሙሉቀን (2010) ጥናት የመስክ መረጃዎች በምልከታ፣ በቃለ መጠይቅና በቡድን ተኮር ውይይት ተሰብስበዋል። የእርሷ ጥናት ዋና ጉዳዩ የሰርግ ክዋኔ ለውጥ ላይ ያተኮረ ቢሆንም ስጦታን በተመለከተ የተነሱ ብዙ ርዕሰ ጉዳዮችን እና በሰርግ ክዋኔ ወቅት የስጦታ ፋይዳ ምን እንደሚመስል ተመልክቷል። ይኸውም በትምም ወይም ውል መያዣ ወቅት ወላጆች ልጅህን ለልጄ ብለው ቃል በሚገቡበት ወቅት እምነትን ለማስጠበቅ ምልክት እንዲሆን ስጦታ እንደሚለዋወጡ (ገጽ፣71)፣ በቅልቅል ወቅት የሙሽራው እና የሙሽሪት ቤተሰብ ለመተዋወቅ እንዲሁም ለአክብሮት ስጦታ እንደሚሰጥ (ገጽ፣41)፣ በሰርግ ወቅት የሙሽሪትን እና ቤተሰቦቿን ክብር ለመጠበቅ ጥሎሽ (ስጦታ) እንደሚለዋዎጡ (ገጽ፣88)፣ በጫጉላ ወቅት ሙሽሪት እና ሙሽራው እንዲቀራረቡ ስጦታ ትልቅ ሚና እንዳለው (ገጽ፣106)፣ ከሰርግ በኋላም በፈቀዳ ወቅት ስጦታ እንደሚሰጥ (ገጽ፣142) ገልጻለች።

የሙሉቀን (2010) ጥናት የዚህ ጥናት ዋና ትኩረት የሆነውን ስጦታ የመቀያየር ልማድ ማንሳቱ እና የጥናት አካባቢ ቀረቤታ መኖሩ በተወሰነ መልኩ ያመሳሳስላቸዋል። ከእርሷ ጥናት ውስጥ እንደተረዳሁት ጥናት ያደረገችበት የባሶሊበን ማህበረሰብ እና የዚህ ጥናት ተጠኝ የሆነው የደብረ ኤልያስ ማህበረሰብ የሰርግ ክዋኔ እንዲሁም በጥናቱ ወቅት የተጠቀሱ ስጦታዎች ተቀራራቢ አንዳንድ ጊዜም ተመሳሳይ ሆነው አግኝቻቸዋለሁ። ነገር ግን የሙሉቀን (2010) ጥናት በሰርግ ክዋኔ ለውጥ ላይ የተሰራ መሆኑ ይህ ጥናት ደግሞ ስጦታ ለማህበረሰብ ደንብ ያለው መታዘዝ ላይ የተሰራ መሆኑ የሚያለያያቸው ዋና ጉዳይ ነው።

ሁለተኛው በተዛማጅነት የቀረበው ጥናት ሉባባ አህመድ በ2012 ዓ.ም በኦሮሚያ ብሄራዊ ክልል "በኢሉባቦር ዞን ዶረኒ ወረዳ በኦሮሞ ማህበረሰብ ድንግልናቸውን ጠብቀው ለትዳር ለበቁ ሴቶች የሚደረግ ሥርዓት ትንተና" በሚል ርዕስ ለኢትዮጵያ ስነ ጽሁፍ እና ፎክሎር ሁለተኛ ድግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት ነው። ጥናቱ በማህበረሰቡ ከሚከወኑ የሰርግ ሥርዓቶች መካከል በNaqataa የጋብቻ ዓይነት ድንግልናቸውን ጠብቀው ለጋብቻ ለበቁ ሴቶች ስለሚደረገው ስርዓት ፤ ስርዓቱ ለማህበረሰቡ ስለሚሰጠውን ማህበራዊና ስነልቡናዊ ፋይዳ እንዲሁም ስርዓቱ

ስላለበት ሁኔታ የሚመረምር ነው፡፡ ጥናቱ ድንግልናቸውን ጠብቀው ለትዳር የበቁ ሴቶች በጋብቻ ወቅት የሚሰጣቸው ስጦታዎች ምንድን ናቸው? የሚለውን ጥያቄ በንዑስ ርዕስነት አካቷል፡፡ አንዲት ሴት ያለውን ፈተና ተቋቁማ ለቁም ነገር በመብቃቷ ማህበረሰቡ አድናቆቱን እና ሙገሳውን በጋብቻ ወቅት በስጦታ እንደሚያረጋግጥ አጥኝዋ (ገጽ 71) ትገልጻለች፡፡ በተጨማሪም በቀለበት ስርዓቱ፣ በሰርግ ጊዜ በባህሉ መሰረት ሁለቱ ተጋቢዎች ግንኙነት ፈጽመዉ ድንግልና የመውሰዱ ሂደት ረኮ ቀሉ (rakoo qaluu) ይባላል፡፡ ሙሽሮቹ ወደ ጫጉላ ቤት ሲገቡም ሙሽራው ካለው በግ አርዶ ከሌለው ደግሞ ጨፌ ቆርጦ ይገባል፡፡ … ከዚያም ቀጥሎ ኢልማ ፉራ (Ilmaa furaa) የሚባል ሥርዓት ይከናወናል፡፡ ይህ ሥርዓት ከግንኙነት በፊት የሙሽራው እናት የሙሽሪትን መቀነት ትፈታለች፡፡ መቀነቷን ከፈታች በኋላ "ድንግል ከሆንሽ ጥጃ ወይም ላም እሰጥሻለሁ" በማለት የስጦታ ቃል ትገባላታለች፡፡ ይህ ስጦታ የሙሽሪት የግል ስጦታ ነው፡፡ ምናልባት ትዳሩ በፍቺ ቢጠናቀቅ እንኳ ይህንን ስጦታ ባል የመካፈል መብት የለውም፡፡ በማለት በጫጉላ ወቅት ሙሽሪት ድንግልናዋን ጠብቃ ከተገች የሚደረጉላትን ሙገሳዎች እና የሚቀርቡላትን ስጦታዎች አጥኝዋ ለመዳሰስ ሞክራለች፡፡

ሌላው በጥናቱ ውስጥ በቀጥታ ስጦታን በተመለከተ የተነሳው ጉዳይ የአርጋ ሚዜ (Argaa Minzee) ስርዓት ነው፡፡ የሙሽሪትን ድንግል መሆን ምክንያት በማድረግ ሚዜዎች ጨፍረው ከሙሽራው እና ከሙሽሪት ቤተ ዘመዶች የሚሰበስቡት ስጦታ አርጋ ሚዜ (Argaa Minzee) ይባላል፡፡ በዚህ ሂደት ሚዜዎች የተለያዩ ስጦታዎችን ከሙሽሮቹ ቤተሰቦች ይሰበስባሉ፡፡ ምሽቱን (በሙሽራው ቤተሰብ ቤት) ምስራቹን ለማረጋገጥ የተቀመጠችው ሴት የደም ሽማውን አምጥታ ለሚዜዎች እንደሰጠች ሚዜዎች ጭፈራ እና ስጦታ መቀበል የሚጀመሩት ከሙሽራው አባትና እናት ነው፡፡ አባትና እናት በአብዛኛው የሚሰጡት ጊደር ነው፡፡ ጊደር የሚሰጥበት ምክንያት ወልዳ ተራብታ ሀብት ትሆናለች ተብሎ ስለሚታሰብ ነው፡፡ ጊደር

ከሌላቸው ወይፈን ይሰጣሉ ይህም የሚሆነው ወይፈኑ ከበሬ በተሻለ ብዙ ጊዜ ስለሚታረስበት ነው፡፡ ቤተሰቡ ጊደር ወይም ወይፈን ከሌላቸው ሁለት እግር ይሰጣሉ፡፡ ማለትም የጊደር ወይም የወይፈን ግማሽ ለመስጠት ቃል ይገባሉ፡፡ በዚህ መሰረት ሁሉም የሰርጉ ታዳሚዎች ለሙሽሮቹ ስጦታ ይሰጣሉ፡፡ በማለት በጋብቻው ወቅት ያለውን የስጦታ ሚና ገልጻለች፡፡የሉባባ (2012) ጥናት ዓላማ እና የጥናት አካባቢ ከዚህ ጥናት ዓላማ እና የጥናት አካባቢ አይመሳሰልም፡፡ ነገር ግን በዚህ ጥናት ውስጥ ዋና ትኩረት የሆነው የደብረ ኤልያስ ማህበረሰቦች ስጦታ የመቀያየር ልማድ መካከል በጋብቻ ወቅት ያለውን የስጦታ ልውውጥ በሌላ

አካባቢም ቢሆን፤ የሉባባ (2012) ጥናት እንደ አንድ ርዕስ ስላካተተ ከዚህ ጥናት ጋር የሚያቀራርበው ጉዳይ ሆኗል።

## 2.2 ንድፈ ሐሳባዊ ዳራ

በአንድ ጥናት ውስጥ ከመስክ የሚሰበሰቡ መረጃዎች በአግባቡ ተሰብስበው ለአንባቢ ግልጽ በሆነ ትርጉም እና በንድፈ ሐሳቦች ታግዘው መተንተን እንዳለባቸው Dundes (1980) ይገልጻል። በተጨማሪም መረጃዎች በተገቢዉ መንገድና በመልክ ካልተደራጁ እንዲሁም ካልተተነተኑ ውጤታቸዉ ስህተት እንደሚሆን ያለዉ (2004፣ 232) ይናገራሉ። ከዚህም አንጻር መረጃውን ለመተንተን የሚረዱ ፣ ለጥናቱ ስምሙ የሆኑ አራት ንድፈ ሃሳቦች ወይም የአተያይ ስልቶች በዚህ ንዑስ ክፍል ተዳሰዋል። እነርሱም አልተሪዝም ቲዎሪ (Alturism theory)፣ ሪስፕሮሲቲ (Reciprocity)፣ ሥነ ፍቺ (semiotics) እና ተግባራዊ (Functionalism) ንድፈ ሀሳቦች ናቸው።

### 2.2.1 አልተሪዝም (Alturism) ቲዮሪ

አልተሪዝም (Alturism) የሚለውን ቃል Oxford "The belief in or practice of disinterested and selfless concern for the well-being of others." ስለ ሌሎች ደህንነት የሚገደው እና ከራስ ወዳድነት ነፃ የሆነ አሳቢነት ወይም እምነት በማለት ይተረጉመዋል። ይህም ማለት ሌሎችን ማስቀደም እና ለራሴ ይቅርብኝ ብሎ መስጠትን፣ በጎ ማድረግን፣ መስዋዕት መሆንን፣ ሽልማት ሳይጠብቅ ሌላውን ሰው መርዳት፣ ለሌሎች ወጪ የሚፈጥሩ ከሆነ የግል ጥቅሞችን ሊያስገኙልዎ የሚችሉ ነገሮችን መተው ፣የግል ወጪዎች ወይም አደጋዎች ቢኖሩም አንድን ሰው መርዳትን፣ እጥረት በሚኖርበት ጊዜም ቢሆን ሀብትን መጋራት፣ ለሌላ ሰው ደህንነት መጨነቅ ማሳየት ወዘተ. ጉዳዮች ያካትታል። በተለያየ የትምህርት ዘርፍ ውስጥ ያሉ ምሁራን ስለ አልተሪዝም ምንነት እና ባህርይ የተለያዩ ማብራሪያዎች ሰጥተውት እናገኛለን። ከእነዚህም ውስጥ ሶሾሎጂስቱ ዊልሰን "alturism is self-destructive behavior performed for the benefit of others." Wilson (1975, 578) አልተሪዝም "ለሌሎች ጥቅም ሲባል የሚደረግ ራስን የመጉዳት ባህርይ" በማለት ከራስ ይልቅ ለሌሎች አብዝቶ የማሰብ እንዲሁም ሌሎችን የማስቀደም ጠባይ እንደሆነ ይገልጻል።

ኢኮኖሚስቱ Margolis (1982) ደግሞ የአልተርስቲክ ጸባይ ያለው ሰው የራሱን ፍላጎቶች ለሌሎች አሳልፎ መስጠቱን እንደ ጥሩ ነገር አይመለከተውም። "What defines altruistic behavior is that the actor could have done better for himself had he chosen to ignore the effect of his choice on others...." (Margolis, 1982;15)።

በአጠቃላይ አልተሪዝም ሌሎች ሰዎችን የሚጠቅም ማንኛውንም እርምጃ ነው። በምርምር ሂደት ውስጥ ይህን ንድፈ ሀሳብ በተለይም የስነ ልቡና ተመራማሪዎች የሰው ልጆችን ውስጣዊ ማንነት ለማወቅ ይጠቀሙበታል። እንደዚህ አይነት ማንነት ያላቸው ሰዎች በተፈጥሮ የተሰጣቸው ነው? ወይስ በመኖር ሂደት ያገኙት? የሚለው ጥያቄም ምሁራንን የሚያከራክር የጥናት ትኩረት ነው። ይህንን ጉዳይ ለማረጋገጥም አጥኝዎች አንድ ጊዜ ሰዎችን ሌላ ጊዜም እንስሳትን በመጠቀም ምርምር ተደርጓል። እንደ (Jane and Hong-Wen,1990 ፡ 31) ገለጻ በዋናነት 4 የተለያዩ አይነት የአልተሪዝም ባህርይዎች እናገኛለን ። እነርሱም

- ✓ በዘር የሚተላለፍ በጎነት (Genetic or kinship altruism) "የማሽላ ዘር ከነአገዳው ቸር" (ደግነት ከቤተሰብ የሚወረስ እንደሆነ የሚያመለክት ምሳሌአዊ አነጋገር)

የዚህ ዓይነቱ  ተግባር የቅርብ የቤተሰብ አባላትን የሚጠቅሙ የበጎ አድራጎት ድርጊቶችን መሳተፍን ያካትታል ። ለምሳሌ ፣ ወላጆች እና ሌሎች የቤተሰብ አባላት የእነርሱ የቤተሰብ አባላትን ፍላጎት ለማሟላት ሲሉ  መስዋእትነት መክፈል ሊሆን ይችላል ። ይኸውም ከስጦታ ጋር ስናገናኘው ለሌሎች የቅርብ ሰዎች ወይም ቤተሰቦች  ሲሉ ራስን መስጠትን ይመለከታል።

- ✓ የሰጥቶ መቀበል በጎነት (Reciprocal altruism) ይህ ዓይነቱ ተግባር በጋራ የመስጠት እና የመቀበል ግንኙነት ላይ የተመሠረተ ነው። ውለታ ተቀባይ አንድ ቀን ውለታውን መመለስ ይችል ይሆናል ነገርግን በአስፈላጊ ሁኔታዎች አንዱ ሌላ ሰውን መርዳት ያካትታል።
- ✓ የተመረጠ በጎነት (Group-selected altruism) ይህ ደግሞ በቡድን ዝምድናቸው ላይ በመመርኮዝ  የበጎ አድራጎት ሥራ መሳተፍን ያካትታል ። ሰዎች የእነሱን ማህበራዊ ቡድን አካል የሆኑ ሰዎችን ለመርዳት ወይም የአንድ የተወሰነ ቡድን ተጠቃሚ የሚያደርጉ ማህበራዊ ጉዳዮችን የመደገፍ ተግባር ነው።
- ✓ ንፁህ በጎነት (Pure altruism)

ንፁህ በጎነት በተጨማሪም ሥነ ምግባራዊ አክብሮት በመባልም ይታወቃል፣ ያለ ምንም ጠብቆት አደገኛ ቢሆንም እንኳ ሌላውን መርዳትን ያካትታል። ይህ ደግሞ ከGenetic altruism የሚለየው ለቤተሰብ አባል ብቻ ሳይሆን ለማንኛውም ሰው መስዋእት መሆንን ከራስ ይልቅ ሌሎችን ማስቀደምን የሚመለከት ነው። "የለጋስ ምስክሩ መስጠቱ" (ስጦታ መስጠት ደግነት የሚገለጽበት መንገድ መሆኑን የሚገልጽ ምሳሌአዊ አነጋገር)

በተጨማሪም የስነልቡና ተመራማሪዎች አልተሪዝም የሚፈጠሩበትን  ምክንያቶች ለማስቀመጥ ይሞክራሉ፡፡ ከእነዚህም ውስጥ Environment /አካባቢ/ እና social norms/ ማኅበራዊ ደንቦች ያላቸው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው፡፡ (verywell mind.com) ይህም ማለት ሰዎች በጎነትን ወይም ከራስ ይልቅ ሌሎችን የማስቀደም ባህርይ በተፈጥሮ ያገኙታል ከሚሉት አጥኝዎች በተጨማሪ የማህበረሰቡ ህጎች እና  ባህሎች ሰዎች በበጎ አድራጎት ባህርይ ውስጥ ይሳተፉ ወይም አይሳተፉ  የሚለው ጉዳይ ላይ ተጽዕኖ ያሳድራሉ በማለት አተያያቸውን ያስቀምጣሉ፡፡ የርህራሄ ድርጊቶችን ሞዴል ማድረግ በተለይም በልጆች ላይ የማህበራዊ እና የርህራሄ እርምጃዎችን ለማዳበር ጠቃሚ መንገድ ሊሆን ይችላል፡፡ በመደጋገፍ ደንብ፣ ለምሳሌ÷ ሌሎች አንድ ነገር ቀደም ብለው ካደረጉልን እነርሱን ለመርዳት ጫና እንዲሰማን የሚያደርግ ማህበራዊ ተስፋ ነው፡፡

ይህ ንድፈ ሀሳብ ስለ አልተሪዝም/ በጎነት፣ ገራገርነት.../ በሰው ልጆች አስተሳሰብ ውስጥ ያሉ ስሜቶችን በመመርመር ሰዎች በጎ ነገሮችን ለሌሎች ስለማድረግ ያላቸው አመለካከት የሚመረመርበት አንዱ መንገድ ነው፡፡ የዚህ ጥናት ትኩረት የሆነው ስጦታን በማንሳትም ለመስጠት የሚያነሳሳው ጉዳይ፣ በልውውጥ ወቅት ያለው የሰጪና የተቀባይ ግንኙነት እና ስጦታውን ከተለዋወጡ በኋላ ያለውን የሰጪና የተቀባይ ጥቅም ተዳሶበታል፡፡ በተጨማሪም ለስጦታ አነሳሽ የሆኑ ምክንያቶች ምንድን ናቸው፣ ለሰጪ እና ለተቀባይ የሚሰጠው ስነ ልቡናዊ አስተዋጽኦ ምንድን ነው? ስጦታ ማንነትን ከመገንባት እንዲሁም መልካም ሰብዕናን ከመፍጠር አንጻር ያለው ፋይዳ ምን ይመስላል የሚሉ ጉዳዮችን  በተጠኝው አካባቢ ያሉ የስጦታ ደንቦችን በማንሳት በዚህ ቲዎሪ አተያይ መሰረት ተመርምሯል፡፡ ይኸውም በመወለድ ጊዜ፣ በጋብቻ ወቅት እና በሞት ጊዜ   በክብረ በዓላት እና በዘመን መቀያየር ወቅት ወዘተ. ያለውን እርስ በእርስ  የመረዳዳት ስሜት  እና ስጦታ የመቀያየር ልማድ በማንሳት ያላቸውን ሁኔታ እንዲሁም ስጦታውን ለመስጠት አነሳሽ የሆኑ ምክንያቶችን ለመመርመር እና እንደዚህ ባሉ ሁኔታዎች ውስጥ ስጦታ መለዋወጥ  ያለውን ጠቀሜታ ለመተንተን ተጠቅሜበታለሁ፡፡

### 2.2.2 መመላለስ (Reciprocity) ንድፈ ሀሳብ

ሪስፕሮሲቲን መመላለስ የሚለው ስያሜ ይቀርበዋል፡፡ ይህ ንድፈ ሀሳብ የጋራ ጥቅም በጋራ ለማግኘት ነገሮችን ከሌሎች ሰዎች ጋር የመለዋወጥ ሂደትን የሚመለከት ነው፡፡ እርስ በእርስ የመተካካት ደንብ፣ በሌላ አነጋገር የመደጋገፍ ደንብ ተብሎ ሊጠራም ይችላል፡፡ አንድ ሰው ሌላውን ለመርዳት ሲል አንድ ነገር ቢያደርግ  የተደረገለት ሰው ውለታውን የመመለስ ግዴታ

እንዳለበት ሆኖ እንዲሰማ የሚያደርግ ማህበራዊ ደንብን የሚመረምር ነው። የሪስፕሮሲቲን ወይም የተደጋጋፊነትን ምንነት በተመለከተ "ተደጋጋፊነት ማለት ቡድኖች እንደ እነሱ ልማድ ደግ ያሉአቸውን ድርጊቶች የሚሸልሙበት እንዲሁም ደግነት የጎደላቸው ድርጊቶችን የሚቃወሙበትና የሚቀጡበትን ስርዓት የሚመለከት ጽንሰ ሀሳብ እንደሆነ እና የ አንድን ድርጊት ደግነት የሚገመግሙት በውጤት ብቻ ሳይሆን ይህንን እርምጃ (ያወጡትን ህግ) ለማጉላት በማሰብም ጭምር ነው። "Reciprocity means that people reward kind actions and punish unkind ones. It takes into account that people evaluate the kindness of an action not only by its consequence but also by the intention underlining this action." Falk & Fischbacher, (2000,1) በማለት ይገልጻሉ።

የመደጋገፍ ደንብ በባህሪያችን ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ሊያሳድር የሚችል አንድ ዓይነት ማህበራዊ ደንብ እንደሆነ የተለያዩ የስነ ልቡና እና የስነ ሰብ ተመራማሪዎች የሚስማሙበት ጉዳይ ነው። ከዚህም ውስጥ ማውስ (1966) በስጦታ ልውውጥ ወቅት ሁልጊዜም አዎንታዊ ምላሽ የሚጠበቅ እንደሆነ በማስገንዘብ "no free gift" በሚል አቋሙ ይታወቃል። ስለ ስጦታ ባደረገው ምርምርም የReciprocity ንድፈ ሀሳብ አተያይን ተመስርቶ ስጦታ በመስጠትና በመቀበል ወቅት ያለውን የማህበረሰብ ደንብ ሲመረምር በስጦታ ውስጥ ሶስት ግዴታዎች እንዳሉ ይናገራል። እነርሱም መስጠት ፣ መቀበል እና መመለስ ናቸው። በሌላ አገላለጽ ፣ የግዴታ ስጦታ ማለቂያ የሌለው ዑደት አካል ነው ። ስጦታ ተቀባዩ የተፈጠረውን ግዴታ በመፈጸም በተመሳሳይ ጊዜ ማህበራዊ ትስስር ይፈጥራል ወይም ያጠብቃል። ማውስ (1966) በማለት ይገልጻል። በአጠቃላይ ሪስፕሮሲቲን ወደ ስጦታ ስናመጣው በልውውጥ ወቅት ያሉ ደንቦችን እና በድግግሞሹ ወቅት ያሉ ጠቀሜታዎችን የሚዳስስ ነው።

በተጨማሪም እርስ በእርስ መደጋገፍ (reciprocity) ለምን ውጤታማ እንደሆነ የሚያብራሩ ከማውስ ተጨማሪ አራት ነገሮችን እነርሱም “የስጦታ የመኖር ዋጋ ፣ የሌላው ዕውቅና መኖር ወይም በተመልካች የተገለፀ መሆኑ፣ የአብሮነት የሞራል አስገዳጅ ባህርይ ያለው መሆኑ እና መደጋገፍ እንዲሁም ልግስናን ከራስ ጥቅም ጋር አዋህዶ ስለሚይዝ ነው” በማለት ይገልጻል። ኮምተር (2007)።

ስጦታን የመመለስ ግዴታ ወይም ስጦታን ከተቀበሉ በኋላ ውለታን የመመለስ ስሜት መሰማት እንደ ማኅበረሰብ ባህል፣ አስተሳሰብ፣ ፍልስፍና እንዲሁም እምነት ይለያያል። ስጦታው ሊመለስም ላይመለስም ይችላል። በዚህ ንድፈ ሀሳብ አተያይ ግን ስጦታ ምልልስ እንደሆነ

መረዳት ይችላል። ስጦታን መመለስ በጊዜ፣ በቀረቤታ መጠን ሊወሰን እንደሚችልም "በቅርበት በሚዛመዱ ሰዎች መካከል የስጦታ ልውውጦች ወዲያውኑ መተካካት አያስፈልጋቸውም። ምክንያቱም ግንኙነቱ ሰዎች ስጦታው በሚፈልጉበት ጊዜ እርዳታ የሚጠብቁበት ሁኔታ ቀጣይነት ያለው ስለሆነ ይህ ከስጦታው በኋላ ብዙ ጊዜ ይከሰታል። ይህም በስጦታ ግንኙነት ዙሪያ ያለው አለመተማመን መጠን እየቀነሰ ይሄዳል" በማለት Ruth (2017,62) ትገልጻለች። ስለዚህ ስጦታ ወዲያውኑ የሚመለስ፣ ከጊዜ በኋላ የሚመለስ ወይም የማይመለስ አከዋወን ሊኖረው እንደሚችል እንረዳለን።

እ.ኤ.አ. በ 1965 ማርሻል ሳህሊን የተባለ አንድ የሥነ ሰብ ጥናት ባለሙያ በዓለም ዙሪያ በሰው ልጆች ማኅበረሰብ ውስጥ የሚከሰቱ ሦስት የተለያዩ የመመለሻ (reciprocity) ዓይነቶች እንዳሉ ተመልክቷል እነርሱም አጠቃላይ (Generalized reciprocity)፣ ሚዛናዊ (Balanced reciprocity) እና አሉታዊ (Negative reciprocity) ናቸው። Marshall .S (1972)

- ✓ አጠቃላይ (Generalized reciprocity)

ይህ ዘርፍ የተጠቃለለ ተደጋጋፊነት የሚባለው ነው። ይህ አይነቱ ተደጋጋፊነት ብዙውን ጊዜ በቤተሰቦች ወይም በጓደኞች መካከል የሚደረግ ልውውጥን ያካትታል። ሰዎች ሌላኛው ሰው ለእነሱ ተመሳሳይ ነገር ያደርግልኛል በሚል ግምት ላይ በመመስረት በቀላሉ ለሌላ ሰው አንድ ነገር ያደርጋሉ። ቀጣይነት ያለው አንዱ ለሌላው በጎ ነገርን የማድረግ ደንብን የሚመለከት ነው። ይህ ዓይነቱ ተደጋጋፊነት ከአልተሪዝም ጋር በትንሹ ይዛመዳል። ይህንን አተያይ ወደ ስጦታ ስናመጣው ደግሞ ስጦታ የሚሰጠው ሰው ከስጦታ ተቀባዩ የሚፈልገው አንዳች በጎ ጠብቆት ኖሮት መስጠትን ወይም ስጦታ ተቀባዩ ስጦታ የመመለስ ግዴታ እንዲሰማው የሚያደርገውን ማህበራዊ ደንብ የሚመለከት ነው።

- ✓ ሚዛናዊ (Balanced reciprocity)

ይህ ዓይነቱ ተደጋጋፊነት የልውውጡን ዋጋ ስሌት በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ ውለታ ይመለሳል የሚል ተስፋን ያካትታል ። በስጦታ ልውውጥ ወቅት ሰዎች በደስታቸው ወይም በሀዘናቸው ወቅት ከወዳጅ ዘመዶቻቸው የተለያዩ ስጦታዎችን ይቀበላሉ በተመሳሳይ ጊዜም ስጦታ ለሰጧቸው እንዲሁ ያደርጋሉ ማለት ነው። በማህበረሰቡ ልማድ ውስጥ አንዱ ለሌላው የሚያደርገው በጎ ነገር እንደ ውለታ የማስቀመጥ እና ውለታ የመመለስ ሁኔታዎች የሚደገፉ ተግባራት ሆነው እናገኛቸዋለን። ከዚህም አንጻር ያለውን የስጦታ ምልልስ ደንብ ይመረምራል።

- ✓ አሉታዊ (Negative reciprocity)

አሉታዊ ተደጋጋፊነት የምንለው ደግሞ የሚከናወነው በልውውጡ ውስጥ የተሳተፈው አንዱ ወገን ከሌላው ሰው የበለጠ ለማግኘት ሲሞክር ነው። ትንሽ ሰጥቶ ብዙ መቀበል የአሉታዊ ተደጋጋሚነት አንዱ ምሳሌ ነው። ሁኔታን የሚመለከት ነው።

የስጦታ ልውውጥ ምንም አይነት ጠብቆት ሳይኖር ከመስጠት በተጨማሪ በማኅበረሰቡ ዘንድ ልማድ እንደመሆኑ መጠን ቀጣይነቱ የሚረጋገጠው የማኅበረበቡን ህገ ደንብ ተከትሎ አንዱ ለሌላው ሲሰጥ ወይም ተከዋኝነቱ አላማውን ጠብቆ መጎልበት ሲችል እና ሲደጋገም ጭምር ነው። ሪስፕሮሲቲን በቀጥታ የራስን ጥቅም ፈልጎ ከመስጠት እና ከራስ ወዳድነት ጋር እንዳናገናኘው መጠንቀቅ እንዳለብን Armin & Fischbacher (2001፣ 2) ይገልጻሉ። "ሪስፕሮሲቲ (ተደጋጋፊነት) ፍጹም ራስ ወዳድ ከመሆን ሊመጣ የማይችል ባህርይ በመሆኑ ያለንን የቃላት ውዥንብርን ለማስቀረት በግልፅ ስንመለከት ሪስፕሮሲቲ እንደ "reciprocal alturism" በጋራ የመስጠት እና የመውሰድ ግንኙነት ላይ የተመሠረተ ሲሆን ውለታ ተቀባይ አንድ ቀን ውለታውን መመለስ ይችል ይሆናል የሚል ተስፋ ያለበት መስጠትን የሚመለከት፣ በአስፈላጊ ሁኔታዎች አንዱ ሌላ ሰውን መርዳትን እንደሚመለከት ነው።

ከዚህም አንጻር አልተሪዝም ስጦታን በለጋስነት ያለምንም ጠብቆት መስጠትን የሚመለከት ሲሆን በሪስፕሮሲቲ ደንብ ደግሞ ከስጦታው በኋላ ምላሽ ይጠበቃል። በዚህም ጥናት ለተገኙ መረጃዎች የ ሪስፕሮሲቲ ንድፈ ሀሳብ በዋናነት ለጥናቱ መተንተኛ ስምሙ ሆኖ ተገኝቷል።

በዚህ ንድፈ ሀሳብ መሰረት በስጦታ ልውውጥ ስርዓት አንዱ ለሌላው ሲሰጥ ወይም ስጦታ ሲቀበል ያለው አስተሳሰብ ምንድን ነው? ስጦታ የመመለስ ግዴታ ወይም ስጦታን እንደ ውለታ ቆጥሮ የማስቀመጥ እና በጎ ምላሽ የመስጠት ሁኔታ በደብረ ኤልያስ ማኅበረሰቦች አስተሳሰብ እና ልማድ ውስጥ እንዴት ይታያል? ስጦታው አዎንታዊ ምላሽ ባይኖረውስ ምን ያስከትላል? ወዘተ. የሚሉ ጉዳዮች ላይ በማተኮር በስፋት ተዳሷል።

### 2.2.3 ሥነ ትእምርት (semiotics) ንድፈ ሃሳብ

ሴሚዮቲክስ ቃሉ ከ ግሪክ sēmeion የተገኘ ፣ ትርጉሙም በስፋት “ወካይ” ወይም “ምልክት” ማለት ነው። ሴሚዮቲክስ ለግንኙነት የሚያገለግሉ ምልክቶች ናቸው። አንዳንድ የተለመዱ ምሳሌዎችን በመጥቀስ በመገናኛ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ ምልክቶችን እና ወካዮችን ሁሉ ለመተንተን እና ለመተርጎም የሚያገለግል መሳሪያ እንደሆነ እና በቋንቋዎች፣ በቃላት፣

በምስል፣ በትራፊክ ምልክቶች፣ በድምጾች፣ በሙዚቃ፣ በማስታወቂያ፣ በህንፃ፣ በፋሽን፣ ሥነ ጽሑፍ እና ሥዕል በአጭሩ ሴሚዮቲክስ ማኅበራዊ እና ግለሰባዊ ንግግሮችን የሚቀርፁ ሁሉንም ትርጉም ያላቸው መዋቅሮችን ያቀፈ ነው በማለት ይገልጻል (Culler, 2002)። የሥነ ትእምርት ጽንሰ ሀሳብ እንደ ባህል ደግሞ አንድ የማህበረሰብ ጥበብ ያለውን ውክልና ወይም ትርጉም የሚመለከት፣ የፍች አሰጣጥን፣ ጥቆማን፣ የነገሩን ነባራዊ ፍቺ እንዲሁም በማህበረሰቡ ውስጥ የሚሰጠውን ትርጉም የሚመለከት ነው። ይህንን አስመልክቶ Danesi (2004) የስነ ፍቺ ወይም ሴሚዮቲክስ ንድፈ ሃሳብ የተመሳስሎ ባህርይን የምሳያ ንጽጽርን፣የዘይቤ አጠቃቀምን፣ የፍቺ አሰጣጥን፣ ጥቆማን፣ የአሰያየም አይነትን፣ ትዕምርታዊ ውክልናን (Symbolism) የሚመለከት ንድፈ ሃሳብ ነው በማለት ይገልጻል። ስጦታ በማህበረሰቡ ዘንድ ትልቅ ትርጉም ያለው ነው ። በዚህ ጥናት ውስጥም ለጥናቱ በተመረጡ አውዶች የሚቀርቡ ስጦታዎች የተሸከሙት መልዕክት ምንድን ነው እና ምን ያህልስ ያግባባሉ የሚሉት ጉዳዮች ተተንትነው ቀርበዋል። ስጦታዎች በውስጣቸው ብዙ ትዕምርቶችን ተሸክመዋል። ለዚህም ማሳያው በተለያዩ ማህበረሰቦች ባህል ውስጥ የተከበሩ እና የሚነቀፉ ስጦታዎች መኖራቸው ለምሳሌ፦ በቻይናውያን ባህል መሰረት ጃንጥላ መስጠት ከስጦታ ተቀባዩ ሰው ጋር የነበረ ግንኙነት እንዲቀጥል አለመፈለግ ነው። (Umbrellas: The word for umbrella, "伞 (sǎn)" sounds like "散 (sàn)" which means "to separate." By giving someone an umbrella, you are suggesting that you want the relationship to end. /www.giftculture.com/ ስጦታዎች በተቀባይ እና በሰጪው እንዲሁም በማህበረሰቡ ዘንድ ያላቸው መልእክት ከባህል አንጻር ልውውጡ የተቸከመው ትዕምርት ከፍተኛ እንደሆነ ከላይ የተመለከትነው የስጦታ ልማድ ያስገነዝባል።

ስጦታ ስለ ሰጪው ማንነት መግለጫ እንዳሁም ተቀባዩ እና ሰጪውን የሚያገናኝ ምልክታዊ መግባቢያ ነው። እንደ Wolfinbarger (1990) ምርመራ ከስጦታዎች ጋር የተዛመዱ አራት የምልክቶች ምድቦች እንዳሉ ይገልጻሉ። እነርሱም፦ ስጦታዎች የተቀባዩ እና የሰጪው ተምሳሌት ናቸው፣ ስጦታዎች የሰጪውን ዕውቀት ተምሳሌት ናቸው፣ ስጦታዎች ለሚከበረው በዓል ተምሳሌት ናቸው እና ስጦታዎች በራሳቸው ገላጭ የሆኑ ትርጉሞችን ይዘዋል የሚል ነው።

ስጦታ የብዙ ማህበራዊ ግንባታዎች፣ የማንነት፣ የአምልኮ ሥርዓቶች፣ የተደጋጋፊነት እና የመሳሰሉት ተወካይ ነው። ስጦታ ሰጪ ብዙ ዓላማዎች ሊኖሩት ይችላል። ለምሳሌ፦ ተቀባዩን ለማርካት፣ የራስን ሁኔታ ለማመላከት፣ የግንኙነቱን ሁኔታ ለመወከል፣ ወዘተ. እንደ አጠቃላይ

ደግሞ ስጦታ በመለዋወጥ ሂደት ውስጥ ስጦታ ሆኖ የተበረከተው ነገር በስጦታ ሰጪው እና ተቀባዩ መካከል አንዳች ትርጉም ያለው እና በተለዋዋጮቹ መካከል ለማስታወሻነት የሚቀመጥ ምልክትም ነው፡፡ በደብረ ኤልያስ ወረዳ ማህበረሰቦቹ ስጦታ በመለዋወጥ ሂደት ውስጥ ያሉ የስጦታ መልዕክቶችና ፋይዳዎች እንዲሁም የሚቀርቡ ስጦታዎች የያዙት ውክልና በአጠቃላይ ከስጦታ በስተጀርባ ያሉ የማህበረሰብ አስተሳሰቦች እና የአተረጓጎም ስልቶች ምን ይመስላሉ የሚሉ ጉዳዮች በጥናቱ ተካተዋል፡፡ በዚህ ቲዎሪም ስጦታዎችን ማን ለማን ይሰጣል? ከስጦታው ጋር አብሮ የሚመጣው መልእክት ወይም የስጦታው ትርጉም ምንድን ነው? በአጠቃላይ ስጦታ በመቀበል እና ስጦታ በመስጠት በኩል ያለው መግባባት ምን ያህል ነው የሚሉ ጉዳዮችን ለመተንተን ጥቅም ላይ ውሏል፡፡

### 2.2.4 ተግባራዊ (Functionalism) ንድፈ ሀሳብ

እንደ ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ አራማጆች አተያይ ማንኛውም የፎክሎር ዘርፍ በሚመረመርበት ወቅት የራሱ የሆነ ማኅበራዊ ተግባር አለው፡፡ Barnard (2004: 61) እንደሚገልጹት ፎክሎር ሶስት ዋና ዋና ተግባራትን ሊወጣ ይችላል፡፡ ከነዚህም ውስጥ አንደኛው የሰው ልጅን ሥነ ህይወታዊ እና ሥነ ልቡናዊ ተግባራት የሚወጣውና በBronislaw Malinowski ምርምሮች ውስጥ የተተገበረው ነው፡፡ ሁለተኛው የፎክሎር ተግባር የሚመነጨው ከራሱ ከሰው ልጅ ባህላዊ አወቃቀር እና በመዋቅራዊ ክፍሎቹ መሀል በሚደረግ መስተጋብር አማካኝነት ነው፤ የሚለው የRadcliffe-Brown የመዋቅራዊ-ተግባራዊነት ንድፈ ሀሳብ ነው፡፡ ሦስተኛው ፎክሎር ወይም ባህላዊ እሴቶች የአንድን ማኅበረሰብ አባላት አንድነትና ኅብር እንዲኖራቸው የማድረግ ተግባር አለው የሚለው የEmile Durkheim ንድፈ ሀሳብ ነው፡፡

እንደ Malinowski (1944: 150) አገላለጽ የተግባራዊነት ንድፈ ሀሳብ፣ ባህል የሰው ልጅ በአካባቢው የሚገጥሙትን ተጨባጭ ችግሮች ለመቅረፍ እና ተፈጥሯዊ ፍላጎቶቹን ለማርካት ሲል የፈጠረው ጠቃሚ መሳሪያ መሆኑን እንዲህ ሲሉ ያስረዳሉ፤ “A culture is essentially an instrumental apparatus by which man is put in a position the better to cope with the concrete specific problems that face him in his environment in the course of the satisfaction of his needs.” ለጥቀውም ባህላዊ ድርጊቶች፣ ሥርዓቶች፣ እሴቶች፣ የተለያዩ ባህላዊ ተቋማት፣ እና ሌሎችም የባህል ክፍሎች የተፈጠሩት የሰው ልጅ ለመኖር የሚያስፈልገውን የምግብ፣ ወሲባዊ ፍላጎቱን ለማርካትና ጎሳውን ለመመስረት የሚያስችለውን የሥነ ተዋልዶ፣ አካላዊ ምቾትን የሚያገኝበትን የመጠለያ፣ ለደኅንነቱ ዋስትና የሚሆነውን የጥበቃ፣ ከጭንቀትና ከውጥረት

አካሉን እንዲንቀሳቀስ የሚረዱትን የተለያዩ ተግባራትን የመስራት፣ ለእድገትና ልማቱ የሚያስፈልጉትን የስልጠና፣ እና ጤናው እንዲጠበቅለት የሚረዳው የማጽዳት፣ እንዲሁም የማኅበራዊ ሥርዓቱን ቀጣይነት ለማረጋገጥ እንደሆነ ገልጠው የተግባራዊነት ንድፉ ማጠንጠኛ ማእከልም ባህላዊ ቁሶች እንደሆኑ አንስተዋል፡፡ የሰው ልጅ በሙሉ ተፈጥሯዊ ፍላጎቶቹን ለማሟላት ቁሶች ያስፈልጉታል፤ እነዚያን ቁሳዊ ፍላጎቶች ለማሟላት ደግሞ ባህል ትልቁን ሚና ይጫወታል ይላሉ፡፡ “In all activities we find that the use of an object as a part of technically, legally, or ritually determined behavior leads human beings to the satisfaction of some need.” (1944: 155)

Barnard (2004: 61) በበኩላቸው Mair (1965: 234)ን ጠቅሰው የMalinowski ተግባራዊ አቀራረብ ከፎክሎር ማኅበራዊ ተግባራት ይልቅ የሰው ልጅ በተፈጥሮው ሊያረካቸው ለሚፈልጋቸው ግለሰባዊ ፍላጎቶች የሚያደላና የሰው ልጅ የማኅበራዊ ፍላጎት የሚያድርበት የምግብ፣ የሥርዓተ ተዋልዶ፣ የአካላዊ ምቾት፣ የደኅንነት፣ የግንኙነት፣ የእንቅስቃሴ እና የእድገት ሰባት ሂደታዊ የለውጥ ደረጃዎች ካሟላ በኋላ እንደሆነ እንደሚከተለው ያስረዳሉ፡፡

> The purpose of institutions is to meet the seven basis human needs; metabolism, reproduction, bodily comforts, safety, movement, growth, and health. Primary institutions provide for these needs and have personnel, ideology, a legal character, continuity, and purpose.
>
> It is the perspective concerned with actions among individuals, the constraints imposed by social institutions on individuals, and relations between the needs of an individual and the satisfaction of those needs through cultural and social frameworks.

በMalinowski አመለካከት የተገለጹት ግለሰባዊ ፍላጎቶች የሚረኩት በየባህሉ ውስጥ በሚገኝ ማኅበራዊ አወቃቀር ሲሆን፣ የማኅበራዊ መዋቅሩም ተግባር በውስጡ ያሉትን ግለሰቦች ሰብዓዊ ፍላጎቶች ማርካት ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ ማንኛውም ማኅበራዊ ተቋም የሚመሰረተው የግለሰቦችን ፍላጎቶች ለማርካት ሲባል ሲሆን በየባህሉ ውስጥ የሚገኙትም ሆነ የሚከወኑት ድርጊቶችም ሆነ የሚመረቱት ቁሶች ተግባር የግለሰቦችን ፍላጎቶች ማርካት ነው፡፡

Barnard (2004: 61) እንደሚያስረዱት የRadcliffe-Brown ትኩረትም ማኅበራዊ አወቃቀር ሆኖ በተለይም በአጠቃላይ ማኅበራዊ ሥርዓት ውስጥ ያሉ ንዑሳን ቡድኖች ወይም መዋቅራዊ

ክፍሎች እርስ በእርሳቸው በሚያደርጓቸው መስተጋብሮች ላይ መሆኑን፣ አንዱ መዋቅራዊ አላባ የሚያደርጋቸው ነገሮች ሁሉ ለወል ማኅበራዊ ሥርዓቱ የሚያደርገው አስተዋፅኦ መኖሩን ያስረዳሉ፡፡ “Structural-functionalism’ tends to be concerned less with individual action or needs, and more with the place of individuals in the social order, or indeed with the construction of the social order itself.”

Radcliffe-Brown (1952: 6) በይበልጥ የሚያተኩሩት በዘር ሀረግ በተዋቀሩ ተቋማት የእርስ በእርስ መስተጋብር አማካኝነት በሚፈጠር አወቃቀር ላይ ነው፡፡ በዘር በሚመሩ ማኅበረሰቦች ውስጥ በቤተሰብ፣ በማኅበራዊ ተቋማት፣ በፖለቲካ እና በኢኮኖሚ ንኡሳን ቡድኖች መካከል የሚደረጉ መስተጋብሮች የተቃኙት በተደነገጉ ማኅበራዊ ጠባዮችና ባህርያት ነው ብለው ያምናሉ፡፡ ስለዚህም በመዋቅራዊ-ተግባራዊ እሳቤ ውስጥ ግለሰቦች በራሳቸው ያን ያህል ትርጉም የላቸውም፤ ትርጉም የሚኖራቸው በማኅበረሰቡ ውስጥ ባላቸው ሥፍራ፣ ወይም በማኅበረሰቡ መስተጋብር ውስጥ በተሰጣቸው መዋቅራዊ ቦታ ነው፡፡ ለእሳቸው ዋናው ትኩረት ማኅበራዊ አወቃቀሮች በሚፈጥሩት መስተጋብር ላይ፤ ማኅበረሰባዊ የተግባራዊነት አቀራረብ ትኩረትም ከግለሰቦች ይልቅ በመዋቅር ላይ ነው፤ መዋቅር የሚያመለክተው ደግሞ የተደራጀ ሥርዓትን ወይም የተደራጁ ክፍሎች አወቃቀርን ነው፡፡

> When we use the term ‘structure’ we are referring to some sort of ordered arrangement of parts or components… the components or units of social structure are persons, and a person is a human being considered not as an organism but as occupying positions in a social structure (1952:6).

መዋቅራዊ ክፍሎች በማኅበራዊ ህይወት ውስጥ ሥርዓት ተበጅቶላቸው የሚሳተፉት፣ በሥርዓቱ ውስጥ ማኅበራዊ ደረጃዎች ያሏቸው ግለሰቦች ናቸው፡፡ የማኅበረሰቡ ውስብስብ የግንኙነት መረብ የተዋቀረው በግለሰቦች መካከል በሚካሄድ ማኅበራዊ ግንኙነትና የእርስ በእርስ መስተጋብር ነው፡፡ የማኅበረሰቡ አባል የሆነ ግለሰብም ወደደም ጠላም በማኅበራዊ ግንኙነቶች ለተዋቀሩት ህጎች፣ ስምምነቶች፣ ደንቦች እና ሥርዓቶች ራሱን ማስገዛት፣ መመራት፣ መገራት ይጠበቅበታል፡፡

Durkheim ደግሞ የፎክሎርን ተግባር የሚያጤኑት በፎክሎራዊ ድርጊቶች አወቃቀርና አያሌ ሰዎችን በአንድ ላይ እንዲያሰባስብ ባስቻለው ተፈጥሮው ላይ እንደሆነ Barnard (2004: 61-65) ገልጸዋል፡፡ ይህንንም ማኅበራዊ ተግባራት እንዴት እና ለምን የዳበሩ የባህል ክፍል እንደሆኑ

ማኅበራዊ አንድነትን (social solidarity and cohesion) ለመመስረት የሚያስችሉ ማኅበራዊ እውነታዎችን በመመርመር አሳይተዋል፡፡ ለምሳሌ ሰዎች በሃይማኖታዊ ሥርዓቶቻቸው ውስጥ የሚወክሏቸው ሃይማኖታዊ ቁሶች ራሳቸውን በተምሳሌት የሚገልጹባቸው ትእምርቶች ናቸው፡፡ አንዳንድ ቁሶች የወል ማንነትን ወካይ ሊሆኑ ይችላሉ፤ ይህም ውክልና የሚሰጠው በራሱ በማኅበረሰቡ ነው፡፡ ከነዚህ መካከል አንድ ማኅበራዊ ቡድን መለያው ወይም አርማው የሚያደርጋቸውንና የሚያምንባቸውን "የተከበሩ ነገሮች" (totem)ን በአስረጅነት ይጠቅሳሉ፡፡ Thompson (2005: 13) (Durkheim 1893)ን ጠቅሰው ስለተከበሩ ነገሮች 'totem' የሚከተለውን ይላሉ፤ "This visible symbol is law. In fact, wherever social solidarity exists, despite its immaterial quality, it manifests its presence by palpable effects, rather than remaining in a state of pure potentiality."

በዚህ ንድፈ ሃሳብ አተያይ መሰረትም የተጠኘው ማህበረሰብ "ሰዎችን በባዶ እጅ መጠየቅ ነውር ነው" የሚለውን ማህበራዊ ደንብ ወካይ (የጋራ ደንብ) በማድረግ በተለያዩ አውዶች ስጦታን መለዋወጡ የሚፈጥረው፣ የሚያዳብረው እንዲሁም የሚያስቀጥለው ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ባህላዊ፣ ሃይማኖታዊ እና ሥነ ልቡናዊ ጥቅም ምን ይመስላል የሚሉ ጉዳዮች ተተንትነዋል፡፡

## 2.3 ጽንሰ ሐሳባዊ ማዕቀፍ

### 2.3.1 ማኅበራዊ ደንቦች (social norms)

የሰው ልጅ ማህበራዊ ፍጥረት እንደመሆኑ እርስ በእርስ የሚያግባቡ ምልክቶችን እና ማህበራዊ ደንቦችን ፈጥሯል፡፡ በኑሮው ውስጥም የቡድኑ አባላት ከደንቡ እንዳይወጡ የሚያደርጉትን ይከታተላል፣ በጎውን ደግፎ ተመሳሳይ ያደርጋል፣ ክፉውን ይነቅፋል፣ ለቀጣይ ትውልድ ያስተላልፋል፡፡ ማህበራዊ ደንቦች በተወሰነ ማህበራዊ ቡድን ውስጥ ተቀባይነት ኣላቸው ተብለው የሚታሰቡ ያልተጻፉ የእምነት፣ የአመለካከት እና የባህሪ ህጎች ሲሆኑ በማህበራዊ ቡድኖች ውስጥ ተቀባይነት ያላቸው የባህሪ ደረጃዎች ናቸው፡፡ እነዚህ ህጎች በማህበረሰቡ ውስጥ ሥርዓትን መተንበይ እና እንዴት ማድረግ እንዳለብን ወይም ተግባራዊ ለማድረግ የሚጠበቅ ሀሳብ ይሰጣሉ፡፡ "ባህል ሰዎች በዙሪያቸው ያለውን ማኅበራዊ እውነታ የሚረዱበት፣ የሚተረጉሙበት፣ የሚገልጹበት እና ምላሽ የሚሰጡበት የጋራ የሆነ እውቀት እና ስርዓት ነው፡፡" ሊድራች (1995) የባህላዊ ደንቦች ወይም ማህበረሰቡ የሚተዳደርባቸው ህጎች በማህበራዊ ህይወት ውስጥ ስምምነት እንዲኖር ይጠቅማሉ፡፡ ከእነዚህም ውስጥ "ስጦታዎች ውጤታቸው ማህበራዊ አብሮነትን እና ግንኙነታቸውን ጠብቆ ማቆየት" እንደሆነ Mauss

(1966) ይገልጻል። ስለዚህ ስጦታ፣ የበጎ አድራጎት እና ትብብር የመተዳደሪያ ደንቦች፣ የመልሶ ማቋቋም ደንቦች እና የስጦታ ልውውጦች ከጊዜ ወደ ጊዜ የሚደጋገሙ እንደመሆናቸው መጠን የግለሰባዊ ግዴታ፣ ምስጋና እና መተማመንን የመሳሰሉ ማህበራዊነትን የሚያጠናክሩ ጉዳዮች በአንድ ጊዜ የማስተሳሰፍን ሚና አላቸው በማለት ይገልጻል።

ስጦታ መለዋወጥ በማኀበረሰቡ ደንብ መሰረት የሚተገበር እና የራሱ የሆነ ህግ ያለው ልማድ ሆኖ እናገኘዋለን። መስጠት በሰው ዘንድ ብቻ ሳይሆን በእንስሳትም ዘንድ የተለመደ ባህርይ መሆኑን በማስታወስ ጉዳዩን ተፈጥሮአዊ የሚያደርጉት አሉ። ነገር ግን ሰው ከእንስሳት የሚለየው ማህበራዊ ስሪት በመሆኑ ለሚያቀርበው ስጦታ ህግ እየሰራለት በመሄድ አሁን ያለውን ቅርጽ ይዟል። በማህበረሰቡ ዘንድ ሰው ደስታ ወይም ሀዘን የተለያየ ነገር ሲያጋጥመው ሌሎችን የሚጠይቀው ከስጦታ ጋር ነው። ለምሳሌ፦ ሰው ሲታሰር "እግዚአብሔር ያውጣህ" የሚባለው ከስጦታ በተለይም ከምግብ ቋጠሮ ጋር ነው። የወለደች አራስ ሴት የሚጠይቀው፣ የክርስትና እናት እና አባት በደብረታቦር ክርስትና ልጃቸዉን የሚጠይቁት ከስጦታ ጋር ነው። ሰው ሲያገባ "እንኳን ለዚህ አበቃህ" የሚባለው ከስጦታ ጋር ነው። ሀዘን የደረሰበትን ሰው እህል ውሀ ተዋጥቶ ነው የሚተዛዘነው ከመስጠት ጋር ነው። ሚች የሚሸኘው ከገንቦ ጠላና ከለምለም እንጀራ ጋር ነው። በእንግድነት ባዶ እጅ መሄድ እንደ ነውር ተግባር የሚቆጠር ነው። የፈጣሪ፣ የቅዱሳን፣ የመላእክት እርዳታን ለመጠየቅ በስማቸው ዝክር፣ ስዕለት እንዲሁም መስዋዕት ስጦታ ይቀርባል። በአጠቃላይ ደስታ ወይም ሀዘን ሲገጥም ወይም የአምልኮ ጉዳይ ሲፈጸም በጋራ እና እርስ በእርስ በመደጋገፍ አንዱ ለሌላው በመስጠት ነው። ምክንያቱም እንደነዚህ ባሉ ሁኔታዎች አንዱ ሌላውን የመጠየቅ ልማድ ጠንካራ በመሆኑ ስጦታ ለመመላለስ ያለው እድልም በዚያው ልክ ሰፊ ሆኖ እናገኘዋለን። በተጨማሪም ሰጦታውን በመቀበል ውስጥ ግኑኝነትን መፈለግ ባለመቀበል ደግሞ አለመፈለግን ለመጠቆም የሚያገለግል ማህበራዊ እሴት ነው። Mathews (2017) በስጦታ ውስጥ ምን ይስጥ፣ እንዴትስ ይቀበል፣ ምንስ አይሰጥ፣ ልውውጡ እንዴት ይካሄድ፣ ስጦታውን ከተቀበለ በኋላ ምን ይደረግ ወዘተ. የሚሉ ጥያቄዎች ሁሉ በማህበረሰቡ ደንብ ውስጥ ምላሽ አላቸው። ይህ ጥናትም የፎክሎር ጥናት እንደሚመክረው ስጦታ በማህበራዊ ኑሮ ውስጥ ያለውን ሚና፣ ማህበረሰቦቹ ከጊዜ ወደ ጊዜ በተደጋጋሚ የሚለዋወጡአቸው ስጦታዎች መካከል ያሉ ደንቦች እና በሚደረጉ ልውውጦች ውስጥ እርስ በእርስ የመደጋገም ተስፋዎች ላይ በማተኮር ለማህበረሰቡ ደንብ እና ህግ ያላቸው ታዛዥነት፣ ትርጉም እና ጠቀሜታዎች ላይ አተኩሯል።

### 2.3.2 ሀገረ ሰባዊ ልማድ

ሀገረሰባዊ ልማድ Dorson (1972) አራቱ የፎክሎር ዘውጎች ብሎ ከዘረዘራቸው ውስጥ ማህበረሰቡ ቅደም ተከተላቸውን ጠብቆ እና ህግና ስርዓት አውጥቶላቸው በተደጋጋሚ የሚከውናቸውን ድርጊቶች የሚመለከት ዘውግ ነው። ይህ የፎክሎር ዘውግ ፎኩ እንደ እርግዝና፣ውልደት፣ ግዝረት፣ ጋብቻ፣ ከአንድ ማህበራዊ ደረጃ ወደ ሌላ ከፍ ማለትን፣ ሞትን የመሳሰሉ የህይወት አጋጣሚዎቹን፣ በወቅቶች መፈራረቅ የሚመጡ እንደ ምርት ማምረት ያሉ ድርጊቶችን ተከትሎ የሚከውናቸው ተደጋጋሚ ድርጊቶች ናቸው። ልማድ ነገሮችን ለማከናወን በማህበረሰቡ ህግ እና ስርዓት መደበኛ በሆነ መንገድ የሚከዎን የቡድን ጥበብ ነው። ይህም በዓመት ውስጥ ከተወሰኑ ጊዜያት ወይም ወቅቶች ጋር፣ ከህይወት ምዕራፍ ሽግግር ጋር፣ ከክብረ በዓላት እና በማህበረሰቡ ዘንድ ከፍተኛ ማህበራዊ ደረጃ የሚሰጣቸው ታዋቂ ሰዎች መታሰቢያዎች ጋር፣ እንዲሁም ከእምነት ጋር የተያያዙ ጉዳዮች እንደሆኑ Sweterlitsch (1997) እንዲህ ያስረዳል።

> Customs are traditional and expected ways of doing things, and they are performed with enough regularity that they become part of a group's social conventions. Calendrical customs are associated with particular times of the year, rites of passage are associated with life transitions, festivals may honour notable individuals or commemorate significant events, and other customs may be related to beliefs held in common by a group (1997, 168).

ከዚህ በተጨማሪ የተለያዩ ምሁራን ለሀገረሰባዊ ልማድ የተለያዩ ብያኔዎችን የሰጡ ሲሆን የሚከተሉትን ለአብነት ማንሳት ይቻላል።

- ✓ "ሀገረሰባዊ ልማድ አንድ ማህበረሰብ ደጋግሞ የሚከውነው፣ ቅደም ተከተላዊ ስርዓት ያለው ማህበረሰባዊ ጥበቦች መጠሪያ ነው" (Dorson, 1972፤3)።
- ✓ "ማህበራዊ ልማድ ሰዎች አጥብቀው የያዟቸው እምነቶችና ልማዶች መነሻ ምንጫቸውና ትርጉማቸው ምንድነው? ሰዎች በአንድ ነገር ለምን ያምናሉ? የሚያምኑባቸው ነገሮችስ ምንድናቸው? የተወሰኑ ልማዶችንስ ለምን ይከተላሉ? የሚሉና መሰል ጥያቄዎችን ለመመለስ የሚሞክር የፎክሎር ዘርፍ ነው" (ፈቃደ፣1991፤1314)።
- ✓ "ልማድ ተደጋጋሚ የሆነ የድርጊት እርምጃ ወይም አንድ የተለመደ ነገርን ደጋግሞ ማድረግ ሲሆን ለባህል አጥኚዎች ደግሞ፣ ልማድ ማለት ከዕለት ተዕለት ገጠመኞች

የሚለዩ ወይም የሚሠሩ ድርጊቶች፣ ለምሳሌ፦ የአንድ ቡድን አባል መሆንን የሚያመለክት ዘይቤን፣ የተለዩ ቃላት፣ ምልክቶች ወይም ድርጊቶች እና ተደጋጋሚ ባህሪን የሚመለከት ጉዳይ ነው" (Sims and Stephens, 2005;16)፡፡

- ✓ "ልማዶች የጋራ እውቀቶችን የሚፈጥሩ ሚዛናዊ ዘዴዎች ናቸው" (Engert, 2016; 341) ፡፡
- ✓ "ሀገረሰባዊ ልማድ አንድ ማህበረሰብ አብሮ በመኖር ሂደት በረጅም ጊዜ ልምምድና ድግግሞሽ የሚያዳብረው ማህበረሰቡም ተቀብሎ በየጊዜው የሚደጋግመው ድርጊትና የባህል አካል ነው" (Vehrer, 2017; 368)፡፡

ከዚህም የምንረዳው በጋራ በመኖር ሂደት ውስጥ ፎክ እንደ ቡድን በጋራ የሚቀበሉት የጋራ አኗኗር ጥበብ ወይም ሎር አለ፡፡ ይህ ሎር የሚከወንበት የራሱ የሆነ አውድ፣ መቼት እና የክዋኔ ስርዓት ይኖረዋል፡፡ ከእነዚህ ሎሮች መካከል ተደጋጋሚነቱ የበዛው ሀገረሰባዊ ልማድ ነው፡፡ ሰዎች በጋራ ሲኖሩ በጋራ የሚቀበሉት፣ የሚያምኑት፣ እንደ ልዩ ጀግና አድርገው የሚቆጥሩት፣ ልዕለሰብ ወይም ሰው ይፈጥራሉ ጀግና ወይም መሪ ብለው የሰየሙት አካል የተወለዱበት፣ የጀግንነት ተግባር የፈጸሙበት ወይም ያረፉበት ቀን ይታሰባል፣ የፈጸሙት ተግባር አርዓያ ሆኖ ህግና ስርዓታቸውን ማስፈጸሚያ፣ወግ፣ ልማድና ስርዓታቸውን ማስተማሪያ ሆኖ፣ ዕለት ዕለት አልያም በሳምንት፣በወር፣ በዓመት እየደጋገሙ ይከውኑታል፡፡ ስለዚህ ሀገረሰባዊ ልማድ አንድ ማህበረሰብ ለህይወቱ ጉዳት ያደርሱብኛል የሚላቸውን ድርጊቶችና አስተሳሰቦች የሚያርቅበት፣ ይጠቅሙኛል የሚላቸውን ደግሞ የሚተክልና የሚያስቀጥልበት በኑሮው ውስጥ ዘወትር የሚተገብራቸው እና እንደ አንድ ቡድን የተለያዩ የህይወት አጋጣሚዎችን ተረድተው፣ መቼቱን፣ አውዱን እና ቅደም ተከተሉን ጠብቀው በተደጋጋሚ የሚከውኗቸው ድርጊቶችን የሚመለከት የፎክሎር ዘውግ እንደሆነ እንረዳለን፡፡

ሀገረሰባዊ ልማድን አብዛኛው የፎክሎር ምሁራን በአራት ዘርፎች ይከፍሉታል፡፡ ለምሳሌ Dorson (1972,4) እነርሱም፦ ሀገረሰባዊ እምነት፣ ሀገረሰባዊ ጨዋታ፣ ሀገረሰባዊ መድሃኒት እንዲሁም ፌስቲቫል እና ክብረ በዓላት ናቸው፡፡ ይህ ዘርፍ ለአራት የተከፈለበት ምክንያት ለአጠናን እንዲመች እንጂ አንዱ በሌላው ቅንጣት ውስጥ የሚኖርበት አጋጣሚ ሰፊ ነው፡፡ ለምሳሌ፦ የዚህ ጥናት ርዕስ የሆነው ስጦታ ሲከወን፦ ስጦታ በግራ እጅ አይሰጠም፣ በደስታ ወይም በሀዘን ጊዜ የቀረበ ስጦታ እንደ ለሰዎች እንዳለው የ ቅርበት መጠን እንዲህ አይነት የህይወት አጋጣሚ በሚከሰትበት ጊዜ ውለታ መመለስ አለበት፣ መስዋዕት እና ስዕለት ሲቀርብ

የስጦታው መልክ እና ንጽህና የስጦታው ዓይነትና መስፈርት የሚወሰነው በማህበረሰቡ ልማድ መሰረት ነው። እንደዚህ ከሚሉ ህጎች በተጨማሪ የሚቀርበው ስጦታ የሚዳሰሰውን ወይም የሚጨበጠውን ጌጣጌጥ፣ መገልገያ እቃዎች፣ የግል ንብረቶች ወዘተ. ወይም የሚቀመሰውን ባህላዊ ምግብ እና መጠጥ ስለሚያካትት በቁሳዊ ባህል ስር፣ ስለ መስጠት የተተረቱ ተረቶችን፣ የተገጠሙ ቃል ግጥሞችን፣ አፈታሪኮችን በመሰብሰብ ደግሞ ከስነ ቃል ጋር በማያያዝ ሊጠኑ ይችላሉ። በሌላ በኩል ደግሞ ከዋኞችን በተመለከተ ለምሳሌ፦ ስጦታው ለእምነት ማስፈጸሚያነት ሲውል፣ ለውቃቤ የጥር፣ የሰኔ፣ የአዲስ ዓመት ላይ የደም ግብር ሲቀርብ፣ ወይም ስጦታ ለፈጣሪ ሲቀርብ ከሀገረሰባዊ እምነት ጋር በማያያዝ፣ ስጦታ ለሰዎች የሚቀርብ ሲሆን ደግሞ ከተለያዩ ፌስቲቫል እና ከበራዎች ጋር፣ ተያይዞ የክዋኔ አንድ አካል ሆኖ ልናገኘው እንችላለን። በአጠቃላይ ብቻውን የቆመ የፎክሎር ቅንጣት ለማግኘት ያዳግታል።

በሀገረሰባዊ ልማድ የፎክሎር ዘውግ ስር ክብረ በዓላት፣ ፌስቲቫሎች፣ የሕይወት ዑደቶች የተለያዩ መንፈሳዊና ባህላዊ (ዓለማዊ) ስርዓቶችን በሚያካትተው ፌስቲቫል እና ክብረ በዓላት ዘርፍ ይጠቃለላሉ። የዚህ ጥናት ርዕሰ ጉዳይ የሆነው ስጦታ መለዋወጥ ባለው ባህርይ ምክንያት በሀገረሰባዊ ልማድ ፎክሎር ክፍል ስር በማካተት ለጥናት ቀርቧል። ፎኩ እምነቱን፣ ማንነቱን፣አስተሳሰቡን የሚገልጽበት እና ከሌሎች ጋር ለመኖር ወይም ማህበራዊ ግኙነቱን ለማጠንከር በተለይም አይቀሬ በሚባሉ የህይወት ዑደቶች ከመወለድ ጀምሮ በተለያዩ የዕድገት ደረጃዎች ውስጥ እያለፈ እስከ እለተሞቱ የሚያደርጋቸው የልደት፣ የምርቃት፣ የጋብቻና የሞት ወዘተ. ስርዓቶችን እንዲሁም በተለያዩ ዓመታዊ ክብረ በዓላት እና ከፍተኛ ቦታ የሚሰጣቸውን ልዩ ቀኖች ስጦታ በመለዋወጥ ያከብራቸዋል። ይህንም ልማድ ባህልና ስርዓቱን ጠብቆ አንዱ ለሌላው ያደርገዋል። ለምሳሌ፦ አንዲት ሴት ልጅ ስትወልድ (እናት ስትሆን) "የማርያም አራስ" ተብላ ለመጠየቅ የማህበረሰቡ ደንብ እንደሚፈቅደው እና እንደ ቀረቤታ መጠን በግልም በቡድንም ስጦታ ይሰጣታል፤ "እንኳን ማርያም ማረችሽ" ትባላለች ።እርሷም በተራዋ ለሌሎች እንዲሁ ታደርጋለች። ይህ ህይወት እስካለ ድረስ የሚቀጥል ተደጋጋሚ የሆነ ድርጊት ወይም ልማድ ነው። ስጦታ የመቀያየር ልማድ ማህበራዊ ኑሮን በማጠንከር በኩል አዎንታዊነቱ የጎላ እንደሆነ እንረዳለን። "በዝግመተ ለውጥ አስተሳሰብ ማህበረሰቡ ስጦታ የመስጠት ልማዱ እርስ በእርስ ቅርርብ ለመጀመር እና ቀስ በቀስም ግንኙነትን አጠንክሮ ወደ መተማመን እና ትብብር እንዲያድግ ያደርገዋል" በማለት በድግግሞሹ ምክንያት ከጊዜ በኋላ የሚመጡ ስጦታ የመቀያየር ጠቀሜታዎች ሎርን እና ቤንትሊ ይገልጻሉ (H. Lorne & W.

Bentley, 1997,485)። በደብረ ኤልያስ ከተማ ውስጥ በተለያዩ ክንውኖች፣ በክብረ በአላት፣ በወቅቶች መፈራረቅ፣ በዘመን መለወጫ፣ በልደት፣ በምርቃት፣ በጋብቻ፣ በሞት፣ በተለይም በደስታ እና ሀዘን ቀናቶች አንዱ ከሌላው ጋር አብሮነቱን ከሚያሳይበት መንገድ አንዱ ስጦታዎችን በመስጠት ነው የዚህ ጥናት ትኩረትም እንደእነዚህ ባሉ አጋጣሚዎች ያሉ ስጦታ የመቀያየር ልማዶች በመግለጽ ትዕምርታቸውን እና ፋይዳቸውን መተንተን ነው።

**መታዘዝ**

መታዘዝ ለነባር ማኅበራዊ ህጎችና ደንቦች መገዛት ነው። አንድ የማኅበራዊ ቡድን አባል በአባልነቱ ለመቀጠልና ማኅበራዊ ተቀባይነት ለማግኘት ወደደም ጠላም ለነባር ስምምነቶች፣ ማኅበራዊ ስርዓቶችና ህጎች ራሱን ማስገዛት፣ መታዘዝ ይኖርበታል። በመታዘዝ እሳቤ ውስጥ የሚገኝ መብት፣ የሚጣል ግዴታም ይኖራል። ከመብቶች መካከል በታመመ ጊዜ መጠየቅ፣ በደከመ ጊዜ መረዳት፣ ባዘነ ጊዜ መጽናናት ሊጠቀሱ ይችላሉ። ግዴታዎቹም ላገኛቸው መብቶች፣ ለተዋሉለት ውለታዎች በዓይነት መመለስ፣ ለመመለስ መጣጣር፣ ካልቻለ ደግሞ ትሁትና ቅን ሆኖ መታየት ይኖርበታል። ያን ካልተገበረ ግን ለማኅበራዊ ደንቦች እንደማይታዘዝ ተቆጥሮ ማኅበራዊ ውግዘት፣ መነጠልና መገለል እጣው ይሆናል።

በተጠኚው ማኅበረሰብ ልማድ ውስጥም ስጦታ መስጠትም ሆነ መቀበል ለማኅበራዊ ደንቦች እንደመገዛት ይቆጠራል። የዚህ ጥናት ትኩረትም በደብረ ኤልያስና አካባቢው በሚኖረው ማኅበረሰብ ልማድ ውስጥ የተለመዱ ስጦታዎችን በመግለጽ፣ ለመታዘዝ ያላቸው አበርክቶ ምን እንደሆነ በጥልቀት ተመርምረዋል።

### 2.3.3 ስርዓተ ከበራዎች

ክብረ በዓላት እና ስርዓተ ከበራዎች ከሀገረሰባዊ ልማድ ዘርፍ ስር የሚመደቡ የተለያዩ የህይወት ገጠመኞችን መነሻ በማድረግ በተለያዩ ስርዓቶች የሚከበሩ ልዩ ቀናቶች ናቸው። የሁለቱ መሰረታዊ ልዩነት የስርዓተ ከበራ ምክንያት አብዛኛውን ጊዜ ሃይማኖታዊ መነሻ ያለው መሆኑ ነው። ይህን አስመልክቶ ሰሎሞን (2007፣ 159) አንድ ማህበረሰብ ያለውን ሃይማኖት እና ባህል መነሻ በማድረግ በከፍተኛ ቅደም ተከተላዊ ስርዓትና በተደጋጋሚ የሚከውናቸው ማህበረ ሃይማኖታዊ ድርጊቶች እንደሆኑ ይገልጻል። በተጨማሪም እነ ሲምስ ደግሞ ሪችዋሎች ከልደት፣ ከጉርምስና ዕድሜ፣ ከጋብቻ እና ከሞት ጋር የተቆራኙ እንደሆኑ እና ከዋኞቹንም ወደ አንድ ቡድን ልማድ የማስገባት ወይም የማስወጣት ሀይል እንዳላቸው Sims and Stephens

(2005, 92) ይገልጻሉ:: ስርዓተ ከበራዎችን ምሁራን በተለያዩ ዘርፎች መድበዋቸዋል ነገር ግን Bell (1977) አመዳደብ ከጥናቱ ጋር የተስማማ ሆኖ ተገኝቷል:: Bell (1977,94) ስርዓተ ከበራዎችን በስድስት ዘርፎች ከፍላዋለች:: እነርሱም፦ የሽግግር ስርዓቶች (rite of passage)፣ የጊዜ ሰሌዳዊ እና የመታሰቢያ ስርዓት (Calendrical and commemorative rites)፣ የልውውጥና የቁርባን ስርዓት (rites of exchange and communion)፣ የስቃይ ስርዓት (rites of affliction)፣ የግብዣ የጾምና ፌስቲቫሎች ስርዓት (rites of feasting, fasting and festivals) እና የፖለቲካ ስርዓተ ከበራዎች (political rituals) የሚሉ ናቸው:: በዚህም ምደባ ውስጥ እያንዳንዱ ዘርፍ የተለያዩ ቅንጣቶችን ይዟል:: ይህ ጥናት በእነዚህ ቅንጣቶች ውስጥ ያለውን የስጦታ ልማድ ይዳስሳል::

- ✓ የሽግግር ስርዓቶች (rite of passage)

የሽግግር ስርዓቶች የሚባሉት ከመወለድ ጀምሮ እስከ ሞት ድረስ ያሉ የህይወት ደረጃዎች ተከትሎ የሚቀርቡ ስርዓተ ከበራዎችን ያጠቃልላል:: እንደ Bell (1977) ገለጻ እነዚህ የአምልኮ ሥርዓቶች እንደ የወሊድ እና የጉርምስና ዕድሜ ካሉ ባዮሎጂያዊ ለውጦች ጋር የተዛመዱ ሊሆኑ ይችላሉ:: Bell (1977,95) የህይወት አውራ ጎዳና ስርዓቶች አንድ ልጅ ከእናቱ አካል ሲወጣ የልደት ስነ ስርዓቶች፣ የመራባት እና የወጣት ጉልምስና ከሚያስከትሉ የሆርሞን ለውጦች ጋር የሚከበሩ ስርዓቶች ናቸው:: በጥናቱ ውስጥ በመወለድ ጊዜ ለተወለደው ልጅ እና ለእናት "ከማሪያም አራስ መጠየቂያ" ስጦታ ጀምሮ፣ የክርስትና አባት እና የክርስትና እናት ስጦታዎች፣ ከአንድ እድሜ ወደ ሌላ መሸጋገር የልደት ቀን አስመልክቶ የሚሰጡ ስጦታዎች፣ በጋብቻ ውስጥ ለሰርግ የሚሰጡ ስጦታዎች፣ የሞት ቀን ቤተሰብ ለማጽናናት የሚደረጉ የማስተዛዘኛ ስጦታዎች ወዘተ. ተዳሰዋል::

- ✓ ጊዜ ሰሌዳዊ እና የመታሰቢያ ስርዓቶች (Calenderical and commemorative rites)

የጊዜ ሰሌዳ እና መታሰቢያ ስርዓተ ከበራዎች ጊዜን ጠብቀው በብርሃን፣ በአየር ሁኔታ፣ በግብርና ሥራ እና በሌሎች ማህበራዊ እንቅስቃሴዎች ወቅታዊ ለውጦች ጋር ተያይዘው በተደጋጋሚ የሚከበሩ ናቸው (Bell 1977, 102):: ከእነዚህ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ስጦታዎች ምርት ከመሰብሰብ ጋር ተያይዞ እሸት ቅመሱ እና ማርያም ባርኪ፣ ክረምት አልፎ አዲስ ዓመት ሲከበር የአደይ አበባ እና እንግጫ ስጦታ፣ ሃይማኖታዊ ክብረ በዓላት ሲከበሩ የሚደረጉ የበዓል ስጦታዎችን ያጠቃልላል::

✓ የልውውጥ እና የቁርባን ስርዓቶች (Rites of Exchange and Communion)

ከታወቁት የሃይማኖታዊ ስነ ስርዓቶች ምሳሌዎች መካከል ሰዎች አንድን ነገር በምላሹ ተግባራዊ እና ቀጥተኛ በሆነ ተስፋ ለአምላክ ወይም ለአማልክት የሚያቀርቡበት እንደ ጥሩ መኸር እና ረጅም ዕድሜ ወይም እንደ ረቂቅ እና ተጨባጭ የሆኑ የጸጋ እና የቤዛነት ልውውጦች ያሉ ስርዓቶች እንደሆኑ Bell (1977,108) ትገልጻለች። በዚህም ውስጥ ሰዎች እና ፈጣሪ ወይም አማልክት የሚገናኙበትን ስጦታዎች ማንሳት ይቻላል። ለምሳሌ፦ በክርስትና አስተምህሮ በቁርባን ስርዓት ውስጥ አማኞቹ የፈጣሪን ሥጋ እና ደም ይቀበላሉ። "ክርስቶስ ዓርብ ሊሰቀል ሲል ሐሙስ ማታ ስለ ሰው ልጅ ድህነት የሚቆረሰውን ሥጋውን እና የሚፈሰውን ደሙን አስረድቶ ህብስቱን ወደ ሥጋ መለኮት ወይኑንም ወደ ደመ መለኮት ለወጦ ሰጠን በምንቆርብበት ጊዜም ይለውጥልናል" ብለው ያምናሉ ማቴ (26፥26)፣ ማር (14፥38)፣ ሉቃ (22፥19)። በዚህም ስርዓት መሰረት የቁርባን ስርዓት በማድረግ የጌታን ሥጋ እና ደም ይቀበላሉ። ይህም የዘለዓለም ህይወትን ለማግኘት ከፈጣሪ የተሰጣቸው ትልቁ ስጦታ ነው። ዮሐ (6፥53) እነርሱም ካላቸው እና ከሚያገኙት ነገር ለፈጣሪ መስዋዕትን ያቀርባሉ። ስለዚህ በዚህ የከበራ ዓይነት ውስጥ ስጦታ ሰዎችን እና አማልክትን የሚያገናኝ ነገር ሆኖ በሰፊው እናገኘዋለን።

✓ የመከራ ስርዓቶች (Rite of affliction)

እነዚህ ስርዓተ ከበራዎች በኑሮ ውስጥ የሚፈጠሩ አደጋዎች ተከስተው ከነበረ እንዳይደገሙ ወይም እንዳይገጥሙ በሚል የሚከበሩ ናቸው። ይህን አስመልክቶ "የመከራ ሥነ ሥርዓቶች የሰው ልጆችን በመከራ ያሰቃያሉ ተብለው የሚታሰቡትን መናፍስት ተፅእኖ ለመቀነስ በሚል የሚከወኑ ስርዓቶች" እንደሆኑ Bell (1977፣115) ትገልጻለች። የመከራ ስርዓተ ከበራዎች ብዙ የማህበረሰቡን ክፍሎች ወደ ድርጊቱ ይጎትታሉ። ለዚህም ምክንያቱ ራስን እና የራስ የሆነውን ነገር ከአደጋ ለመጠበቅ የሚደረግ በመሆኑ ነው። በእነዚህ ስርዓተ ከበራዎችም ውስጥ ስጦታ ያለው ሚና ከፍተኛ ነው። ለምሳሌ፦ አንድ ሰው የሆነ ክብረ በዓልን ጠብቆ በግ የማረድ ልማድ ከነበረው ሁልጊዜም ማድረግ አለበት አለበለዚያ ግን አደጋ ይደርስበታል ተብሎ ይታመናል። ማህበረሰቡ የሚፈራውን ነገር እንዳይከሰት ከተከሰተ ደግሞ እርሱ ወደሚፈልገው ሰላማዊ ህይወት እንዲመለስ "እንዲህ እሰጣለሁ" በማለት ስዕለት የመሳል ልማድ አለው። ስዕለት ደግሞ የስጦታ አንድ ቅንጣት ነው። በተጨማሪም ዝክር ማድረግ፣ አስራት በኩራት መክፈል፣

ምጽዋት መስጠት፣ መስዋት ማቅረብ፣ የደም ግብር ማድረግ ወዘተ. ከእነዚህ ጋር ተያይዘው የሚነሱ ስጦታዎች ናቸው።

✓ የመጾም፣ መፈሰክ እና ክብረ በዓላት ስርዓቶች (Fasting, Feasting and Festivals)

ይህ የስርዓተ ከበራ አይነት የጾም መያዝን ወይም ቅበላን፣ በጾም ወቅት ያሉ ስርዓቶችን ፣ ከጾም ማለቅ ወይም መፈሰክ ጋር ያሉ ስርዓቶችን እና ክብረ በዓላቶችን ያጠቃልላል። እነዚህ ስርዓቶች ወቅትን ጠብቀው የሚመጡ ሃይማኖታዊ ከበራዎች ናቸው። በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ውስጥም ሆነ በሙስሊሙ ማህበረሰብ የሚጾሙ የተለያዩ አጽዋማት ይገኛሉ። በክርስትና ህግ ምጽዋት መስጠትና ድሆችን ማሰብ የሁልጊዜ ተግባር መሆን እንዳለበት የሃይማኖቱ ህግ ያዛል ፤ በሙስሊሙም ዘንድ ተመሳሳይ ነው። ነገር ግን በጾም እና በመፈሰኪያ ወቅት ለድሆች መስጠት ከሌላው በተለየ አብዝቶ ይተገበራል። በተጨማሪም በዓላት የሰዎችን ማህበራዊ ግንኙነት ለማጠንከር መንገድ የሚከፍቱ እና ለመሰጣጣት የሚያነሳሱ ናቸው። በቅበላ እና በክብረ በዓላትም ወቅት ዘመድ ከዘመዱ ተጠራርቶ አንዱ ለሌላው በመስጠት ያሳልፈዋል። በዚህ የከበራ ስርዓት ውስጥም ጾምን ወይም የጾም መፈሰክ ተከትሎ የሚቀርቡ እንደ ድግስ ወይም ግብዣ ያሉ የምግብ የስጦታ ዓይነቶች ተዳሰዋል።

✓ የፖለቲካ ስርዓቶች (Political Rites)

ፖለቲካዊ ስርአተ ከበራዎች በተለይ የፖለቲካ ተቋማትን (እንደ ንጉሥ ፣ ግዛት ፣ የመንደሩ ሽማግሌዎች) ወይም የልዩ የምርጫ ክልሎች የፖለቲካ ፍላጎቶችን የሚገነቡ ፣ የሚያሳዩ እና የሚያራምዱ ስርዓቶችን ያካተቱ ናቸው ሊባል ይችላል። Bell (1977,128) ፖለቲካዊ ስርአተ ከበራዎች የስልጣን ሹመት፣ ሽግግር ወይም ሽረት ሲደረግ ወይም አንዲት ሀገር የነጻነት ወይም የድል በዓሏን ስታከብር የሚደረጉ ስርዓቶችን የሚያጠቃልል ነው። በዚህም ስርዓተ ከበራ ውስጥ ስጦታ ያለው ሚና ቀላል አይደለም። ኢትዮጵያ በንጉሳውያን አገዛዝ በነበረችበት ወቅት የሀገር ገዠዎችን ለመተያያ፣ እጅ ለመንሳት፣ ክብር ለማሳየት ፣ አንዱን ሀገር ከሌላው ጋር ግንኙነትን ለማጥበቅና ለማስቀጠል ወዘተ. ስጦታ ከፍተኛ ሚና እንደነበረው የታሪክ ድርሳናትና በየሙዚየሙ የተቀመጡ ለኢትዮጵያ ከየሀገሩ የተላኩ ስጦታዎች ያስረዳሉ። እነዚህ ስርዓተ ከበራዎች እንደ ጊዜው የፖለቲካ ስርዓት ሊለዋወጥ ቢችልም የሀገሪቱ የድል እና የመታሰቢያ በአላትን ለጀግኖች የምስጋና እና የክብር ሽልማቶችን በመስጠት ይከበራል።

### 2.3.4 የስጦታ ልማድ

የመስጠት ጽንሰ ሀሳብ እንደ ግለሰብ በሁሉም አስተሳሰብ ውስጥ ይኖራል ተብሎ ይገመታል:: አተገባበሩ ግን ይለያያል :: መስጠት እንደ ቡድን የራሱ የሆነ ደንብ፣ህግ እና ስርዓት፣ እንዲሁም የክዋኔ አውድ ተለይቶለት በተለያዩ ስያሜዎች በተለያዩ ማህበረሰቦች ዘንድ ይተገበራል:: ለምሳሌ፣ ሰዎች ከልዕለ ተፈጥሮ ጋር ከሚያደርጓቸው ስጦታዎች መካከል በክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች ዘንድ የተለመዱ እንደ መስዋዕት ማቅረብ፣ ስዕለት ማስገባት፣ አስራት በኩራት መስጠት ወዘተ. ስጦታዎችን እናገኛለን:: እነዚህ ስጦታዎች የተለያየ ምክንያት፣ የተለያየ የክዋኔ አውድ እና የተለያየ መቼት ያላቸው ነገር ግን እያንዳንዳንዱ አማኝ ከእምነቱ ህግና ስርዓት ሳይወጣ ከሚከውናቸው ልማዶች ናቸው:: Schwartz & Howard (1982, 1984) "helping behavior is affected by norms." የመርዳት ጠባይ በማህበረሰብ ደንብ ወይ ልማድ ተጽእኖ ይደረግበታል::" በማለት የማህበረሰብ ደንቦች ስጦታ ላይ ያላቸውን ሚና የጎላ እንደሆነ ያስረዳሉ::

ከእነስኳርትዝ ሀሳብ የምንረዳው ነገርም መስጠት በተለያዩ ሀገራት የሚኖሩ ሰዎች የሚተገብሩት ጉዳይ ቢሆንም አተገባበሩ የአካባቢውን ባህል እና የአኗኗር እንዲሁም የህይወት ፍልስፍና መሰረት ያደረገ መሆኑን ነው:: መስጠት በራሱ ልማድ ሊባል አይችልም:: በመስጠት ውስጥ ያሉ የማህበረሰብ ስምምነቶች ግን ልማድ ያሰኙታል:: የመስጠት ልማድ ውስጥ ስጦታ ሰጪ ምን ይስጥ?፣ ለማን ይስጥ?፣ መቼ ይስጥ ?፣ እንዴት ይስጥ?፣ ስጦታ ተቀባዩስ ከማን ይቀበል?፣ መቼ ይቀበል?፣ እንዴት ይቀበል? እና እንዴትስ ይመልስ? የሚሉ ጉዳዮች የማህበረሰቡን ህግ መሰረት አድርገው ምላሽ የሚሰጣቸው ጥያቄዎች ናቸው::

በተጨማሪም ስጦታን ልማድ ከሚያሰኙት ባህርያቶች አንዱ ተደጋጋሚነቱ ነው:: ማህበረሰቡ ስጦታን የሚለዋወጥበት ህግ ጊዜውን እና ቅደም ተከተሉን ጠብቆ መከወኑ ልማድ ያሰኘዋል:: አብዛኛውን ጊዜ ወቅትን ወይም የህይዎት አጋጣሚዎችን ተከትለው የሚቀርቡ ስጦታዎች ማህበረሰቡ በተደጋጋሚነት ይከውናቸዋል:: ለምሳሌ፦ በደብረ ኤልያስ ከተማ የሚኖሩ ማህበረሰቦች ካላቸው የስጦታ ልማድ አንዱ የደብረ ታቦርን በዓል ተከትሎ የክርስትና እናት ወይም አባት ለክርስትና ልጁ ሙልሙል ወይም ድፎ ዳቦ ስጦታ ይዞ ይጠይቃል:: ይህ ልማድ የክርስትና እናት ወይም አባት እና ልጅ በህይወት እስካሉ ድረስ በየዓመቱ በተደጋጋሚ ሲያደርጉት የኖሩት ልማድ ነው:: በተጨማሪ ለጋብቻ የሚሰጥ ጥሎሽ፣ ለወላድ፣ ለሕጻናት፣ ለሽማግሌዎች፣ ለጀግና፣ ለልጅ የሚሰጥ የእናት ዕቃ ፣የአባት ዕቃ፣ መሳሪያና ልዩ ልዩ

ቁሳቁሶች፣ ታሞ ጤና ላጣ፣ ዘመንን ለመቀበል፣ በደብረ ዘይት በዓል ለሃይማኖት አባት፣ ለክርስትና ልጅ፣ ጤና፣ ልጅ ሀብት ወዘተ. ጉዳዮች ፍለጋ የሚሳሏቸው ስዕለቶች እና መስዋዕቶች ለፍቅር መግለጫ፣ ዝምድናን ማጠናከሪያ፣ ደም ማድረቂያ ወዘተ. እንዲሆን ለጋብቻ ወይም ለአበልጅነት ልጅን መስጠት፣ እሸት ሲደርስ እሸት ቅመሱ ብሎ ወዳጅን መጠየቅ የተለመዱ እና በተደጋጋሚ የሚከወኑ ጉዳዮች ናቸው።

### 2.3.5 የስጦታ ዓይነቶች

በስጦታ ክዋኔ ውስጥ ስጦታ ተቀባይ፣ ሰጪ እና ለስጦታነት የሚቀርበው ነገር ተሰናስሎ እናገኘዋለን ። ከዚህም ተነስተን ስጦታን ይበልጥ ግልጽ ለማድረግ የስጦታ አይነቶችን በሶስት መንገዶች ልንከፍላቸው እንችላለን። እነዚህም አከፋፈሎች ከዋኝን እና ለስጦታነት የሚቀርበውን ነገር መሰረት ያደረጉ ናቸው። የመጀመሪያው ስጦታ ከከዋኝ አንጻር ሰዎች ለ ልዕለ-ሰብ ወይም ልዕለ-ሰብ ለሰዎች እና ሰዎች ለ ሰዎች የሚያቀርቡት ስጦታ ብለን በሁለት፤ እንዲሁም በሁለተኛነት ስጦታን ለስጦታነት ከሚቀርቡ ነገሮች አንጻር የማይዳሰሱ(ረቂቅ) ስጦታዎች እና የሚዳሰሱ (ረቂቅ ያልሆኑ) ስጦታዎች በማለት በሁለት ከፍለን ልናያቸው እንችላለን።

ሀ. ስጦታ ከከዋኝ አንጻር

- ✓ ሰዎች ለ ልዕለ-ሰብ ወይም ልዕለ-ሰብ ለ ሰዎች

እነዚህ ስጦታዎች እምነትን እና ሃይማኖትን መሰረት አድርገው የሚከወኑ ናቸው። ማህበረሰቡ ከሚከውናቸው ስጦታዎች መካከል ከእነርሱ በላይ ለሆኑ አማልእክት የሚያቀርባቸው ስጦታዎች እና እነርሱም ከአማልእክት ተሰጡኝ ብሎ የሚቀበላቸው ስጦታዎች ይጠቀሳሉ። የመጀመሪያው አማልእክት ለሰው ልጆች የሚሰጧቸው ስጦታዎች ናቸው። ሃይማኖት ያለው ማህበረሰብ ከሰው በላይ የሆነ አካል ( ፈጣሪ ወይም አማልእክት) ለመኖር የሚያስፈልገንን ነገር እንዲሁም በህይወታችን ጉዞ ለሚገጥመን ችግር በሚታይ ወይም በረቀቀ መልኩ እርዳታ ይሰጡናል ብሎ ያምናል። ይኸውም ልዕለ ሰብ ለሰው ልጆች የሚሰጧቸው ስጦታዎች ናቸው። እነዚህን ስጦታዎች ለመዘርዘር የጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ ይገድበናል። ነገር ግን ማህበረሰቡ የፈጣሪ ስጦታ መኖሩን በተለያዩ ክንውኖቹ ይገልጻቸዋል። በደብረ ኤልያስ ብቻ ሳይሆን በአብዛኛው የኢትዮጵያ ማህበረሰብ ዘንድ የተለመደ አንድ ምርቃት አለ። ይኸውም በእለት ተእለት ህይወቱ በጎ ነገር ለሚያደርጉለት "እግዜር ይስጥልኝ" ወይም "አምላክ ይስጥልኝ" የሚለው የዘወትር ምላሽ ሲሆን ማህበረሰቡ ስጦታ ከሰውም ከፈጣሪም ዘንድ መኖሩን ስለማመኑ የሚያረጋግጥ ነው። ሁለተኛው ደግሞ ሰዎች በተለያዩ ፍላጎቶቻቸው እርዳታን ከፈጣሪ ሲጠይቁ ወይም

ለተደረገላቸው ነገር ምስጋና ሲያቀርቡ ከሚከውኗቸው ስጦታዎች መካከል ለምሳሌ፦ ስዕለት፣ መስዋዕት፣ መባ፣ አስራት በኩራት ማቅረብ፣ በሀገረሰባዊ እምነቶች ውስጥም ከብት እንዲረባ፣ ንብ ማር እንዲሰጥ፣ ጤና እንዲገኝ፣ ከመጥፎ አጋጣሚ እንዲጠብቀን በማለት የደም ግብር ( ፍራጅ) ማቅረብ፣ በአዲስ አመት የቂቤ እና የበርበሬ ድቁስ በእቃ(በጉችማ) መሙላት ፣ በአዲስ አመት እና በሰኔ እንዲሁም በህዳር ሚካኤል በሶ አንፈርፍሮ ሰው ከመቀመሱ በፊት ለአዋይ እያሉ መርጨት (መስጠት) ምስጋና ማቅረብ ወዘተ.ይጠቀሳሉ። በፈጣሪና በሰዎች መካከል የሚደረግ ስጦታ የተለያዩ ጥቅሞች ያሉት ሲሆን ዋና አላማው በመካከላቸው ያለን የገዢነት እና የተገዢነት ግንኙነትን ማጠንከር ፣ በመካከል ያለ ፍቅርን መግለጽ፣ ምስጋና ወይም ይቅርታን ማቅረብ ይጠቀሳሉ ። ይህንን ሀሳብም ማውስ "Gifts to men and to gods have the further aim of buying peace." ወይም "ለሰዎች እና ለአማልክት የሚደረጉ ስጦታዎች ሰላምን የመግዛት ተጨማሪ ዓላማ አላቸው።" (Mauss 1966, 14) በማለት ያጠናክረዋል። በአጠቃላይ ሰው ከፈጣሪው ጋር የሚለዋወጠው ስጦታ ከከዋኝ አንጻር አንድ ብለን የምንመድበው የስጦታ አይነት ነው።

- ✓ ሰዎች ለሰዎች

ይህ የስጦታ አይነት ሰዎች ከሌሎች ሰዎች ጋር በቡድን ወይም በግል የሚያደርጓቸው፤ ቅርበትን እና የተለያዩ አላማዎችን መሰረት አድርገው የሚከውኗቸው ስጦታዎች ይመለከታል። ማህበረሰቡ ህግ አውጥቶላቸው፣ አብሮነቱን እና ማህበራዊነቱን የሚያስጠብቅበት፣ ፍላጎቱን የሚገልጽበት፣ በዓሉን የሚያደምቅበት፣ ለሌሎች ያለውን አክብሮት የሚያሳይበት ወዘተ. የስጦታ አይነት ነው።

ለ. ለስጦታነት ከሚቀርቡ ነገሮች አንጻር

የስጦታ ዓይነቶችን በተመለከተ Belk እንዲህ ይገልጻል። ስጦታ በቋሚነት ያለ ቅርስ ፣ የተገዙ ምርቶች እና አገልግሎቶች (የሰላምታ ካርዶችን እና ተጓዳኝ መጠቅለያዎች)፣ በግል የተሰሩ ዕቃዎች፣ አገልግሎቶች፣ ቀደም ሲል በባለቤትነት የተያዙ ምርቶች እና ንብረቶች ወይም የሰውነት አካላት እና ደም ሊሆኑ እንደሚችሉ ይገልጻል (W.Belk,1977,3)። ከዚህም ሀሳብ በመነሳት ስጦታዎች በቁስ የሚገለጹ ወይም ረቂቅ የሆኑ ነገሮች ሊሆኑ እንደሚችሉ መረዳት ይቻላል።

- ✓ የማይዳሰሱ (ቁሳዊ) ያልሆኑ ስጦታዎች

የማይዳሰሱ ወይም ረቂቅ ስጦታዎች የሚባሉት ከከዋኝ አንጻር በሰዎች መካከል ወይም በሰው እና በፈጣሪ ሊከወኑ የሚችል ነገር ግን በቁስ የማይገለጹ የስጦታ አይነቶች ናቸው፡፡ በራስ ተነሳሽነት (በደግነትም) ይሁን በማህበረሰብ ደንቦች (በግብረ ገብነት) አሊያም የሃይማኖት ትዕዛዛትን ለመጠበቅ በሚል ምክንያት የራስ የሆነን በቁስ የማይገለጽ ሀብት ለሌላው መስጠትን ይመለከታል፡፡ ለምሳሌ፦ ጊዜን፣ እውቀትን፣ ፈቃድን(ልብን)፣ ሀሳብን፣ ህይወትን መስጠት ፣ ነጻ አገልግሎት ወይም ጉልበትን መስጠት ወዘተ. በቁስ ከማይገለጹ ስጦታዎች መካከል ይጠቀሳሉ፡፡ ከእነዚህ ስጦታዎች መካከል በማህበረሰቡ ዘንድ የሚከዎኑ ነገር ግን በቁስ ከማይገለጹ ስጦታዎች አንዱ የሰዎች እገዛ በሚፈለግበት ማንኛውም ጊዜ ለምሳሌ፦ ጎጆ ለመስራት፣ ከብት ለማገድ፣ ምርት ለማምረት፣ የአካባቢ ጥበቃ ለማድረግ (ለልማት ስራ)፣ ድግስ ለመደገስ በአጠቃላይ በደስታ እና በኃዘን እንዲሁም በዕለት ተዕለት ክንውኖች ውስጥ ስራን በደቦ እና በትብብር መስራት የጉልበት ስጦታ ነው፡፡ ይህን የጉልበት እገዛ ማድረግ በማህበረሰቡ የሚደገፍ እና ለአብሮነታቸው እንደ ውዴታ ግዴታ የሚቀመጥ የስጦታ ልማድ ነው፡፡ ስለዚህ ከቁስ በተጨማሪ ልንዳስሳቸው የማንችል ነገር ግን በተግባር የስጦታ አይነቶች እንዳሉ ከዚህ እንረዳለን፡፡

- ✓ የሚዳሰሱ (ቁሳዊ ) ስጦታዎች

ሰዎች እርስ በእርስ እና ለፈጣሪ ቁሳዊ የሆኑ ስጦታዎችን ያቀርባሉ፡፡ ይህ የስጦታ አይነትም በሚዳሰስ እና በሚጨበጥ መልኩ የሚቀርቡ ቁሳዊ የሆኑ ስጦታዎችን ያጠቃልላል፡፡ የቁስ ስጦታዎች ገንዘብን ጨምሮ ልዩ ልዩ መገልገያ እቃዎች፣ ምግብና መጠጦች፣ አልባሳት፣ ጌጣጌጦችን ወይም በተፈጥሮ የተገኙትን እንደ መሬት፣ ደምን፣ የሰውነት ክፍሎችን፣ እንስሳትን፣ እህል ወዘተ. ያሉ የግል ንብረቶች ናቸው፡፡ በሚታዩ እና ተጨባጭ በሆኑ ስጦታዎች ውስጥ የስጦታው አይነት ፣ መጠን፣ ቀለም፣ ቁጥር ወዘተ.ጉዳዮች ህግ እና ደንብ ተቀርጾላቸው ይተገበራሉ፡፡ በዚህም ምክንያት በቁስ የሚገለጹ ስጦታዎች ቁሳዊ ካልሆኑ ስጦታዎች የበለጠ ትዕምርታዊ ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ ስጦታዎች ትዕምርታዊ መሆናቸው ደግሞ ከጀርባቸው ያለውን መልእክት፣ የሰጪውን እና የተቀባዩን ማንነት፣ ፍላጎት፣ አስተሳሰብ፣ ባህል፣ ሃይማኖት፣ ለዓለም ያለውን እይታ፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ደረጃ፣ ወዘተ. ያንጸባርቃል፡፡ "ስጦታዎች ከቁሳዊ ባህርያቸው የበለጠ ከጀርባቸው አንድ ረቂቅ የሆነ መልዕክትን ይጠቁማሉ፣ እናም የሆነ ነገር መስጠት ማለት በከፊል ራስን መስጠት ነው፡፡"

በማለት የሁለቱን የስጦታ አይነቶች (በቁስ የሚገለጹትን እና ረቂቅ የሆኑትን) ተደጋጋፊነት ማውስ (1966፣ 68) ይገልጻል፡፡

### 2.3.6 ስጦታ ለመስጠት አነሳሽ የሆኑ ምክንያቶች

አንድ ክዋኔ ለመከወን ግላዊ፣ ሃይማኖታዊ፣ ባህላዊ ወይም ሌሎች መነሻ ምክንያቶች አሉት፡፡ መነሻ ምክንያታቸውም በአከዋወን ሁኔታቸው ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል፡፡ ለምሳሌ፦ የገና በዓል ለማክበር አነሳሽ የሆነው ምክንያት የክርስቶስ መወለድ ነው፡፡ የበዓሉም አከባበር የሃይማኖቱን አስተምህሮ የተከተለ ነው፡፡ ስጦታ ለመስጠትም  አነሳሽ የሆኑ ምክንያቶች አሉት፡፡ በዋናነት ግን የራስ አስተሳሰብ ወይም እምነት እና የሚኖሩበት አካባቢ ባህል  እንደ አነሳሽ ምክንያቶች ይጠቀሳሉ፡፡ እነዚህን ምክንያቶች ለሁለት በመክፈል ውስጣዊ እና ውጫዊ ምክንያቶች ማስቀመጥ እና በውስጣቸው ብዙ ቅንጣቶችን መዘርዘር ይቻላል፡፡ እነዚህ ሁለት ምክንያቶች እርስ በእርስ ተደጋጋፊነት አላቸው፡፡ ለምሳሌ፦ ስጦታ ለመስጠት አነሳሽ ከሆኑ ምክንያቶች አንዱ ደግ መሆን ነው፡፡ ደግነት ውስጣዊ ምክንያት ሲሆን ማህበረሰቡ ደግ እንዲሆን ግን የባህል ህግ እና የሃይማኖት አስተምህሮ ያለው ሚና ቀላል አይደለም፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ውጫዊ ምክንያቶች ወይም ማህበረሰቡ የፈጠራቸው ህግና ስርዓቶችም ከውስጣዊ አስተሳሰብ እና የህይወት ፍልስፍና የመነጩ ናቸው፡፡ ስለዚህ ሁለቱም ምክንያቶች በተደጋጋፊነት የሚቆሙ ጉዳዮች ቢሆኑም ከፋፍሎ ማየቱ ምክንያቶችን በግልጽ ለመረዳት ያስችላል፡፡

ሀ.ውስጣዊ ምክንያቶች

ስጦታ ለመስጠት የሚያስገድዱ ውስጣዊ ስሜቶች ይኖራሉ፡፡ በስጦታ ውስጥ ያለምንም ጠብቆት የራስን ነገር አሳልፎ መስጠት እና በሌሎች ደስታ መደሰት የሰዎችን ውስጣዊ ማንነት በተሻለ ለመረዳት የሚጠቅም ሆኖ ማግኘታቸውን የስነ ልቡና ጥናቶች ይገልጻሉ፡፡ በስጦታ መለዋወጥ ዙሪያ ከተነሱ ጥናቶች ውስጥም altruistic ማንነት ያላቸው ሰዎች ለሰዎች በመስጠት የሚደሰቱ እንደሆኑ ጠቁመዋል፡፡ Anik (2009, 18), Cronk (1988,5) ስጦታ ለመስጠት አነሳሽ ከሆኑ ውስጣዊ ምክንያቶች ደግነት፣ ፍቅር፣ ዝምድና (ቅርበት) እንደምሳሌ ይጠቀሳሉ (Belk 1979)፡፡

- ✓ ደግነት

"ደግ ሰው ከእንጀራው ቆርሶ ከወጡ አጥቅሶ" በማህበረሰቡ ውስጥ ደግነት ከሚገለጽባቸው መንገዶች አንዱ መስጠት እንደሆነ የሚገልጽ አባባል ሲሆን ስጦታ ለመስጠት አነሳሽ ከሆኑ ምክንያቶች አንዱ የደግነት ባህርይ መኖር እንደሆነ ያስረዳል፡፡ ብዙ ተመራማሪዎችም ደግነት

ስጦታ ለመስጠት አነሳሽ ምክንያት እንደሆነ ይገልጻሉ። ከእነዚህም ውስጥ አንትሮፖሎጂስቱ Cronk ለመስጠት ደግነት እንደሚያነሳሳ ሲገልጽ reciprocityን እንደ የስጦታ ንግድ ይመለከተዋል። ደግነት ግን ስጦታ ተቀባዩንም ይሉንታ የሚያስይዝ እና ውለታ ለመክፈል ኃይል ያለው መሳሪያ ነው፤ ስጦታ ለመስጠ ዋናው ምክንያት ደግነት እንጂ reciprocity (ስጦታን የመመለስ ደንብ) አይደለም ይለናል። "Reciprocity means gift trading and gift trading is a benevolent weapon and gives that power to embrrass  the recipient and to force repayment" (Cronk, 1988,23).

- ✓ ፍቅር

ፍቅር ሌላውን እንደ ራስ የመውደድ ስሜት ነው። ይህን በተመለከተ "ፍቅር በቅርበት ፣ በስሜታዊነት እና በቁርጠኝነት ተለይቶ የሚታወቅ የስሜቶች እና ባህርይዎች ስብስብ ሲሆን ይኸውም እንክብካቤን፣ ቅርበትን፣ ጥበቃን፣ መስህብን  እና መተማመንን ያካትታል።" በማለት https://www.verywellmind.com ትርጉሙን ያስቀምጣል። ስጦታ ለመስጠት አነሳሽ ከሆኑ ውስጣዊ ምክንያቶች አንዱ ፍቅር ወይም ሌላውን እንደራስ መውደድ ነው። አንድ ሰው ፍቅሩን የሚገልጸው ራሱን እና የራሱ የሆኑ ነገሮችን ለሚወዳቸው በመስጠት ወይም በማጋራት እንደሆነ ነባራዊ ሁኔታዎች ያስረዳሉ። "In one way or another, gifts are used to symbolise love and devotion between two partners". (G. Raymond 1990,10) "በአንድ ወይም በሌላ መንገድ ስጦታዎች በሁለት አጋሮች መካከል ያለ ፍቅርን እና አምልኮን ለማመልከት ያገለግላሉ።" እንደማለት ነው። ብዙ  የፍቅር አይነቶች ሲኖሩ ለምሳሌ እናት ለልጇ ያላት ፍቅር አንዱ ነው። ይህም ፍቅር  በሰዎች ብቻ ሳይሆን በእንስሳት ዓለም ውስጥ የምንረዳው ሲሆን እናት ለልጇ ስትል ራሷን አሳልፋ ትሰጣለች የእርሷ የሆነውን ሁሉ ለልጇ ታደርጋለች። በተጨማሪ በተቃራኒ ጾታ መካከል ያለ ፍቅርም እንዲሁ ወንድ ለሴቷ ሴቷም ለወንዱ ስጦታ በመለዋወጥ ፍቅራቸውን ይገላለጻሉ። ለምሳሌ፦ በባህል ውስጥ አንድ ወንድ አንዲትን ሴት ሲወዳት ሎሚ ይወረውርባታል። እርሷም ከወደደችው ሎሚውን እንደ ስጦታ ትቀበለዋለች በአጠቃላይ ከላይ ባነሳናቸው ምሳሌዎች ውስጥ ስጦታ ለመለዋወጥ አነሳሽ የሆነው ምክንያት ፍቅር ወይም መዋደድ ነው።

- ✓ ዝምድና ወይም ቅርበት

ዝምድና በሁለት ክፍሎ ማየት ይቻላል። የመጀመሪያው የስጋ ዝምድና ሲሆን በመወለድ የሚገኝ ነው። ይኸውም አንዱ ከሌላው የመልክ እና የጠባይ መመሳሰሎችን የሚወርስበት ነው።

እናት አባት አያት... እንደ ኢትዮጵያውያን ባህል እስከ ሰባት ትውልድ ያለውን፣ እህት ወንድሞችን፣ የእናት እና የአባት እህት ወንድሞችን እና የቅርብ ዘመዶችን ያጠቃልላል:: ከስጋ ዝምድና በተጨማሪ ማህበረሰብ ዝምድናን የሚመሰርትባቸው የተለያዩ መንገዶች አሉት:: ለምሳሌ ጥናቱ የተደረገበት አካባቢ ጋብቻ፣ ክርስትና ማንሳት፣ ጡት መጣባት፣ የሃይማኖት አባት እና ልጅ መሆን፣ጉርብትና ዝምድና የሚመሰረትባቸው ምክንያቶች ናቸው::ስጦታ ለመለዋወጥ አነሳሽ ከሆኑ ምክንያቶች መካከልም ዘመድ ወይም ቅርብ ሆኖ መገኘት አንዱ ነው:: ይህን አስመልክቶ walker ስጦታ ለመቀያየር ዝምድና እና ማህበራዊ ቅርርብ የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ እንደሆነ እና እንደ ቅርርቡም መጠን ስጦታ የመመለስ ጠብቆቱ እንደሚለያይ እንዲህ ትገልጻለች:: "Kinship and social connectedness play an important role in determining the motives attached to gift-giving. There is a clear hierarchy. Close kin and connections receive 'disinterested gifts where no (immediate) returns are expected". R.walker (2018, 61) በባህል ውስጥ የተለያዩ ችግሮች ወይም የደስታ ቀናት እና ክብረ በዓላት በሚመጡበት ጊዜ ስጦታ ይዞ ዘመድ እና ወዳጅ የመጠየቅ ልማድ በሰፊው እናገኛለን:: ይህም ማለት ለመስጠት ዝምድናው ወይም ቅርርቡ ይገፋፋዋል ስለዚህ በስጋም ሆነ በሌሎች ምክንያቶች የተፈጠረ ዝምድና እና ቅርርብ ስጦታ ለመስጠት አነሳሽ ከሆኑ ውስጣዊ ምክንያቶች እንመድበዋለን::

- ✓ ልዩ ልዩ ስሜቶች

የሰው ልጆች በእለት ተእለት ኑሮአቸው ውስጥ በሚፈጠሩ መልካም ወይም ክፉ አጋጣሚዎች ምክንያት የተለያዩ ውስጣዊ ስሜቶችን ያስተናግዳሉ:: ከእነዚህ ስሜቶች ውስጥም ደስታ፣ ሀዘኔታ፣ የጥፋተኝነት ስሜት ወዘተ. ይገኙበታል:: እነዚህ ስሜቶች ስጦታ ለመስጠት የሚያነሳሱ ጉዳዮች ናቸው:: ለምሳሌ አንድ ሰው ሲደሰት ደስታውን ለመግለጽ፣ ሲያዝን ሀዘኔታውን ለሌሎች ለማሳየት ወይም ጥፋት አጥፍቶ ይቅርታ ለመጠየቅ ስጦታ የመስጠት ልማድን በሰፊው እናገኛለን:: ማህበረሰቡ በማህበራዊ ህይወቱ ውስጥ ሲደሰት ወዳጅ ዘመድ ጠርቶ የደስታ ተካፋይ ማድረግና ደግሶ ማብላት፣ የበደለውን ይቅርታ ሲጠይቅ ካሳ መስጠት የተለመዱ የስጦታ ባህሎች ናቸው:: ስለዚህ ስጦታ ለመስጠት አነሳሽ ከሆኑ ምክንያቶች በዕለት ተእለት የሚገጥሙ ልዩ ልዩ የውስጥ ስሜቶች ሊሆኑም ይችላሉ::

ለ. ውጫዊ ምክንያቶች

ስጦታ ለመስጠት በሚያነሳሱ ውጫዊ ምክንያቶች ውስጥ ስጦታ ከሰጪ የግል ፍላጎትና ሀሳብ አልፎ የኑሮ አካባቢ፣ ሃይማኖት፣ እና ባህል እንዲሁም ሌሎች ምክንያቶች እንዲሰጥ ወይም እንዲመልስ ግፊት አድርገውበታል ወይ? የሚሉ ጉዳዮች የሚነሱበት ነው።

✓ ሃይማኖት

ሃይማኖት ካሉት በርካታ ትርጉሞች ውስጥ ሰዎች ከፈጣሪያቸው ጋር ያላቸው ግንኙነት ምን መምሰል እንዳለበት የሚያሳይ መንገድ መሆኑ ነው። ከእነዚህ መንገዶች ውስጥ ስጦታ መስጠት ሰው የፈጣሪውን ህግ የሚፈጽምበት አንድ መንገድ እንደሆነ ተቀምጦ ይገኛል። በደብረ ኤልያስ የሚገኙ ማህበረሰቦች አብዛኛው የክርስትና ሃይማኖት እና በተወሰነ ደረጃ የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ናቸው። በሁለቱም ሃይማኖቶች ውስጥ መስጠት የጽድቅ መንገድ እንደሆነ ተጽፏል።

✓ የክርስትና ሃይማኖት ስለ ስጦታ ያለው አስተምህሮ

ክርስቲያኖች በቅድስና ትምህርት ያምናሉ። አንድ ሰው ለመቀደስ (ቅዱስ ለመባል) ካለው ቀንሶ መስጠት ብቻ ሳይሆን ያለውን ሁሉንም ዓለማዊ ዕቃዎች ሸጦ ለድሆች መለገስ እና ራስን ባዶ እስከ ማድረግ ይደርሳል። በዚህ ሃይማኖት መንገድ ያለፉ የብዙ ቅዱሳን ታሪክም ይህን ይናገራል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ፍጹምነት የሚገኘው በመስጠት እንደሆነ ክርስቶስ በምድር ላይ ሲኖር የተፈጸመ አንድ ታሪክ ያስረዳል። ታሪኩም አንድ ሀብታም ወደ ክርስቶስ ቀርቦ "የዘለዓለም ህይወት እወርስ ዘንድ ምን ላድርግ "ባለው ጊዜ" አስርቱን የእግዚአብሔር ትዕዛዛት አክብር" ብሎ ይመልስለታል፤ ሀብታሙም ትዕዛዛቱን ከልጅነቱ ጀምሮ እየፈጸመ እንዳለ ሲነግረው ክርስቶስ አንዲት ነገር ሲመልስለት ይታያል። "አንድ ነገር ጎደለኽ ኺድ፥ ያለኽን ኹሉ ሸጠኽ ለድኻዎች ስጥ፥ በሰማይም መዝገብ ታገኛለኽ፥ መስቀሉንም ተሸክመኽ ና፥ ተከተለኝ" (ማር 10፥16- 21) እና (ሉቃ 18፥22) ከዚህም በተጨማሪ በክርስትና ሃይማኖት ውስጥ ለፈጣሪ ወይም ለባለእንጀራ ስጦታ ሲቀርብ ምን መምሰል እና እንዴት መደረግ እንዳለበት ህግ እና ስርዓት ተቀምጦለት ይገኛል። በመጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈ የሁለት ወንድማማቾች የስጦታ ታሪክ ( ዘፍ 4፥2-5) ላይ የሚገኝ ሲሆን ለእግዚአብሔር መስዋዕትን ማቅረብ ከዚያ በፊት በመጽሐፍ ቅዱስ ተጽፎ አይገኝም። በዚህ ክፍል ባለ ታሪኮቹ ቃየን እና አቤል የምድራችን የመጀመሪያዎቹ ወንድማማቾች እንደሆኑ ያስረዳል። አቤል እረኛ ሲሆን ቃየን ደግሞ ገበሬ ነበር። ሁለቱም ለእግዚአብሔር መስዋዕትን ሊያቀርቡ ተነሱ። እረኛው አቤል

ከበጎቹ በኵራትና ከስቡ አቀረበ፡፡ ገበሬው ቃየን ደግሞ ከምድር ፍሬ አቀረበ፡፡ እግዚአብሔር ወደ አቤልና ወደ መስዋዕቱ ተመለከተ፤ ወደ ቃየንና ወደ መስዋዕቱ ግን አልተመለከተም፡፡ ፈጣሪ የአንዱን ስጦታ ተቀብሎ የሌላውን ለምን አልተቀበለም ለሚለው ጥያቄ ዲያቆን አምሀ በለጠ የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

> እግዚአብሔር አስቀድሞ የተመለከተው የቀረበለትን መስዋዕት ሳይሆን የአቅራቢዎቹን ልብ ነበር፡፡ አቤል ለእግዚአብሔር መስዋዕት ሲያቀርብ በንጹሕ ልቦና እና በፍርሀት እንደነበረ መስዋዕቱን ለማቅረብ ያደረገው ቅድመ ዝግጅት ያሳያል፡፡ "ከበጎቹ በኵራት እና ከስቡ አቀረበ" ነው የሚለው፡፡ ከበጎቹ መካከል በኩራቱን መርጦ ከሥጋውም ደግሞ ስቡን መርጦ ተጨንቆ ነበር ያቀረበው፡፡ ቃየን ግን በግዴለሽነትና በትዕቢት የተሞላ ነበር፡፡ የምድርን ፍሬ ሲያቀርብም ያለ ምንም ጥንቃቄ ግርዱን አግበስብሶ አቀረበ፡፡ ለማቅረብ የተዘጋጀ አለመሆኑ ለፈጣሪው ያለውን ንቀት ያሳያል፡፡ ይህን በትዕቢት የተሞላ ልብ ይዞ ደግሞ እንኳን የምድርን ፍሬ የአቤልን ዓይነት ስብ ቢያቀርብም ኖሮ እንኳን እግዚአብሔር አይቀበለውም ነበር፡፡ አምላክ ‹እንደ ልቤ› ብሎ የጠራው ቅዱስ ዳዊት የእግዚአብሔርን የልብ ፍላጎት እንዲህ ሲል ተናገረ "መስዋዕትን ብትወድስ በሰጠሁህ ነበር ፤ የሚቃጠለውም መስዋዕት ደስ አያሰኝህም፡፡ የእግዚአብሔር መስዋዕት የተሰበረ መንፈስ ነው፡፡ የተሰበረውንና የተዋረደውን ልብ እግዚአብሔር አይንቅም፡፡" (መዝ. 50፥16-17) እግዚአብሔር ከስጦታ ቀድሞ ሰጪውን ያያል፡፡ ለዚህም ነው "ወደ አቤልና ወደ መሥዋዕቱ ተመለከተ" የሚለው (ቃለመጠይቅ 28/08/2013 ዓ.ም)፡፡

ማህበረሰቦቹ በሃይማኖት እና በባህል ህግጋት የሚመሩ ሲሆን ስጦታ ምን መምሰል እንዳለበት ተረድተው ሁልጊዜም በፈጣሪ ወይም በሰው ፊት ለስጦታ የሚቀርብ ነገር የተመረጠ መሆን እና በንጹህ ልብ መደረግ እንዳለበት እነዚህን ቅዱሳን ተብለው የሚጠሩ ሰዎችን የህይወት ልምድ አስረጂዎች በማንሳት በሰውም በእግዚአብሔርም ፊት የሚያስደስት ስጦታ ለማቅረብ የሃይማኖቱን አስተምህሮ ይተገብራሉ፡፡

የእስልምና ሃይማኖት ስለ ስጦታ ያለው አተያይ ደግሞ እንደሚከተለው ነው፡፡

እስልምና እንደ ሌሎቹ ሃይማኖቶች ተከታዮቹን ለግለሰብ እና ለማህበራዊ ደህንነት 'እንዲሰጡ' ያዛል። አጠቃላይ የሀብት ጽንሰ -ሀሳብ በእስልምና እንደ ፈጣሪ ስጦታ ተደርጎ ይወሰዳል። ለሰጪው የሰጠው ፈጣሪ ከፊሉን ለድሆች እንዲያደርገው ያዛል። ስለዚህ ድሆች በአንድ ሰው ሀብት ላይ መብት አላቸው። የሚል አስተሳሰብ ያለ ሲሆን ነቢዩ ሙሐመድ እንዲህ አስተምረዋል፦ "ከእርሱ በስተቀር ጥላ በሌለበት ቀን ሰባት ሰዎች በአላህ ጥላ ሥር ይጠለላሉ። እነሱም - ፍትሐዊ ገዥ፣ በአላህ አምልኮ ውስጥ ያደገ ወጣት፣ ልቡ ከመስጊድ ጋር የተሳሰረ ፣ለአላህ ብለው የሚዋደዱ ሁለት ወንዶች፣ በውበቷ እና በአቀማመጥ የተጠራችው አላህን የምትፈራ ሴት ፣ በጎ አድራጎት የሚሰጥ እና መስጠቱን የሚደብቀው ሰው፣ እና አላህን ለብቻው የሚያስታውስ እና ዓይኖቹ እንባዎችን ያፈሰሰ ሰው (ሳሂህ አል ቡኻሪ ቅጽ 2፣ ሐዲስ ቁጥር 504)።

በዚህ ሀሳብ ውስጥ በስድስተኛ ደረጃ የሚሰጥ ሰው በመጨረሻው የፍርድ ቀን በፈጣሪ እንደሚጠለል ተጠቅሶ እናገኛለን። ለሌሎች ሲሰጥም መስጠቱን የሚደብቅ መሆን እንዳለበት ይገልጻል። ይህም ማለት ስጦታ ድብቅ ወይም ሚስጢራዊ ተደርጎ መከወን አለበት ብለው እንደሚያምኑ ያሳያል። ቅዱስ ቁርአን ፍትሃዊነትን እና ለጋስነትን የሚያዝዝ ሃሳባዊ (ማህበራዊ) ትብብርን ያጎላል። የሀብታሞችን መስገብገብ ሲያወግዝ፣ ሌሎችን ለመርዳት ከሀብታቸው የሚያወጡትን እንደ እውነተኛ በጎ አድራጎት ይደግፋል። የሃይማኖቱ ተከታዮችም ህግና ስርዓቱን ለመጠበቅ መስጠትን እንደ ጽድቅ ስራ ቆጥረው ይተገብሩታል። ስለዚህ በክርስትናም በእስልምናም ሃይማኖት ውስጥ በጎ ስጦታ መስጠት ከፈጣሪ የሚያገናኝ ስራ እንደሆነ ያስተምራሉ።

በአጠቃላይ አንድ ቡድን ስጦታዎችን እንዲለዋወጥ ወይም እንዲረዳዳ ሃይማኖት ያለው አስተምህሮ አነሳሽ ምክንያት ሊሆነው እንደሚችል እንረዳለን።

### ሀገረሰባዊ እምነቶች ስጦታ ስለመስጠት ያላቸው ልማድ

ሀገረሰባዊ እምነት (folk belief) የሀገረሰባዊ ልማድ አንድ ዘርፍ ሲሆን ማህበረሰቡ ከአደጋ የጸዳ ኑሮ ለመኖር ጥሩ እድል ያመጣሉ ብሎ የሚያስባቸውን ድርጊቶች የሚፈጽምበት፣ አደጋ ያመጡብኛል ብሎ ያሰባቸውን ክንውኖች ደግሞ የሚከላከልበት፤ በአጠቃላይ ማህበረሰቡ ችግሮችን ለመፍታት እና ቀድሞ ጥንቃቄ ለማድረግ የፈጠራቸው ያልተጻፉ አካባቢያዊ የረጅም ጊዜ የኑሮ ልምዶችን ያጠቃልላል። "ሀገረሰባዊ እምነት ከቦታ ቦታ እንደሚለያይ እና በኢትዮጵያ

ውስጥ የሚገኙ የተለመዱ ሀገረሰባዊ እምነቶች ምልኪ፣ ጥንቆላ፣ አስማት፣ ተፈጥሮን የመቆጣጠር ሀይል፣ ቡዳ፣ ዛር፣ አድባር" እንደሚገኙበት ሰሎሞን (2007፣108) ይገልጻል፡፡

በሀገረሰባዊ እምነቶች ክዋኔ ውስጥ ስጦታ መስጠት የሚደገፍ እና አንዳንድ ጊዜም እንደ ግዴታ የተቀመጠ ጉዳይ ነው፡፡ ጥናቱ በተደረገበት አካባቢም በተዘረዘሩት የሀገረሰባዊ እምነት ቅንጣቶች ውስጥ ስጦታ መስጠት በረከትን፣ እርቅን፣ ጤናን እንደሚያመጣ አለመስጠት ደግሞ ክፉ ነገር እንደሚያደርስ ይታመናል፡፡ ለምሳሌ፦ በጥንቆላ ሂደት ውስጥ መስዋት ማቅረብ ለችግሮች መፍትሔ ያመጣል ተብሎ ለሚታመነው ሀይል መለመኛ ሆኖ ያገለግላል፡፡ ያን መስዋዕት በተለመደው ጊዜ አለመስጠት ደግሞ በተቃራኒው በረከት ማጣትን፣ የጤና መቃወስን እና ጸብን ሊያስከትል እንደሚችል ስለሚታመን ስጦታው በተለመደው ጊዜ እና የስጦታ ደንብ መሰረት ይቀርባል፡፡ በተጨማሪ ከብት እንዲረባ፣ እንዳይሞት እና ከአደጋ እንዲከለከል ጊዜውን ጠብቆ የደም ግብር ማድረግ ወዘተ. በተጠኘው ማህበረሰብ ሀገረሰባዊ እምነት የተለመዱ የስጦታ አይነቶች ናቸው፡፡ ማህበረሰቦቹም ከአደጋ ይጠብቀናል የሚሉት ሀይል እንዳይጣላቸው፣ ከችግሮች እንዲጠበቁ እና በፊታቸው ካለው ችግር እንዲወጡ ወዘተ. ስጦታዎችን ያቀርባሉ፡፡ ለስጦታቸውም የራሳቸው ህግ አላቸው፡፡ እነዚህ ህግጋት በስጦታው ዓይነት፣ ቀለም፣ መጠን እንዲሁም የስጦታ አቀራረብ ምን መምሰል እንዳለበት የተቀመጡ የስጦታ ልማዶች ናቸው፡፡ ለምሳሌ፦ የደም ግብር በሚቀርብበት ወቅት ስጦታው በግ ከሆነ ምን ዓይነት ቀለም? (ጥቁር፣ ነጭ፣ ቡራቡሬ ወዘተ.)፣ ምን ያህል መጠን (እድሜ፣ ብዛት)፣ እንዴት ባለ ሁኔታ መታረድ እንዳለበት( የሚታረድበት አቅጣጫ፣ ቦታ) ወዘተ. ጉዳዮች የተቀመጠ የማህበረሰብ ልማዳዊ ህግ አላቸው፡፡ ከዚህም የምንረዳው ሀገረሰባዊ እምነቶች ስጦታን ለማድረግ አነሳሽ ምክንያቶች እንደሆኑ ነው፡፡

ሐ. ክብረ በዓላት እና ልዩ ልዩ ዝግጅቶች

ክብረ በዓላት እና ልዩ ልዩ ዝግጅቶች ሲባል የህይወት አጋጣሚዎችን እና ደረጃዎችን እንዲሁም ወቅቶችን ጠብቀው የሚከበሩ ቀናቶችን ይመለከታል፡፡ ስጦታ ለመስጠት አነሳሽ ከሚሆኑ ምክንያቶች አንዱ ቀኖች ከዘወትራዊው በተለየ አንዳች አጋጣሚን መሰረት አድርገው ሲከዎኑ ነው፡፡ በዚህም ውስጥ ስጦታ የክዋኔው አንድ አካል ሆኖ ይመጣል፡፡ ለምሳሌ፦ የልደት ስጦታ መነሻ ምክንያቱ የባለ ልደቱ በዚያች ቀን መወለድ ነው፣ የሰርግ ስጦታም መነሻ ምክንያቱ ጋብቻው ነው፡፡ ስለዚህ ክብረበዓላት እና ዝግጅቶች ስጦታ ለመስጠት አነሳሽ ምክንያቶች ናቸው፡፡

መ. ውለታ መቀበል

ውለታ ማለት ቀድሞ ለተደረገ መልካም ነገር አዎንታዊ ምላሽ መስጠትን ይመለከታል። አብሮ በመኖር ሂደት ውስጥ አንዱ ለሌላው በጎ ነገርን ሲያደርግ የተደረገለትን መልካም ነገር አስቦ ውለታ መመለስ በማህበረሰቡ ዘንድ የሚያስመሰግን ተግባር ሲሆን፤ ውለታ አለመመለስ ወይም አዎንታዊ ምላሽ አለመስጠት ደግሞ የሚያስነቅፍ፤ ከማህበራዊ ህይወት እስከመገለል ሊያደርስም የሚችል ተግባር ነው። "የማይመልስ ባለ ዕዳ የሰጡትን ይቀበላል።" የሚል ምሳሌአዊ ንግግርን ማህበረሰቡ ይነገራል። ይህ አባባል ውለታ ወይም ብድር መመለስ የሚደገፍ ተግባር መሆኑን ያስረዳል። ወደ ስጦታ ስናመጣው ደግሞ አንድ ሰው ከዚህ በፊት ከሌላ ሰው ወይም ከፈጣሪ ስጦታ ወይም ማንኛውንም መልካም ነገር ተቀብሎ ከነበር ያንን ውለታ ለመመለስ ያለውን ስጦታ ይሰጣል። ስለዚህ ስጦታ መቀበል ስጦታ ለመስጠት አነሳሽ ምክንያቱ ሊሆን ይችላል። ስጦታ መስጠት በውለታ ላይ የተመሰረተ እንደሆነ የውለታ ምልልሱም ማህበራዊነትን የሚያጠነክር እንደሆነ ኮምትር ይገልጻል። "gift exchanges are based on reciprocity and that their function is to establish and stabilize social bonds within a wide range of human activity" Komter (2007,78). በቃለ መጠይቅ ወቅት ወ/ሮ የዝና ታመነ የተባሉ አንድ ተጠኝ በልጃቸው ክርስትና ወቅት ተገኝቼ ድግስ ደግሰው የሚያበሉት ለምንድን ነው? ብዬ ለጠየቅኋቸው ጥያቄ "ከሰው ጋር ለመኖር ሲበሉ መጠራራት ያስፈልጋል። በዚያም ላይ በየ ሰርጉ፣ በየ ምርቃቱ፣ በየ ድግሱ ዞሬ የበላሁትን ካልመለስሁማ ነውር ነው። እኔም በየ ጥሪው ቤት ስሄድ ተሸክሜ የሄድሁት አቆልቋይ እና ስጦታ የምመልሰው ደግሼ ስጠራ ነው" የሚል ምላሽ ሰጥተውኛል። በዚህም ምላሽ ውስጥ ስጦታ ለመስጠት ከሚያነሳሱ ምክንያቶች አንዱ ቀድሞ ስጦታ መቀበል እንደሆነ እንረዳለን።

### 2.3.7 የስጦታ ተግባራት

የሰው ልጅ በአካባቢው ባሉ ልማዶች አማካኝነት ማንነቱን ይገልጻል። እነዚህም ልማዶች በማህበረሰቡ ማህበራዊ ትርጓሜዎች ይሰጣቸዋል። ስጦታ ካሉት ተግባራት ውስጥም የሰጪ እና የተቀባይን ማንነት፣ ማህበራዊ ደረጃ፣ ሃይማኖት፣ ወዘተ. የመግለጽ በስጦታው የአድርግ እና የአታድርግ ህጎች አማካኝነት የማስተማር እና ከህጉ ሲወጣ በመንቀፍ የመቆጣጠር እና የማጠናከር ተግባራት ይገኙበታል።

ስጦታ ሰጪ ለተቀባዩ ስጦታውን ሲያቀርብ በስጦታው አማካኝነት ራሱን እና ባህሉን ያሳውቃል፡፡ ራሱን ሲባል የግል ፍላጎቶቹን እና ማንነቱን፣ የሚወደውን፣ የሚያስደስተውን ያሳውቃል፡፡ ስጦታ ትዕምርታዊ ነው፡፡ ትዕምርት አንድ ነገር ከጀርባው ያለው መልእክት ይመለከታል፡፡ የስጦታ ትዕምርት ሲባል ደግሞ ስጦታ በመስጠት ሂደት ውስጥ ሰጪና ተቀባዩ የሚለዋወጡት  መልዕክት ምንድን ነው?፣ የሚቀርበው ስጦታ ከባህል አንጻር እንዴት ይተረጎማል? ስጦታው የሰጪውን እና ተቀባዩን ማንነት እንዴት ይገልጻል? የሚሉ ጉዳዮችን ያጠቃልላል፡፡ ለምሳሌ፦ ገበሬ ከሚያመርተው ምርት፣ ሸክላ ሰሪው ከሰራቸው ቁሳቁሶች፣ ሸማ ሰሪው ከሰራቸው አልባሳት፣ ከብት አርቢው ከሚያረባቸው እንስሳቶች ወይም ከእንስሳት ተዋእፆዎች ወተቱን፣ ቅቤውን፣ አይቡን መርጦ ሊሰጥ ይችላል፡፡ ካለው ነገር ላይ በመረጣቸው የስጦታ ምርጫዎች አማካኝነት የእርሱን ፍላጎት እና የማህበረሰቡን ህግ ማጤን ያስችላል፡፡ በተጨማሪም በስጦታው አይነት እና መጠን ውስጥ የሰጪውን የስራ መስክ፣ ማህበራዊ ደረጃ፣ ሃይማኖት ወዘተ. ይገልጽበታል፡፡ ባህሉን ይገልጻል ሲባል ደግሞ ከዋኙ ስጦታውን የአካባቢውን ማህበራዊ ደንብ ተከትሎ ሲያቀርብ በስጦታው አማካኝነት ማህበራዊ ማንነቱን የሚያንጸባርቅበት በመሆኑ ነው፡፡ ይህን ከማሳወቅ በተጨማሪ በስጦታው አማካኝነት ያላቸውን ልማድ ያጠነክርበታል፣ ለቀጣይ ትውልድም ያስተላልፍበታል፡፡ እነዚህ በስጦታው አማካኝነት የሚገኙ አብሮ የመኖር እና የመተባበር ልማዶችን ለማስቀጠል ንጹህ የሆነውን እና በፍቅር የቀረበውን ስጦታ በማበረታታት በግዴለሽነት የቀረበውን ደግሞ በመንቀፍ የስጦታን ህግ ይቆጣጠሩበታል፣ ከሰውም ከፈጣሪም ጋር ያላቸውን ቀረቤታ ያጠናክሩበታል፡፡ ስጦታ የማህበረሰቡን ባህልን ከመጠበቅ  እና ማህበራዊ አብሮነቱን ከማጠንከር በተጨማሪም የተለያዩ ኢኮኖሚያዊ፣ ስነልቡናዊ፣ ሃይማኖታዊ ጠቀሜታዎቹ በጥናቱ ተዳሰዋል፡፡

## ምዕራፍ ሶስት፡- የአጠናን ስነ ዘዴ

### 3.1 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

ይህ ምርምር ከዓይነታዊ ምርምር የሚመደብ ሲሆን "ዓይነታዊ ምርምር አመለካከትን፣ ባህርይን፣ ልምድን በቃለ መጠይቅ ወይም በተተኳሪ የቡድን ውይይት የሚያጠና የምርምር ዘዴ ነው። ከተሳታፊዎች ጥልቅ የሆነ አስተያየት ለማግኘት የሚሞከርበት፣ በአመለካከት፣ በባህርይ ወይም በልምድ ላይ ተመስርቶ የሚጠና ነው። እንዲሁም ለጥናቱ አስፈላጊና ዘላቂ የሆኑ ጥቂት ሰዎች ብቻ የሚሳተፉበት የምርምር ዘዴ ነው" (Dawson 2007, 15-16)።

ምርምር ውጤቱ እውነተኛ እንዲሆን የመረጃ መሰብሰቢያ እና መተንተኛ ዘዴዎቹ መስማማት አለባቸው። በመጀመሪያ ስለ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ስናነሳ ያለው (2004፣147) "የምርምር ውጤቶች በመረጃ ላይ የተመረኮዙ ሲሆን መረጃዎቹ ደግሞ በመሰብሰቢያ ዘዴዎቹ ላይ" በማለት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች አጥኝዎች የተለያዩ መረጃዎች በምን ዓይነት መንገድ መሰብሰብ እንዳለባቸዉ የሚጠቁሙ የምርምር ምሰሶዎች በመሆናቸው ለጥናቱ የሚስማሙ ዘዴዎች እንደሚያስፈልጉ ያስረዳል። ስለዚህ ትክክለኛ እና በመረጃ የተደገፈ ጥናት ለማድረግ፤ መረጃውን ለመሰብሰብ ለዚህ ጥናት የተሻሉ የምላቸውን ሦስት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ተጠቅሜአለሁ። እነርሱም፦ ቃለ መጠይቅ ፣ ምልከታ እና ተተኳሪ ቡድን ውይይት ናቸው።

#### 3.1.1 ምልከታ

ምልከታ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ መረጃዎችን ለመሰብሰብ መረጃው ወደሚገኝበት እና ጉዳዩ በሚከወንበት ቦታ በአካል ቀርቦ በመገኘት አምስቱንም የስሜት ህዋሶች በመጠቀም መረጃዎችን ከምንጩ የምንሰበስብበት እና በክዋኔ ወቅት የከዋኞችን ስሜት ዳር ሆኖ በመመልከት ወይም ተሳትፎ በማድረግና የከዋኞችን ስሜት በመጋራት መረጃ የምንሰበስብበት ዘዴ ነው። ዋነኛ ፋይዳውም ተመራማሪው በራሱ ዐይን የተሻሉ መረጃ ስለሚያገኝበት ነው።

በተጨማሪም፣ ምልክታ በስነ ሰብ ጥናቶች ላይ በብዛት ጥቅም ላይ የሚውል የመረጃ መሰብሰቢያ ዓይነት ሲሆን፣ ተመራማሪው በአካባቢው ያሉ ነገሮች ከሚያይለት አተያይ በዘለለ ጥልቅ አስተሳሰብ እና አስተውሎትን ተላብሶ ለምርምሩ ዓላማ ሲል የሚያደርገው እይታ እና እይታውን ለማድረግ ሳይንሳዊ መንገድን እና መሳርያዎችን የሚጠቀምበት ነው ሲል kotari (2004,345) ይገልጻል። በዚህም መሰረት የስጦታ ክዋኔዎችን ለማየት በሰርግ እና በክርስትና ድግስ እናቴ የተጋበዘችበትን አጋጣሚ ተጠቅሜበታለሁ። በዚህም መሰረት ስጦታ

የሚያመጡትን ሰዎች ስምና ያመጡትን የስጦታ ዓይነት እየመዘገቡ ሲቀበሉ ለመመልከት ችያለሁ። በተጨማሪም ታህሳስ 1 የነብዩ ኤልያስ ዓመታዊ ክብረ በዓል ላይ በቤተክርስቲያን እና ጥቅምት 16 በአባ ፈቂህ የመቃብር ስፍራ በመገኘት ለስለት እና ለነዳያን የሚሰጡትን የስጦታ ዓይነቶች እና የአተገባበር ደንቦች ለመመልከት ችያለሁ። በተጨማሪም ፈቃደኛ የሆኑ ተጠኚዎችን ጠይቄ በተለያዩ ዝግጅቶች የተሰጣቸውን ስጦታዎች ተመልክቻለሁ። ምልከታ በዋናነት ንቁ ተሳትፎ እና ኢ-ንቁ (ታዛቢ) ተሳትፎ በመባል ይከፈላል። ይህን ጥናት ኢተሳትፎአዊ በሆነ የምልከታ ዘዴን በመጠቀም በፎቶካሜራ የታገዘ መረጃ ለመሰብሰብ ተችሏል።ምክንያቱም የስጦታ ክዋኔ የሚከወንበት ዓላማ ከባለ ጉዳዮች ወይም ስጦታ ከሚለዋወጡ ሰዎች ውጪ ስለማያሳትፍ ነው።

### 3.1.2 ቃለ መጠይቅ

ቃለ መጠይቅ የተለያዩ መረጃዎችን ለማግኘት ቃላዊ የሆነ መንገድን ተከትሎ መረጃ መሰብሰብን ይመለከታል። ይህ ዘዴ ከመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ውስጥ መረጃ ሰብሳቢው እና መረጃ ሰጭው በአካል በመገናኘት ጥያቄ የሚቀርብበትና ምላሽ የሚሰጥበት ነው። ፈቃደ (1998፣81) "ቃለ መጠይቅ በቃል የሚቀርብ መጠይቅና በሁለት ሰዎች መካከል የሚደረግ የፊት ለፊት ተራክቦ ነዉ።" በማለት ይገልጻሉ። በዚህም መሰረት ከመረጃ ሰጪዎች ጋር ፊት ለፊት በመገናኘት የቃል ጥያቄ በማቅረብ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ችያለሁ።

ቃለ መጠይቅ በዋናነት በሦስት ዓይነት መንገዶች ይካሔዳል። እነርሱም ዝግ፣ ነጻ እና ከፊል ነጻ ይባላሉ። ያለው (2004፣ 180) "ነጻ ቃለ መጠይቅ በአብዛኛው ጥልቅ እና እና የተብራራ መረጃ ለመሰብሰብ ያገለግላል።" በማለት ገልጿል። በዚህ ጥናት ውስጥ በቃለመጠይቁ ጥልቅ እና የተብራራ መረጃ ለመሰብሰብ ነጻ ቃለ መጠይቅን የተሻለ ሆኖ በመገኘቱ ተግባራዊ ተደርጓል። በተጨማሪም ለመረጃ አቀባዮች ከጥናቱን ዓላማ ያልወጣ ነጻነት በመስጠት ለስጦታ ያላቸውን እሳቤ በጥልቀት ለማወቅና እና ስጦታ በማህበረሰቡ የተለያዩ ጉዳዮች ውስጥ ያለውን ሚና በስፋት ለመመርመር ይህ የቃለ መጠይቅ ዘዴ ተጠቅሜአለሁ።

ጥናቱ 3 የሃይማኖት አባቶችን እና 3 የሀገር ሽማግሌዎችን፣ በስራ ድርሻቸውም ሼህ፣ ቄስ፣ዲያቆን፣ ነጋዴ፣አርሶ አደር፣የቤት እመቤት፣ መምህር የሆኑ 13 ወንዶች እና 7 ሴቶች በአጠቃላይ 20 ተጠኚዎችን፣ አሳትፏል። ዓላማውን ለማሳካት ተጠኚዎችን በእድሜ፣ በጾታ፣ በማህበራዊ ደረጃ እና በስራ ድርሻቸው ሁሉን አቀፍ አሳታፊ ለማድረግ ጥረት አድርጓል። በመረጃ ስብሰባ ወቅትም ስጦታ ማለት ምን ማለት ነው? መቼ መቼ ይሰጣል? ስጦታ ተቀባይ

ስጦታውን እንዴት መቀበል አለበት? ስጦታ በመስጠት ሂደት ውስጥ የሚደገፈውና ነውር የሆነው ምንድን ነው? ምን ጥቅም አለው? ወዘተ. የሚሉ መሪ ጥያቄዎችን አዘጋጅቼ ጠይቄያለሁ፡፡ ቃለ መጠይቁም እንደ አስፈላጊነቱ በመደጋገም ለምሳሌ የስጦታዎችን ትርጉም ጥልቅ ማብራሪያ ለማግኘት እና እያንዳንዱ ተጠኝ እንደ ቡድን ያለውን እይታ ምን እንደሆነ ከምላሻቸው ለመረዳት እንዲሁም ከገለጻቸው ለነገሩ ያላቸውን ግንዛቤ እና አመለካከቶቻቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡ ይኸውም የስጦታ ደንቦች የቆየውን ልማድ ቀጣይነት ለመረዳት እንዲቻል ነው፡፡

### 3.1.3 ተተኳሪ የቡድን ውይይት

ተተኳሪ የቡድን ውይይት ከተለያዩ መረጃ ሰጪዎች የተገኙ መረጃዎች የተለየ ዓይነት አቅጣጫ በመያዝ የጥናቱ መረጃ የተዛባ እንዳይሆን ይጠቅማል፡፡ በተጨማሪም በቃለ መጠይቅም ሆነ በምልከታ ያልተሟሉ፣ ግልፅ ያልሆኑ፣ ማብራሪያ የሚፈልጉ፣ ወዘተ. ጉዳዮችን እርግጠኛ እና ሁሉን አቀፍ ስምሙነት ለመፍጠር የሚደረግ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ነው፡፡

ስለሆነም በስጦታ መለዋወጥ ዙሪያ በቃለ መጠይቅ እና በምልከታ የሚገኙ መረጃዎች ላይ የሚፈጠሩ የመረጃ ልዩነቶች፣ ግልጽ ያልሆኑ ምላሾች ማብራሪያ የሚፈልጉ መረጃዎችን ይበልጥ ግልጽ ለማድረግና ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ የቡድን ተኮር ውይይት ለማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በጥናቱ እቅድ መሰረትም ስብጥሩን በጾታ በመክፈል በሰርግ እና አራስ ቤት የሚዘዎትሩ ስጦታዎችን በተመለከተ ያገቡ እና የወለዱ ሴቶችን አካቶ አንድ ቡድን እና የሃይማኖት አባት በተገኙበት ደግሞ ሌላ ቡድን አሰባጥሮ ሁለት ቡድን ተኮር ውይይት ለማድረግ ታስቦ ነበር፡፡ ነገርግን በተጠኝዎች ፈቃደኛ አለመሆን ሰበብ ከሴቶች ጋር ውይይቱን ለማድረግ አልተቻለም፡፡ ሌላኛውን ውይይት ግን 1 የሃይማኖት አባት ጨምሮ 8 ተሳታፊዎችን በመምረጥ ሚያዚያ 1 ቀን 2013 ዓ.ም ተካሂዷል፡፡ የተመረጡ ናሙናዎችም በቃለ መጠይቅ መረጃ ስብሰባ ወቅት ስለጉዳዩ የተሻለ ዕውቀት እና ልምድ እንዲሁም ተሞክሮ አላቸው ተብለው የታሰቡ እንዲሁም ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች በተሻለ ለማብራራት የሞከሩ ናቸው፡፡ የውይይቱ መሪ ጥያቄዎች ስጦታ ምንድን ነው? በሰርግ እና በሌሎች የስጦታ ክዋኔ ወቅት የተቀመጡ ማህበራዊ ደንቦች ምንምን ናቸው? ከጾታ እና ማህበራዊ ደረጃ አንጻር እንዴት ይታያሉ? እንዲሁም ስጦታ ምላሽ አለው ወይ የሚሉ ናቸው፡፡

### 3.2 የናሙና አመራረጥ ዘዴ

ናሙና በልዩ ልዩ ምክንያቶች የተነሳ የጥናቱን አካላይ አባላት በሙሉ በመውሰድ በጥናቱ ተሳታፊ ለማድረግ ሳይቻል ሲቀር ወይም ማስተላለፍ አስፈላጊ ሳይሆን ሲቀር ነገር ግን አጠቃላዩን ስንወስድ መረጃ ሊሰጡን የሚችሉ ሰዎችን መርጠን መረጃ እንዲሰጡን የምናደርግበት መንገድ እንደሆነ ያለው (2004፣120) ይገልጻሉ፡፡ ይህ ጥናት እነማንን የሚፈለገው መረጃ ሊሰጡ ይችላሉ？ወይም የትኞቹ የጥናቱ አካላይ አባላት በጥናቱ ቢሳተፉ አስፈላጊውን መረጃ ላገኝባቸው እችላለሁ？የሚሉ ጥያቄዎችን በማንሳት የጥናቱን ዓላማ ለማሳካት ተሳታፊዎችን መርጧል፡፡

ተመራማሪዎች ሁለት አይነት የናሙና አመራረጥ አይነቶች በመጠቀም መረጃ ሰጪዎችን መለየት እንደሚችሉ ያለው (2004፤120) ይገልጻሉ፡፡ እነሱም ወሳኝ (Nonprobablity sampling) እና እድል ሰጪ (Random or Probability sampling) ናቸው፡፡ በዚህ ጥናት ወሳኝ የንሞና ዘዴን በመጠቀም እና  ዓላማ ተኮር የሆነ ስልትን በመከተል መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ ዓላማ ተኮር ንሞና የምርምሩን ዓላማ መሰረት በማድረግ መረጃ የሚሰበሰብበት ዘዴ ነው፡፡  ከዚህም አንጻር ጥናቱ ሁሉንም ሰው ከማሳተፍ ይልቅ ማህበረሰቡ የሚቀያየራቸውን ስጦታዎች ምንነትና ምክንያታዊነት በአጠቃላይ በስጦታ ዙሪያ ከሌሎች በተሻለ ልምድ አላቸው የተባሉ መረጃ ሰጪዎችን በጥቆማ እና በተሳትፎ ብቃት መርጦ በማሳተፍ መረጃው ተሰብስቧል፡፡

### 3.3 የመረጃ መተንተኛ ዘዴ

መረጃ መተንተን ሲባል የተለያዩ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን በመጠቀም እና መረጃ ሰጭዎችን በመምረጥ የተሰበሰቡ መረጃዎችን በተገቢው የመረጃ መተንተኛ ስልት ማስቀመጥና ማብራራትን ይመለከታል፡፡ ያለዉ (2004፣ 232) በዚህም መሰረት የጥናት ውጤት ለማግኘት የሚሰበሰቡት መረጃዎች በትክክለኛ የአተናተን ስልት ማስቀመጥ አስፈላጊ ይሆናል፡፡

ይህ ጥናት ዓይነታዊ ምርምር ዘዴን ተከትሎ ስለ ስጦታ ልማድ በምልከታ፣ በቃለ መጠይቅ እና በቡድን ተኮር ውይይት ፣ ዓላማ ተኮር የመረጃ አሰባሰብ ስልትን በመጠቀም የተገኙ መረጃዎችን በመጠን ይህን ያህል በማለት ሳይሆን በዓይነት ተንትኖ የጥናቱን ውጤት አቅርቧል፡፡ የዚህ ጥናት ትንተና ሂደት በቃለ መጠይቅ እና በቡድን ተኮር ውይይት የተገኙ መረጃዎችን ወደ ጽሑፍ ከመቀየር ጀምሮ የሃሳብ ድግግሞሹን በማውጣት ከጥናቱ ዓላማ አንጻር የይዘት ምደባ በማደርግ ፤እንዲሁም በምልከታ የተገኙ መረጃዎችን ደግሞ ከፎቶ ጋር

በማያያዝ ነው። ጥናቱን በዓይነታዊ የምርምር ስልት አካሄድ የከበራን (Ritual) አከፋፈል አጋዥ በማድረግ እና በሦስት የተለያዩ ንድፈ ሃሳቦች አተያይ ተተንትኗል። እነርሱም የመመሳሰስ ንድፈ ሀሳብ፣ አልተሪዝም ንድፈ ሀሳብ እና ትዕምርታዊ ንድፈ ሀሳብ ናቸው። ከእነዚህም ውስጥ የመመሳሰስ እና አልተሪዝም ንድፈ ሃሳቦችን በመጠቀም በዋናነት ተጠኝው ማህበረሰብ ስጦታ ለመሰጣጠት አነሳሽ የሆነውን ምክንያት ለመለየት ተሞክሯል ፤ በተጨማሪም ሁለቱም ቲዎሪዎች በመስጠት ሂደት የሚገኙ ጠቀሜታዎችን ስለሚያነሱ ስጦታ ያለውን ሁለንተናዊ ፋይዳ ለመተንተን አገልግለዋል። ሌላው የጥናት አላማ ስጦታ ያለውን ትዕምርት መተንተን ሲሆን በትዕምርታዊ አተያይ ንድፈ ሃሳቦች ተተንትኖ ቀርቧል። ስለሆነም ስጦታ ለመስጠት አነሳሽ የሆኑ ምክንያቶችን፣ የሚሰጡትን ፋይዳ እና ያላቸውን ፍቺ በዓይነታዊ ምርምር ስልት ሶስት የመተንተኛ ንድፈ ሀሳቦችን አጋዥ አድርጎ ቀርቧል።

## ምዕራፍ አራት፡- አካባቢያዊ ዳራ

### 4.1 የደብረ ኤልያስ አመሰራረት ታሪክ

ደብረ ኤልያስ፣ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት፣ በምስራቅ ጎጃም አስተዳደር ዞን ከሚገኙ ሀያ አንድ ወረዳዎች መካከል አንዷ ስትሆን፣ ከክልሉ ዋና ከተማ ባሕር ዳር 257 ኪ.ሜ ከዞኑ ርዕሰ ከተማ ደብረ ማርቆስ ደግሞ 42 ኪ.ሜ በስተደቡብ አቅጣጫ ትገኛለች፡፡ በአጼ ዘርዓ ያዕቆብ ዘመነ መንግስት በሰፊው ይደረግ የነበረው የጨዋ ወይም ወታደርን በየ ቦታው የማስፈር ሂደት ለደብረ ኤልያስ እና ለደብረ ኤልያስ ቤተ-ክርስቲያን መመስረት ዐቢይ አስተዋጽኦ እንዳደረገ ይነገራል፡፡ ወደ ማቻከል የመጣውን የጨዋ ወታደርና ሰፋሪ ከሌላው ለየት የሚያደርገው የሚታዘዘው በንጉሡ ዘንድ ከፍተኛ ተሰሚነትና ስልጣን ባለው የንጉሡ አማች ድል አሰማ መሆኑ ነው፡፡ የድል አስማ ሚስት እስክንድርያ የተሰኘችው የአጼ ዘርዓ ያዕቆብ ልጅ ናት፡፡ ድል አሰማ ወደ ጎጃም ማቻከል ከመምጣቱ በፊት ይኖር የነበረው ይፋት ሲሆን፤ ያስተዳድር የነበረው ይህንን አከባቢ ነበር፡፡ ወደ ጎጃም ሲመጣም የነብዩ ኤልያስን ታቦት አብሮ ይዞ መጣ፡፡ ወረዳውም ደብረ ኤልያስ የሚለውን ስያሜ ያገኘውም የነብዩ ኤልያስ ደብር በአካባቢው መደበሩን ተከትሎ ነው (ደብረ ኤልያስ የጥበብ ማዕከል፣199፣3)፡፡ በደብረ ኤልያስ ከተማ የሚገኘው የደብረ ገነት ነብዩ ኤልያስ ዓመታዊ ክብረ በዓልም በየዓመቱ ታህሳስ 6 ይከበራል፡፡ በዚህም ዓመታዊ ክብረ በዓል የሃይማኖቱ ተከታዮች የሆኑ የአካባቢው ማህበረሰቦች ለቤተክርስቲያኑ አገልግሎት ስጦታዎችን፣ ስዕለቶችን ያመጣሉ፡፡

ከደብረ ኤልያስ መመስረት በኋላ በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የመጀመሪያ አጋማሽ ከከተማው በስተሰሜን 10 ኪ.ሜ ርቀት ላይ የሚዘኝ ቀበሌ ውስጥ ድብዳቢ የተባለ ከፍተኛ ገበያ መቋቋመ፡፡ ይህ ገበያ ሊቋቋም የቻለው በአከባቢው በሰፈሩ ሙስሊም ነጋዴዎች ነው፡፡ በደብዳቢ የሚኖሩ ሙስሊም ነጋዴዎች በቁጥር እየተበራከቱና በኢኮኖሚና በሃይማኖት እየጠነከሩ እስከ 19ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ ድረስ ቆይተዋል፡፡ ለመጠናከራቸው ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረገው የፈቂህ ያሲን ወደ ድብዳቢ መምጣት ነው፡፡ እኚህ ሰው የመጡት ከጎንደር ሲሆን ፈቂህ የሚለው ማዕረጋቸው እንደሚያመለክተው በእስልምና የሃይማኖት ትምህርት የበቁ ሊቅ ነበሩ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ እንደ ቅዱስ የሚቆጠሩ ናቸው፡፡ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ሙስሊም ነጋዴዎች ከተለያዩ የጎጃም አካባቢዎችና ገብያዎች ወደ ደብዳቢ መጥተው ሰፍረዋል፡፡ ፈቂህ ያሲነ ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩ የተቀበሩትም በደብዳቢ ነው፡፡ መታሰቢያቸውም ጥቅምት 16 ቀን በመቃብራቸው በደማቅ ሁኔታ ይካሄዳል (ደብረ ኤልያስ የጥበብ ማዕከል፣199፣4)፡፡

አባ ፈቂህን ሙስሊሞች ከተለያዩ ቦታዎች በመምጣትም በየዓመቱ ይዘክሯቸዋል፡፡ በዓሉን ሲያከብሩም የእርድ ስነ ስርዓት ግብዣም በማድረግ ነው፡፡ ከዚህም የምንረዳው በደብረ ኤልያስ ወረዳ የሚገኙ ማህበረሰቦች ከኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት በተጨማሪ የእስልምና ተከታዮች በጋራ የሚኖሩባት ቦታ መሆኗን ነው፡፡ ሙስሊም እና ክርስቲያኑም ከሃይማኖቱን በጠበቀ መልኩ በተለያዩ ማህበራዊ ክንውኖች በሀዘን እና ደስታ ወቅቶች፣ በንግድ አብሮ ይሳተፋል፡፡




ፎቶ፦ የደብረ ኤልያስ ወረዳ ካርታ

## 4.2 የደብረ ኤልያስ መልክአምድራዊ ገጽታ እና መስህቦች

በወረዳው ውስጥ በብዛት ከሚታወቁ ቅርሶች መካከል  የአባ ተክለ አልፋ ምስሶ፣ ደብረ ገነት ኤልያስ ጥንታዊ ቤተ ክርስቲያን፣ የንጉስ ተክለ ሃይማኖት የትውልድ ቦታ የሆነው ገነት አቦ ቤተ ክርስቲያን፣ የአባ ፋቂህ ያሲን የመቃብር ቦታ እንዲሁምብሄረ ብፁአን አዬ መልክአ ስላሴ አንድነት ገዳም ናቸው፡፡ በደብረ ኤልያስ ወረዳ  57 የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን እና 2 መስጊዶች ይገኛሉ፡፡ ነገሮች ውስጥም ጥንታዊው እና በአብነት ትምህርት አሰጣጥ የታወቀው የደብረ ገነት ነብዩ ኤልያስ ቤተክርስቲያን ውስጥ የሚገኙ በአፈ ታሪክ "እንዲህ ከመሆናቸው

በፊት ለአምላክ ባለመታዘዛቸው ምክንያት የሙሽራ እና ሙሽሪት ድንጋዮች ተለወጡ" የሚባል አፈታሪክ የሚነገርላቸው ሁለት ድንጋዮች በደብረ ገነት ነብዩ ኤልያስ ቤተክርስቲያን ውስጥ ይገኛሉ።

ደብረ ኤልያስ በምስራቅ ጎዛምን፣ በምዕራብ ደንበጫ፣ በሰሜን ማቻከል ወረዳዎች እንዲሁም በደቡብ ኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ወለጋ ዞን ያምስኗታል። ወረዳዋ በ16 የገጠር ቀበሌዎች ፣ በ2 የከተማ ቀበሌዎች፣በ1 ንዑስ የገጠር ከተማና በ2 ታዳጊ የገጠር ከተሞች የተከፋፈለ ሲሆን በአጠቃላይ 21 የከተማና የገጠር ቀበሌዎችን የያዘ ነው። እነዚህም ደ/ኤልያስ ከተማ 01፣ ደ/ኤልያስ ዙሪያ፣ አበሽብ፣ የቀጋት፣ ደጅባ፣ የጓራት፣ የሜዘኝ፣ ግብየዊት፣ የደንበኝ፣ የግዳድ፣ ጎፍጭማ ታዳጊ ከተማ፣ ጎፍጭማ ዙሪያ፣ ደጎልማ፣ ጥጃ ጎጠር፣ ጓይ ንዑስ ታዳጊ ከተማ፣ ገነት ታዳጊ ከተማ፣ ጫጎ እና ዋሜት ቀበሌዎች በመባል ይታወቃሉ። የወረዳዋ የመሬት አቀማመጥ ከፍታው ከባህር ወለል በላይ 1,500 እስከ 2,150 ሜትር ይደርሳል። ከዚህም ውስጥ ሜዳማ 76,100,535 ሄክታር፣ ተራራማ 6,638.05 ሄክታር፣ ሸለቋማ 12,111,755 ሄክታር፣ ወጣገባ 21,593.04 ሄክታር፣ ረግረጋማ 163.08 ሄክታር ነው። የማህበረሰቡ አብዛኛው ክፍል በግብርና የሚተዳደር ሲሆን በአጠቃላይ ካለው 53,278 የህዝብ ብዛት 83.1% የሚሆነው የገጠር ነዋሪ ቀሪው 16.9% ደግሞ በደብረ ኤልያስ ከተማ የሚኖር ነው። ከግብርና ምርቶች ስንዴ፣ በቆሎ ፣ጤፍ፤ ሰሊጥ፣ኑግ፣ እጣን ወዘተ. ይገኙበታል።ነገር ግን ከግብርና በተጨማሪ በ ልዩ ልዩ የንግድ ስራዎች ይተዳደራሉ። (በልማት እቅድ ክትትል ግምገማ ቡድን በሶሺዮ ኢኮኖሚክስና እስታትስቲክስ ባለሙያ የተዘጋጀ ብሮሸር 2013 ዓ.ም)

## 4.3 የደብረ ኤልያስ ማህበረሰብ ዝምድ መመስረቻ መንገዶች

ማኅበረሰቦቹ  በኑሯቸው ውስጥ በተለያዩ ምክንያቶች ማኅበራዊ አብሮነታቸውን ለማስቀጠልም በተለያዩ ማኅበራዊ እና ሃይማኖታዊ ጉዳዮቻቸው ስጦታ መቀያየር እንደ ምሳሌ ማንሳት እንችላለን። ለምሳሌ፦ ዝምድና መፍጠሪያ መንገዶቹን ስንመለከት የስጦታን ሚናን በሰፊው እናገኛለን። ጋብቻ (ልጅህን ለልጄ ብሎ መስጠት)፣ አበልጅ (ክርስትና በማንሳት ልጅን መስጠት)፣ ጡት መጣባት ወይም የስጋ ተወላጅ ያልሆነን ሰው አቅፎ የማኖር፣ የወላጅ እና የልጅ ግንኙነት መፍጠርና ሀብትን ሁሉ መስጠት ወይም የማውረስ አንዱ መንገድ ነው።

በጋብቻ ልማድ  ዝምድናን ለመፍጠር ወዳጅነትን ለማጠንከር፣ በጸብ የሻከረ ግኑኝነትን ሳይቀር ለማለሳለስ፣ ልጅን በመስጠትና ልዩ ልዩ ስጦታዎችን በመቀያየር ማህበረሰቡ አብሮ ለመኖር ሲል ያወጣቸውን ደንቦች፣ ለማጽናትና ለማስቀጠል የስጦታ ሚና ከፍተኛ እንደሆነ በጥናቱ

የተዳሰሰ ጉዳይ ነው። በተጨማሪም ከጋብቻ ጋር በተያያዘ በጋብቻ ዕለት የሚደረጉ ስጦታዎች ጥሎሽ፣ ለሕን መጠበቅ ለወላጆቿ የሚሰጥ ስጦታ፣ ጋብቻ ከተፈጸመ በኋላ ሙሽራዋ ከባሏ ቤተሰብ ወደ ወላጆቿ ቤት ስትመለስ ለዘመድ ጥየቃ፣ የጫጉላ ቤት ስጦታዎች፣ ለአዲስ ጎጆ መውጫ ወይም ለማቋቋሚያ ከቤተሰብ የሚሰጣቸው ስጦታ ሁሉ እንደ አካባቢው ህግና ደንብ የሚፈጸም ነው።

ከጋብቻ ሌላም ማኅበረሰቦቹ ለተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮቻቸው ለምሳሌ፦ በደም ዋጋ ለመታረቅ የሚች ወገኖች ሲስማሙ ካሳ (ስጦታ) ይቀርባል። በሞት ጊዜ በስጦታነት የሚቀርብ ውርስ እና በኑዛዜ የሚተላለፉ ስጦታዎች አሉ። ለነፍስ አባት፣ ለክርስትና ልጅ፣ ለአባት፣ ለእናት፣ ለታላቅ፣ ለወለደች ሴት፣ ለዳረች እናት ወዘተ በእነዚህ ሁሉ ጉዳዮች ውስጥ ስጦታ እና የስጦታ ህግ አለ። በተለያዩ ወቅቶች ለምሳሌ፦ እህል ያለው ሰው እሸት ሲደርስ "እሸት ቅመሱ" ብሎ፤ ከብት ያለው ሰው ለቅበላ ወይም ጾም ሲፈታ ወተቱን ይዞ ወዳጆቹን ይጠይቃል።

ከሃይማኖት ጋር በተያያዘም ከደብረ ኤልያስ ከተማ እና ከድብዳቢ ውጪ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት ተከታዮች ናቸው። ከዚህ በፊት እንደተገለጸው በወረዳዋ ውስጥ ወደ 57 የሚጠጉ አብያተ ክርስቲያናት ሲኖሩ በየታቦታቱ ንግስ ወቅት በአካባቢው ልማድ "የሀገራችን ዓመት በዓል" በማለት ያከብራሉ። ድግስ ደግሰው በየአካባቢው የሚኖሩ ወዳጅ ዘመዶቻቸውን እና ወደ ቤታቸው የሄደውን እንግዳ ሁሉ ይጋብዛሉ። በየገጠር ቀበሌው የሚገኙ አድባራት ዓመታዊ ክብረ በዓል ውስጥ፦ የነብዩ ኤልያስ ክብረ በዓል ታህሳስ 1 (በደብረ ኤልያስ ከተማ) ፣ የቅዱስ ሚካኤል ክብረ በዓል ጥር 12 ( በአበሽብ፣ በየቁልጭ፣ በየጠንጠር፣ በምችግ፣ በጉለት፣ በየንራት፣ በየግዳድ እና በየፉይ አካባቢዎች) የቅዱስ ጊዎርጊስ ክብረ በዓል ጥር 18 (በእነጋት፣ በአታንጎ፣ በየገወጥ፣ በየደንበኝ፣ በመቤሽ እና በጅረት አካባቢዎች) የኪዳነ ምህረት ክብረ በዓል የካቲት 16 (በየቀጋት እና በለምለሚት አካባቢዎች) የአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ክብረ በዓል መጋቢት እና ጥቅምት 5 (በዝርኝ፣ በየሳሰር፣ በመያት፣ በጫጎ እና በገነት አካባቢዎች) የቅድስት ድንግል ማርያም ክብረ በዓል ጥር 21( በቦሽቃ፣በደለደል፣ በግብጻዊት፣ በመልቃ፣ በድጅም እና በጥጃጎጠር አካባቢዎች) የቅዱስ ገብርኤል ክብረ በዓል ታህሳስ 19 (በጨባ፣ በጫጎ እና በደጅባ አካባቢዎች) የመድኃኒያለም ክብረ በዓል ጥር 27 (በጅረሰብ እና በመጨኔ አካባቢዎች) የአቡነ ተክለ ሃይማኖት ክብረ በዓል ታህሳስ 24 (በጠራሞ እና በደጅባ አካባቢዎች) በዓሉን እንደ ሃይማኖታዊ ክብረ በዓል ብቻ ሳይሆን እንደ አካባቢው ዓመት በዓል ቆጥሮ

ከወዳጅ ዘመድ ጋር  የማክበር ልማድ አላቸው፡፡ እንዲሁም ጥቅምት 16 የአባ ፊቂህ መታሰቢያ በዓል ድብዳቢ በሚገኘው የአባ ፊቂህ መቃብር ስፍራ በመሄድ ያከብሩታል፡፡

በዚህ ጥናት ውስጥም በወረዳው ከሚገኙ ከተማዎች እና የገጠር ቀበሌዎች መካከል የደብረ ኤልያስ ከተማን ማህበረሰቦችን ተጠኝ በማድረግ ያለው የስጦታ ልማድ ተመርምሯል፡፡

## ምዕራፍ አምስት፡- የመረጃ አቅርቦትና ትንተና

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ በደብረ ኤልያስ ከተማ የሚኖሩ ማኅበረሰቦች ስጦታ ለመስጠትና ለመቀበል ያሉአቸውን ማኅበራዊ ደንቦችና አነሳሽ ምክንያቶችን በመግለጽ፣ የስጦታዎቹ ዓይነት፣ ትዕምርት እና ፋይዳዎቻቸው ተተንትነዋል። በዚህ ክፍል በዋናነት በተቋማዊ ሃይማኖቶችና በባህላዊ እምነቶች ውስጥ የሚከወኑ መስዋእቶች፣ ስእለቶችና መብዓዎች፣ በጋብቻ ወቅት የሚቀርቡ ጥሎሾች፣ በወሊድ ጊዜ የሚቀርቡ የአራስ መጠየቂያዎች፣ የደከሙን ለማገዝ፣ ያዘኑትን ለማጽናናት የሚደረጉ ድጋፎች ሁሉ እንደስጦታ ተቆጥረው ተመርምረዋል።

### 5.1 የሽግግር ወቅት ሥርዓተ ከበራዎች ስር የሚገኙ ስጦታዎች

በዚህ ክፍል ውስጥ በመወለድ፣ በማደግ እና በሞት ወቅት የሚሰጡ ስጦታዎች ቀርበዋል።

#### 5.1.1 በመወለድ ጊዜ ያሉ ስጦታዎች

- ✓ የገንፎ ስጦታ

ይህ ስጦታ የሚዘጋጀው በወለደችው ሴት ወይም በአራሷ ቤት ሲሆን በወለደች በሶስተኛ ቀኗ በትልቅ ድስት ገንፎ ይገነፋል። እርሷም "ኑ ገንፎ ቅመሱ" በማለት የምትፈልጋቸውን ሰዎች ትልክባቸዋለች። የተዘጋጀውን ገንፎም ተሰብስበው ይበላሉ። የሚጠሩትም ሰዎች በዋናነት የአጥሚት እና የገንፎ እህሉን ለማዘጋጀት በጉልበት ያገዙ ሴቶች ናቸው። ይህን አስመልክቶ በቃለመጠይቅ ወቅት እማዋይ "ገንፎ ብሉ የሚባለው በወለደች በሶስተኛ ቀኗ ጎረቤት እና የገንፎ እህሉን የፈተጉላት ሰዎች ጠርታ ቡና አፍልታ በመጥራት ነው። እነርሱ እሷን ብለው ሲለፉ ስለነበር ያዘጋጁትን ማቅመስ እና ማመስገን እነርሱም ነፍሰጡር ሲሆኑ በጉልበት ማገዝ አለባት ለምን ብትይ ማህበራዊ ኑሮ ለመኖር ሲባል ነው።" በማለት ይገልጣሉ።

በዚህ የስጦታ ልውውጥ ጎረቤት ለመውለድ የደረሰችን ሴት በአራስነቷ ለሚያስፈልጋት እህል ዝግጅት የጉልበት ስጦታ እንደሚያደርጉ እና እርሷም በወለደች ጊዜ ጎረቤቶቿ ላደረጉላት ትብብር ገንፎ በማብላት ምስጋናዋን እንደምታቀርብ ወይም ውለታ ለመመለስ እንደምትጥር እንመለከታለን። በማህበረሰቡ የስጦታ ደንብ ውስጥ ሰው እህል ውሃ ይዞ ለመጠየቅ ሲመጣ ስጦታ ተቀባዩ

በሪስፕሮሲቲ ንድፈ ሃሳብ አተያይ መሰረት በስጦታ ክንውን ውስጥ መጀመሪያ የሰጠው ሰው ላበረከተው ስጦታ ከተቀባይ በጎ ምላሽ እንደሚኖረው ያምናል ስጦታ ተቀባዩም ውለታ የመመለስ ግዴታ ይሰማዋል። ምልልሱም ወዲያው የሚመለስ እና ከጊዜ በኋላ የሚመለስ

አንዳንድ ጊዜም የማይመለስ አከዋወን ያለው ሲሆን በዚህ የስጦታ ደንብ ውስጥ ነፍሰጡር ሴትን በጉልበት ሲረዱ ከወለደች በኋላ ገንፎ አዘጋጅታ እንደምትጠራቸው ከጊዜ በኋላም እነርሱ ነፍሰጡር ሲሆኑ በጉልበት እንደምታግዛቸው ይጠብቃሉ፡፡ ስጦታ ተቀባይም ደንቡን ጠብቃ ምስጋናዋን በስጦታ ታቀርባለች፡፡ በዚህም አማካኝነት ማህበረሰቡ የስጦታ ምልልሱን ቀጣይነት በመጠበቅ እርስበርስ የመረዳዳት እና አብሮ የመኖር መስተጋብሩን ለማስቀጠል የሚጠቀምበት አንድ መሳሪያ እንደሆነ እንረዳለን፡፡

- ✓ የአራስ መጠየቂያ ስጦታዎች

አንዲት ሴት የእርግዝናዋን ወራት ጨርሳ ልጅ ከወለደች ጀምሮ እስከ አርባ ወይም ሰማንያ ቀናቶች ድረስ ረፍት ታደርጋለች፡፡ እንደ ሀዘን እና የጤና እክሎች ያሉ አስገዳጅ ችግሮች እስካልተከሰቱ ድረስም ከቤቷ ወጥታ ህዝብ በተሰበሰበባቸው ቦታዎች አትታይም፡፡ ለእርሷ እና ለልጇም አስፈላጊ የሆነ ጥበቃ እና እንክብካቤ ይደረግላታል፡፡ ጠንክራ ሆና ወደ በፊት ብርታቷ እስክትመለስ ድረስም  ጎረቤቶቿ ፣ ወዳጆቿ እና ዘመዶቿ "እንኳን ማርያም ማረችሽ" ወይም “እንኳን በቀኝ አቆመሽ” እያሉ የተለያዩ ስጦታዎችን ያመጡላታል፡፡ የአራስ መጠየቂያ ስጦታን አስመልክቶ ወይዘሮ የሺእመቤት (ቃለመጠይቅ፣14/08/2013 ዓ.ም፣ ደ/ኤልያስ) የተባሉ ተጠኝ የአራት ልጆች እናት ሲሆኑ በቃለ መጠይቅ ወቅት አራስ ቤት የሚወሰደው ስጦታ ያለውን ደንብ  እንዲህ አስረድተዋል፡፡

> አንድ ሴት ስትወልድ የመጀመሪያዋን ወንድ ተወለደች እንክብካቤው ልዩ ነው፡፡ ባሏ ወይም የባሏ አባት ሙክት ያርድላታል፣ እንዲያውም ገንዘብ ታለው በየሳምንቱ ይታረድላታል፡፡ እናቷም በህይወት ታለች ታርሳታለች፣ በየሶስት ቀኑ ቅቤ ትቀባታለች፣ ዘመድ ጎረቤቱም ላም ታለው ላሚቱን ሞክሮ ወተቲቱን ያጠጣታል ቅቤ ይቀባታል፡፡ ከብት ተሌለውም ጭብጦውን ጨብጦ ወይ ወጪቱን ሰርቶ ቋጥሮ ያመጣላታል፡፡ በገንቦ ጠላ እንጀራ ይወሰዳል፡፡ እስተ ክርስትናው ድረስ እንኳን ደስ አላችሁ፣ አንችንም እንኳን በቀኝ አቆመሽ እየተባለ እህል ውሃ ተይዞ ይጠየቃል፡፡

በዚህ የስጦታ አተገባበር ማህበረሰቡ ለአንዲት ሴት በአራስነቷ ከሚሰጧት ስጦታዎች መካከል እንደ በግ (ፍየል) ፣ ገንፎ፣ ጭብጦ፣ ቅቤ እና ወተት ወዘተ. ያሉ የተለያዩ ገንቢ ምግቦችን ነው፡፡ ሰጭዎች አባወራ፣ ቤተሰቦቿ እና ወዳጆቿ ሲሆኑ ስጦታውን የሚያበረክቱላትም የደስታዋ ተካፋይ መሆናቸውን ለመግለጽ እና ቤተሰብ ሲሆኑ ደግሞ እርሷን የመንከባከብ ሀላፊነትን ለመዎጣት ጭምር ነው፡፡ ከቃለመጠይቁ የምንረዳውም የአራስ ስጦታ አብዛኛውን

ጊዜ ዓይነትና መጠናቸው እንደ ሰጭው አቅምና ዝምድና ሁኔታ ሊለያይ እንደሚችል ወይም የሚቀርበው ስጦታ በኢኮኖሚያዊ አቅም እና በሰዎች መካከል ባለ ቅርበት ሊወሰን እንደሚችል ነው፡፡ በተጨማሪም ሰጭዎች በሚያቀርቡት ስጦታ ውስጥ ማንነታቸው ይገልጻሉ፡፡ ለምሳሌ፦ ከብት አርቢዎች ወተት እና የወተት ተዋጽዎችን በስጦታነት ሲያበረክቱ እንመለከታለን፡፡ አራስ ለመጠየቅ እነዚህ ሁሉ ስጦታዎች ያላቸውን አስፈላጊነት ምን እንደሆነ እና ስጦታው ባይኖር ያለው አሉታዊነት ምን እንደሚመስል (ወ/ሮ  እማዋይ 14/8/2013 ዓ.ም ደ/ኤልያስ) እንዲህ አስረድተዋል፡፡

> እንኳን አራስ ዘንድ ሌላ ሰው ዘንድም ባዶ እጅ መሄድ ነውር ነው፡፡ ለብቻው ቢያጣ እንኳን ካለው ጎረቤቱ  ጋር ተደምሮ ይሄዳል፡፡ ምክንያቱም ተሰቃይታ እና ብዙ ደም አፍሳ ስለምትወልድ እንድታገግም ጥሩ ምግብ ያስፈልጋታል፡፡ አራስ ስለሆነች እና ስለምታጠባ ቶሎ ቶሎ ስለሚርባት እርሷም  አይን አይን ማየቷ አይቀርም፡፡ ሰው ይህን ተረድቶ ጠንክራ እስክትነሳ አለሁ አለሁ ማለት ይገባዋል፡፡ ቤተሰብ አጠገቧ ከሌለ ደሞ እርሷ ከተኛች የሚያበስለው አይገኝም፡፡ ስለዚህ ምግብ ተቋጥሮ ገንፎ ተገንፍቶ ይጠየቃል፡፡ የሚቋጠረው እህል ውሃውም ደም የሚተካ ሰውነት የሚሆናት ተመርጦ ነው፡፡ ሰው እንዲያው ሀብት እያለው ስስት የያዘውም ካለ እርሱም ተራው ደርሶ ሲወልድ  ብድሩ ይመለስለታል፡፡

በዚህ ምላሽ ውስጥ ማህበረሰቡ መውለድ ተፈጥሮአዊ ጉዳይ መሆኑን በመገንዘብ በራሱ ሲደርስ እንዳይጎዳ አስቀድሞ በመስጠት እንደ ውለታ የሚያስቀምጥበት የአኗኗር ጥበብ እንዳለው እንረዳለን፡፡ በተጨማሪም አራስ በባዶ እጅ አይጠየቅም የሚል ደንብ እናገኛለን፡፡ ከዚህ ህግ መውጣት ለሃሜት /ለትችት/ ያጋልጣል፡፡ በአንጻሩ እንደድንጋጌው መገኘት ደግሞ ያስከብራል፤ ትልቅ ያሰኛል፤ በአርአያነት ያስጠራል፡፡ የስጦታው ዓይነትም አራሷን ለመንከባከብ በወሊድ ጊዜ የወጣውን ፈሳሽ የሚተካላትን እና የነበረውን አካላዊ ጉዳቷን የሚጠግን እንዲሁም የቀድሞ ጥንካሬዋ እንዲመለስ ጠቃሚ የሚለውን መርጦ ይሰጣል፡፡ በዚህም በአራስነት ጊዜ ያለው የአመጋገብ ስልት እና የምግብ ምርጫ የአካል ጥንካሬ እንዲሁም ኃይልና ሙቀት የሚሰጡት ምግቦች እንደሆኑ እንረዳለን፡፡ በተጨማሪም በስጦታ ምርጫው እርስ በእርስ ያለውን መተሳሰብ የሚያሳይበት እንዲሁም ሰጪው ከአራሷ እና ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር ያለውን ማህበራዊ ግንኙነት የሚያጠናክርበት፣በኢኮኖሚ የሚደግፍበት አንዱ መንገድ እንደሆነ እንረዳለን፡፡

- ✓ የክርስትና ስጦታዎች

በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት ተከታዮች ዘንድ ወንድ ልጅ በተወለደ በአርባኛ ቀኑ ሴት ልጅ ደግሞ በሰማኒያ ቀኗ ወደ ቤተክርስቲያን በመሄድ ይጠመቃሉ ወይም የሃይማኖቱ ተከታይነታቸውን ያረጋግጣሉ። ጥናቱ በተደረገበት አካባቢም አብዛኛዉ ህዝብ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት ተከታይ በመሆኑ ከመውለድ በኋላ ክርስትና ማስነሳት የተለመደ ነው። ከክርስትናው ጋር ተያይዞ የተለያዩ ስጦታዎችን በማድረግ ይደሰታሉ። ከክርስትና ጋር የሚገናኙ ስጦታዎችም የሚከተሉት ናቸው።

- ልጅን መስጠት

ይህ ልማድ በተጠኘው ማህበረሰብ ዘንድ አንድ ህጻን ክርስትና በሚነሳበት ጊዜ ወላጅ ለታቦት ወይም ዘመድ መሆን ለፈለገ ሰው ልጁን የሚሰጥበት ልማድ ነው። ልጅ ለታቦት የሚሰጥበት ምክንያትም ህጻኑ በስለት የተገኘ ወይም በጤናው ላይ ችግር ያለበት ሲሆን ወይም ወላጅ ከሚሰጠው ታቦት ጋር ጥልቅ የሆነ ፍቅር ሲኖረው እንደሆነ (ወ/ሮ ንጹህ፣ቃለ መጠይቅ 06/08/2013ዓ.ም፣ ደ/ኤልያስ) ይገልጻሉ።

> በክርስትና ጊዜ ልጅ ለታቦት የሚሰጠው በመጀመሪያ እናት እና አባት መውለድ እንቢ ሲላቸው ልጅ እንዲሰጣቸው ስዕለት ያደርጋሉ። ልጁ ሲወለድም በክርስትናው ለታቦት ይሰጣል። የመጀመሪያ ልጅ ከሆነ እና ወንድ ከሆነ ለቤተክርስቲያን አገልጋይ ይሆናል። ሌላው ደግሞ ህጻኑ ከተወለደ ጤና የማያድር ከሆነ ጤናው እንዲስተካከል ክርስትና ለተነሳበት ታቦት ይሰጣል። አንዳንድ ሰው ደግሞ ከታቦት ሁሉ አብልጦ ለሚወደው ታቦት ልጁን ይሰጣል። ያው ወዳጅነቱን ለማጠናከር ፣ ልጁን እንደ ወላጅ እንዲንከባከብለት ለታቦቱ ነግሮ ልጁን ይሰጠዋል። አሊያም ለወዳጁ ይሰጠዋል።

ከዚህም የምንረዳው ማህበረሰቡ ልጅን ለታቦት በመስጠት የጤና ሁኔታን ማስተካከል፣ ከመጥፎ ነገር መጠበቅ እና ልጁ እና የልጁ ወላጆች ከታቦት ጋር ያላቸውን ግንኙነት ማጠናከር የሚችሉበት መንገድ እንደሆነ እንደሚያምን ነው።

ከታቦት በተጨማሪ ወላጅ ልጁን ለወዳጁ ይሰጣል። ይህም የዝምድና መፍጠሪያ ልማድ አበልጅነት ይባላል። አበልጅነት ዝምድናውን ለፈለገው ሰው ልጅን በመስጠት የሚፈጸም ነው። በመስጠት ሂደቱ ውስጥ ሰጪው ወላጅ፣ ለስጦታ የሚቀርበው ነገር ልጅ፣ ስጦታ ተቀባዩ ደግሞ የክርስትና እናት ወይም የክርስትና አባት ነው። በዚህ የዝምድና መፍጠሪያ ደንብ የክርስትና እናት ወይም አባት ከወላጆቹ ቀጥሎ ለልጁ እንክብካቤ ያደርግለታል። ስለ አበልጅ

ምንነት በአማራ ባህል የተለመደ እና የክርስትና አባት ወይም እናት በልጁ ጥምቀት ጊዜ ከልጁ ወላጆች ጋር የሚመሰርት እንደሆነ (ጌቴ፣1998፣78) "This is a very common practice in every Amhara household. God parenthood that is, establishing an abälej', takes place at the time of baptism, when a child is christened at the local parish church" በማለት ይገልጻል፡፡ በአማራ ማህበረሰብ ዘንድ የተጠኝውን የደብረ ኤልያስ ማህበረሰብ ጨምሮ አበልጅ መሆን ወይም ልጅን መስጠት ዝምድና የመፍጠሪያ አንድ መንገድ ነው፡፡ አበልጅነት ሃብት የሌላቸው ሰዎች ካላቸው ፣ለአካባቢው መጤ የሆኑት ከኗሪው ፣ ልጅ መውለድ የማይችሉት ልጅ ካላቸው ጋር በመዎዳጀት ዘመድ የሚሆኑበት እና ዘመድ ከሆኑት ሰው እንዲሁም ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር ያላቸውን ትስስር የሚያጠናክሩበት ትልቅ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ስነልቡናዊ ፋይዳ ያለው ዝምድና መፍጠሪያ መንገድ ሲሆን ዝምድናው የሚመሰረትበት ዋና መሳሪያ ደግሞ ስጦታ (ልጅን መስጠት) ሆኖ እናገነዋለን፡፡

- የክርስትና ድግስ ስጦታዎች

በተጠኝው ማህበረሰብ በክርስትና ወቅት ድግስ የማብላት ልማድ አለ፡፡ ባለ ክርስትናዎቹ ቤተክርስቲያን ሄደው የክርስትና ስርዓቱን ከጨረሱ በኋላ በመኖሪያ ቤታቸው ምግብ መጠጥ አዘጋጅተው ክርስትና ያነሱትን የሃይማኖት አባቶች፣ በአራስነት ወቅት የጠየቋቸውን ወዳጅ ዘመዶች እንዲሁም በአካባቢው የሚገኙ ችግረኞችን ድግስ እንደሚያበሉ በምልከታ እና በቃለመጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ የተጠሩ ወዳጅ ዘመዶችም የተለያዩ ስጦታዎችን ይዘው ይሄዳሉ፡፡ ይህን አስመልክቶ አቶ ዋለ (ቃለመጠይቅ፣ 08/08/2013ዓ/ም፤ደ/ኤልያስ) እንደሚከተለው ያስረዳሉ፡፡

> አንድ ሰው ለወግ ለማዕረግ በቅቶ ዘሩን ተክቶ ሲያበቃ ክርስትና አስነስቶ ድግስ ደግሶ "ኑ ልጃችሁን መርቁ" እያለ ይጣራል፡፡ የተጠራውም ሰው ቤተሰብ ወይም የቅርብ ወዳጅ ከሆነ የደስ ደስ እንጀራውን እና ጠላውን ጭኖ ይሄዳል፡፡ አቅሙ የማይፈቅድ ከሆነ እንደ አቅሙ አረቄ ወይ ለልጁ ልብስ ታልሆነም ደግሞ ብር ጠቅለል ተደርጎ ስጦታ ሰጥቶ በልቶ ጠጥቶ እንኳን ለዚህ አበቃችሁ ብሎ ይመለሳል፡፡ እንግዲህ ባለክርስትናው ደግሞ እገሌ ይህን አመጣልኝ ብሎ በልቡናው ጽፎ ያስቀምጠዋል፡፡ በሌላ ጊዜም የተሰጠውን ወይም ተዚያም አብልጦ ይመልሳል፡፡

ከዚህም የምንረዳው በማህበረሰቡ ዘንድ በክርስትና ወቅት ምግብ እና መጠጥ ልብስ እንዲሁም ገንዘብ ለስጦታነት የሚቀርቡ ሲሆን የክርስትና ስጦታውም ደስታን ለመግለጽ፣ ምስጋና

ለማቅረብ፣ ማህበራዊ ግንኙነትን ለማስጠበቅ እንዲሁም ችግረኞችን በመጋበዝ የመረዳዳት ባህልን ለማጠናከር እንደሚያገለግል ነው። በተጨማሪም "ኑ ልጃችሁን መርቁ" የሚለው የክርስትናው ጥሪ ልጁ የአባትና የእናቱ ብቻ ሳይሆን የቤተ ዘመዱ፣ የአካባቢው ሰው ጭምርም እንደሆነ የሚጠቁም ነው። በዚህ ሂደት ውስጥ ልጃቸውን፣ አንድም ለታቦት ሰጡት፤ አንድም ለክርስትናአባት /እናት/ ሰጡት፤ አንድም፣ በጥሪው ቃል እንደተመለከተው ለሁሉም ሰው ሰጡት - "ኑ ልጅችሁን መርቁ!" ሲሉ። በድግስ ወቅት የተጠራው ሰው ለባለ ድግሱ ቅርብ የመሆን እና የደስታ ስሜት፣ ያልተጠራው ደግሞ የመገለል እና የመከፋት ስሜት ይሰማዋል። በዚህም ውስጥ ደግሶ ማብላት በሰዎች መካከል ያለውን የግንኙነት ገመድ የሚያጠብቅ እና ይበልጥ የሚያቀራርብ አለመስጠት ደግሞ በተቃራኒው ግንኙነትን የሚያሻክር ሆኖ እናገኘዋለን።

- ✓ የሀቂቃ ስጦታዎች

በደብረ ኤልያስ ከተማ ውስጥ እስላምዬ (ወላስማ) ሰፈር የእስልምና እምነት ተከታዮች በብዛት ይኖራሉ። በዚያም ተገኝቼ በወሊድ ወቅት ያለውን ማህበራዊ አብሮነት እና የስጦታ ልማድ ጠይቁአለሁ። ስለ ጉዳዩም ሼህ እስሚ (ቃለመጠይቅ 18/08/2013 ዓ.ም፣ ደ/ኤልያስ) ምላሽ ሰጥተውኛል።

> በእስላም አንዷት ሴት ስትወልድ ክርስቲያኑም ሙስሊሙም ጎረቤት ይጠይቃታል። ሴቶች ቅቤ ይቀቧታል፣ ኩል ደቁሰው ይኩሏታል፣ ህጻኑን ያጥቡላታል፣ ምግብ ጠዋት እና ማታ ያመጡላታል። አባወራውም በአራስነቷ እያረደ በደንብ ይንከባከባታል። በአርባ ቀኑ ህጻኑ ሀቂቃ ይወጣለታል። ይኸውም ልደት ማክበር በሙስሊም ስለማይፈቀድ የሀቂቃው ድግስ በደንብ ተደግሶ ይከበርለታል። በሀቂቃው ቀን የተጠራው ሰው ስጦታ ያመጣለታል። የሚመጣው ስጦታም አብዛኛው ጊዜ ልብስ ነው። ሌላው በሙስሊም መጠጥ ስለማይፈቀድ ከእርሱ ውጪ እንጀራ፣ ወጥ፣ ቡና፣ ስኳር ተይዞ ይሄዳል። በሀቂቃው አባት ለልጁ ከንብረቱ ይህን እሰጣለሁ ብሎ ቃል ይገባለታል።

ከዚህ የምንረዳው በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ለህጻን ክርስትና ሲከበር በሙስሊም ደግሞ ሀቂቃ እንደሚወጣለት ነው። በሁለቱም ስርዓቶች ውስጥ ስጦታ እንደሚደረግ ከመረጃው የምንረዳ ሲሆን በተጠኘው ማህበረሰብም በሃይማኖት ምክንያት ስርዓተ ከበራው ቢለያይም በሁለቱም ላይ ያለው የስጦታ ሚና ግን ተቀራራቢ ዓላማ ያለው መሆኑን በመረጃ ስብሰባ ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል። ይኸውም ሚና ደስታን መግለጽ፣ ማህበራዊ ግንኙነትን ማጠናከር

እና የህጻኑን የወደፊት ህይወት ምቹ ማድረግ ነው። በተጨማሪም አማኙ ልጁን ለታቦት በሚሰጥበት ጊዜ ሙስሊሙም የልጁን ሀቂቃ በሚያወጣበት ጊዜ ከፈጣሪው ጋር ያለውን ግንኙነት የማጠናከር ፋይዳው ከፍተኛ ሆኖ እናገኘዋለን።

### 5.1.3 ማደግን ተከትሎ የሚሰጡ ስጦታዎች

- ✓ የልደት ስጦታዎች

ልደትን ማክበር በተመለከተ በውጭው ዓለም የተለመደ የጥናት ትኩረት ቢሆንም በኢትዮጵያውያን ባህል ውስጥ ግን በታሪክ እንደምንሰማው ከነገስታቱ ውጪ ልደት የማክበር ልማዱ አልነበረም። በአሁኑ ወቅት ግን በከተማ እና ከተማ ቀመስ በሆኑ አካባቢዎች እየተለመደ የመጣ ይመስላል። ልደት ማክበር እና የልደት ስጦታ መስጠት በአካባቢው ከዚህ በፊት ያልነበረ ልማድ ቢሆንም ጥናቱ በተደረገበት ወቅት የህጻናት ልደት ሲከበር በመመልከቴ ስለጉዳዩ የቡድን ተኮር ውይይት አድርጊያለሁ። በዝግጅቱም ማህበረሰቡ ምግቦችን እና መጠጦችን እንዲሁም የተለያዩ ዝግጅቶችን በማዘጋጀት ጎረቤት በመጥራት ያከብራል። ልደት በሚከበርበት ወቅት ባለልደቱን እንኳን አደረሰህ ለማለት፣ በቀጣይ ዓመትም በሰላም እንዲደርስ መልካም ምኞትን ለመግለጽ ስጦታ ይሰጣል። ይህን አስመልክቶ በቡድን ተኮር ውይይት (01/09/2013ዓ.ም ደ/ኤልያስ) የተገኘው መረጃ

> በእኛ ጊዜ እንኳን ልደት ሊከበርልን ይቅርና የተወለድንበትን ዘመን እንኳን በስትክክል የሚያስበው አልነበረም። የሚያስበውም ቢኖር በዚህ ጊዜ ተወለድህ ለማለት እንጂ ደግሶ የሚያከብር እናት እና አባት አልነበረም። አሁን አሁን ግን ምን መጣ? አንድ ሰው ልጅ ሲወልድ በየዓመቱ እህል ውሃ አዘጋጅቶ ዳቦ ደፍቶ "ልደት" ይልና "ኑ አቢን መርቁልን" "ኑ ሚጣን መርቁልን" እያለ ይጣራል። መቼስ በእኛ ሀገር "ጠሪ አክባሪ ነው።' ይባላል። ለባለ ልደቱ ህጻን ብስኩትና ከረሜላ፣ ገንዘብ ካለም መጫወቻ ነገር ተገዝቶ ወይም አረቄ ተይዞ ይሄዳል። መቼስ ባዶ እጅ አይሄ፤ እንጂ ልደት አይከበርም ነበር።

ከምላሹ እንደምንረዳው ለልጅ ልደት ማክበር ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየተለመደ የመጣ ነገር እንደሆነ፣ በአካባቢው ልማድ ልደት ለህጻናት ብቻ የሚከበር መሆኑን እና በዝግጅቱም ስጦታ የመስጠት ልማድ እንዳለ ለመረዳት ተችሏል። ለስጦታ የሚቀርቡ ነገሮችም ለህጻኑ መጫዎቻ እና የሚበሉ ጣፋጭ ነገሮች ወይም ወደ ልደቱ ቤት ለመግባት የሚሆን አረቄ ሲሆን የስጦታው ምክንያትም ጠሪውን ለማክበር እና ለማስደሰት እንዲሁም ድግስ ቤት ሲሄድ ባዶ እጅ መሄድ ነውር እንደሆነ በማህበረሰቡ ስለሚታመን መሆኑን እንረዳለን።

- ✓ ጋብቻ

ጋብቻ ማለት በማህበረሰቡ ልማድ እድሜአቸው ለጋብቻ ደርሷል ተብለው የሚታሰቡ ተቃራኒ ጾታዎች (ወንድ እና ሴት) ህጋዊ በሆነ መንገድ ማህበራዊ ዝምድና የሚፈጥሩበት ልማድ ነው። ይህን አስመልክቶ ካህሳይ (2008፣75) "ጋብቻ በአንድ ወንድና ሴት መካከል የሚፈጸም፣ ተጋቢዎች በአካልም በመንፈስም አንድነት ፈጥረው የሚኖሩበት፣ የቤተሰብ መሰረት የሚጣልበት፣ ማህበራዊ ስርዓት ነው" በማለት ይገልጻሉ። በተጠኘው ማህበረሰብ ውስጥ ጋብቻ የሚፈጸምበት መንገድ የተለያየ ነው። የመጀመሪያው በሁለቱ ተጋቢዎች ስምምነት የሚመሰረት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በሁለቱ ወላጆች ፈቃድ ዝምድና ለመፍጠር፣ ደም ለማድረቅ ወይም ቂም ለመሻር ወዘተ. ምክንያቶች "ልጅህን ለልጄ" ተባብለው የሚሰጣጡበት የጋብቻ አይነት ይጠቀሳል። ይህን አስመልክቶ አቶ ዋለ (ቃለመጠይቅ 08/08/2013 ዓ.ም፣ደ/ኤልያስ) የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተውኛል።

> ወትሮ ትዳር ሲመሰረት የወንድ እና የሴቷ ወላጆች መዛመድ ሲፈልጉ ጨዋ የሆነችውን ሴት መርጠው በወንድነቱ በስራ ወዳድነቱ ለተመሰከረለት ልጅ ይድሯታል። የሰርጉ ቀን እስቲደርስም ሙሽሮች አያውቁም ነበር። አሁን ደግሞ ዘመን ተቀይሮ ቤተሰብ የሚሰማው ሰርጉ ሲቃረብ ሆኗል እነርሱ የፈለጉት እንጂ አባት ለወዳጁ ልጁን መስጠቱ እየተዘነጋ መጥቷል። እንጂ በጋብቻማ ወዳጅነት ይጠነክራል። የተጣላም ሰው ቢሆን ልጁን በመስጠት የቆዬ ጠቡን የቆዬ ቂምን በልጁ ይሽራል።

ከዚህም የምንረዳው ማህበረሰቡ ልጅህን ለልጄ በማለት በሚገነባው ትዳር ውስጥ ስጦታ ሆኖ የሚቀርበው ልጅ ዝምድናን የመመስረት እና የሻከረ ግንኙነትን የማለስለስ ሀይል እንዳለው ነው።

ጋብቻ ሲመሰረት የተለያዩ ስርዓቶችን ያልፋል። ከእነዚያ ስርአቶች ውስጥ የሰርግ ስነስርዓት አንዱ ነው። በሰርግ ስነስርዓት ውስጥ ያሉ የስጦታ አይነቶችን ቅድመ ሰርግ ስጦታ (ከሰርግ በፊት ያሉ ስጦታዎች)፣ ጊዜ ሰርግ ስጦታ (በሰርጉ ጊዜ የሚቀርቡ ስጦታዎች) እና ድህረ ሰርግ ስጦታ ( ከሰርጉ በኋላ የሚቀርቡ ስጦታዎች) የጥናቱ ዋና ርዕሰ ጉዳዮች በመሆናቸው ከሌሎች ክዋኔዎች ተለይተው በትኩረት ቀርበዋል።

✓ ቅድመ ሰርግ ስጦታዎች

ቅድመ ሰርግ ስጦታዎች ጋብቻ ከመፈጸሙ በፊት ወይም ከሰርጉ ቀን በፊት ያሉትን ስጦታዎች ይመለከታል። ይኸውም የመጀመሪያው ትጭጭት በሚደረግበት ወይም ውል በሚያዝበት ቀን ያለው የስጦታ ስምምነት ነው። ውል የመያዣ ቀንን አስመልክቶ አቶ ጥበቡ (ቃለመጠይቅ 18/08/2013ዓ.ም፣ደ/ኤልያስ) የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተዋል።

> …ውል የሚያዝበት ቀን እንጀራ እና ወጥ ይዘጋጅና ጠላው ይበጠበጥና። የሙሽራው እና የሙሽሪት ወገን ይማከራል። ለሙሽሪት ልብስ ፣ ጫማ፣ ለጆሮዋ ወርቅ፣ ለጣቷ ወርቅ አድርጎ በደንቡ መሰረት ለሰርጉ ቀን እንደሚወስዳት ቃል ይገባል። በተጨማሪም ከሙሽራው ወገን አባት ተነስቶ ከብትም ሆነ መሬት ወይም ሌላ ቋሚ ንብረት እየጠቀሰ ይሄን እሰጣለሁ ይላል። የሙሽሪት አባትም የወንድ አባት በሰጠ ይሄን እሰጣለሁ ብሎ ቃል ይገባል። … ቃሌን ባጥፍ ነብዩ ኤልያስ እንዲህ ያርገኝ እያለ በሚያምነው ታቦት ይምላል። ይህን እሰጣለሁ ይህን አደርጋለሁ ተባብለው ስምምነት ላይ ሲደርሱ የሰርጉ ቀን ይቆረጥና ተመራርቀው ያድርሰነ ተባብለው ይለያያሉ።

ከዚህ ምላሽ የምንረዳው በማህበረሰቡ ህግ ሰርግ ከመደረጉ በፊት ውል የመያዣ ቀን እንዳለ እና በዚያም ቀን የወደፊት ተጋቢዎች ኑሮ ለመመስረት የሚያስፈልጋቸውን ለመስጠት የሙሽራው እና የሙሽሪት ቤተሰቦች የስጦታ ዝርዝር የሚያወጣበት እንዲሁም ቃል የሚገቡበት ቀን እንደሆነ ነው። በዚህም ስጦታ ጋብቻ ለመመስረት አንዱ መስፈርት እንደሆነ እንረዳለን። በተጨማሪም ውል በሚያዝበት ቀን በስጦታው ከተስማሙ ብቻ ጋብቻው እንደሚፈጸም ከቀጣዩ የአቶ ደፋሩ (ቃለመጠይቅ 18/08/2013 ዓ.ም፣ደ/ኤልያስ) ምላሽ መረዳት እንችላለን።

> የውሉ ቀን ሙሽሮቹ ለወደፊት ሰርተን እናገኛለን እንጂ ሀብት ንብረት አንፈልግም ካሉ መቼም የወደፊት ህይወት እንዲስተካከል አባትም እናትም ያቅሙን ያደረጋል። እንጂ የሙሽራው ወገን እና የሙሽሪት ወገን ድርድር ውስጥ አይገባም። ግን የደንቡ ይደረጋል። ለምሳሌ፦ የምታገባው ልጃገረድ ከሆነች ለልጃገረድ የሚገባውን ሙሉ ልብስ፣ የጣት ቀለበት ወርቅ፣ የጆሮ ጉትቻውን ወርቅ አስሮ ይወስዳታል። ያንን ካላደረገ ግን የልጃገረድ ወጉ ስላልሆነ ሰርጉ ሊፈርስ ይችላል። እሷም ቤተሰቦቿም እሺ አይሉም። ልጃገረድ አግብቶ-እንደፈታ ሳይሸለም አይወጣም። አግብታ የፈታች ከሆነች ደሞ ሙሽሪት የፈለገችውን ያህል ገንዘብ ጥሎሽ ጥሎ ይወስዳታል እንጂ ዝም ተብሎ መግባት ነውር ነው። ሽማግሌ ሲመጣ እንኳን የሙሽሪት ቤተሰብ "እጅ ከምን"

ይሏቸዋል፡፡ እነርሱም "ከሸማ ጥቅል ከወርቅ እንክብል" ብለው ይመልሱላቸዋል፡፡ እንዲህ የሚሉት ለምንድን ነው ብትይኝ በሰርግ ጊዜ ልብስ ማልበስ እና ወርቅ ማሰር ደንብ ስለሆነ ነው፡፡ … ሁለቱ ተጋቢዎች ከለመዱ በኋላ ቤተሰብ በውሉ ቀን ቃል የገባውን ወይም ከዚያ ጨምሮ ይሰጣል፡፡

ከዚህ የምንረዳው ጋብቻውን በማህበረሰቡ ህግ መሰረት ለመፈጸም ስጦታ ያለው ሚና ከፍተኛ እንደሆነ ሲሆን በቅድመ ጋብቻው ስርዓት የሙሽራው እና የሙሽሪት ቤተሰቦች የስጦታ ድርድር አድርገው የጋብቻ ስምምነት ላይ እንደሚደርስ ነው፡፡ የስጦታው ደንብም ሙሽሪት ልጃገረድ ከሆነች በብዙ የወርቅ ጌጣጌጥ እና የሸማ አልባሳት ስጦታዎች እንደምትታጭ እንዲሁም አግብታ የፈታች ከሆነ ደግሞ የፈለገችው ገንዘብ ተጥሎ እንደምታገባ ቃለመጠይቁ ያስገነዝባል፡፡ በማህበረሰቡ ልማድ መሰረት ሙሽራው ለሚያገባት ሴት ወርቅ ያስርላታል፡፡ ወርቅ ያሰረችው ሴትም በክብር እንደወጣች ያላሰረችው ደግሞ ክብሯ ዝቅ እንዳለባት ተደርጎ ይቆጠራል፡፡ በዚህም ልዩነት ውስጥ ስጦታው የክብር መግለጫ እና ማህበራዊ ደረጃን ማሳያ ሆኖ ሲያገለግል እንመለከታለን፡፡ በተጨማሪም የልጆችን ህጋዊ የሆነ ቤተሰብ መሰረት ለማስያዝ እና የወደፊትን ኑሮ ለማስተካከል ወላጅ ያለውን ኃላፊነት እንዴት እንደሚወጣ እንዲሁም ስጦታ በመስጠት በኢኮኖሚያቸው የተደራጁ አዲስ ተጋቢዎችን ለመመስረት ያለውን ማህበራዊ ልማድ እንረዳበታለን፡፡ ሙሽራው ወይም የሙሽራው ቤተሰብ ሙሽሪትን ለመውሰድ ፈቃደኛ ከሆነ የሙሽሪት ቤተሰብ የጠየቀውን ነገር ተስማምቶ ይሰጣል፡፡  ወይም በስጦታው ምክንያት አይተዋትም፡፡ በዚህም ውስጥ ስጦታ ምርጫን መጠቆሚያ እና ውዴታን (ፈቃድን) ማሳያ ሆኖ ሲያገለግል እናገኘዋለን፡፡ የስጦታውን ዓይነት ስንመለከት ደግሞ ሽማግሌዎች “ከሸማ ጥቅል ከወርቅ እንክብል” አለን የሚሉት የሙሽራውን ሀብት ልክ በግነት መልክ ለመግለጽ ነው እንጂ ያን ሊሰጥ እንዳልሆነ (ካህሳይ፣ 2007፣79) ይገልጻሉ፡፡ ነገር ግን ሸማ ማልበስ በማህበረሰቡ የወርቅ ስጦታ መስጠትን በተመለከተ ቄስ ላመስግን (ቃለመጠይቅ 14/08/2013ዓ.ም፣ ደ/ኤልያስ) የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተውኛል፡፡

ይህ ሴትን ልጅ በከበረ ማዕድን ማጨት ከጥንት ጀምሮ የመጣ ነገር ነው፡፡ የከበረ ድንጋይ ስልሽ ወርቅ፣ እንቁ፣ አልማዝ ወይም ሌላ ሊሆን ይችላል፡፡ አባቶቻችን እንደሚሉት እግዚአብሔር አዳምን ሔዋንን ማጫ እንዲሆነው እንቁ ሰጠው ያንንም ወስዶ ለሔዋን ሰጣት… እና ከጥንት ጀምሮ ሲወራረስ የመጣ ባህል ስለሆነ ሴት ልጅ በወርቅ በከበረ ማዕድን ትታጫለች፡፡ ሰብአሰገል ክርስቶስ በተወለደ ጊዜ የወርቅ፣ የእጣን

እና የከርቤ ስጦታ ሰጥተውታል። በዚያ ስጦታ ውስጥም ምሳሌ እና ትንቢት ይገኛል። አባቶቻችን እንዳስተማሩን ወርቅ ለመንግሥቱ፣ ዕጣን ለመለኮቱ፣ ከርቤ ለሞቱ ምሳሌ ናቸው። ወርቅ መገበራቸው ወርቅ ጽሩይ ነው፤ ጽሩየ ባሕርይ ነህ ሲሉ፤ እንዲሁም በአንተ ያመኑ ምዕመናንም ጽሩያነ ምግባር ወሃይማኖት ናቸው ሲሉ። አንድም ወርቅ የሃይማኖት ምሳሌ ነው። የሃይማኖት ጽሩይነቱና ግብዝነቱ የሚታወቅ መከራ ሲቀበሉበት ነውና። ወርቅ ባህርይው በራሱ አስተማሪ ነው። ወደ ሰርጉ ስጦታም ስናመጣው ወርቅ በእሳት ተፈትኖ እንደሚወጣው ሴቲቱም በሙያዋ በጠባዩአ ብዙ ተፈትና ነው ለክብር የምትበቃው። ኋላም በትዳሯ እንደ ወርቅ እንደምትፈተን ትንቢት ይይዛል። ወርቅ በጆሮ ፣በጣት መታሰሩ ሴቲቱ ለወንዱ ጌጡ ክብሩ በመሆኗ ነው። እሷ ካከበረችው ሁሉ ያከብረዋል ከናቀችው ደግሞ ይኼ ሚስቱን ያልቀጣ እየተባለ ይናቃል። በተጨማሪም ፍጹም ፍቅር በወርቅ ይመሰላል በማለት ይመልሳሉ።

በማህበረሰቡ ባህል ውስጥ ሴትን ልጅ በወርቅ ስጦታ ማግባት እርሷን እንደ ማክበር ይቆጠራል። የወርቅ ስጦታ የተለያዩ ትዕምርቶችን ተሸክሞ ይገኛል። ከእነዚህም ውስጥ ስልጣንን፣ ክብርን፣ ንግስናን ወክሎ እናገኘዋለን። በዚህም ምላሽ ውስጥ የምንረዳው ለሴት ልጅ ወርቅ መስጠት ክብርን እና በፈተና ውስጥ አልፎ ጥሩ ደረጃ መድረስን  እና የሰጪውን ፍቅር የሚያመላክት ትርጉም እንዳለው ነው። በዚህም ክዋኔ ውስጥ  ወንዱ ለሴቷ የወርቅ ስጦታ በመስጠት በማህበረሰቡ የሚደገፈውን ክብርን በመጠበቅ የሴቷን የወደፊት ኑሮ እና ስነ ልቡና የማስተከል ሚናው ከፍተኛ እንደሆነ እንረዳለን።

- ✓ የሰርግ ቀን ስጦታዎች

ሰርግ ህጋዊ የሆነ ጋብቻ ለመመስረት የሙሽሪት ቤተሰብ እና የሙሽራው ቤተሰብ በየመኖሪያ ቤታቸው ምግብ መጠጥ በማዘጋጀት እና ወዳጅ ዘመዶቻቸውን በመጋበዝ የሚያሳልፉት የደስታ በዓል ነው። በማህበረሰቡ ዘንድ መስጠቱ እና ደግነቱ የሚታወቀው እንደ ክርስትና እና ሰርግ ባሉ ዝግጅቶች ደግሶ ሲያበላ ነው። በተጨማሪም ከዚህ በፊት የበላውን ድግስ በተራው ጠርቶ በማብላት ውለታ የመመለስ ልማድ አለው። ስለዚህ የሰርግ ድግስ በሰርግ ቀን ካሉ ስጦታዎች መካከል አንዱ እና ዋነኛው ነው። በዚህ የስጦታ ሂደት  ሰጪና ተቀባይ የሚሆኑት የሙሽሮች ቤተሰብ እና የአካባቢው ማህበረሰቦች ናቸው። በሰርግ ድግስ የተጠራ ሰውም ወጉ ደርሷት ለዳረች እናት "እንኳን ደስ አላችሁ" በማለት የተለያዩ ስጦታዎችን ይዞ ይመጣል። እነዚህ በአካባቢው የተለመዱ ስጦታዎች እንደ ቀረቤታ እና እንደሰጪው ደግነት መጠን ይለያያል።

በሰርግ ወቅት በማህበረሰቡ የተለመዱ ስጦታዎችን በተመለከተ ወ/ሮ ንጹህ (ቃለ መጠይቅ 06/08/2013 ዓ.ም፣ደ/ኤልያስ) የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

> በሀገራችን አባባል “ሰርግ እና ሞት አንድ ነው” ይባላል ያው ሁለቱም በድጋሚ ስለማይመጡ ነው፡፡ አንድ ጊዜ ያገባ ሰው ቢፈታና ሌላ ቢያገባም እንደመጀመሪያው ብዙ ዝግጅት አይደረግለትም፡፡ በሰርግ ዝግጅት ቤተሰብ ሰንጋ ጥሎ፣ ጠላ ጠምቆ ፣ ደግሶ በዚህ ቀን "መጥታችሁ ልጃችንን እንድትመርቁ" እያለ ወዳጅ ዘመዶቹን ይጠራል፡፡ የተጠራው ሰውም የወዳጁን ደስታ ለመካፈል ይዞ የሚሄደውን ሲያዘጋጅ ይሰነብታል፡፡ ዘመድ ከሆነ ለድግስ የሚያስፈልገውን እና የቻለውን እንጀራ እና ጠላ ጭኖ ከዋዜማው ጀምሮ ይሄዳል፡፡ ይሄ አቀልቋይ ይባላል፡፡ ሌላው የተጠራው ሰውም ባዶ እጁን አይመጣም ለጎጆ መውጫ የሚሆኑ እቃዎችን፣ ለምሳሌ የሙሽሪት ጓደኞች ለማስታወሻ እንዲሆናት ዳንቴል ጠልፈው ወይም ሞሰብ ሰፍተው፣ ሙሽሪት የምትጠጣበት የሙሽራ ዋንጫ አሰርተው ይሰጧታል፡፡ ከሙሽራው ቤተሰብም ለሙሽሪት እናት ኩታ ለአባትዬው ጋቢ ይሰጣል፡፡ ያም የሚደረገው ለክብራቸው ነው፡፡ ... የሰርጉ እድምተኛም ባዶ እጁን አይመጣም፡፡ ጎረቤቱ የሀበሻ አረቂ ከፍ ሲልም የፈረንጅ አረቂ ገዝቶ ይሄዳል፡፡ ዝግጅት ያነሰው ከሆነም ገንዘብ ይሰጣል፡፡

በዚህ ምላሽም ማህበረሰቡ ልጁን ሲድር ደግሶ በማብላትና የደስታው ተካፋይ በማድረግ እንዲሁም የተጠራውም ሰው ደስታውን ለመግለጽ ስጦታ ይዞ በመሄድ እንደሆነ ነው፡፡ በዚህ ገለጻ ውስጥ ደግሶ ማብላት ወይም ስጦታን መስጠት የደስታ መገለጫ እና የደግነት ማሳያ መንገድ እንደሆነ እንረዳለን፡፡ በተጨማሪም ሙሽራው ለሙሽሪት እናት እና አባት ክብር በሚሰጣቸው ልብስ ውስጥ ማህበረሰቡ ስጦታን ለክብር መግለጫ እንደሚጠቀምበት እንረዳለን፡፡

- ✓ አቀልቋይ

የተጠኘው ማህበረሰብ በሰርግ ድግስ ወቅት በሙሽሮች ቤተሰቦች ላይ ያለውን የድግስ ወጪ ሸክም ለመቀነስ "አቀልቋይ" የሚባል ማህበራዊ የስጦታ ደንብ አውጥቶ እርስ በእርስ የመተጋገዝ ልማድ አለው፡፡ አቀልቋይ ማለት ለተጋቢዎች ወይም ለቤተሰቦቻቸው ቅርብ የሆኑ ዘመዶች እና ወዳጆች በቤታቸው ደግሰው( እህል ውሃ አዘጋጅተው) ወደ ድግሱ ቤት በመውሰድ ለሰርግ የተጠሩ ትን ሰዎች የማብላት ልማድ ነው፡፡ ማህበረሰቡ ስለ አቀልቋይ መያዝ ያለውን ልማድ ወይዘሮ ዝይን (ቃለመጠይቅ 16/09/2013ዓ.ም፣ደ/ኤልያስ) እንዲህ ያስረዳሉ፡፡

እናት አባት ወጉ ደርሶት ልጁን ሲድር ከሌላው ቀን በበለጠ ብዙ ይደግሳል። እርሱም ሲደግስ ማን አገዘኝ ይላል። እንግዲህ እንደ ደንቡ በአቀልቋይ ይደጎማል። አቀልቋይ የሚይዘው መቼም እህት ወንድም ወይ የቅርብ ዘመድ ከሆነ የሙሽሮች የክርስትና እናት ወይም አባት፣ የጡት ልጅ ካለ ግዴታው ነው ያግዛል። ምነ ዘመድም ዘመድ ነው። የክርስትና እናት እና አባትም ያው ልጁ እንዳገባለት ስለሚቆጠር ነው።የጡት ልጅም እንደ ልጅ ነው። አንዳንድዜ ግን የባዕድ ዘመድ የሆነ ሰው አለ እርሱም ለወዳጁ ያልሆነ ብሎ እንጀራውን ጋግሮ ጠላውን በጥብጦ ወጡ ደግሞ እሰርጉ ቤት እንዲዘጋጅ ዘይቱን፣ ሽንኩርቱን፣ በርበሬውን ሳይቀር ይዞ እድግሱ ቤት ይመጣል። ያ ያመጣው እህል ውሃም ለእሱ እንደደረሰው እድምተኛ አንተ በዚህ ቁምልኝ አንተ በዚህ አብላልኝ ተብሎ በተነገረው መቀመጫ ልክ እንግዳውን ይሸኝበታል። ደግሞ ያ ለአቀልቆይ የተባለው ድግስ ተበልቶ አይቀርም። አቀልቆይ የተያዘለት ሰው በተራው ደግሞ ሰርግ ወይ ሌላ ድግስ ሲጠራ አቀልቋይ ለያዙለት ሰዎች ሲሆን ከተሰጠው ጨምሮ ውለታ ይመልሳሉ። በማለት ይገልጻሉ።

ማህበረሰቡ አቀልቋይ ብሎ በሚጠራው የስጦታ ደንብ ውስጥ ሰጪው የቅርብ ዘመድ እና ወዳጅ ሲሆን ተቀባዩ ደግሞ ድግስ የሚደግሰው ሰው ነው። ይህም ስጦታ እርስ በእርስ የመደጋገፍን እና ዝምድናን ወይም ቀረቤታን የመግለጽ ሚና ያለው የስጦታ አይነት ነው። ምክንያቱም በድግስ ወቅት ሩቅ የሆነ ሰው እንደማንኛውም እድምተኛ ተጋብዞ የሚሄድ ሲሆን ለደጋሾቹ ቅርብ የሆነ ሰው ግን አቀልቋይ በመያዝ (አብሮ በመደገስ) አጋርነቱን ያሳያል። በተጨማሪም በአቀልቋይ ክዋኔ ደንብ መሰረት አንዱ ለሌላው በመስጠት ቀጣይነት ያለው የስጦታ ምልልስ ያለበት ሲሆን በዚህም ውስጥ ማህበረሰቡ ስጦታ በመስጠት እና በመቀበል ያለውን ማህበራዊ ትስስር የሚያጠናክርበት ማህበራዊ ልማድ እንደሆነ እንረዳለን።

✓ ለሙሽሪት የሚዘጋጁ ስጦታዎች

በሰርጉ ቀን ሙሽሪት ውል ሲያዝ ቃል የተገባላትን ልብስ፣ የወርቅ ጉትቻ፣ ጫማ፣ ጃንጥላ እና ሽቶ ወዘተ. በሙሽራው መልክተኛ በኩል ተቀብላ ተሞሽራ ትጠብቀዋለች። ሙሽራው ሲመጣም ቀለበት ያስራሉ። በዚህም ውስጥ ስጦታ የሁለቱ ተጋቢዎች ፈቃድ እና ውዴታ ማሳያ ሆኖ ሲያገለግል እንመለከታለን። በምልከታ ወቅት የሰርጉ ዝግጅት በሙሽሪት ቤት ከተጠናቀቀ በኋላ ወደ ባሏ ወገኖች ልትሄድ ስትዘጋጅ ለሰርጓ የሰፋችውን ሞሰብ ወርቅ ውስጥ በትልቁ ሞሰብ ሙሉ ድፎ ዳቦ እና በትንሿ ደግሞ እንጀራ በወጥ ተደርጎ ከግል እቃዎች ጋር ሲጫን

በተጨማሪም ከታረደው ከብት ታላቅ ወይም አንድ እግር ተቆርጦ ሲሄድ ለማየት ችያለሁ:: እንዲህ የሚደረግበት ምክንያትም በማህበረሰቡ ሞሰብ ባዶ ስለማይቀመጥ እና በባዶ እጅ መሄድ እንደ ነውር ስለሚታይ እንደሆነ አቶ ጥበቡ (ቃለመጠይቅ 18/08/2013 ዓ.ም፣ ደ/ኤልያስ) እንዲህ ይገልጻሉ:: "... እንኳን አዲስ ጎጆ ወጪ ቀርቶ ለሌላውም ሰው መሶብ ባዶ አይቀመጥም አዲስ ኑሮ በባዶ እጅ ቀርቶ በብዙ ሀብትም ያስፈራል:: ሌላው ሙሽሪትን ይዞ ለሚሄደው እንግዳ እንዲሆን ተላቁ (ታላቅ)ተቆርጦ አብሮ ይላካል:: ምክንያቱም ሙሽሪት ባዶዋን ብትሄድ የሙሽራው ቤተሰብ ያነውሯታል::" ከዚህም የምንረዳው በማህበረሰቡ ዘንድ ለወደፊት መጥፎ ነገር (እጦት) እንዳይከሰት በመስጠት ወይም በባዶ ባለመንቀሳቀስ እንደሚከላከሉ ነው:: በዚህ ክዋኔም  ስጦታውን እንደ መልካም ምኞት መግለጫ ሲመለከቱት እናያለን::እንዲህ ባለ ስርዓት የሰርጉ ቀን ካለፈ በኋላ ሙሽሪት ወደ ሙሽራው ቤተሰቦች ትሄዳለች:: በዚያም ጫጉላ ይሰራላቸዋል የተለያዩ ስጦታዎችም ከሰርጉ በኋላ ይቀጥላሉ::

✓ ድህረ ሰርግ ስጦታዎች

በባህላዊው የሰርግ ሥርዓት ውስጥ ሙሽሮች በጫጉላ የሚቆዩበት ወቅት አንድ ወር እንደሆነ እና ሙሽሪት ደግሞ እስከ አንድ ሳምንት ድረስ ተሸፋፍና እንደምትቀመጥ እርሷንም ለማየት የተለያዩ ስጦታዎችን እንደምትሰጥ ወ/ሮ እማዋይ (ቃለመጠይቅ 14/08/2013 ዓ.ም፣ደ/ኤልያስ) እንደሚከተለው ይገልጻሉ::

> ከሰርጉ በኋላ በወንዱ ቤት ጫጉላ ተሰርቶ ትቀመጣለች:: እስከ ሳምንት ድረስ አጫዋቿ እና ሙሽራው ካልሆነ በቀር ሙሽሪት ተሸፋፍና ስለምትቀመጥ መልኳን፣ ውበቷን ማየት የፈለገ ዝም ብሎ ማየት አይችልም:: ወደ ጫጉላ ተጠግቶ ለአጫዋቿ ሙሽሪትን ማየት እንደሚፈልግ ነግሮ ከ ሳንቲም፣ ከማርዳ ወይም ከዛጎል ያገኘውን መርጦ ስጦታ ይሰጣታል :: ሙሽሪትም ስጦታውን ተቀብላ መልኳን ታሳየዋለች ፣ለሚጠይቃትም መልስ ትሰጠዋለች:: ከሳምንት በኋላ እየለመደች ስትመጣ መሸፋፈኗን ትተውዋለች:: እስከ አንድ ወር ድረስም በጫጉላ ትቆይና ፈቃጅ ሲመጣ ወደ ቤት ትገባለች::

በዚህ ምላሽ ሙሽሪት ወደ አዲስ አካባቢ እና ቤተሰብ ስትቀላቀል የእንግዳነት ስሜት እና ፍርሀት ሊሰማት እንደሚችል በማሰብ እንድትለማመድ ለማድረግ ሳንቲም፣ ማርዳ እና ዛጎል ስጦታ በመስጠት ሊአግባቡአት እንደሚሞክሩ ተመልክተናል:: በዚህም ውስጥ ማህበረሰቡ ስጦታን ወደ አዲስ አካባቢ ለሚሄድ ሰው እንደ ማላመጃ ሲጠቀምበት እንመለከታለን:: የስጦታ ዓይነቶችን ስንመለከት ማርዳ እና ዛጎል በማህበረሰቡ ዘንድ የተለመዱ ማጌጫዎች ሲሆኑ ማርዳ

በክር ተሰክቶ ለአንገት እና ለእግር ጌጥ እንዲሁም ህጻናት ቁንጮአቸውን ሲሰሩ ማሳመሪያ ሆኖ ያገለግላል፡፡ እንዲሁም ዛጎል ለልጅ ማዘያ (ከቆዳ ለሚሰራ አንቀልባ) ማጌጫ ሆኖ ያገለግላል፡፡ እነዚህ ስጦታዎች ለምን እንደተመረጡ እማሆይ ህብስቴ (ቃለመጠይቅ 22/05/2014 ዓ.ም፣ ደ/ኤልያስ)

> ማርዳ እና ዛጎል የሚሰጣትማ ለጊዜው እንድትጫዎትበት፣ በአንገቷ እንድታስረው ኋላም ልጅ ስትወልድ ዛጎሉን በአንቀልባ ማርዳውን በልጇ አንገት እንድታደርገ ነው፡፡ ምክንያቱም ዛጎሉ በእኛ አካባቢ ጫጫቴ ይባላል በአንቀልባው ላይ ሆኖ ሲንጫጫ ልጁን ያጫውተዋል፡፡ ሌላው ቡዳ ከሁሉ ለይቶ ሙሽራ እና ህጻንን ስለሚያጠቃቸው ለመከላከል ማርዳው በአንገት ይታሰራል፡፡ ማርዳ ከሰው ዓይን ይጠብቃል ይባላል፡፡ በማለት ገልጸዋል፡፡

ከዚህም የምንረዳው ማህበረሰቡ በስጦታው አማካኝነት መልክት የማስተላለፍ ልማድ እንዳለው ጭምር ሲሆን ማርዳ በመስጠት ቡዳ ሙሽራ ይወዳልና ሙሽሪት ከቡዳ ተጠንቀቂ ብለው ሲያሳስቧት ጫጫቴ በመስጠት ውለጅ ክበጅ ብለው መልካም ምኞታቸውን ሲገልጹላት እንመለከታለን፡፡

- ✓ የፈቀዳ ስጦታዎች

ፈቀዳ ማለት በአካባቢው ዘዬ መሰረት ማየት (መመልከት) እንደማለት ነው:: ሙሽሪት መልመዷን እና አጠቃላይ ያለችበትን ሁኔታ ለማየት የሚመጡበት ስርዓት ነው:: ሙሽሮች ጫጉላ በገቡ በአንድ ወራቸው ፈቃጅ ወደ ወንዱ ቤተሰብ ይመጣል:: ለፈቀዳው ሲመጡም የተለያዩ ስጦታዎችን ይዘው ይመጣሉ:: ይህን አስመልክቶ (በቡድን ተኮር ውይይት 01/09/2013 ዓ.ም) በተገኘው ምላሽ

> … እንደ ድሮው ባይሆንም( ስርዓቱ) ሙሽሮች ጫጉላ ተሰርቶላቸው አንድ ወር ከቆዩ በኋላ እንደ ደንቡ የእሷ (የሙሽሪት) እህት፣ እህት ከሌላት የወንድሟ ሚስት እና ወንድሟ እንዲያም ካልሆነ ከእናት እና ከአባቷ ሌላ የሆነ ሰው ሙሽሪት መልመዷን ሊያዩ (ሊፈቅዱ) በግ ወይም ፍየል፣ አገዳ፣ የአማቷ እና የሙሽሪት  መቀነት ይዘው ይሄዳሉ:: ለምንድነው ያን የሚያረጉ ብትይኝ ወደ አማት ቤት ባዶ እጅ መሄዱ ነውር ስለሆነ ኋላም… በድሮው ጊዜ ቆንጆይቱ (ገና ያላገባችው) ምሪ የሚባል ልጃገረዶች ወገባቸውን የሚታጠቁበት ከቆዳ እና ከጫጫቴ (ዛጎል ማለት ነው)  የሚሰራ ነገር አለ

> እርሱን ፈትታ መቀነት የምታስርበት ቀን ስለሆነ መቀነት እህቷ ወይም የወንድሟ ሚስት ይዘውላት ይሄዳሉ፡፡ የዚያን ቀን ወደ አማቷ ቤት ትገባለች … ፈቃጆቹ ሲመጡም መልመዷን ለማሳየት ቶሎ ብላ የቤቱን ምሰሶ ትይዛለች፡፡ የዚያን ጊዜ የመጣው ፍየል ይታረዳል ደስታ ይሆናል፡፡ ለአማትየውም የክብራቸው ለሴትነታቸው መገለጫ መቀነት ይሰጣቸዋል፡፡ … ቤተሰቦቿ ለፈቀዳው ሲመጡ እንዳታሰቀልል (እንዳትናፍቅ) ያመጣጡትን አገዳ ይሰጧታል፡፡

ከዚህ ምላሽ እንደምንረዳው ሙሽሪት ካገባች በኋላ ከወላጆቿ ተነጥላ ወደ አዲስ ቤተሰብ እና ወደ አዲስ አካባቢ ስለምትሄድ እህት ወንድሞቿ ሊያዩአት እንደሚሄዱ ፤ በሚሄዱበትም ወቅት በግ ወይም ፍየል፣ ሸንኮራ አገዳ ፣ መቀነት ይዘው እንደሚሄዱ ነው፡፡ በዚህም ውስጥ ስጦታ ወደ አዲስ አካባቢ እና ማንነት ለሚቀላቀሉ የእንግድነት ስሜት እንዳይሰማቸው ለማድረግ እና ከበሬታን ለማሳየት ሲጠቀሙበት እናያለን፡፡

- ✓ የገላጭ ስጦታዎች

ፈቀዳ በተደረገ በሳምንቱ ወይም በሁለት ሳምንቱ ገለጣ የሚባል ስርዓት አለ፡፡ ይኸውም ስርአት የሙሽሪት እናት እና አባት ለሙሽራው ቤተሰብ ስጦታ የሚልኩበት እንዲሁም ጫጉላው የሚፈርስበት ቀን ነው፡፡ ይህንን አስመልክቶ እማሆይ ህብስቴ (ቃለመጠይቅ 21/08/2013 ዓ.ም፣ደ/ኤልያስ)፡፡ እንደሚከተለው ያስረዳሉ፡፡

> … ገላጭ የተባለ ሙሽራይቱ ከጫጉላ የምትወጣበት መንደርተኛው ሁሉ እንደ ጫጉላው በማርዳ እና ጫጫቴ (ዛጎል) ሳይሆን እሷን በግላጭ የሚያይበት ቀን ስለሆነ ነው፡፡ የተሰራው ጫጉላም የዚያን ቀን ይፈርሳል፡፡ … የግላጭ ቀን እንደገና እንጀራው ተጋግሮ ጠላው ተበጥብጦ ጎረቤት ይጠራል፡፡ ገላጭ ሲመጣም ባዶ እጁን አይመጣም፡፡ የሴቲቱ እናት ጤፉን አስፈጭታ የጤፍ ዱቄት በማዳበሪያ ተደርጎ በአህያ ተጭኖ ይላካል፡፡ እንዲያውም ሀብት ካላቸው ያልተፈጨ እህልም አብሮ ተጭኖ ይላካል፡፡ እንዲህ የሚሆን ለምን ብትይኝ ሙሽራው እና ሙሽራይቱ በጫጉላ ይላመዳሉ ይዋደዳሉ፡፡ የሙሽሮች እናትና አባት ደግሞ በመስጠት፣ ይችን ቅመሱ፣ ይችን ልበሱ ሲባባሉ በሩቅ መዋደድ መከባበር ይመጣል እልሻለሁ፡፡

ከዚህ ምላሽም የግላጭ ስጦታ ሰጪዎች የሙሽሪት ወላጆች ሲሆኑ ተቀባዮቹ ደግሞ አማቾች ናቸው፡፡ ማህበረሰቡ ግላጭ በሚለው ስርዓት ውስጥ የሙሽሪት ቤተሰቦች ለሙሽራው ቤተሰብ

እህል ጭነው እንደሚልኩ እና በዚህ የመስጠት ሂደት ውስጥ በጋብቻ የተዛመዷቸውን ሰዎች ማንነት ለማወቅ እንደሚጠቀሙበት እንረዳለን። በስጦታ ውስጥ ከሚታወቁ ነገሮች አንዱ ግላዊ ማንነት ሲሆን እንደ ስጦታው አይነት እና መጠን ሰጪው ንፉግ ነው ወይስ ለጋስ? የሚለው ይለይበታል። ብዙ ከሰጠ ለጋስ ነው ካልሰጠ ደግሞ ንፉግ ነው ተብሎ የመፈረጅ ልማድ አለ። ሌላው በስጦታ ማህበራዊ ደረጃው ይታይበታል ሰጪው ሀብታም ነው? መካከለኛ ነው? ወይስ ያጣ? በዚህም ውስጥ በጋብቻ የተዛመዳቸው ቤተሰቦች ያላቸውን ሁለንተናዊ ማንነት ለማወቅ እና በስጦታ ልውውጥ ውስጥ ማህበረሰቡ የተጋቢ ቤተሰቦች ዝምድናቸውን ለማጠናከር እና ግንኙነታቸውን ለማለሳለስ የፈጠራቸው ጥበቦች እንደሆኑ እንገነዘባለን። በተጨማሪም የእርስ በእርስ ግንኙነቶችን ከማስቀጠል አንጻር የስጦታ ሚና ከፍተኛ እንደሆነ እንረዳለን።

✓ የመልስ ስጦታዎች

ከገላጭ በኋላ የሚመጣው ስርዓት መልስ ይባላል። መልስ የሚጠሩት የሙሽሪት ቤተሰቦች ሲሆኑ ከጊዜ ወደ ጊዜ ፈቀዳ ላይ የነበረው ስርአት እየቀረ እንደመጣ እና በሰርጉ እለት ሙሽሪት ወደ ባሏ ቤተሰቦች ከገባች በኋላ መልስ መጥራት እየተለመደ የመጣ ነገር መሆኑን ተናግረው የመልስ ጊዜ ስጦታዎችን እማሆይ ህብስቴ (ቃለመጠይቅ 21/08/2013 ዓ.ም፣ ደ/ኤልያስ)። እንደሚከተለው ገልጸዋል።

> ...እንደ ወትሮው (እንደ ድሮው) ቢሆንማ ከሰርግ በኋላ በወሩ ፈቀዳ ተብሎ ይሄዳል። ከፈቀዳው በኋላ በወሩ ደሞ የሙሽሪት ቤተሰቦች መልስ ይጠራሉ። አሁን አሁን ግን ፈቀዳው እየቀነሰ መጥቷል። የገላጭ ዱቄት መላክ እና መልስ መጥራት፣ የመልስ ይዞ መሄድ ግን አልቀረም። ... ለመልሱ ሙሽራው ሙሽሪትን ይዞ ሲመጣ ባል አንድ ሙክት በግ ፣ ለሙሽሪት እናት ኩታ (ነጠላ) እና መቀነት፣ ለአባትዬው ጋቢ ይዞ ይሄዳል። ይሄ በደንቡ የማይቀር ወጋችን ነው።

ከዚህም የምንረዳው ሙሽራው  በመልስ ዝግጅት ውስጥ የበግ ስጦታ ለአማቶቹ ይዞ የመሄድ ልማድ እንዳለ ነው። በዚህ የስጦታ ክዋኔ ውስጥ ሰጪው ሙሽራው ሲሆን ተቀባዮቹ ደግሞ የሙሽሪት እናት እና አባት ወይም ቤተሰቦች ናቸው። በበግ ስጦታው ውስጥ በሰጪ እና በተቀባይ ዘንድ ትዕምርታዊ ተግባቦት አለ። ይህን አስመልክቶ እማሆይ ህብስቴ "... እንዲያው ሙሽራው ያጣ የነጣ ቢሆንም ...ሌላ ሌላው ቀርቶ የመልሱ ከየትም  ብሎ በግ ይዞ መሄድ አለበት። ያለዚያ ግን አማቶቹ ቢንቀን ነው ብለው ያስቡበታል።" በማለት ስጦታውን ይዞ መሄድ የአክብሮት በተቃራኒው ስጦታውን ይዞ አለመሄድ ደግሞ የንቀት ወይም አማቶቹን ያለማክበር

ምልክት እንደሆነ ያስረዳሉ። ስለዚህ በመልስ ጥሪ የበግ ስጦታ ማቅረብ በማህበረሰቡ ደንብ ያለ እና ግንኙነትን የማለሳለስ ሚና እንዳለው እንረዳለን።

✓ የጎጆ መውጫ ስጦታዎች

የሰርግ ጊዜያቶች ካለቁ በኋላ ሙሽሮቹ በማህበራዊ፣ በባህላዊ እና በኢኮኖሚያዊ ህይወታቸው የጎለበቱ እንዲሆኑ የተለያዩ ስጦታዎችን ወይም ጎጆ መውጫዎችን ከሁለቱም ወገን ቤተሰቦች ማቋቋሚያ፣ ራሳቸውን እንዲችሉ እና በእግራቸው እንዲቆሙ ማድረጊያ ይቀበላሉ። አዲስ ህይወት ለመጀመር የሚያስፈልጋቸው መሰረታዊ ፍላጎቶች በትብብር ይሟሉላቸዋል። ይህንን አስመልክቶ አቶ ዋለ (ቃለመጠይቅ 08/08/2013 ዓ.ም፣ ደ/ኤልያስ) በሰጡት ምላሽ "ልጆች በእናት እና በአባት ቤት የነበራቸውን ህይወት እነርሱ እናት እና አባት ስለሚሆኑ ሲያገቡ አይቀጥሉትም። ስለዚህ እናት እና አባቶቻቸው በሚሰጧቸው መሬት ላይ ጎጆ ይቀልሳሉ። ይህን የሚያደርጉት ግን ሙሽሮቹ ከተለማመዱ በኋላ ነው" በማለት ይገልጻሉ። የጎጆ መውጫ ስጦታዎችን አስመልክቶ አይነታቸውን ከዚህ ቀጥሎ በዝርዝር እንመለከታለን።

- መሬት እና ከብት

በተጠኘው ማህበረሰብ ውስጥ ለአዲስ ጎጆ ወጪዎች የመሬት እና የከብት ስጦታ የተለመደ ነው። ይህን አስመልክቶ አቶ አያሌው (ቃለመጠይቅ 16/08/2013ዓ.ም፣ደ/ኤልያስ) የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተውኛል።

> አዲስ ጎጆ ወጪማ ለመቋቋም ብዙ ነገር ያስፈልገዋል። እናት እና አባት ልጅ አሳድገው ለወግ ለማዕረግ ካበቁ ኋላ መቋቋሚያ የሚሆን ነገር መስጠትም አለባቸው። እንግዲህ በኛ ሀገር "ተከብት እንስት ተሀብት ርስት" እየተባለ ይተረታል። ዋናው ስጦታ መሬት እና ከብት ነው። ከከብት ደግሞ ላም (እንስት) ከሆነች ወልዳ አራሽ በሬዎችን ስለምታደርስ ተከብት እንስት ይባላል። እና መሬት እና ከብት ለገበሬ ወሳኝ ስጦታዎች ናቸው። ምክንያቱም ያለ መሬትና ያለ ከብት አርሶ መብላት አይቻልም። ዞሮ ዞሮ መሬት ለልጅ ነው። እኛም መሬታችንን ከእናት አባታችን የተሰጠን ውርስ ስለሆነ ማለት ነው ። እናት አባት ደግሞ ወጥቶ ወርዶ ልጁን ማቋቋም አለበት። እንዲያውም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየተለወጠ መጣ እንጂ የወንድ እናት እና አባት ባሉበት መንደር ሙሽራው ሚስቱን ይዞ ይመጣና ... የመሀሉ የእናት የአባት ቤት ዳር ለዳር ደግሞ መሬት ተቆርሶ ጎጆ ተቀልሶ ለልጅ ይሰጣል። አጠገብ ለአጠገብ እናት አባት እየተጦረ

ይኖራል፡፡ እያለው እንዲህ የማያደርግ እናት እና አባት ለሌላው ሰው ብዙ ቢያደርግ እንኳ የተጠላ ነው፡፡

ከቃለ መጠይቁ የምንረዳው ነገር ማህበረሰቡ የመሬት እና የከብት ስጦታዎችን ለልጆቹ በመስጠት ያለውን ማህበራዊ ኃላፊነት እንደሚወጣ ሲሆን ስጦታ ተቀባዩ ልጆች ሲወልድም ለልጆቹ እንዲሁ ያደርጋል፡፡ በዚህ የስጦታ ደንብ ውስጥ ማህበረሰቡ በስጦታው አማካኝነት ያለውን የስራ፣ የአስተሳሰብ እንዲሁም የአኗኗር ዘይቤ እንዴት እንደጠበቀው እና እንዳስቀጠለው ማየት እንችላለን፡፡ ከስጦታ ባህርያቶች ውስጥ የሰጪውን ማንነት የማንጸባረቅ እና በተቀባዩ ማንነት ላይ ተጽዕኖ የመፍጠር አቅም መኖሩ ይጠቀሳል (Belk, 1976)፡፡

በዚህ የስጦታ ሽክርክሪት ውስጥ ደግሞ የተጠኘው ማህበረሰብ መተዳደሪያ የሆነው ግብርና አሁን ያለበት ሁኔታ ለመድረሱ የስጦታ ሚና ከፍተኛ እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡ ይህም ማለት በመሬት እና ከብት ስጦታ ውስጥ ሰጪው (እናት እና አባት) መሬት እና ከብት ለልጆቹ ሲሰጥ አብሮ የሚያስተላልፈው ነገር ግብርናን ነው ማለት ነው፡፡

- ጉልማ

ጉልማ ማለት አንድ ሰው የእህል መሬት ለጊዜው (መሬት እስኪያገኝ) ድረስ እንዲጠቀም የመፍቀድ ልማድ ነው፡፡ በአካባቢው ማህበረሰብ ውስጥ ወላጅ ለአዲስ ተጋቢ ሙሽሮች ጉልማ ይሰጣል ወይም ይጎልማል፡፡ አዲስ ተጋቢዎች የራሳቸው የእርሻ መሬት ሳይኖራቸው ሲቀር እናት እና አባት መሬት እና በሬ ሰጥተው በጉልበታቸው እንዲጠቀሙበት እና እህል እንዲያገኙ የሚረዱበት ልማድ ነው፡፡ በዚህ ልማድ ውስጥ ለመሬት የሚከፈል ዋጋ አይኖርም፡፡ ይህን አስመልክቶ አቶ ምንውየለት (ቃለመጠይቅ 03/08/2013ዓ.ም፣ደ/ኤልያስ)

> እናት እና አባት አዲስ ተጋቢ ሙሽሮችን የመሬት ስጦታ ሊሰጧቸው አቅም ከሌላቸው ወይ ተጋቢዎቹ እስቲለምዱ ድረስ መሬት መስጠቱ ሲከብዳቸው የሌላ ሰው እጅ እንዳያዩ ለጊዜውም ቢሆን እሸቱን እንዲቀምሱበት ጉልማ ይጎልሙላቸዋል፡፡ ጉልማ ማለት በራስ መሬት ልጅ በጉልበቱ አርሶ ምርቱን እንዲወስድ ማድረጊያ ደንብ ነው፡፡ በማለት ይገልጻሉ፡፡

ከዚህም የምንረዳው ጉልማ አዲስ ተጋቢ ሙሽሮችን ለመደገፍ የሚሰጥ የመሬት ስጦታ ሲሆን በማህበረሰቡ ህግ ውስጥ ጉልማ ለሰጪው ተመላሽ ሊሆን የሚችል ደንብ ያለው የስጦታ አይነት እንደሆነ ነው፡፡ በዚህም ውስጥ ማህበረሰቦቹ በኢኮኖሚው የጠነከረ ቤተሰብ ለማቋቋም

ስጦታን እንዳንድ ብልሃት ሲጠቀሙበት እንመለከታለን፡፡ ጉልማን በተመለከተ አበራ (2006፣ 77) የሚሰጠው ለልጅ፣ ለተወላጅ ወይም ላገለገለ ለማንኛውም ሰው እንደሆነ ገልጸው "ባለመሬት አንድ ወይም ሁለት እና ሶስት ማሳ ወይም ከዚያ ያነሰ መሬት ለእሸት፣ ለምርት ብሎ ለሌላ ሰው ይሰጠዋል ባለ እርስቱ ጉልማ የሰጠውን ሰው በፈለገ ጊዜ ሊነቅለው ይችላል፡፡ እስከዚያው ድረስ ባለ ጉልማው ለባለመሬቱ የሚያካፍለው አበል ሳይኖር መሬቱን እያረሰ ይጠቀምበታል" በማለት ይገልጻሉ፡፡

- የእናት እቃ እና የአባት እቃ ስጦታዎች

የእናት እቃ ተብለው ለአዲስ ጎጆ ወጪ የሚሰጡ ስጦታዎች ከእናት ወደ ሴት ልጅ የሚተላለፉ ናቸው፡፡ እነዚህም በአይነት ሲገለጹ የቤት መገልገያ ቁሳቁሶች እንደ ፣ጋን ፣እንስራ ፣ስፌት፣ምጣድ የመሳሰሉትን ያጠቃልላል በተጨማሪም ጌጣ ጌጦች እንደ ክታብ፣ ድሪ፣ ጠገራብር፣ አልቦ፣ ሙዳይ፣ አምባር ወዘተ. ይጠቀሳሉ፡፡ የአባት እቃ የሚባሉት ደግሞ ወንድ ልጅ ሲያገባ የሚሰጡ ናቸው፡፡ ወንድ ልጅ ከሌለ ወይም ጸብ እና መሰል ችግሮች ካልተፈጠሩ በቀር ለሴት አይሰጥም፡፡ ለሴት ከተሰጠ ደግሞ ለወንድ ልጇ ታስተላልፈዋለች፡፡ ይኸውም መሳሪያ፣ ጦርና ጋሻ፣ጎራዴ፣ ጩቤ፣ የአባት ዋንጫ ወዘተ. ይጠቀሳሉ፡፡ እነዚህ ስጦታዎች ከእናት ወደ ሴት ልጅ እንዲሁም ከአባት ወደ ወንድ ልጅ የሚተላለፉበትን ምክንያት ወይዘሮ ዝይን (ቃለመጠይቅ 16/09/2013 ዓ.ም፣ደ/ኤልያስ) እንዲህ በማለት ያስረዳሉ፡፡

> የእናት እቃ ለሴት ልጅ የሚሰጠውማ ለሴቱ የሚበጀው ስለሆነ ነው፡፡ አሁን ጋኑን ለወንድ ልጅ ቢሰጡት የልጁ ሳይሆን የምራት እቃ ነው እሚሆን፡፡ በዚያ ላይ ክታቡ፣ አልቦው፣ ጠገራ ብሩ የሴት ጌጦች ናቸው፡፡ ጠገራ ብሩም ደግሞ ስትወልድ ይጠብቃታል፡፡ በኛ ዘንድ ሴት ስትወልድ ምናምን ነገር እንዳያገኛት ተብሎ በአራስነቷ ብቻዋን አትቀመጥም፡፡ ብር፣ ብረት ነገር ደሞ ይጠብቃታል፡፡ ስለዚህ እናት ለሴት ልጇ የሚበጃትን ትሰጣታለች፡፡ የአባትም እቃ እንዲሁ ለወንዱ የሚበጀው ስለሆነ መሳሪያውን እንደ ወንዶች የጀግንነት ስራ እንዲሰራበት ድንበር እንዲጠብቅበት ሲያገባ (አካለመጠን ሲደርስ) ስጦታ ይሰጠዋል፡፡

በዚህ የስጦታ ክዋኔ ውስጥ ሰጪው ወላጅ ሲሆን ተቀባይ ደግሞ ወደ ትዳር የገባ ልጅ ነው፡፡ ከቃለ መጠይቁ የምንረዳው ደግሞ ማህበረሰቡ ስጦታን ለሴት ለወንድ ብሎ የመክፈል ልማድ እንዳለው ሲሆን፤ ለዚህም ምክንያቱ ጾታን መሰረት አድርጎ የሰራቸው የስራ ክፍፍሎች፣

የአጊያጊያጥ ደንቦች እና እንደ መውለድ ያሉ ተፈጥሮአዊ ሁኔታዎች እንደሆኑ ነው፡፡ በተጨማሪም ማህበረሰቡ ስጦታን ከጠቃሚነቱ አንጻር የመስጠት ልማድ ወይም አስተሳሰብ እንዳለው እንረዳለን፡፡

- ✓ ሞት

ሞት በህይወት መንገዶች ውስጥ አይቀሬ ከሚባሉ እና ሁሉም ሰው ከሚያልፍባቸው መንገዶች እንደ መወለድ ያለ አይቀሬ እውነት ነው፡፡ የሰው ዘር በሙሉ በሕፃንነትም ይሁን በጎልማሳነት እንዲሁም በእርጅና ይሞታል፡፡ ለሞት ያለው እሳቤ ግን ከማህበረሰብ ማህበረሰብ ይለያያል፡፡ የተጠኝው ማህበረሰብ ሞትን የሚያይበት የተለያየ ዓይነት የሃይማኖት እና የባህል መነጽር አለው፡፡

- ✓ ማስተዛዘኛ (የእዝን እንጀራ)

በተጠኝው ማህበረሰብ ውስጥ በሞት ምክንያት የሚመጣውን የመከፋት ስሜት በመደጋገፍ እና እርስ በእርስ በማስተዛዘን ያሳልፈዋል፡፡ በሀዘን ጊዜ ቤተሰቡ የሞተበትን ሰው ለማጽናናት የአካባቢው ሰው ስጦታ በመውሰድ የሟችን ቤተሰብ ያስተዛዝናል፡፡ የእዝን እንጀራ መውሰድ የተጀመረበትን ምክንያት እና ያለውን ልማድ በተመለከተ አበራ (2006፣181) እንዲህ ይገልጻሉ፡፡

> በኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖች ልማድ እና ባህል ሰው ነፍሱ ከስጋው ተለይታ የቀብሩ ስነስርዓት እስኪከናዎን ድረስ የሟቹ ቤተሰቦች እህል ውሃ አይቀምሱም በተለይ በገጠሩ አንድ ሰው ሲሞት … በሩቅና በቅርብ ያለው ዘመድ እስኪሰባሰብ ድረስ ቀብሩ የሚዘገይበት አጋጣሚ ስለሚኖር ኃዘንተኞች ይጎዳሉ፡፡ … የገጠር ቀባሪዎች ራቅ ካለ አካባቢ ስለሚመጡ ሕዝቡም ሆነ ካህናቱ ከቀብር መልስ ኀዘንተኞች ቤት በመሄድ ለመሰናበት አይችሉም፡፡ በዚህ ምክንያት የእዝን እህል ውሃ (ዕንባ አድርቅ) ከሬሳው ጋር አብሮ ወደ ቤተክርስቲያን እንዲሄድ ተደርጎ ከቀብር መልስ ቀባሪው እደጀ ሰላሙ ተሰብስቦ እህል ውሃ እንዲቀምስ ይደረጋል፡፡ ይህ እንዳለ ሆኖ የአካባቢው ሰዎች ጠላ፣ እንጀራ እና ወጥ ወዘተ. በመያዝ ወደ ሀዘንተኞች ቤት ሄደው ለቀስተኞችን ያረጋጋሉ፣ ያስተዛዝናሉ፡፡

በማህበራዊ ህይወት ክንውኖች ውስጥ ስጦታ መስጠት የእርስ በእርስ ግንኙነትን የማጠናከር እና የማለሳለስ ሚና ሲኖረው በተቃራኒው አለመስጠት ደግሞ ግንኙነትን ሲያሻክር ወይም

ሲያቀያይም እንመለከታለን። ይህ ክስተት ከሚሆንባቸው ነገሮች አንዱ የሀዘን ጊዜ ነው። ማህበረሰቡ በሀዘን ጊዜ አይዞአችሁ መባባልን ይደግፋል። ይህም የማስተዛዘኛ ስጦታዎችን በመውሰድ እንጂ በባዶ እጅ አይደረግም። ስጦታውም በመከራ ጊዜ ከጎን በመሆን ፍቅርን በማሳየት፣አለሁ ባይነትን መንገሪያ መንገድነው። ይህን አስመልክቶ ወይዘሮ ጥሩዓለም (ቃለመጠይቅ 25/08/2013ዓ.ም፣ደ/ኤልያስ) በአካባቢያቸው ያለውን የማስተዛዘን ልማድ እንደሚከተለው ይገልጻሉ።

> መቼም ዞሮ ዞሮ ከቤት ኖሮ ኖሮ ከመሬት ነውና ነገሩ ሰው መሞቱ ወይ የቅርብ ዘመዱን ማጣቱ አይቀርም። ይህን አስቦ እድሩን ይገባል። ... በኛ አካባቢ ሰው ሲሞት በተከታታይ እስከ ሰልስት (ሶስተኛ ቀን) ድረስ እመቃብሩ እየተሄደ ከዚያም እስከ አርባው ድረስ እሁድ እሁድ እየተሄደ ይለቀሳል። ከለቅሶ በኋላም 'ዋይ ብሎ ጉርስ አይቀርም' ይባላልና ሬሳው በወጣበት ቤተሰብ ዘንድ ጎረቤቱ ማስተዛዘኛ ይዞ መሄድ ግድ ነው። ምክንያቱም ሀዘን የማይገባበት ቤት የለም። ሰው በሀዘን እና በደስታው የተደረገለትን ነገር ከሌላውቀን ለይቶ ፍክ ይለዋል። (ይታወሰዋል) የሞተው ቢሄድም ለካንስ ሰው አለኝ እያለ ይጽናናበታል። የእዝን እህል ውሃ በግልም በጋራም ይወሰዳል። የሚወሰደው ነገር ... እንጀራ፣ ወጥ፣ጠላ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ቡና፣ ስኳር፣ ሻይቅጠል ተይዞ ይሄዳል። የሚወሰደው እንጀራውም ደንብ አለው ... በግልሽ ከሆነ ከሶስት ያላነሰ መሆን አለበት። እና የሚሄደው እንጀራ ጎደሎ ቁጥር መሆን አለበት ሶስት፣ አምስት፣ ሰባት እንዲያ ... ምክንያቱም ሀዘን ስለሆነ ሙሉ ቁጥር አይሄድም ይባላል።

በቃለመይቅ እና በምልከታ የተገኙ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት በተጠኝው ማህበረሰብ ዘንድ የሞተን ሰው ቤተሰቦች ለማጽናናት የተለያዩ የማስተዛዘኛ ስጦታዎች  እንደሚወሰዱ እና እነዚህ ስጦታዎች ደግሞ የእርስ በእርስ ማህበራዊ ግንኙነቶችን የማጠናከር ሚና እንዳላቸው ነው። የእዝን እንጀራ ቁጥርን በተመለከተ ጎዶሎ ቁጥሮች ተደርገው እንደሚወሰዱ እና ይህም የሚሆንበት ምክንያት ሙሉ ቁጥሮች የደስታ ፣ ጎደሎ ቁጥሮች ደግሞ የሀዘን መገለጫዎች ተደርገው የመታየት ልማድ ስላላቸው መሆኑን እንረዳለን። የሚያመጡትን የእንጀራ ቁጥርም ጎደሎ በማድረግ ሀዘናቸውን እና በሟች ምክንያት የተሰማቸውን የመጉደል ስሜት ይገልጻሉ። በዚህም ስጦታ በውስጥ ያለን ስሜት መግለጫ ትዕምርት ሆኖ እናገኘዋለን።

✓ ተዝካር

ይህ ስርዓት በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት ተከታዮች ዘንድ በህይወት የሌለን ሰው ነፍሱ ከሥጋው የተለየችበትን ቀን ቆጥሮ የመዘከር ልማድ ነው፡፡ ለክርስቲያኖች ሞት ከዚህ ዓለም ወደ ሌላኛው ዓለም መሸጋገሪያ መንገድ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ሞት ለጊዜው የነፍስ ከሥጋ መለየት እንጂ የሰው ለዘላለም መጥፋት አይደለም የሚል እሳቤ አላቸው፡፡ በበሽታውም ሆነ በአደጋ የሚሞቱ ሰዎች ግን ለንስሓ የበቁም ሆነ ያልበቁ ስለሚሆኑ በሕይወት ያሉ ሰዎች ለሞቱት ነፍሳት ሰላም ማግኘት ዝክር ያደርጋሉ፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፈ ሲራክ ላይ ‹‹ልጄ ሆይ፥ ለሞተ ሰው አልቅስለት፥ እዘንለትም፤ ራስህን አሳዝን፤ እንደ ሥርዓቱም መታሰቢያ አድርግለት›› ይላል፡፡ (ሲራ 38፥16-23) በተጨማሪም ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች የተላከውን የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ሲያስረዳ "አንድ ሰው ኃጢአተኛ እንደሆነ ቢሞት የምንችለውን ያህል ልንረዳው ይገባል፡፡ የምንረዳውም በለቅሶና በሐዘን ሳይሆን በጸሎት፣ በምጽዋትና በቁርባን ነው"፡፡ ይህንም ትእዛዝ መሰረት በማድረግ ክርስቲያኖች የእረፍት መታሰቢያ በዓልን ሳልስት፣ ሰባት፣ አስራ ሁለት፣ ሰላሳ፣ አርባ፣ ሰማኒያ፣ መንፈቅ፣ ሙት-ዓመት እና ሰባት ዓመት በማለት በጸሎት እና የተለያዩ ስጦታዎችን በማቅረብ ያስቧቸዋል፡፡ ይህንን አስመልክቶ ዲያቆን አምኀ (ቃለ መጠይቅ 28/08/2013ዓ.ም፣ደ/ኤልያስ)

> ለሞቱ ሰዎች መታሰቢያ ወይንም ተዝካር ማድረግም አንዱ የቤተክርስቲያን ሥርዓት ከመሆኑ በተጨማሪ ለሙታን ምሕረትን ለመማጸን ይረዳል፡፡ በጸሎት፣ በመሥዋዕት፣ በመብራት፣ በማዕጠንት እና በምጽዋት መታሰቢያ ይደረግላቸዋል፡፡ በጸሎተ ፍትሐት ዳዊት መድገም፣ ገንዘብ በመለገስ፣ የሙት ስም በጸሎት እንዲነሣ፣ ቅዳሴ እንዲቀደስ እና ቁርባን እንዲቆርብ ማድረግ ተገቢ ነው፡፡ እስከ አሁን ድረስ ቤተ ክርስቲያን ይህን ያህል ደግሳችሁ አብሉ ብላ አታውቅም፡፡ በባህሉ ግን አንዳንዴ ያለውን ሁሉ አሟጦ የመደገስ አጉል ልማድ ይታያል፡፡ በቤተክርስቲያን ህግ ግን ለሙታን ስለ ሙታን በዋናነት ሦስት ነገሮች ይደረጋሉ፡፡ አንደኛው ከሣልስት ጀምሮ በፍትሐ ነገስት በተደነገጉት የመታሰቢያ ቀናቶች በሟች ስም የነፍስ ይማር ጸሎተ ፍትሐት ማድረግ፥ ሁለተኛ በሟች ስም መሥዋዕተ ቁርባን ማቅረብ፣ ሦስተኛ ደግሞ በሟች ስም ለድሆች ምጽዋት መስጠት ማለትም በገንዘብና በዓይነት/ ልብስ በማልበስ፥ ምግብ በማብላት ነፍስ ይማር ብለው እንዲጸልዩ የሚያደርግ ምጽዋት መስጠት ነው፡፡ ይህ ለድሆች ምጽዋት የመስጠት ሁኔታ በእህል ውሃም በገንዘብም ሊሆን ይችላል

በማለት ይገልጻሉ፡፡

በተጠኘው ማህበረሰብም ውስጥ ተዝካር የማውጣት ልምድ ያለ ሲሆን በዚህም ውስጥ የስጦታ ህግ እናገኛለን። ይኸውም የሟች ቤተሰብ ለቤተክርስቲያን ለቁርባን መስዋዕት የሚያስፈልጉትን እንደ ስንዴ፣ ዘቢብ፣ እጣን፣ መብራት ወዘተ. በመስጠት በቅዳሴ ጊዜ ጸሎተ ፍትሐት ሲደረግ የሟች ስም ተጠርቶ ነፍስ ይማር እየተባለ እንዲጸለይለት ይደረጋሉ። በተጨማሪም በተዝካሩ ቀን የቀደሱ ካህናት ተጠርተው በቤተክርስቲያን ዝክር ይሰጣል፣ ለነዳያን የሟችን ልብስ በመለገስ፣ ገንዘብ በመስጠት እና በመመገብ ነፍስ ይማር እያሉ እንዲመርቁ ያደርጋሉ። ስለዚህ በማህበረሰቡ የስጦታ እሳቤ ውስጥ ስጦታ ያለው ጥቅም በህይወት ላለ ሰው ብቻ ሳይሆን ለሞተ ሰውም ጭምር እንደሆነ በማመን በሞተ ሰው ስም የሚሰጥ ስጦታ በወዲያኛው ዓለም ያለን ኑሮ ያስተካክላል የሚል አስተሳሰብ እንደሚያራምዱ እና እንደሚተገብሩ እንገነዘባለን። ይህም በመጽሐፍ ቅዱስ ያለውን ቃል ስንመለከት ማቴ 25፥ 31-40

> የሰው ልጅ በክብሩ በሚመጣበት ጊዜ ከርሱም ጋራ ቅዱሳን መላእክቱ ሁሉ በዚያን ጊዜ በክብሩ ዙፋን ይቀመጣል። …በጎችን በቀኙ ፍየሎችንም በግራው ያቆማቸዋል። ንጉሡም በቀኙ ያሉትን እንዲህ ይላቸዋል፡፡ እናንተ የአባቴ ቡሩካን ኑ ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ። ተርቤ አብልታችሁኛልና፣ ተጠምቼ አጠጥታችሁኛልና፣ እንግዳ ሆኜ ተቀብላችሁኛልና፣ ታርዤ አልብሳችሁኛልና፣ ታምሜ ጠይቃችሁኛልና፣ ታስሬ ወደ እኔ መጥታችኊልና። ጻድቃንም መልሰው ይሉታል ጌታ ሆይ ተርበህ አይተን መቼ አበላንህ ወይስ ተጠምተህ አይተን መቼ አጠጣንህ እንግዳ ሆነህስ አይተን መቼ ተቀበልንህ ወይስ ታርዘህ አይተን መቼ አለበስንህ፡፡ንጉሡም መልሶ፡እውነት እላችኊለሁ፥ከሁሉ ከሚያንሱ ከነዚህ ወንድሞቼ ለአንዱ እንኳ ስላደረጋችሁት ለእኔ አደረጋችሁት ይላቸዋል።

በዚህ ቃል መሰረት የተራበን ማብላት፣ የተጠማን ማጠጣት፣ የታመመን መጠየቅ፣ የተራቆተን ማልበስ፣ የታሰረን መጠየቅ እና እንግዳን መቀበል ሁሉ አንዱ ለሌላው ማድረግ የሚገባዉ በፈጣሪ የተወደደ እና በፍርድ ሰዓት የሟችን ነፍስ የሚረዳ በጎ ስጦታ ነው። የሚል እምነት ስላላቸው ስጦታውን እንደ እጅ መንሻ በመገልገል በሟች ስም የተቸገሩትን በማብላት በማጠጣት እና በማልበስ ለሟች ይጸልዩለታል ።

በተጨማሪም ለቁርባን የሚሆን ስንዴ፣ ዘቢብ፣ እጣን፣ መብራት ወዘተ. ስጦታዎች በሟች ስም መስጠት ነፍሱን ይረዳታል ተብሎ ይታመናል። እነዚህ ስጦታዎች ከሌሎች ተመርጠው

በመቅረባቸው ድህነት እንዴት ያመጣሉ? ብለን ስንጠይቅ (ሲራክ 32፥9) “መስዋእት እግዚአብሔርን ደስ ያሰኘዋል።” እና (ወደ ዕብራውያን 11፥14) ደግሞ “አቤል ከቃየል ይልቅ የሚበልጥ መስዋእት ለእግዚአብሔር በእምነት አቀረበ በዚህም እግዚአብሔር ስለ ስጦታው እርሱ ጻድቅ እንደሆነ ተመሰከረለት። ሞቶም ሳለ በመስዋእቱ እስካሁን ይነገራል።” የሚል ቃል እናገኛለን። ከዚህም በመነሳት ንጽህና ለእግዚአብሔር የሚቀርቡ ስጦታዎች አንድ መስፈርት ሆኖ እናገኘዋለን። ስለዚህ እግዚአብሔር ንጹህ መስዋእት ይወዳል። የሚወደውን ንጹህ ስጦታ መስጠት ደግሞ ከሞት በኋላ ባለው ህይወት በጎ ምላሽ ይኖረዋል በማለት በህይወት ያሉት መርህ አድርገው ሲተገብሩት እንመለከታለን።

## 5.2 በጊዜ ሰሌዳዊ እና የመታሰቢያ ስርዓት ከበራዎች ስር የሚገኙ ስጦታዎች

✓ የአዲስ ዓመት(እንቁጣጣሽ) ስጦታዎች

የኢትዮጵያውያን ዐውደ ዓመት (አዲስ ዓመት) እንቁጣጣሽ በሚል ስያሜው ይታወቃል። በክርስቲያኖች ዘንድ ደግሞ የብሉይ ኪዳን የመጨረሻው ነቢይና የሐዲስ ኪዳን ስማዕት በሆነው በመጥምቁ ዮሐንስም ስም ቅዱስ ዮሐንስ በማለት ይጠራል። እንቁጣጣሽ የሚለው ስያሜ በተመለከተ (ንቡረዕድ ኤርሚያስ፣ ገጽ 334-337) ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት በተሰኘው መጽሐፋቸው ትርጉም እንደሚከተለው ይገልፁታል።

> ኢየሱስ ክርስቶስ በበረት ተወልዶ ሣለ ሰብአ ሰገል እየሰገዱ እጅ መንሻቸውን እንዳቀረቡለት እናዘክራለን፤ በዚያን ጊዜ እነሆ ሰብአ ሰገል ለሙሽራው እናትና ለአራሲቱ ሙሽሪት … ድንግል ማርያም “ለአንቺም ዕንቁ ለጣትሽ እነሆ!” ብለው ስጦታቸውን አበርክተውላት ነበር። የሰማይ መላእክትና የምድር ሠራዊት የምስራች ደስታቸውን በአንድነት በገለጹባት በዚች የልደት ቀን ዛሬም እኛ ኢትዮጵያውያን የአበባ ጉንጉናችንን ይዘን ስለእናት አገራችንና መቅደስ ንግሥታችን እርስ በእርሳችን “እንቁጣጣሽ!” እንባባላለን።

ከዚህም በተጨማሪ (ነብዩ ልዑል፣1965 ዓ.ም) በመነን መጽሔት እንቁጣጣሽ ምንድን ነው? ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተዋል።

> እንቁጣጣሽ ግጫ ማለት ነው፣ ግጫ ደግሞ የሣር ዓይነት ነው። የአበባ የእርጥብ ስጦታ መስጠት የተጀመረው በኖኅ ዘመን ነው። ኖኅ የጥፋት ውሃ በጎደለ ጊዜ መጉደሉን ለማረጋገጥ ርግብን ልኳት የወይራ ቅጠል አምጥታለች። እርሱም

የመርከቡን ጣራ አንስቶ ከወጣ በኋላ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት በማቅረብ ልዩ ልዩ ፀዓዳ ሽታ ያላቸውን አበቦች አቅርቧል። ንግሥተ ሳባ ወደ ንጉሥ ሰሎሞን ዘንድ ስትሄድ 500 ደናግልት ተከትለዋት ነበር። የእልፍኝ አሽከሮቿም እነሱ ሲኾኑ የአበባውም የእንቁጣጣሽ አሰጣጥ በእነሱ ተፈጽሟል። ስለዚህ ዛሬ ልጃገረዶች አበባ ቀጥፈው ግጫ ነቅለው ሽልመው የሚያቀርቡበት ነው። ይህም በአበው ዘንድ ሲያስመርቃቸው በጎረምሳው ዘንድ ደግሞ የመታጨት ዕድል ያስገኝላቸዋል።

በእንቁጣጣሽ ዕለት በየሀገሩ የሚፈፀሙት ባህሎች የተለያዩ ሲሆኑ ጥናቱ በተካሄደበት ማህበረሰብ በዚህ ዕለት ግጫ እና የአደይ አበባ በመቅጠፍ "እንቁጣጣሽ" በማለት ጎንጉነው ይሰጣሉ። ተቀባዮችም "በየዓመቱ ያምጣሽ" እያሉ ግጫ እና አበባውን ይቀባላሉ። ከተቀበሉም በኋላ ገንዘብ ይሰጧቸዋል። እነርሱም ባገኙት ስጦታ የፈለጉትን ዕቃ ገዝተው የእንቁጣጣሽ በረከት እያሉ እንደ ማስታወሻ አድርገው ይጠቀሙበታል። በተጨማሪም ህጻናት እንግጫ ነቅለው ጎንጉነው በየ ዘመድ እና ጎረቤት ቤት "እንቁጣጣሽ!" እያሉ ይዞራሉ። ሰዎችም ወደቤታቸው አስገብተው ቂቤ ያላቸው ቂቤ ቀብተው ሳንቲም ሰጥተው ይልኳቸዋል። ይህን ልማድ በምልከታ ወቅት ለማረጋገጥ የተቻለ ሲሆን በቃለ መጠይቅ ወቅትም በአዲስ ዓመት ስላለው የመሰጣጣት ባህል እና ስለ እንግጫ ማሰር እማሆይ ህብስቴ (ቃለመጠይቅ 21/08/2013 ዓ.ም ደ/ኤልያስ) የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተውኛል።

> ባገራችን አዲስ ዓመት  እንግጫ(ግጫ) ተነቅሎ አድዮ አበባ (አደይ አበባ) ተይዞ እንቁጣጣሽ እየተባለ ነው የሚከበር። እንዲያውም የእንግጫ ነቀላው ... 'የቅዱስ ዮሐንስ ያልዘፈነች ቆንጆ ቆማ ትቀራለች እንደ ሰባር ጎጆ' እየተባለ ይዘፈናል። ይሄ ከጥንትም የነበረ ሴቷ አበባ አየሽወይ ስትል ያያት ያጫት ስለነበር ነው። አሁን አሁን ግጥሙ እና ዜማው ተዘነጋ እንጂ። እንግጫ ጎንጉኖ እንቁጣጣሽ ማለቱ አልቀረም። ...ብቻ ህጻን
>
> ይሁን እንጂ ወንዱም  ሴቱም እንግጫውን ጎንጉኖ በአንገቱ ተሸክሞ ይመጣና 'እንቁጣጣሽ' ብሎ የቤቱ ምሰሶ ላይ ያስራል። የቤቱ ባለቤትም 'እያመቱ ያምጣሽ' ብሎ መርቆ ከብት ካለው ቅቤውን ቀብቶ ወተቱን አጠጥቶ ይልካቸዋል። ከሌለውም የዓመት በአል ዳቦ ይሰጣል። ብቻ ሳይሰጥ አይሸኝም። ምነ ብትይኝ ድሮ የጎረቤት ልጅ እንደ ራስ ልጅ ነበር ወዲያውም... የልጁ እናት እና አባት እገሌ ምን ሰጠህ? ብለው ሲጠየቁ የማያሳፍር ስጦታ መሆን አለበት። ... የጎረቤት ልጅ ለዓውዳመት እንግጫ ይዞ ካልመጣ

እገሌ ልጁን ያልላከ ምን አስቀይሜው ነው ይባላል። እና ዓውዳመት የሚሆነውም በሽጋው ቀን እህል ሲዘረዝር የሚያፈራውም አበባ ሲያወጣ ነው። የዚያን ግዜ አድዮ አበባውን ቆርጠው እንግጫውን ጎንጉነው እንቁጣጣሽ እያሉ ይዞራሉ።

በዚህም ምላሽ እንቁጣጣሽ መባባል፣ የእንግጫ ስጦታ መሰጣጣት ማህበራዊ ግንኙነትን ለማጠናከር እንደሚጠቀሙበት፣ ህጻናት ለምለም ሳር(ግጫ) ይዘው የአዲስ ዓመት ብስራትን እንደሚያደርሱ እንመለከታለን። በዚህ የስጦታ ልውውጥ ውስጥ ሰጪዎቹ ህጻናት ሲሆኑ ተቀባዮቹ ደግሞ የአካባቢው ማህበረሰቦች ናቸው። በማህበረሰቡ ልማድ ውስጥ ህጻናት ሀጢያት (መጥፎ ስራ) የሌለባቸው፣ ንጹህን ተደርገው ይቆጠራሉ። በዚህም መሰረት ልዩ ልዩ ክንውኖችን ለመስራት ንጽህና የሚያሻው ነገር ሲኖር ለህጻናት ቅድሚያ ይሰጣል።

ይህን አስመልክቶ ቄስ ላመስግን (ቃለመጠይቅ 14/08/2013፣ደ/ኤልያስ) የአዲስ ዓመት ስጦታ ለመስጠት ህጻናት ለምን ተመረጡ? ለሚለው ጥያቄ “ህጻን ንጹህ ባህርይ ነው። አባታችን ኖህ ከጥፋት ውሃ በኋላ ቁራን ልኮት የምስራች ይዞ አልመጣም ርግብ ግን የዋህ ናትና ምስራቹን ይዛ ተመልሳለች። እና ህጻናትም እንደ ርግብ የዋህን በመሆናቸው ዓውዳመቱን በብስራት ለመጀመር ህጻናት ግጫ ይዘው ይዞራሉ።” በማለት መልሰውልኛል። ከዚህም የምንረዳው በማህበረሰቡ የስጦታ ደንብ ውስጥ ንጽህና አንዱ መስፈርት መሆኑን ነው። በተጨማሪም የስጦታው አይነት ለምለም ሳር (ግጫ) መሆኑ አዲስ ዓመት የሚከበረው ክረምት አልፎ የብራ እና የልምላሜ እንዲሁ እህል ለማፍራት አበባ የሚያሳይበት ወቅት በመሆኑ ያለውን ነባራዊ ሁኔታ ይወክላል። በዚህም ውስጥ ስጦታ የሰጪውን አካባቢያዊ ሁኔታ የመግለጽ አቅም እንዳለው እንረዳለን። ለአውድ ዓመት ከእንግጫ በተጨማሪ የተለያዩ ስጦታዎች ይከዎናሉ። ለምሳሌ፦ መስዋዕት ይቀርባል (ይታረዳል) ካልታረደ (አውዳመቱ ደም ካልፈሰሰለት) ችግር ይገጥማል ተብሎ ይታመናል፣ የቂቤ እና የድቁስ እቃ ይሞላል። በሶ ተንፈርፍሮ ከመቀመሱ በፊት "አዋይ ይቅመስ" እየተባለ መሬት ይበተናል። እነዚህ ልማዶች በየዓመቱ የሚደረጉ እና ሳይደረጉ ከቀሩ በረቂቅ መናፍስት ቁጣ ዓመቱ የሀዘን ይሆንብናል በማለት የሚከዎኑ ስጦታዎች ናቸው። እነዚህን የስጦታ ክዋኔዎች በመከራ ስርዓተ ከበራዎች የሚሰጡ ስጦታዎች ዘንድ በስፋት እንመለከታቸዋለን።

- ✓ እሽት ቅመሱ

ወቅትን ተከትለው ከሚከወኑ ነገሮች አንዱ ከግብርና ስራ ጋር በተያያዘ ምርት የማምረት እና የመሰብሰብ ሁነቶች ናቸው። በደብረ ኤልያስ ማህበረሰብ ዘንድ የጥቅምት እና የህዳር ወር እሽት

የሚደርስበት ወቅት በመሆኑ በእርሻ ስራ የሚተዳደረው ገበሬ እሸት ቆርጦ ከተማ ላሉት ዘመዶቹ፣ ወዳጆቹ:: "እሸት ቅመሱ" ብሎ ያመጣላቸዋል:: ይህን አስመልክቶ ወ/ሮ የዝና (ቃለመጠይቅ 19/08/2013 ዓ.ም ደ/ኤልያስ):: እንዲህ ያስረዳሉ::

> ... ይሄ ከድሮም ጀምሮ የነበረ ወግ ነው:: እከተማ ያለው ሰው በገቢያው እንዳሁኑ እሸት መሸጥ ሳይጀመር እሸት ለመቅመስ ልቡ ያስቀልላል (ያምረዋል):: ዘመድ ወይ ወዳጅ ከገጠር ያለው ሰው ግን በክረምት ድንች ተጭኖ፣ በጥቅምት እና በህዳር ማሽላው፣ ባቄላው፣ አተሩ እሸት፣ ንብ ታለው ማሩን ቆርጦ፣ በታህሳስ ደግሞ ከአውድማው እህል ይመጣለታል:: መቼም ሰው ያለውን ነው የሚሰጠው እና የገጠሩም ሰው እንደ ከተማው ነግዶ ስለማያተርፍ ገንዘብ ወይ ልብስ ልስጥ ቢል አይችልም:: የከተማውን ሰው ደሞ እህል ወይ ከብት አምጣ ብትይው እንደ ገበሬው አይኖረውም:: ስለዚህ የሀገሩ ዓመት በዓል ደርሶ ወይ ድግስ ኖሮበት ካልጠራ በቀር ሌላ ነገር ስለማያገኝ ዘመዶቹን የሚጠይቅ እሸት ይዞ ነው:: በደንባችን ደሞ እሸት የማያቀምስ ዘመድ እንደ ዘመድም አይቆጠር እንኳን ለሚያውቁት ሰው ለባእድ እንኳን እሸት አይከለከልም:: ሀላፊው ሁሉ ለሚበላው...::

ስጦታ ካሉት ባህርያት ውስጥ ስጦታ ሆኖ የሚቀርበው ነገር የሰጪውን ማንነት የመግለጽ አቅም መኖሩ አንዱ ነው:: (Belk,1976) "እሸት ቅመሱ" ተብሎ የሚመጣ ስጦታ ደግሞ በግብርና የሚተዳደሩ ማህበረሰቦች ዘንድ ብቻ ሊገኝ የሚችል የስጦታ ዓይነት ነው:: ከቃለመጠይቁ ምላሽ የምንረዳው ማህበረሰቦቹ ከመተዳደሪያ ስራቸው ጋር አያይዘው ያመጡት የእሸት ስጦታ ልማድ የእርስ በእርስ ማህበራዊ ግንኙነታቸውን እና ዝምድናቸውን ለማጠናከር፣ ለማለሳለስ እና ለማስቀጠል ያለው አዎንታዊ አስተዋጽኦ ከፍተኛ እንደሆነ እንረዳለን:: ይህን አስመልክቶ በቡድን ተኮር ውይይት(1/09/2013 ዓ.ም) የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው እሸት ቅመሱ ተብሎ የመጠየቁ ዋናው ምክንያት እንዴት ከረማችሁ ብሎ ወዳጅን ለመጠየቅ እና ለመመራረቅ እንደሆነ ነው:: በተጨማሪም አዲሱን እህል ለወዳጅ ለዘመድ ማቃመስ በረከት ይኖረዋል የሚል እሳቤ እናገኛለን፡፡ በማህበረሰቡ ደንብ እሸት መቅመስ እንደማይከለከል ገልጸዋል:: ይህን በተመለከተ ካህሳይ (2008፣ 381) እሸት መቅመስ ለምን እንደማይከለከል እንዲህ በማለት ያስረዳሉ::

> ... እንደዛም ሆኖ በተራበ አንጀቱ በደከመ ጉልበቱ አርሶ፣ ቆፍሮ፣ ዘርቶ፣ አርሞእና ኮትኩቶ ለፍሬ ሲደርስት ደስታ እንጂ ስስት አይሰማውም:: መሆኑም

> በእሸት ወቅት መንገደኛ በእርሻ ማሳ አጠገብ ሲያልፍ ሸምጥጦም ይሁን ቆርጦ ቢበላ የሚከለክለው የለም። እንዲያውም መንገደኛ ይሉኝታ ይዞት ዝም ብሎ ከሄደ የእርሻው ባለቤት(ጠባቂ) እሸት ቅመስ ብሎ ይጋብዘዋል። ... ከዚህም በተጨማሪ እሸትና ጥንቅሽ የደረሰለት ገበሬ ብቻውን አይቀምስም። ለጎረቤቶቹ ሁሉ 'ዓመት ዓመት ይድገመን' እያለ ያድላቸዋል። ተቀባዮችም እህል ይታፈስ ይርከስ ሳቢ በሬውን አራሽ ገበሬው ይባርክ። ኑሮአችሁ ሕይወታችሁ እንደ እሸት የለመለመ ይሁን ወልዳችሁ ሳሙ ዘርታችሁ ቃሙ በማለት ይመርቃሉ።

በተጠኘው ማህበረሰብ ዘንድ የእሸት ስጦታ እንደማይከለከል እና ከዘመን ዘመን ከወቅት ወቅት በደህና መሸጋገርን፣ ጤና መሆንን ወዘተ. መጠያየቂያ፣ ማህበራዊ ግንኙነትን ማጠናከሪያ በሰጪ እና በተቀባይ መካከል ያለን ግንኙነት ማደሻ ሆኖ ሲያገለግል እንመለከታለን። ምክንያቱም እሸት አሮጌውን እህል መሻሪያ በመሆኑ ለአምራቹ ማህበረሰብ እሸት ራሱ ቀምሶ የቅርብ ወዳጆቹን ያቀምሳል። በዚህም ውስጥ ግንኙነቱን በማደስ ከሸቱ ጋር አዲስ የቅርርብ ስሜት እንዲፈጥር ያግዘዋል። ስለዚህ የእሸት ስጦታው እህሉ ከመስጠት ጋር እንዲባረክ ይረዳዋል በሚል እሳቤ እንደሚከወን እንዲሁም በሰጭ እና ተቀባይ ዘንድ ያለውን የእርስ በእርስ ግንኙነትን ለማጠንከር ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳለው እንረዳለን።

- ✓ ማርያም ባርኪ

ይህን የስጦታ አይነት ማህበረሰቡ ምርት በሚሰበስብበት ወቅት ከአውድማው ላይ የመጀመሪያውን ቀንሶ "ማሪያም ባርኪ" ስጦታ በአካባቢው ለሚገኝ ቤተክርስቲያን ይሰጣል። በዘመነ ብሉይ የእሸት መስዋዕት ይቀርብ እንደነበር ካህሳይ (2008፣383) ከመጽሐፍ ቅዱስ ኩፋ(8፥31)ን ጠቅሰው "ሰዎች የዘሩት አዝመራ ከድርቅ፣ ከተምችና አንበጣ፣ ከበረዶ እና ከጎርፍ ተርፎ ለፍሬ ሲደርስላቸው እነሱ ከመቅመሳቸው በፊት የመጀመሪያውን ለእግዚአብሔር መመስገኛ መስዋዕት አድርገው ያቀርቡ ነበር።" በማለት ይገልጻሉ። በተጠኘው ማህበረሰብ ዘንድ እስከ አሁንም ድረስ ማሪያም ባርኪ እያለ ከእህሉ መጀመሪያ የሚሰጠው የስጦታ ደንብ አለ። ይህን አስመልክቶ አቶ ምትኩ (ቃለመጠይቅ 21/08/2013ዓ.ም፣ደ/ኤልያስ) ይህንን ምላሽ ሰጥተዋል።

> እህል ተበራይቶ ከተወቃ በኋላ ከአውድማው ተሰፍሮ ወደቤት አይገባም። እንደ ደንቡ ተመጀመሪያው በእፍኝ ወይ በሌላ መስፈሪያ ከእህሉ ተነስቶ ለማሪያም ባርኪ እየተባለ ይቀመጣል ያ የተቀመጠውም እህል ለቤተክርስቲያን መባ ይሰጣል። ለምን ቢባል ገበሬ

በሰኔ ለሚበላው ሳያስቀር ፈጣሪውን አምኖ አዛኝቷን አምኖ እህሉን አውጥቶ በመሬት ይበትናል። እኔም ገበሬ ስለሆንሁ አውቀዋለሁ...አዛኝቷ ማርያም ተልጂ ጋር የዘራነውን ጤፍ፣ የዘራነውን ስንዴ፣ የዘራነውን ገብስ፣ በዝናብ አብቅላ ተክፉ ጠብቃ ለአውድማ እንዲበቃ ስለረዳችን ለማመስገን እንዲያው ታገኘነው እህል የመጀመሪያውን አፍሰን እንሰጣለን። ደሞም ለማሪያም ባርኪ ያልተቀነሰለት እህል በረከት የለውም። ማርያም ባርኪ ማለት በራሱ ጸሎት ነው። የተመረተውን ምርት እሷ እንድትባርከው በሰላም ተበልቶ እንዲያልቅ እንድታደርገነ ነው።

በዚህም ምላሽ ማህበረሰቡ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት ተከታይ በመሆኑ ከእህሉ ቀንሶ በድንግል ማርያም ስም ለቤተክርስቲያን የእህል ስጦታ እንደሚያቀርብ የተረዳን ሲሆን፤ የስጦታ ልማዱ ከምርት መሰብሰብ ጋር ተያይዞ ምስጋና ለማቅረብ፣ እና ለማስባረክ (መልካም እድሎችን እንዲያመጣ ለማድረግ) በሚል የሚከወን መሆኑን እንረዳለን። ማህበረሰቡ ለአምላኩ ስጦታ ለመስጠት አብዛኛውን ጊዜ የመጀመሪያውን ይመርጣል። ይህን አስመልክቶ ቄስ ላመስግን (ቃለመጠይቅ 14/08/2013ዓ.ም፣ ደ/ኤልያስ) "የመጀመሪያ ነገር ያጓጓል እና ስስት ያስይዛል። ስስት ደግሞ የመስጠት ተቃራኒ ነው። ስለዚህ ስስትን በማጥፋት የምትጓጊለትን የመጀመሪያ ነገር በመስጠት ያለሽን ፍቅርሽን ታሳያለሽ። ከተረፈ ነገርማ መስጠት ቀላል ነው።" በማለት የመጀመሪያ ነገርን ለምሳሌ፦ (የመጀመሪያ ልጅን፣ የመጀመሪያ ምርትን፣ የመጀመሪያ ጉርሻን፣ የመጀመሪያ እድልን ወዘተ.) መስጠት የእውነተኛ ፍቅር መገለጫ እንደሆነ ምክንያቱን ያስረዳሉ። በማሪያም ባርኪ ስጦታ ውስጥ ከዋኞቹ በማህበረሰቡ ውስጥ እህል የሚያመርቱ የምርት ባለቤቶች ሲሆን ተቀባይ ደግሞ ፈጣሪ ነው። የሚሰጠው እህል ወደቤት ከመግባቱ በፊት ከመጀመሪያው ለመነሳቱ ምክንያት ግን ለምስጋና እና ቀሪው እንዲባረክ ወይም በረከት እንዲኖረው ያደርጋል የሚል እሳቤ እንደሆነ ከቃለመጠይቁ ምላሽም ሆነ "ባርኪ" ከሚለው ስያሜ ማረጋገጥ ይቻላል። በዚህ የስጦታ ክዋኔ ውስጥም ማህበረሰቦቹ ለፈጣሪያቸው ያላቸውን የአመስጋኝነት፣ የተገዢነት እና የታማኝነት ስሜት የሚያሳዩበት እንዲሁም "ስሰጥ ይበዛልኛል ወይም በመስጠት መባረክ" የሚል አስተሳሰብ እና እምነት እንዳላቸው እንረዳበታለን።

✓ የክብረ በዓላት ስጦታዎች

በማህበረሰቡ ዘንድ ክብረ በዓላት በልዩ ልዩ ዝግጅቶች ታስበው ይውላሉ። ማህበረሰቡ ለክብረ በዓላት የሚሰጠው ቦታ ከፍተኛ መሆኑ እና በዓልን በጋራ የማክበር ልማዱ ጠንካራ መሆኑ

ስጦታዎችን አንዱ ለሌላው እንዲሰጥ መንገድ ይከፍታል። ስለዚህ ስጦታ ለመቀያየር ክብረ በዓላት እና ዝግጅቶች ከዘወትር ቀናቶች በበለጠ የተመረጡ እና አነሳሽ ሆነው እናገኛቸዋለን። የደብረ ኤልያስ ማህበረሰብ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ እና በተወሰነ ደረጃ የሙስሊም ማህበረሰቦች የሚኖሩበት አካባቢ በመሆኑ ከሃይማኖት ጋር በተያያዘ እንደ ኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖች እና ሙስሊሞች በሚያከብሯቸው በዓላት እና በድግስ ሰበብ አንዱ ለሌላው የማብላትና የማጠጣት ወይም የመስጠት ባህል አላቸው። ከበዓላቶቹ ጋር ተያይዞ እንደ ማህበረሰብ ያዳበሯቸው የስጦታ ልማዶች የሚከተሉት ናቸው።

- ✓ ለንሰሃ አባት የሚሰጡ ስጦታዎች

በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ከሚከበሩ በዓላት ውስጥ ደብረ ዘይት ስለ ዳግም ምጽአት ወይም ፈጣሪ ለፍርድ የሚመጣበትን ሰዓት በማሰብ እና ስለዚያች ቀን በመማማር የሚከበር በዓል ነው። ይህ በዓል በመላው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ክርስቲያኖች በቤተክርስቲያን የተለያዩ ዝግጅቶችን በማድረግ የሚከበር ሲሆን በተጠኘው ማህበረሰብ ዘንድ በዚህ በዓል ቀን ለየት ያለ የስጦታ ልማድ አላቸው። ይኸውም ልማድ ምዕመኑ የንስሃ አባትን የመጠየቅ እና ስጦታ የማበርከት ልማድ ነው። ይህን በማስመልከት አቶ አበበ (ቃለመጠይቅ 01/09/2013 ዓ.ም ደ/ኤልያስ) ስለ በዓሉ አከባበር ምክንያት እና ስለ ስጦታው የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተውኛል።

> ደብረ ዘይት ጌታችን ያረገበት ተራራ ስም ነው። የእግዚአብሔር ዳግም ምጽአት የሚታሰብበት እለት ነው። ፈጣሪ ለፍርድ ሲመጣ ሁላችንንም እንደ ስራችን ይፈርድልናል። ስለዚህ በጎውን ስራ መስራት፣ የተራበውን ማብላት፣ የታረዘውን ማልበስ፣ የታመመውን መጠየቅ፣ የታሰረውን ማስፈታት እንዳለብን እንማራለን። … በቤተክርስቲያን በዓሉን ካከበርን በኋላ የራሳችን ደንብ አለን። የየሰው ንስሃ አባት የዚያን ቀን  እህል ውሃ አዘጋጅተው እቤታቸው የመጥራት ልምድ ስላላቸው።የንስሃ ልጆችም ተሰብስበን ሻሽ፣ ካባ፣ መቋሚያ፣ መስቀል ወይ ገንዘብ ብቻ ስጦታ እንወስድላቸዋለን። ንስሃ አባታችንን በየቤታችን የተለያየ ዝግጅት ሲኖር ወይም የግል ጉዳያችን ሲኖር እንገናኛቸዋለን። እሳቸውም ታከተኝ ሳይሉ ሁላችን ወደ ነፍሳችን እንድንመለከት እየመከሩ በደስታው እየተደሰቱ፣ ሀዘን ሲኖር ደሞ እያጽናኑ የከረሙትን እኛም እንደልጅነታችን እየታዘዝን የደብረ ዘይትን ዓመት በዓል በእሳቸው ዘንድ ስጦታ ይዘን

> በዓመት አንድ ጊዜ በቤታቸው ተሰብስበን እናከብራለን፤ እንመካከራለን። ይገርምሻል የዚያን ቀን መጥቶ የማያውቀው ንስሃ ልጅ ሁሉ ነው የሚሰበሰበው።

ንስሃ አባት ማበጀት ወይም ንስሃ አባትና ልጅ መሆን በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት አማኞች ዘንድ የተለመደ ህግ እና እንደ ማህበረሰብ ደግሞ ዝምድና መፍጠሪያ አንዱ መንገድ ነው። ንስሃ አባት በሌላ አነጋገር "የነፍስ አባት" እየተባለ ይጠራል። ይኸውም በክርስትናው አስተምሮ ውስጥ ፈጣሪ ለንስሃ አባት  በነፍስ ላይ ስልጣን ሰጥቶታል የሚል አስተምህሮ ስላለው ነው። በዚህም ምክንያት በህይወት ያደረጉትን መጥፎም ሆነ ጥሩ ስራ በውዴታቸው ከንስሃ አባት ጋር ይወያያሉ። ከዚህም የተነሳ ቅርርባቸው እንደ ቤተሰብ በመሆኑ በደስታም ይሁን በሀዘን አይነጣጠሉም። በተጠኘው ማህበረሰብ ዘንድ የንስሃ አባቶቻቸውን በደብረ ዘይት በዓል ስጦታ ይዘው እንደሚጠይቋቸው እና የንስሃ ልጆችም በንስሃ አባታቸው ድግስ እርስ በእርስ እንደሚገናኙ ከቃለመጠይቁ መረዳት ይቻላል። በዚህም ውስጥ ስጦታ የሚሰጡት ምእመናን ሲሆኑ ተቀባይ ደግሞ የንስሃ አባቶች ናቸው። ለንስሃ አባቶቻቸው የሚያቀርቧቸው ስጦታዎች ለሃይማኖት አባት ሊያስፈልጋቸው የሚችሉ አልባሳት ሲሆኑ ማህበረሰቡ በሰዎች ፍላጎት ላይ ተመርኩዞ የመስጠት ልማድ እንዳለው እንረዳለን። በተጨማሪም ስጦታው ያላቸውን ግንኙነት ለማጠንከር  እና በድግሱ ተገኝቶ ደግሞ አብሮነትን የማሳየት ሚና እንዳለው መጥቶ የማያውቅ ንስሃ ልጅ የዚያንቀን እንደማይቀር ቃለመጠይቁ ያስረዳል። በዚህም ስጦታው ያገለገለን አባት ምስጋና ለማቅረብ የሚረዳ ሲሆን የተራራቀን አባት እና ልጅ የማቀራረብ ሃይማኖታዊ ፋይዳ ያለው እንደሆነ እንረዳለን።

- ✓ ለኦርቶዶክሳዊ ምእመን የሚሰጥ ስጦታ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ከሚከበሩ በዓላት ውስጥ የትንሳኤ በዓል አንዱ ነው። ከበዓሉ በፊት አንድ ቀን ቀድሞ ቅዳም ስዑር የሚባል በዓል ይከበራል። ይህም በዓል ከስቅለት በዓል ቀጥሎ ቅዳሜ ቀን ክርስቶስ በመቃብር ያደረበት ቀን ይከበራል። በዚህም ክብረ በዓል ካህናት በክርስቲያኖች ቤት እየዞሩ ቃጭል እየመቱ ቄጤማ ያድላሉ ወይም የቄጤማ ስጦታ ያበረክታሉ። ይህ ስጦታ የሚሰጥበትን ምክንያት እና ያለውን ትዕምርት በተመለከተ ዲያቆን አምሀ (ቃለመጠይቅ 28/08/2013 ዓ.ም ደ/ኤልያስ) የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተውኛል።

> ቅዳም ስዑር ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በከርሠ መቃብር የዋለበት ቀን ነው።ከዚህ በተጨማሪም በዚህች ዕለት ቄጤማ ይታደላል። ቄጤማ መታሰሩ ከሰሙነ ህማማት ጋር የሚገናኝ ሳይሆን ከኖኅ ታሪክ ጋር የተያያዘ ነው። የኖኅ ዘመን ሰዎች

ኃጢያት በመስራታቸው ምክንያት እግዚአብሔር አምላክ ሊያጠፋቸው ሲል ኖኅን መርከብ እንዲሰራ አድርጎ እርሱን እና ቤተሰቦቹን እንዲሁም ከሁሉም እንስሳት ወንድ እና ሴት አድርጎ ከመዓቱ አድኖታል፡፡ በኋላም ርግብ ልኳል፡፡ የጥፋት ውሃው መጉደሉን ለማሳየት ርግብ ቄጤማ ይዛ ተመልሳለች፡፡ ይህንን የምሕረት ቀን ለማዘከር በተመሳሳይ መልኩ ጌታ ተሰቅሎ ምህረት መጥቷልና ለዚህ ምልክት እንዲሆን ቄጤማ ይሰጣል፡፡ የተሰጠውን ቄጤማም በራስ ላይ ይታሰራል፡፡

በዚህ ምላሽ ውስጥ በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት ተከታዮች ዘንድ የቅዳም ስዑርን በዓል በማስመልከት ካህናት ለምዕመናን የሚሰጡት የለምለም ቄጤማ ስጦታ፣ የደስታ እና የምስራች ማብሰሪያ ምልክት ሆኖ እንደሚያገለግል እንረዳለን፡፡

✓ ለክርስትና ልጅ የሚሰጡ ስጦታዎች

ይህ ስጦታ በደብረ ታቦር ክብረ በዓል ይሰጣል፡፡ የደብረ ታቦር በዓል በቤተክርስቲያን ትምህርት ሙሴ እና ኤልያስ ከጌታ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር በደብረ ታቦር ተራራ የተነጋገሩበትን ቀን በማሰብ በየዓመቱ ነሀሴ 13 የሚከበር በዓል ነው፡፡ ይህ ሲሆን፣ በአገራችን የክረምቱ አፈና ተወግዶ የብርሃን ወገግታ የሚታየውም በዚህ በዓል ወቅት ስለሆነ ዕለቱ 'ቡሄ' የሚለውን ስያሜ እንዳገኘ እና በዚህ እለትም በተጠኘው ማህበረሰብ አካባቢ ያለውን የስጦታ ልማድ ቄስ ላመስግን (ቃለ መጠይቅ፣ 15/08/2013 ዓ.ም)፡፡እንዲህ በማለት ያስረዳሉ፡፡

> ቡሄ ማለት ብራ፣ ብርሃን፣ ደማቅ ማለት ነው፡፡ ጌታችን ብርሃነ መለኮቱን የገለጠበት በዓል ስለሆነ የብርሃን በዓል በማለት የቡሄ በዓል እንላለን፡፡ ወቅቱ የክረምት ፤ጨለማ አልፎ ብርሃን የሚወጣበት፤ ሰማይ ከጭጋጋማነት ወደ ብሩህነት የሚለወጥበት የመሸጋገሪያ ወቅት ነው፡፡ 'ቡሄ ከዋለ የለም ክረምት፤ ዶሮ ከጮኸ የለም ሌሊት' ይባላል፡፡ የዚያን ቀን ጅራፍ ይጮኻል፡፡ በሌላ በኩልም ዳቦ የሚጋገርበት በዓል ነው፡፡ በዚህ ቀን ጌታችን ብርሃነ መለኮቱን የገለጠበት ስለነበር እረኞች ጨለማው ቀን መስኋቸው ሲጫወቱ ልጆቻቸውን ፍለጋ የወጡ ወላጆች ዳቦ ጋግረው ይዘውላቸው ወጥተዋል፡፡ አሁንም በዓሉ የዳቦ በዓል እስኪመስል በየቤቱ ይነገታል (ይጋገራል)፡፡ መሰረቱ እንዲያ ሆኖ በሀገራችን የክርስትና እናት እና አባት የቡሄ ዳቦ ጋግረው ለክርስትና ልጆቻቸው ስጦታ ይወስዳሉ፡፡ ልጅም ለቡሄ 'የክርስትና እናቴ ዳቦ ታመጣልኛለች' 'የክርስትና አባቴ ዳቦ ያመጣልኛል' ብሎ ይጠብቃል፡፡ ክርስትና እናት ወይም አባት በአንዳንድ ችግር ምክንያት ዓመቱን ሙሉ ወደ ልጃቸውን ሳይሄዱ ቢቀሩ

> እንኳን የቡሄ ዳቦ ይዘው በዓመት አንድ ጊዜ ይጠይቃሉ። እንጂ እንደ መሀል ሀገር ለቡሄ እየጨፈሩ ሳንቲም መቀበል የለም። በባህላችን የደብረ ታቦር ዳቦ ይዞ ያልጠየቀ ክርስትና እናት እና አባት እንዳለም አይቆጠርም።

ከቃለ መጠይቁ ምላሽ በማህበረሰቡ ውስጥ ከበዓሉ ጋር ተያይዞ አበልጅ (የክርስትና እናት እና አባት) ልጁን የዳቦ ስጦታ ይዞ እንደሚጠይቅ እንረዳለን። ስጦታው ቤተሰባዊነትን፣ ፍቅርንና መተሳሰብን መግለጫ ሲሆን  በተጨማሪም በዓሉን አስመልክቶ የክርስትና እናት እና አባት ልጁን በሚጠይቅበት ወቅት ቤተሰባዊ ግንኙነቱ እየጠበቀ እንደሚሄድ እና ይህ ሳይሆን ሲቀር ግን ግንኙነቱን እንደሚያሻክረው "የደብረ ታቦር ዳቦ ይዞ ያልጠየቀ ክርስትና እናት እና አባት እንዳለም አይቆጠርም።" የሚለው አገላለጽ ያስረዳል፡፡ ስለዚህ የቡሄ ዳቦ ስጦታ በተጠኝው ማህበረሰብ ዘንድ  ከዋኙ የሚታወቅ እና የራሱ የሆነ ህግ ያለው ዝምድናንን መጠበቂያ እና ማስቀጠያ መንገድ ነው። ይህን አስመልክቶ አቶ ደምል (ቃለመጠይቅ 08/09/2013 ዓ.ም፣ ደ/ኤልያስ) በሰጡት ምላሽ

> አበልጅነት እየጠነከረ የሚሄደው በሁሉም ነገር ሲጠያየቁ አልሆን ካለ ደሞ የቡሄ ዳቦይቱን ጋግሮ ልጅን ሲጠይቁ ነው። ...መጠያየቁማ ሁልዜስ ቢሆን ምን ይል ነበር እንዲያው የማይቻል ከሆነ ግን ልጅ ነፍስ እስቲያውቅ እስከ 15 ዓመት እንዲያ ዳቦ ተይዞ የመጠየቅ ደንብ አለን፡፡ ያለዚያ ለልጁ ዳቦ ወዶብኝ ነው? (ዳቦ መስጠት ክብዶት ነው?) እየተባለ ያስተቸዋል። ... ልጁ ራሱ ዐይኑ ሲቃብዝ ነው የሚውል። ዳቦ በቤቱ ጠፍቶ ሳይሆን ከክርስትና እናቱ ወይ አባቱ የለመደው ስላለ ነው በማለት ያስረዳሉ።

በዚህም ውስጥ በተጠኝው ማህበረሰብ የቡሄን በዓል ተከትሎ የሚቀርበው የዳቦ ስጦታ ሰጪው ክርስትና እናት ወይም ክርስትና አባት ሲሆን ተቀባዩ ክርስትና ልጅ ነው። ስጦታውም ዝምድናን የማጠናከር እና የማስቀጠል ሚና ያለው እንዲሁም የስጦታው አይነት ዳቦ መሆኑ ክርስቶስ ብርሃነ መለኮቱን በገለጠበት ዕለት እናቶች ለልጆቻቸው ዳቦ ይዘውላቸው የመሄዳቸው ምሳሌ እና ሃይማኖታዊ መነሻ ያለው ስጦታ እንደሆነ እንረዳለን።

- ✓ የንግስ በዓላት ስጦታዎች

በተጠኝው ማህበረሰብ ዘንድ ከሚከወኑ ከበራዎች መካከል ከኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት ጋር በተያያዘ የሚከበሩ የፈጣሪ፣ የጻድቃን፣ የመላእክት ዓመታዊ የመታሰቢያ በዓላት ናቸው። እነዚህንም ክብረ በዓላት የሀገሬው ነዋሪ ዓመቱን ጠብቆ፣ ልክ እንደ መኖሪያ አካባቢው ዓመት

በአል ቆጥሮ፣ ደግሶ የማክበር ልማድ አለው። ከዓመታዊ ክብረ በዓሉ ጋር ተያይዞም በሚያዘጋጀው ድግስ በየአካባቢው ያሉትን ዘመዶቹን ለዓመት በአሉ እንዳትቀሩ እያለ ይጋብዛል። ይህንን ልማድ አስመልክቶ ያለውን አከዋወን እና እሳቤ (በቡድን ተኮር ወይይት 01/09/2013 ዓ.ም)። ተጠኝዎች እንደሚከተለው ያስረዳሉ።

> የየአገሩ ዓመት በዓል በቀዬው እንደተደበረው ደብር ነው የሚከበር። አሁን በአንዱ ጎጥ ያለው ደብር የሚካኤል ከሆነ ከህዳር፣ ከጥር፣ ከሰኔ በአንዱ ዓመትባሉ ይሆናል። አገሩ ሲጠራም በደብሩ ስም ነው። ለምሳሌ፦ አበሽብ ሚካኤል፣ የቁልጭ ሚካኤል፣ እነጋት ጊዎርጊስ እየተባለ ... አሁን የኤልያስ ዓመት በዓል በታህሳስ አንድ ነው የሚከበር። የዚያን ጊዜ በዓሉን እንደ ክርስቲያን ሁሉም ሰው በግሉ ያከብራል። በደብረ ኤልያስ የሚኖረው ግን ደግሶ ያበላል። ዓመቱን ሙሉ ያላገኘውን ዘመዱን፣ እሸት ያመጣለትን ወዳጁን እና በገጠሩ ያለውን የሚቀርበውን ሰው እንደ አቅሙ ደግሶ ያበላል ያጠጣል። የኔቢጤው ሁሉ ከወትሮው በተለየ ይዘከራል፣ ሳንቲምም እህል ውሃም የብዙ ቀን ያገኛል። ይሄ እንግዲህ በዓሉ ሰበብ ተደርጎ የሚደረግ የጽድቅ ስራ ነው። ዘመዱን መጥራቱ ደግሞ ዝምድናውን ሸብ አርጎ ለመያዝ ይጠቅማል። ኤልያስ እየኖረ የታህሳስ ያልጠራ ዘመድ ቅያሜ አለበት። ሌላውም "ምነ ለአገራችሁ ዓመት በዓል ሳትጠሩኝ?" ብሎ ያገምጣል፤ ያኮርፋል።

ከዚህም የምንረዳው ማህበረሰቡ የተራራቀውን ዘመዱን እና ወዳጁን ለማቅረብ በዓሉን ተከትሎ ግብዣ እንደሚያደርግ እና በዚህም ዝምድናውን እንደሚያጠናክር ነው። በዚህ ክዋኔ ውስጥ ድግሱ እንደ ዝምድና ማጠንከሪያ የሚያገለግል፣ ለነዳያን በሚደረገው ስጦታ ደግሞ ጽድቅን ለማግኘት እና የመረዳዳት ባህልን ለማጠናከር ጠቃሚ እሴት መሆኑን እንረዳለን። በተጨማሪም ከዚህ በፊት የጠራውን እና የተለያዩ ስጦታዎችን ለምሳሌ፦ እሸት ያመጣለትን ዘመድ ውለታ የሚመልስበት የስጦታ ዓይነት እንደሆነ እንረዳለን።

✓ አባ ፈቂህ መታሰቢያ በዓል ሰጦታዎች

የአባ ፈቂህ ክብረ በዓል በተጠኘው ማህበረሰብ ውስጥ የእስልምና እምነት ተከታዮች በየ ዓመቱ ጥቅምት 16 ድብዳቢ በሚባለው ቀበሌ አካባቢ በሚገኘው የመቃብር ስፍራ በመገኘት የሚያከብሩት ዓመታዊ የመታሰቢያ በዓል ነው። በዚህ ክብረ በዓል በብዛት የግብዣ እና የስዕለት ስርዓቶች ይፈጸማሉ። ይህን አስመልክቶ ሼህ እስሚ (ቃለመጠይቅ፣ 18/08/2013 ዓ.ም፣ደ/ኤልያስ) የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተውኛል።

> አባ ፊቂህ በታሪካቸው ከጎንደር ከመጡ በኋላ በደብረ ኤልያስ ወረዳ ድብዳቢ በተባለው አካባቢ ይኖሩ እንደነበር ይነገራል። እዚያ ሲኖሩ ብዙ ተአምር ያረጉ ነበር። ለምሳሌ በገብያ ወቅት ሰይጣን በመንገዳቸው እየገባ እንዳይገበያዩ የአካባቢውን ሰዎች ብዙ ያስቸግር ነበር እና እሳቸው ሁለተኛ እንዳይደርስ አርገው አባረውታል … እና አባ ፊቂህ እዚህ አካባቢ ኖረው ጥቅምት 16 ቀን ወደ አላህ ተጠርተዋል። የመቃብር ስፍራቸውም በአሁኑ ሰዓት እዚያው ድብዳቢ ይገኛል። በወረዳው ሙስሊም የሚኖረው በድብዳቢ የተወሰኑ ሰዎች እና በደብረ ኤልያስ ከተማ ውስጥ እስላምዬ መንደር ነው። አሁን የደብረ ኤልያስ ሙስሊም 'አባ ፊቂህን' እያለ ሲምል ከሩቅ ያስታውቃል። ስለ እሳቸው ዝና የሚያውቁ ሁሉ በየዓመቱ በቦታው በመገኘት በዓሉን ያከብራል። እሳቸውም ብዙ ተዓምር ያረጋሉ። ለበዓሉም በስለት የሚመጣው የሚታረደው ፍየል እና በግ፣ ገንዘቡ ለጉድ ነው። እና የመጣው የስዕለት ገንዘብ ተጠራቅሞ በየዓመቱ ለበዓሉ ማክበሪያ ይውላል። በበዓሉ የመጣው በግና ፍየል ታርዶ ደሙን በግንባር ይቀባል። ሥጋውም እዚያው እየተበላ ዱአ ይደረጋል። እና በበዓሉ ሙስሊሙ ብቻ ሳይሆን ክርስቲያኑም በንግድ ይሳተፋል እና አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ያልወለዱ ሴቶችም ስዕለት ተስለው የመቃብር አፈራቸውን ወስደው ይወልዳሉ። ስዕለታቸውን ያመጣሉ። ለክርስቲያኑም ለብቻው በግ ወይ ፍየል አርዶ እንዲበላ ይሰጠዋል። ከመጣው ህዝብ ጋር አብሮ በዓሉ ይከበራል።

በሼህ እስሚ ምላሽ ውስጥ የአባ ፊቂህ መታሰቢያ በዓልን ለማክበር በስዕለት መልኩ የሚመጡ የተለያዩ ስጦታዎች እንዳሉ እና የሙስሊሙ ማህበረሰብ በዓሉን ለማክበር የበግ እና የፍየል ስጦታዎች የማቅረብ እና የቀረበውን መስዋዕት ደም የመቀባት ልማድ እንዳላቸው ለመረዳት ችለናል። በዚህ ክዋኔ ውስጥ በአባ ፊቂህ ስም የተሰበሰቡ ሙስሊሞች ለክርስቲያኖችም የበግ እና የፍየል ስጦታዎችን እንደሚሰጡና በዓሉን በጋራ እንደሚያከብሩ ተረድተናል። በዚህ በዓል ሙስሊሞች ለክርስቲያኖች የሚያቀርቡት ስጦታ የሃይማኖት እና የማንነት ልዩነቶች ሳይመለከቱ ማህበረሰቡ እርስበርስ የማቀራረብ እና ማህበራዊ ግንኙነትን የማጠንከር እንዲሁም የማስቀጠል ሚና እንደሚጫወቱ እንረዳለን።

### 5.3 በመከራ ስርዓተ ከበራ ውስጥ የሚገኙ ስጦታዎች

- ✓ የደም ግብር

በማህበረሰቡ ዘንድ ወቅቶች በተፈራረቁ ቁጥር ከሃገረሰባዊ እምነቶች ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ የደም ግብሮች አሉ፡፡ ከእነዚህም ውስጥ አንዱ በአካባቢው አነጋገር "ፍራጅ" ማድረግ ነው፡፡ ፍራጅ ማለት ድንገት ከሚመጣ አደጋ ለመጠበቅ የሚቀርብ የደም መስዋዕት ነው፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ ፍራጅ ከተደረገ ወይም ደም ከፈሰሰ ከአደጋ እንጠበቃለን፣ ካልተደረገ ደግሞ ችግር ይፈጠርብናል በሚል እምነት ወቅቱን ጠብቀው የደም ግብር የማቅረብ ልማድ አላቸው፡፡ ይህን አስመልክቶ አቶ ምትኩ (ቃለመጠይቅ፣ 21/08/2013 ዓ.ም፣ደ/ኤልያስ) ፍራጅ የሚቀርብበትን ወቅት እና ምክንያት እንደሚከተለው ምላሽ ሰጥተውኛል፡፡

> …በእኛ ዘንድ ጥቅምትን ህዳርን እና ሰኔን ጠብቆ ፍራጅ ይደረጋል፡፡ የጥቅምቱ ፍራጅ ለምንጩ ነው፡፡ በጋው ሲመጣ ምንጩ እንዳይደርቅ እኛ እና ከብቶቻችን የምንጠጣው እንዳናጣ እወንዙ ዳር የምንጭ ፍራጅ በግ ይታረዳል፡፡ …በህዳር እና በሰኔ ደሞ የከብት ፍራጅ ይባላል፡፡ ለእርሱም እንዲሁ ለከብቱ ይበጃል ተብሎ በግ ይታረዳል፡፡ …የሚታረደው በግ ጥቁር ያልሆነ፤ ቀይ ወይም ነጭ ቀለም ያለው ነው፡፡ የፍራጁ ቀን የታለበ ትኩስ ወተት በቅል ተደርጎ እንደገና እንጀራ እና ድቁስ (በርበሬ) ይዘጋጃል፡፡ እና የሀገሬው ሰው (ወንዱ) ተሰብስቦ ከብቱን በአንድ ያግድና ለፍራጁ የሚሆነው በግ ቀርቦ ታርዶ ደሙ በእቃ ተደርጎ ከመጣው ወተት ጋር ተቀላቅሎ ለከብቱ ይረጫል፡፡ ስጋውም ከመጣው እህልና ውሃ ጋር እዚያው ይበላል፡፡ እንዲህ የሚደረገው ላሚቷ እንድትወልድ … እንድትከብድ እና ወተት እንድትሰጥ ከብቱ ሁሉ ከበሽታ እንዲጠበቅ ነው፡፡ አሁን አሁን ንብ ማነቡ እየቀረ ሲመጣ እንጂ የንብ ቀፎ ያላቸው ሰዎች ንቡ እንዲገባ፣ ማር እንዲገኝ ተብሎ የንብ ፍራጅ እንደ አቅሚ ዶሮ ከጳጉሜ እስከ መስከረም 5 ባለው ቀን ይታረዳል፡፡ ያንን ደም በለመደበት ጊዜ ፍራጁ ይደረጋል፡፡ እንዲያ ካልተደረገ ደግሞ ከብት ይታመማል፣ ምርት ይቀንሳል፣ ላሞች ይነጥፋሉ፣ 'አዋይ ይቆጣል' ይባላል፡፡

በዚህም ክዋኔ ውስጥ ማህበረሰቡ አሉ ብሎ ከሚያምናቸው መናፍስት ጋር ያለውን ግንኙነት ላለማሻከር ወይም ለማለሳለስ ስጦታ እንደሚያቀርብ እንረዳለን፡፡ ይህ ክዋኔ በኦሪት ዘመን የተፈጸመ አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ጋር ይቀራረባል፡፡ ታሪኩም እስራኤላውያን በግብጽ ባርነት በነበሩበት ዘመን የግብጽ ንጉሥ (ፈርኦን) የእስራኤልን ህዝብ አለቅም ብሎ ነበር፡፡ እግዚአብሔርም የንጉሡን እንቢተኛነት አይቶ ብዙ መቅሰፍቶችን አመጣበት፡፡ ኦሪት ዘጸአት (12፥1-13) ስናነብ የደም መስዋዕቱን ታሪክ እናገኘዋለን፡፡

> እግዚአብሔርም በግብጽ አገር ሙሴንና አሮንን እንዲህ ብሎ ተናገራቸው፦ ይህ ወር የወሮች መጀመሪያ ይሁናችሁ የዓመቱም መጀመሪያ ወር ይሁናችሁ። ለእስራኤል ልጆች ኹሉ ተናገሩ በሏቸውም፦ በዚህ ወር በዐሥረኛው ቀን ሰው ሁሉ ለአባቱ ቤት አንድ ጠቦት ላንድ ቤትም አንድ ጠቦት ይውሰድ። የቤቱ ሰዎች ቍጥርም ለጠቦቱ የማይበቃ ቢሆን ርሱና ለቤቱ የቀረበው ጎረቤቱ እንደ ነፍሶቻቸው ቍጥር አንድ ጠቦት ይውሰድ እያንዳንዱም እንደሚበላው መጠን ከጠቦቱ ይካፈሉ። የእናንተ ጠቦት ነውር የሌለበት የአንድ ዓመት ተባት ይኹን ከበጎች ወይም ከፍየሎች ውሰድ። በዚህም ወር እስከ ዐሥራ አራተኛው ቀን ድረስ ጠብቁት የእስራኤልም ማኅበር ጉባኤ ሁሉ ሲመሽ ይረዱት። ከደሙም ወስደው በሚበሉበት ቤት ሁለቱን መቃንና ጉበኑን ይቅቡት። ...እኔም በዚያች ሌሊት በግብጽ አገር አልፋለሁ በግብጽም አገር ከሰው እስከ እንስሳ ድረስ በኵርን ሁሉ እገድላለሁ በግብጽም አማልክት ሁሉ ላይ እፈርድባቸዋለሁ እኔ እግዚአብሔር ነኝ። ደሙም ባላችሁበት ቤቶች ምልክት ይሆንላችኋል። ደሙንም ባየኹ ጊዜ ከእናንተ አልፋለሁ እኔም የግብጽን አገር በመታሁ ጊዜ መቅሠፍቱ ለጥፋት አይመጣባችሁም።

የመጽሐፍ ቅዱሱን ታሪክ ስንጨርሰው ፈጣሪ ባዘዛቸው መሰረት በጉን አርደው ደሙን በመቃን እና በጉበናቸው በመቀባታቸው ምክንያት በግብጻውያን ላይ የደረሰው የበኩር ልጅ እና እንስሳ ሞት ሲድኑ እናነባለን። ኢትዮጵያውያን በታሪክ ከክርስትና በፊት በንግስተሳባ አማካኝነት ኦሪትን ተቀብላ ነበር። የኦሪት መስዋዕት ይቀርብባቸው የነበሩ ቦታዎችም ከጥንታዊ አብያተ ክርስቲያናት ጋር አሁንም ድረስ ይጎበኛሉ። ስለዚህ በተጠኘው ማህበረሰብ አካባቢ የሚደረገው የደም ስጦታ ልማዶችም መነሻቸው ይህ ሊሆን የሚችልበት መንገድ ሰፊ እንደሆነ የስጦታ አከዋወኑ ያስረዳል። ከሚቀርቡት ፍራጆች (የደም ስጦታዎች) መካከል ለምሳሌ፦ በከብት ፍራጅ ወቅት በጉ ይታረድና ደሙ ይፈሳል። የቀረው ደም እንዲሁም ወተት ተቀላቅሎ ከብቱ ሁሉ ይረጫል። ይህ ክዋኔ ደግሞ ከአልታሰበ አደጋ እና ከመናፍስት "አዋይ ቁጣ ያድናል" ተብሎ ይታመናል። በአጠቃላይ ማህበረሰቡ በግብርና የሚተዳደር በመሆኑ ከኑሮው ጋር በተያያዘ የሚጠጣው ውሃ፣ የሚያሳድጋቸው ከብቶች እና የሚያረባቸው ንቦች የሚፈልገውን አይነት ውጤት እንዲሰጡት እንዲሁም ድንገተኛ አደጋ እንዳይከሰትባቸው በሚል የሚከውናቸው እርዶች ወይም ከመናፍስት ጋር ላለመጣላት የሚያቀርባቸው የደም ስጦታዎች ከአማልክት ጋር

ያለን ግንኙነት የማጥበቅ እና የማለሳለስ ሚና እንዳላቸው በማመን እንደሚከውናቸው እንረዳለን።

✓ ጉችማ (የቅስፈት ቅል) እና የቡቅር ስጦታዎች

ጉችማ ማለት በማህበረሰቡ ዘንድ የተነጠረ ቅቤ ወይም በጨው እና በውሃ የተንተከተከ በርበሬ (ድቁስ) የሚቀመጥበት ከቅል የሚሰራ ባህላዊ መገልገያ ቁስ ነው። ቡቅር ደግሞ ከብቅል እና ከጤፍ ቂጣ ብቻ የሚዘጋጅ ባህላዊ መጠጥ ነው። በማህበረሰቡ ባህል ውስጥ ለአዲስ ዓመት እና ለገና በቂቤው ጉችማ አዲስ የነጠረ ቂቤ፣ በድቁሱ ጉችማ አዲስ የተዘጋጀ ድቁስ ፣ በቅል ማር እና አሞሌ ጨው ለብቻው ተሰቅሎ መቀመጥ እንዲሁም በጋን ደግሞ ጌሾ፣ እንኩሮ እና ደረቆት ያልገባበት ከብቅል እና ከቂጣ የተዘጋጀ ድፍድፍ መቀመጥ አለበት አለበለዚያ ግን መናፍስት "አዋይ" ወይም የእናት የአባት አምላክ (ቆሌ ) ይቆጣል አደጋም ይደርስብናል የሚል አስተሳሰብ አላቸው። የተዘጋጀው ጉችማ "የቅስፈት ቅል" ጋኑም "የቆሌ ጋን" የሚል ስያሜ ተሰጥቶት ጉችማው በቤት ምሰሶ ላይ ይንጠለጠላል ጋኑም ቦታ ተለይቶለት ይቀመጣል ። የሰቀሉትን ማር፣ አሞሌ ጨው፣ ቂቤ እና ድቁስ እንዲሁም የደፈደፉትን ቡቅር "አዋይ" ፣ "ቆሌ" ፣ "የአባት አምላክ" እያሉ ለሚጠሩት አካል ለበዓል  እንዳቀረቡት መስዋዕት ወይም ስጦታ ይቆጥሩታል። ይህንን ሀገረሰባዊ እምነት በተመለከተ  ወይዘሮ ዝይን (ቃለመጠይቅ፣ 16/09/2013 ዓ.ም) ያለውን እሳቤ እንደሚከተለው ያስረዳሉ።

> … በእኛ አካባቢ ጋን ወይም ጉችማ የሌለው ሴት የለም መቼስ …ከሁሉ ቀን ለዓውዳመት ሲሞሉት ደስ ይላል። አንዳንድ ሰው ግን ከእናት ከአባት የመጣ አምልኮ ያለበት አለ። እና ከዘወትር ምግቡ ለይቶ ለአባት አምላክ ለቆሌ እያለ ለይቶ ያስቀምጣል። እና የእንቁጣጣሽ ፣የገና ፣ የፋሲካ ፣ የህዳር ሚካኤል፣  የጥር ሚካኤል እና የሰኔ ሚካኤል ብቻ ያ የቅስፈት ቅል (ጉችማ) ከተሰቀለበት ወርዶ ጋኑም ተከፍቶ ይቀመሳል። ያውም የሚቀምሰው የወለደ (በጋብቻ ተዛምዶ የወለደ ምራት ወይ አማች) እና ዘመድ ብቻ ነው። እንጂ ሌላ ቀን ከዘወትር ጉችማ እና ጋን ነው የሚበላው የሚጠጣው። እማወራ ወይ ልጅ ካልሆነ በቀር  ቅሉን እና ጋኑን መንካትና መክፈት እንዲሁም መጨመር አይችልም። ግም ነው (መጥፎ ነው)። በዚያ ላይ ሁልዜ የቻለ ተዓመት ሁለት ጊዜ የእንቁጣጣሽ እና የገና ጉችማው ወርዶ እንደገና በአዲስ ማር፣ በአዲስ ቂቤ፣ በአዲስ ድቁስ እና አሞሌ ጨው ይተካል። ጋኑም ያለው ተሚጦ አዲስ ይጠነሰስበታል። ያልቻለ ግን በእንቁጣጣሽ ማደስ አለበት። የዚያን ጊዜ አደጋ ሊያደርስ

የመጣው አዋይ የተሰቀለለትን ጉችማ እና የተቀመጠለትን ጋን ባዶ ሆኖ ማግኘት የለበትም፣ ያስለመደ ሰው ማስቀረትም አይገባውም፡፡ ምክንያቱም አዋይ በመሿሚያው ቀን ሲዘዋወር በጋኑ፣ በጉችማው ሲያገኝበት ያንን ቀምሶ ይሄዳል፡፡ ሲያጣበት ግን ተናዶ ቤተሰብ ይጎዳል፣ ጤና ይታጣል፣ ሀብት ንብረት ይጠፋል፣ እህል በረከት አይኖረውም ይባላል፡፡

ከምላሹ እንደምንረዳው ማህበረሰቡ "አዋይ" ብለው ለሚጠሩት አካል ለብቻው ቅል እና ጋን በማዘጋጀት የተለያዩ ስጦታዎች እንደሚያስቀምጡበት ነው፡፡ እነዚህ የስጦታ ማስቀመጫ እቃዎች “የቅስፈት ቅል (ጉችማ)” እና “የቆሌ ጋን” የሚል ስያሜ አላቸው፡፡ ከስያሜው እንደምንረዳው ቅሉ “የቅስፈት ቅል” የተባለበትን ምክንያት ከቤቱ ባለቤት በቀር ሌላ ሰው ከነካው አሊያም ባዶውን ካገኘው ተቀባዩን እንደሚያስቆጣው እና እንደሚያስቀስፈው ስለሚታሰብ መሆኑን፤ ጋኑም “የቆሌ ጋን” የተባለበት ምክንያት ቆሌ ለሚሉት አካል ስጦታ ማስቀመጫ ቢቻ ስለሚያገለግል መሆኑን በቃለመጠይቁ ውስጥ እንረዳለን፡፡ ማህበረሰቦቹ ለቆሌ (ለአዋይ) ብለው ባዘጋጁቸው ሦስት ቅሎች ቂቤ፣ማር እና ድቁስ እንዲሁም አሞሌ ጨው በጋን ደግሞ ድፍድፍ አድርገው በዓመት ሁለት ጊዜ "አዋይ" ለሚሉት አካል ስጦታ የመስጠት ልማድ አላቸው፡፡ ይህ ስጦታ ያለውን ደንብም በዝርዝር ስንመለከት፦ የመጀመሪያው ህግ "የቅስፈት ቅሉ" እና "የቆሌ ጋኑ"  የሚከፈትባቸው ቀናቶች የተመረጡ ናቸው፡፡ እነርሱም (እንቁጣጣሽ፣ ገና፣ ፋሲካ፣ ህዳር ሚካኤል፣ ጥር ሚካኤል፣ ሰኔ ሚካኤል ሲሆኑ እነዚህም ቀናቱ የተመረጡበት ምክንያት  "በእነዚህ ቀኖች ነው "አዋይ" "ቆሌ" የሚነግሰው ወይም ቤቱን የሚጎበኘው" ተብሎ ስለሚታሰብ መሆኑን በቃለመጠይቅ ወቅት ለመረዳት ተችሏል፡፡ የሚቀርበውን ስጦታ በተመለከተ ለምን ቂቤ፣በርበሬ፣ማር እና አሞሌ ጨው ተመረጠ ከመጠጥስ ቡቅር ለምን ሆነ ለሚለው ጥያቄ " አዋይ ስለሚወደው እንዲቀምሰው ነው" የሚል ምላሽ ለማግኘት ችያለሁ፡፡ ነገር ግን እነዚህ ምግቦች በጥንቃቄ ከተያዙ ዓመቱን ሙሉ ሳይበላሹ ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ መሆናቸውም እንደ ተጨማሪ ምክንያት ሊጠቀስ ይችላል፡፡ በተመረጡት ቀናት ለአዋይ ተብሎ የተቀመጠውን ነገር ቤተሰቡ ሲቀምስ አብሮ ይቀምሳል ተብሎ ይታሰባል፡፡ ሁለተኛው ህግ የተቀመጠውን ቂቤ፣ድቁስ እና ማር እንዲሁም ድፍድፍ መክፈትም ሆነ መቅመስ የሚችለው የቤተሰቡ አባል ብቻ ነው፡፡ እንዲያ ካልሆነ ግን ቅስፈት ይመጣል ተብሎ ይታሰባል፡፡ ሦስተኛው እና ዋነኛው ህግ አዋይ የለመደው ስጦታ በተለመደው ቀን በጭራሽ መቅረት የለበትም የሚል ነው፡፡ ይህም የሚደረገው ከመናፍስት ቁጣ ለመሸሽ

ሲባል እንደሆነ ተረድተናል። በዚህም ክዋኔ ውስጥ ማህበረሰቦቹ ስጦታን በረከት እና ጤና ለማግኘት እና በረቂቅ መናፍስት ቁጣ ምክንያት ይመጣሉ ብለው ከሚያስቧቸው አደጋዎች ለመጠበቅ ጭምር እንደሚከውኑት እንረዳለን።

✓ በሶ መርጨት ወይም መበተን

ይህም ልማድ አዲስ ዓመትን፣ ህዳር ሚካኤልን እና ሰኔ ሚካኤልን ተከትሎ የሚከዎን ነው። በምልከታ እና በቃለ መጠይቅ ወቅት ለማረጋገጥ እንደሞከርሁት በተጠኛው አካባቢ አብዛኛው ማህበረሰብ በእነዚህ ቀናቶች በሶ ያስፈጫል። የተዘጋጀው በሶም  የበዓሉ ቀን በቅስፈት ቅል በተቀመጠው ቂቤ ተንፈርፍሮ ይበላል። ነገር ግን ከመቀመሱ በፊት ከተንፈረፈረው በሶ እየተነሳ ወደመሬት በአራቱም አቅጣጫ "ማረኝ(ን) የአባቴ የእናቴ አምላክ እየተባለ የመበተን ወይም ስጦታ የማቅረብ ልምድ እናገኛለን። ይህንንም የተበተነ በሶ ለአዋይ ተሰጠ ተብሎ ይታመናል። በተጨማሪም  በእነዚህ ቀናት በሶ ካልዞረበት፣ የለመደው ከቀረ ችግር ይገጥመናል የሚል እምነት አላቸው። ይህ ስጦታ የሚከወንበትን ምክንያት ወይዘሮ ዝይን (ቃለመጠይቅ 16/09/2013ዓ.ም፣ ደ/ኤልያስ) "የእንቁጣጣሽ፣ የህዳር እና የሰኔ ሚካኤል በቤቱ በሶ ካልዞረበት በሽታ ይገባል። ከበሶው ሲቀምሱም መጀመሪያ ማረኝ እያሉ ማቅመስ ተለምዷል። ምነ መማጠኛ ነው። ለሰው እንኳን ይኼን አርግልኝ ተብሎ እጅ መንሻ ይሰጣል።" በማለት መልሰውልኛል። ከዚህም የምንረዳው ማህበረሰቡ ለረቂቅ መናፍስት ስጦታ በመስጠት ምህረት እና ይቅርታ የሚጠይቁ ሲሆን በዚህም ስጦታን እንደ መተያያ ወይም ፍላጎትን ለመሟላት እንደ እጅመንሻ የመጠቀም ልማድ እንዳላቸው ነው።

## 5.4 የቁርባን እና ልውውጥ ስጦታዎች

✓ ቁርባን

ቁርባን ቃሉ የሱርስት ቃል ሲሆን ትርጉሙም ያለ ዋጋ በነጻ የሚቀርብ መባ ፣ አምሀ ወይም እጅ መንሻ ማለት እንደሆነ የሺጥላ (2011፣1) ይገልጻሉ። ከዚህም ቀጥሎ በብሉይ ኪዳን ዘመን እስራኤላውያን ስለ ኃጢያታቸው ሆነ ስለ እግዘብሔርን ክብር ብለው የሚያቀርቡት የእንስሳት ደም ቁርባን ይባል እንደነበር ገልጸው በሐዲስ ኪዳን ግን ቁርባን ማለት እግዚአብሔር ራሱን ከሰው ልጆች ጋር ለማስታረቅ መባ አድርጎ ያቀረበው አማናዊው መስዋዕት ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆነ በአጠቃላይ በክርስትና ህግ ቁርባን ማለት የሐዲስ ኪዳኑ በግ የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋ እና ደም መሆኑን ያስረዳሉ። (ማቴ 26፥ 27)

በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት ውስጥ የቁርባን ስርዓት ይደረጋል፡፡ በተጠኘው ማህበረሰብ ዘንድም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሃይማኖቱን ህግጋት በማክበር እና የቁርባን ስርዓቱን በመካፈል የጌታን ሥጋ እና ደም ይቀበላሉ፡፡ ይህም ፈጣሪ በሁሉም እድሜ እና ጾታ ውስጥ ላሉ የወንጌል ልጆች ያለ ዋጋ የሰጠው ትልቅ ስጦታ እንደሆነ እና በዚህም ስጦታ ዘላለማዊ ድህነት፣ ከፈጣሪ ጋር አንድነት ይኖረናል፤ በሥጋው እና ደሙ እንማጸንበታለን፣ ኃጢያታችን ይሰረይበታል ብለው ያምናሉ፡፡ በማህበረሰቡ ልማድ ውስጥ ለቆራቢ የሚሰጠው ማህበራዊ ደረጃ ከፍ ያለ ሲሆን ለምሳሌ፦ በዓለማዊ ጋብቻ ውስጥ ይኖሩ የነበሩ ሰዎች ለቁርባን የሚያስፈልገውን ቅድመ ዝግጅት አድርገው ሲቆርቡ ትልቅ ድግስ ይደረጋል፡፡ ይህንን ልማድ አስመልክቶ አቶ ዋለ (ቃለ መጠይቅ 09/08/2013ዓ.ም፣ደ/ኤልያስ) የሚከተለውን ምላሽ ያቀርባሉ፡፡

> እንግዲህ ሰው ፍጹም አይደለምና በወጣትነት ጉልበት ሳለ ምኑም ምኑም ውስጥ ይገባል፡፡ በእኛ አካባቢ ባህል ደግሞ የቤተክርስቲያን አገልጋይ ዲያቆን ካልሆነ ጋብቻውም በቤተክርስቲያን ስርአት አይፈጸምለትም፡፡ እንደ ባህሉ ቤተሰብ ተጠይቆ እንዲያ ተብሎ ነው፡፡ መቼም ፈጣሪ ሁልጊዜም እንዲቀርቡት ይፈልጋልና ብዙ ይታገሳል፡፡ ሰው እድሜው ሲጨምርም ወደ እግዚአብሔር መሄድ መቅረብ ሲጀምር ንስሃ ገብቶ ከባለቤቱ ጋር ይቆርባል፡፡ የዚያን ጊዜ በሰማይም የፈጣሪ እና የመላእክት ደስታ ነው፡፡ በታች በመሬት ደግሞ  የቆራቢዎቹ፣  የወለዷቸው ልጆች፣ የጎረቤት የዘመዱ ሁሉ ደስታ ስለሆነ ድግስ ይደገሳል፣ ልጆቻቸው አቆልቋይ ይይዛሉ፣ ጎረቤት ሁሉ 'ጸበል ቅመሱ' እየተባለ ይጠራል፡፡ ለቆረቡት ባልና ሚስትም ነጭ ሻሽ፣ልብስ ከሌለም አረቄ ተይዞ ይሄዳል፡፡ የተጠራው ሰውም ያንን ግብዣ የደስደስ ተጋብዞ 'የጽድቅ ያድርግላችሁ' እና 'ለቆብ ያብቃችሁ' እያለ መርቆ ይሄዳል፡፡ ከዚያ በኋላ ያለው ክብርም ይጨምራል፡፡ ወንዱ አባ እገሌ ሴቲቱ እማ እገሌ ትባላለች፡፡ በማለት ያስረዳሉ፡፡

ከዚህም ምላሽ ማህበረሰቡ የፈጣሪ ስጦታ ነው ብሎ የሚያምነውን ቅዱስ ቁርባን ህጉን ጠብቆ በመቀበል ያለውን የክብር እና የሚፈጥረውን የደስታ ስሜት እንረዳለን፡፡ በተጨማሪም እግዚአብሔር ለሰው ልጆች መስጠትን ያስተማረው አንድያ ልጁን በመስጠት እንደሆነ እና ይህንንም አብነት በማድረግ በምላሹ ለፈጣሪ ፍጹም ፍቅርን፣ ተገዥነትን፣ አክብሮትን ወዘተ. በማሳየት የቁርባን ስርዓት እንደሚያደርጉ ወይም የፈጣሪን ስጋ እና ደም እንደሚቀበሉ ተረጋግጧል፡፡ ቁርባን በሁሉም ማህበራዊ ወይም ኢኮኖሚያዊ ደረጃ ያለ፣ በሁሉም እድሜ ላይ

የሚገኝ እና የእምነቱ ተከታይ የሆነ ማንኛውም ሰው ያለ አድሎ የሚቀበለው ስጦታ ሲሆን። ባለው ስርዓት እና ህግ የቤተክርስቲያኒቱን አማኞች አንድነት የሚያጠናክር፣ እንደ አንድ አካል ፣ አንድ ህብረት የማድረግ ሚና ያለው የስጦታ ዓይነት መሆኑ ተረጋግጧል።

✓ ስዕለት

ስዕለት ስለ አንድ ጉዳይ መሳካት አብዛኛውን ጊዜ ከሰው በላይ ከሆኑ አማልእክት እንዲሁም ከፈጣሪ እርዳታ መጠየቅ እና ጉዳዩ እንዲፈጸም በምላሹ ጊዜ ጠቅሶ "እንዲህ እሰጣለሁ " "እንዲህ አደርጋለሁ" ብሎ ቃል መግባትን ይመለከታል። ጥናት በተደረገበት የደብረ ኤልያስ ከተማ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት ተከታዮችም ሆነ የሙስሊሙ ማህበረሰቦች ስዕለት የማድረግ ልማድ አላቸው። የሚቀርበውም ስዕለት በዓይነት እና በተግባር የሚገለጽ ሆኖ እናገኘዋለን። ማህበረሰቦቹ እለት ተእለት ባላቸው ገጠመኝ እና የህይወት ውጣውረድ ውስጥ እርዳታ ሲያስፈልጋቸው ወደ ፈጣሪ ወይም ፈጣሪ ወደመረጣቸው ቅዱሳን በመቅረብ ችግራቸው እንዲፈታ ይጸልያሉ የገጠማቸው ችግር ሲቀረፍላቸው ደግሞ ለፈጣሪ ስጦታ አመጣለሁ በማለት ቃል ኪዳን ይገባሉ። ከተጠኝዎች ውስጥ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ አማኞች በስዕለት ወቅት የሚያቀርቡትን ስጦታ በተመለከተ ቄስ ላመስግን (ቃለ መጠይቅ 14/08/2013ዓ.ም፣ ደ/ኤልያስ) እንደሚከተለው ይገልጻሉ።

> እግዚአብሔር ሁሌም ከእኛ ተለይቶ ስለማያውቅ ሰው በማንኛውም ጊዜ ስዕለት መሳል ይችላል፤ ይሰማልም። … በእኛ አካባቢ ለስዕለት የተለያዩ ዓይነት ስጦታዎች ይቀርባሉ። ይኸውም ሰው እንደ አቅሙ ስለሚሳል እና የስጦታ ትንሽ ስለሌለው ነው። እንግዲህ ገበሬው ከስንዴው ቆንጥሮ ያመጣል፣ ነጋዴው ደግሞ ከገንዘቡ ይሰጣል፣ ሌላው ሰውም የወርቅ ጥላ፣ መብራት፣ እጣን፣ ዘቢብ፣ መጋረጃ ይሰጣል። አሁን በደብረ ኤልያስ ከተማ በደንብ የሚታወቀው ልጅ ለመውለድ እንቢ ያለው ሰው በነብዩ ኤልያስ ቤተክርስቲያን ውስጥ የምትገኘውን የሙሽራ ድንጋይ ተሸክሞ ቤተክርስቲያኑን እየዞረ ለነብዩ ይሳላል። ብዙ እናቶችም ልጅ ተሸክመው መጥተው ስዕለታቸውን ያስገባሉ። የስዕለት ልጃቸውን ለቤተክርስቲያን አገልጋይ እንዲሆን የሚሰጡም አሉ። ይህ ልማድም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው። መካኒቱ ሀና ሳሙኤልን የሚያህል ነብይ በስዕለት ወልዳ ለእግዚአብሔር ቤት እንዲያገለግል እንደሰጠች፣ እመቤታችንም ተመሳሳይ ታሪክ አላት። በስዕለት ተወልዳ ላም ለቤተክርስቲጣን ነው የተሰጠችው። እና የስጦታው አይነት ብዙ

ነው። ብቻ ስዕለት እግዚአብሔር ለዋለለት ውለታ ምስጋና ማቅረቢያ እና እጅ መንሻ ነው እንጂ ሰው እንዳለው አቅም ነው የሚሰጠው።

በማህበረሰቡ ዘንድ ባህሉን እና ሃይማኖቱን ተከትሎ የሚሳላቸውን ስዕለቶች የመክፈል ግዴታ አለበት። ይህን አስመልክቶ ቄስ ላመስግን (ቃለ መጠይቅ፣ 14/08/2013 ዓ.ም፣ደ/ኤልያስ) "እግዚአብሔር ያለ ስዕለት ያለ ልመና ራሱ አስቦ የሚያስፈልገንን ያደርግልናል። አምላክን የጠየቅነው ነገር የሚጠቅመን ወይ የሚጎዳን መሆኑን እርሱ ስለሚያውቅ ይፈጽምልናል ወይም አይፈጽምልንም። ነገር ግን በራሳችን ፈቃድ የተሳልነውን ስዕለት ተናግረን ማስቀረት ኃጢያት እና እግዜርን ቃል መብላት ነው።" በማለት ስዕለት በቃል መሰረት የሚፈጸም ስጦታ መሆኑን ይገልጻሉ። በዚህም ምላሽ ውስጥ የምንረዳው የክርስቲያኑ ማህበረሰብ በኑሮው ውስጥ የሚገጥሙትን ልዩ ልዩ  ችግሮች ለመፍታት መጸለይ እና ስዕለት መሳል( ለፈጣሪ ስጦታ ለመስጠት ቃል መግባት) መፍትሔ አድርጎ የመጠቀም ልማድ እንዳለው ነው። በክርስቲያኑ ማህበረሰብ ዘንድ ስዕለት በሁለት ዓይነት መንገድ ሲፈጸም እንመለከታለን። ይኸውም ምስጢራዊ እና ይፋዊ በሆነ መንገድ ነው። ስዕለት ሚስጢራዊ የሚደረገው አብዛኛውን ጊዜ ሰጪው እንዲህ አደረገ ወይም ይኼን ሰጠ ተብሎ በሰዎች ፊት እንዳይመሰገን ፣ የስጦታውን ዋጋ በወዲያኛው ዓለም ለማስቀመጥ እና በምድራዊ ህይወቱ እንዳይታበይ የሚሉ ምክንያቶች ይጠቀሳሉ። ሌላው ምክንያት ደግሞ የሰጪው ምክንያት ግላዊ ምስጢር ሲሆን ነው። በተጠኚው ማህበረሰብ አካባቢ ከክርስቲያኑ በተጨማሪ የሙስሊሙም ማህበረሰብ ስዕለት የመሳል ልማድ እንዳለው በአባ ፈቂህ የመታሰቢያ በዓል ላይ በስፋት ለመመልከት ተችሏል። በዚህ ክብረ በዓል ወቅት የተለያዩ ችግሮቻቸውን ለአባ ፈቂህ በመናገር በየዓመቱ የበግ እና የፍየል እንዲሁም የገንዘብ ስጦታ ይወስዳሉ። ይህም አባ ፈቂህ ችግሮቻቸውን ስለፈቱላቸው ምስጋና ለማቅረብ እና የተሳሉት ስለተሰማ ደስታቸውን ለመግለጽ ነው።

## 5.5 በጾም እና ፍስክ ወቅት ያሉ ስጦታዎች

ጾም ለመንፈሳዊነት ብቻ ሳይሆን ማህበራዊ ህይወትን ለማሳደግ ብዙ ጠቀሜታዎች ያሉት ነው። ምክንያቱም በጾም ወቅት ከሌላው በተለየ መልካም ነገር በመስራት የማሳለፍ ሁኔታ ማየት የተለመደ ነገር ነው። ሰዎች በጾም ወቅት በመልካም ሰብእና የመኖር ልማድ ያዳብራሉ፣ ከመልካም ሰብዕና ጋር መልካም ጉርብትና ይፈጠራል። በዚያም መተጋገዝ፣ መረዳዳት አይዞህ አይዞሽ መባባል ይመጣል። በተጠኚው ማህበረሰብ ውስጥ የጾም እና የፍስክ ጊዜያቶች ከሌላው ቀን በተለየ ስጦታ የሚለዋወጡበት ወቅት እንደሆነ መረጃዎች ያመላክታሉ። አብዛኛውን ጊዜ

ግን የፍስክ ጊዚያቶችን ተከትሎ እርስ በእርስ ያለው የስጦታ ልውውጥ ከጾሙ ወቅት በበለጠ ይተገበራል፡፡ ይህን አስመልክቶ አቶ ደምል (ቃለመጠይቅ 08/09/2013 ዓ.ም፣ ደ/ኤልያስ) ምግብ ይዞ ወዳጅን ለመጠየቅ የትኛው ጊዜ ይመረጣል? ለሚለው ጥያቄ

> አኻ ሰው ከጠየቁ አይቀርማ በብላቲቱ (በፍስክ) ነውእንጂ፡፡ የዚያን ጊዜ ወተትም፣ ስጋም እንደልብ ይበላል፡፡ ድግስም በጾም ሲሆን ደስ አይልም፡፡ ምነ ድግስ ደስታ ነው ጾም ደሞ ተአቅቦ ከምግብ መከልከል ነው፡፡ እና እሰው ዘንድ ሲሄዱ በብላት ሲሆን ለጠያቂው ስጋይቱን ወጥ ሰርቶ ሲሄድ ደስ ይለዋል፡፡ ለዚያ እኮነው ለዓመት በዓል ሰውን መጋበዝ ፤ጠያቂም በየሰውቤት መሄድ የለመደው፡፡ ... ግን ግድ ጊዜው ጾምም ከሆነ ለምን ብላት አልሆነም ተብሎ ዘመድ ሳይጠየቅ አይቀርም በማለት ያለውን ልማድ ይገልጻሉ፡፡

በማለት የምግብ ስጦታዎች ከጾም ወቅት ይልቅ በፍስክ ጊዜ ተመራጭ እንደሆኑ እና በማህበረሰቡ ልማድ የምግብ ስጦታዎችን ለመለዋወጥ የፍስክ ምግቦች ቅድሚያ እንሚሰጣቸው ያስረዳሉ፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ በማህበረሰቡ ደንብ ውስጥ ጾም ለመጀመር (ለቅበላ) ወይም ጾም ሲያልቅ (ለፍስክ) የወለደች ላም ያለው ሰው ለጎረቤቶቹ እርጎ አከማችቶ ማግደፊያ ወተት እንደሚሰጥ በምልከታ እና በቃለመጠይቅ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ የማግደፊያ ወተት መስጠትን አስመልክቶ ወይዘሮ ዝይን (ቃለመጠይቅ፣ 16/09/2013 ዓ.ም፣ ደ/ኤልያስ) እንደሚከተለው ያስረዳሉ፡፡

> ጦም በተፈታ ጊዜ የምትሞከር/የምትታልብ/ላም ያለው ሰው ወተቲቱን አጠራቅሞ ማግደፊያ ወተት ቅመሱ ይላል፡፡ ይሄ ለሰውም ለከብቱም ይበጃል፡፡ ምነ ለሰውም ያለው ለሌለው መስጠት በተለይ ዓመት በዓል ሲደርስ ከብት ያለው ሰው ለሌለው ወተት ቅመስ ሲለው ለማህበራዊ ኑሮው ይበጀዋል፡፡ እንዲያው ሞሳም ትሁን እከሌ እኮ ለዓመት በዓል አምሮኝ እንዳይቀር ማርጠቢያ አመጣልኝ ይላል፤ 'ከእርጥብ አይለያችሁ' ብሎ ይመርቃል፡፡ ለሰጪውም ደስ ይለዋል ... በሰው ያስወድደዋል፡፡ ላሚቱንም ሲጦም የሰነበተ ሁሉ ወተቷን ቀምሶ 'ሺ ጥገት ያርጋት' እያለ ሲመርቃት እግዜር ይባርካታል፡፡ በማለት ይገልጻሉ፡፡

በማግደፊያ ስጦታ ውስጥ ሰጪዎች የሚታለብ ወተት ያላቸው ሰዎች ሲሆኑ ስጦታ ተቀባዮች ደግሞ የቅርብ ወዳጆች እና ጎረቤቶች ናቸው ለስጦታ የሚቀርበው ነገርም አብዛኛውን ጊዜ እርጎ እና ትኩስ ወተት ናቸው፡፡ የስጦታው አነሳሽ ምክንያት የጾም መፈታት እና ጉርብትና ሲሆን

በዚህ ክዋኔ ውስጥ ማህበረሰቡ የማግደፊያ ወተት መስጠት ሰጪውን ያስባርካል የሚል እምነት እንዳላቸው በቃለ መጠይቁ ምላሽ ውስጥ ካለው ምርቃት እንረዳለን። ከዚህም ክዋኔ ማህበረሰቡ ስጦታ መስጠት ለመልካም ጉርብትና እና በፈጣሪ ዘንድ ለመባረክ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳለው አስቦ የሚተገብር መሆኑን እንረዳለን።

- ✓ የፍልሰታ ጾም ስጦታዎች

የፍልሰታ ጾም ሐዋርያት የቅድስት ድንግል ማርያምን ትንሳኤ ለማየት እንዲበቁ ሱባኤ ገብተው የጾሙት ሲሆን የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት ተከታዮች ምንጊዜም ከነሐሴ 1 እስከ ነሐሴ 16 ድረስ ከህጻናት ጀምሮ እስከ አዛውንት ድረስ የሚጾሙበት ወቅት ነው። በተጠኚው አካባቢ አብዛኛውን ጊዜ አዋቂዎች ጾሙን ከቅዳሜ እና እሁድ ውጪ ባሉት ቀናት የተፈጨ እህል ባለመመገብ ወይም ጥራጥሬ ብቻ በመብላት በሱባኤ ያሳልፉታል። በምልከታ እና በቃለ መጠይቅ ወቅት እንዳረጋገጥሁት ጾሙን አስመልክቶ የተለያዩ የስጦታ ልማዶችን አስተውያለሁ። እነዚህን ስጦታዎች አስመልክቶ እማሆይ ህብስቴ (ቃለመጠይቅ፣ 21/08/2013 ዓ.ም፣ ደ/ኤልያስ) እንደሚከተለው ይገልጻሉ።

> የፍልሰታ ጦም የሚለየው ነገር ህጻናት ሳይቀሩ የሚጦሙት ነው። እና በዚህ ጊዜ ጽጌረዳውም ሌላውም አበባ ስለሚፈነዳ ህጻናት እየቆረጡ በምስለ ማርያም ስር ይጎዝጉዛሉ። እንደገና ቄጤማውን ጠጅሳሩን ደሞ ጦሚቱ እስክታልቅ ውዳሴ ማርያም ትርጓሜ ለሚያስነብበው እና በቤተክርስቲያን ውስጥ ሱባኤ ለገቡት እየተወሰደ በእግራቸው ስር ይጎዘጎዝላቸዋል። ሰውም ለድንግል ማርያም ለነብዩ ኤልያስ ብታደርሱኝ እንዲህ ብታረጉልኝ ጨፌ እጎዘጉዛለሁ ብሎ ይሳላል። ... በደንቡ መሰረት የቆረበ የመነኮሰ እና አቅሙ የፈቀደለት ሰው በጥሬ ይጦማል። ጥሬ ቀቅሎ ጦሚቱ እስክታልቅ በየዓመቱ የሚዘክርም ሞልቷል። በፍልሰታ ጦም ብዙ ሰው ንፍሮ ቀቅሎ ወይም ጥሬ ቆልቶ ለቆራቢ እና ለጧሚ ይሰጣል። ያ ሁሉ ሱባኤ የያዘው ሰው እጸድቅ ያለ በሚሰጠው ጥሬ ጦሙን ሊጨርስም ይችላል።

ከዚህም የምንረዳው በተጠኚው ማህበረሰብ ውስጥ ክርስቲያኑ በተለይ በፍልሰታ ወቅት የአበባ እና የቄጠማ ስጦታ ለቤተክርስቲያን የመስጠት እንዲሁም ጥራጥሬ ደግሞ ለሰዎች የመዘከር ልምድ እንዳላቸው ነው።

✓ ዘካ እና ሰደቃ (Zakah and Sadaqah)

ዘካ በሙስሊሙ ማህበረሰብ ዘንድ አንድ አማኝ ፈጣሪው ከሰጠው ሀብት ላይ ቀንሶ ለተቸገሩት ሰዎች ሊያደረገው የሚገባ ግዴታዊ በጎ አድራጎት ሲሆን ሰደቃ ደግሞ ምጽዋትን ጨምሮ በፍቃደኝነት ላይ የተመሰረቱ መልካም ስራዎችን በለጋስነት ማደረግን የሚመለከት ስራ ነው። ዘካ እና ሰደቃ መስጠትን አስመለክቶ ሼህ እስሚ (ቃለመጠይቅ 18/08/2013 ዓ.ም፣ ደ/ኤልያስ) እንደሚከተለው ያብራሩታል።

> ዘካ መስጠት ለአንድ ሙስሊም ግዴታው ነው። ምክንያቱም አላህ የሰጠውን ሃብት ለድሆች ማካፈል ስላለበት። ይህን አለማድረግ ግን እነሱን ድሃ እሱን ሃብታም ባደረገው ፈጣሪ ፊት ወቀሳ አለበት። ሌላው በሁለት ነገሮች እንጂ ቅናት የለም ይባላል። ይኸውም፡- አላህ ቁርኣንን ሰጥቶት ሌት ተቀን የሚቆምበት ሰው እና አላህ ገንዘብ ሰጥቶት ሌት ተቀን በሚለግስ ሰው ነው። ስለዚህ መስጠት በሙሰሊም የተደገፈ እንደ ግዴታም የተቀመጠ ጉዳይ ነው። በእውነቱ ብዙ ጥቅሞችም አሉት። ውሃ እሳትን እንደሚያጠፋው ሁሉ ሰደቃም ወንጀልን /ኃጢኣትን/ ታጠፋለች። ሰደቃ ገንዘብን ያፀዳል። በዛዛታ፣ በመሀላ እና በውሸት በኩል ገንዘብ ላይ የሚደርሰውን ቆሻሻ ያጠራል። ነብዩ ነጋዴዎችን ሲመክሩ ‘ይህ ንግድ ዛዛታና መሀላ የተቀላቀለበት ነው። በሰደቃ አጥሩት።’ ብለዋል። ሰደቃ አንድ ባሪያ እምነቱ እውነተኛ ስለመሆኑ ማመላከቻ ጭምር ነው። ስለዚህ አንዱ ለአንዱ በጎ ማደረግ በተቸገረ ጊዜ ሰደቃ መስጠት በመጽሐፋችንም የተቀመጠ ነው። በአጠቃላይ በቁርኣንና ሆነ ሐዲስ ትእዛዝ የተላለፈባቸውን ምጽዋትን የሚያነሳሱ መልእክቶችን በጥልቀት ስንመለከት ከሰደቃ የሚበልጡ መልካም ስራዎች ይኖራሉ ብሎ ለመገመት ይከብዳል። ዑመር አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና እንዲህ እስከማለት ደርሰዋል፡- ‘ስራዎች እንደሚፎካከሩ ተነገረኝ። ሰደቃ (ምጽዋት) እኔ የሁላችሁም በላጭ ነኝ ትላቸዋለች።’ አሉ። እኛም በአላህ ትእዛዝ መሰረት አላህ በረዳን መጠን እያንዳንዱ ለራሱ የሚሰራው በጎ ነገር ቢኖርም በእኛ አካባቢ (ደ/ኤልያስ) ያሉ ሙስሊሞች ሲቸገሩ በመወያየት ንግድ ወይም ሌላ ስራ እንዲጀምሩ እቁብ ሰብስበን በመስጠት እንረዳዳለን። በጦም ጊዜ የተቸገሩትን ቅድሚያ እናበላለን።

ከዚህም ምላሽ በተጠኝው ማህበረሰብ ዘንድ የእስልምና እምነት ተከታዮች መደጋገፍ እና መረዳዳትን ከጽድቅ ስራዎች አንዱ አድርገው እንደሚያስቡ እና በእምነቱ መንገድ ለመጓዝ፣ ፈጣሪን ለማስደሰት፣ ኃጢያታቸውን ይቅር ለማስባል (ኃጢያታቸውን ለማካካስ) ሀብታቸውን

ለማስባረክ እንዲሁም በሌሎች ምክንያቶች ሰደቃ እንደሚያደርጉ ነው፡፡ በዚህም ውስጥ እርስ በእርስ በመረዳዳት ያላቸውን ማህበራዊ ግንኙነት የሚያጠናክሩበት እና ኢኮኖሚያቸውን የሚያሻሽሉበት መንገድ እንደሆናቸዉ እንረዳለን፡፡

- ✓ ዳረጎት

ማዕድን (ምግብን) በሞሰብ ሆኖ በጋራ መመገብ የኢትዮጵያውያን የጋራ ልማድ ነው፡፡ በተጠኘው ማህበረሰብ ዘንድ ማዕድ በሚቀርብበት ወቅት በሞሰቡ ዙሪያ ከተቀመጡት በማህበራዊ ደረጃ የሃይማኖት አባት ወይም በእድሜ የበለጠው እና ወንድ የሆነ ሰው ጸልዮ ከሁሉ በፊት ከማዕዱ ቆርሶ ባርኮት ይሰጣል፡፡ እንዲሁም በስተመጨረሻም ምግብ ከበሉ በኋላ ምርቃት ተደርጎ ቀሪ ምግብ እየተጠቀለለ ዳረጎት ይሰጣል፡፡ ይህን የስጦታ አይነት እሳቤ እና የአከዋወን አስመልክቶ አቶ አያሌው (ቃለመጠይቅ፣ 16/08/2013ዓ.ም፣ ደ/ኤልያስ) እንደሚከተለው ገልጸውታል፡፡

> ...መሶብ ሲቀርብ እንዲህ እንዳሁኑ መብራት ሳይኖር በፊት ከደገላ የሚሰራ ገታ፣ ጫቅማ ሰክተን እናበራ ነበር እና አባቶች እና ሌሎች ቤተሰቦች እራት በልተው እስቲጨርሱ ድረስ መብራት የሚያበሩት ሞሰሳ ልጆች (ትንንሽ ልጆች) ናቸው፡፡ ከዚያ ኩራዝም ፋኖስም መጣ ያ በግርግይ ብቻውን ተቀምጦም ስለሚበራ የሚይዝ ሰውም አያስፈልገውም፡፡ ... እና አባቶች እራት ተበልቶ ሲያልቅ እንጀራ አስተርፈው መብራት ይዘው ለነበሩት ከዚያ ማዕድ ጠቅለል እያደረጉ በእጅ በእጃቸው ዳረጎት ይሰጧቸዋል፡፡ ልጆችም ከአንገታቸው ሰበር እያሉ በሁለት እጃቸው ይቀበላሉ፡፡ አሁንም መቼም መብራት ማብራቱ ቢቀርም አባት ካለ አባት ከሌለ እናት ከማዕዱ ቆርሰው ለልጅ፣ ለወዳጅ እንደገና በማዕድ ጊዜ ቆሞ ሳገለገለ ሰው ሁሉ ዳረጎት ይሰጣሉ፡፡ ... ዳረጎት ከአባት ከእናት የሚሰጥ ትልቅ ቡራኬ ነው፡፡ ለተቀባይ ጥሩ እድል፣ ሀብት በረከት ያሰጣል የእናት የአባት በረከት ያሳድራል፡፡

ዳረጎት በስጦታው አማካኝነት የሚመጣ ሌላ በረከት እንደሚኖር በማመን የሚከውኑት የምግብ ስጦታ አይነት እንደሆነ እንረዳለን፡፡ ከምላሹ እንደምንረዳው ዳረጎት የሚቀበሉት ልጆች፣ የቅርብ ወዳጅ፣ እና በማዕድ ያገለገሉ ናቸው፡፡ ከዚህም የምንረዳው ማህበረሰቡ ምግብ በሚመገብበት ወቅት ያለውን መተሳሰብ እና አብሮነት ሲሆን በባህሉ መሰረት የተጣላ ሰው አብሮ ለማዕድ አይቀመጥም (አብሮ ቆርሶ አይበላም)፡፡ የተጣላ ሰው ከእርቅ በኋላ ደግሞ አብሮ በመብላት እና በመጎራረስ መታረቁን ያሳያል፡፡ ስለዚህ ከማዕድ ቆርሶ መስጠት በቤተሰብ እና በወዳጅ መሀል

ያለውን ቀረቤታ ለማጠናከር ሲጠቀሙበት እናስተውላለን። በተጠኘው ማህበረሰብ ዘንድም ዳረጎት ያለውን አከዋወን ስንመለከት ሰጪው ከሚበላው ቆርሶ በተቀባይ እጅ ያኖረዋል፣ ተቀባይም ሁለት እጁን ዘርግቶ በአንገቱ ሰግዶ ይቀበላል። ይህ ማህበረሰቡ ለማዕድ ፣ ለታላቅ እና ለስጦታ ያለውን ትልቅ አክብሮት ያስገነዝባል።

## 5.6 የስጦታ ፋይዳ

በዚህ ጥናት ስለ ስጦታ በቀረቡት የመረጃ ትንተናዎች ውስጥ በደብረ ኤልያስ ከተማ የሚኖሩ ማህበረሰቦች በተለያዩ ክዋኔዎቻቸው ዘንድ ያላቸውን የስጦታ ልማድ እና ስጦታውም የማህበረሰቡን ደንብ ጠብቆ ያለውን አከዋወን ተመልክተናል። በዚህ ንዑስ ርዕስ ደግሞ በተጠኘው ማህበረሰብ ዘንድ ያሉትን የስጦታ ክዋኔዎች እንደምሳሌ በማንሳት ስጦታ ያለውን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ፣ ባህላዊ፣ ሃይማኖታዊ እና ስነ ልቡናዊ ፋይዳዎች እንመለከታለን።

### 5.6.1 ማህበራዊ ፋይዳ

ስጦታ ከሚሰጠው ፋይዳ በዋናነት ማህበረሰቡ እርስ በእርስ ያለውን ቅርርብ እና ማህበራዊ አብሮነት የማለሳለስ፣ የማስጠበቅና የማስቀጠል ሚና ይጠቀሳል። ይኸም ማለት ማህበረሰቡ በእለት ተእለት ክንውኖቹ ውስጥ ለሌሎች ሰዎች በሚያደርገው የስጦታ ልውውጥ የሚያስተላልፈው አገልግሎት ወይም ቁስ ብቻ ሳይሆን ስጦታ ለሚቀበለው ሰው ያለን የቅርብነት ስሜትና ግንኙነትን ለመመስረት ያለውን ፍላጎት ጭምር ነው። ስለዚህ መስጠት በዙሪያችን ካሉ ሰዎች ጋር ያለንን ግንኙነት ጠብቆ ለማቆየት እና ለማጠናከር ወሳኝ ሆኖ እናገኘዋለን ።

በተጠኘው ማህበረሰብ አብሮ ለመኖር በሚያደርጉት ክንውን ውስጥ በተለያዩ ጊዜያት ስጦታ የመለዋወጥ ልማድ ያላቸው ሲሆን ስጦታውን በደስታ ቀናቶች ለምሳሌ፦ የወለደች እናት ለመጠየቅ፣ ለክርስትና ለሀቂቃ፣ ለሰርግ ወዘተ. ደስታን ለመግለጽ እና በሀዘን ጊዜ ከጎን በመሆን ፍቅርን ማሳየት አለሁ ባይነትን መንገሪያ መንገድ፣ ሆኖ ሲቀርብ ወይም እንደ ማጽናኛ ሲጠቀሙበት ተመልክተናል። በተጨማሪም ወቅቶች ሲፈራረቁ፣ ሰብል ሲደርስ፣ በአዲስ ዓመት እና በተለያዩ ክብረ በዓላት፣ እሸት በሚበላበት ወቅት ወዘተ. ስጦታ ይዞ በመጠያየቅ ዝምድናቸውን ማጠናከሪያ መንገድ ሆኖ ሲያገለግል አይተናል። ሰርግ በወዳጅ ዘመድ ትብብር ሲደገስ ተመልክተናል። ይህ ትብብርም ማህበራዊ ኑሮን በማጎልበት በኩል ከፍተኛ ሚና እንዳለው እንረዳለን። በበዓላት ወቅት ብቻ ሳይሆን በተለያዩ ክንውኖች ለምሳሌ፦ በግብይት ወቅት እቃ ሲሸጡ ከክፍያ ውጪ ምርቃት በመስጠት በሻጭ እና በገዢ መካከል

ያለን ግንኙነት የማለሳለስ እና የማጠናከር እንዲሁም ደንበኝነትን የመፍጠር ሚና ያለው የግብይት ልማድ ፤ ከብት፣ መሬት ወይም ቤት ሲሻሻጡ መመራረቂያ ፍንጥር በመጠጣት ወይም በመገባበዝ የተሻሻጡት እቃ በፍላጎት ላይ የተመሰረተ እንደሆነ እና ከግብይቱ በኋላ ያላቸውን ግንኙነት የማስቀጠል ፍላጎት እንዳላቸው የሚገልጹበት፤ ከዚህም በተጨማሪ በእቁብ ደንብ ውስጥ ገንዘቡ የደረሰው ሰው ዋስ ለሆኑት ሰዎች የመጋበዝ እና ምስጋና የማቅረብ ወዘተ. ልማዶች አላቸው።

በዚህ ማህበረሰብ ውስጥ በተለያዩ ዝግጅቶች ሰበብ አንዱ ለሌላው የሚያቀርበው ስጦታ የሆነ ጊዜ እና ሁኔታ ላይ ሰጪው ምላሽ የሚጠብቅበት እንዲሁም ስጦታ ተቀባይ ደግሞ እንደ ውለታ አንዳንዳንድ ጊዜም እንደ እዳ የሚያስቀምጥበት የስጦታ ደንብ እናገኛለን። ነገር ግን ሰጭው ከሚሰጠው ሰው ትርፍ አገኛለሁ ብሎ ሳይሆን በለጋስነት ማድረግ እንዳለበት እንዲሁም ተቀባይ ደግሞ የሰጭውን ውለታ መዘንጋት እንደማገባው የስጦታ ደንቡ ያስገነዝባል። ይህ አይነቱ ጠባይ በማኅበረሰቡ የተጠላ እንደሆነ በስጦታ ወቅትም እቀበል ብሎ መስጠት እንደማይገባ በቃለመጠይቅ ወቅት "ይሰጡ ብሎ ከሰጠ ቆጥቦ የበላ በለጠ" በማለት የአገሩን አባባል የነገሩኝ አቶ አያሌው (ቃለመጠይቅ፣ 16/08/2013፣ ደ/ኤልያስ) በማኅበረሰቡ ዘንድ ትርፍ አገኛለሁ ብሎ ከመስጠት አለመስጠት እንደሚሻል እና ስጦታ ያለ አሉታዊ ጠብቆት መፈጸም አለበት የሚል አስተሳሰብ እንዳለ በጥናቱ ለማረጋገጥ ተችሏል።

ይህ የስጦታ ምልልስም ማህበረሰቦቹ ያላቸው ቅርርብ እና እርስ በእርስ ያላቸው የመረዳዳት ስሜት የማጠናከር ሚናን ይጫወታል። ስጦታ መስጠት ህብረተሰቡን የሚያዋህድ ሂደት እንደሆነ Sherry (1983) ትገልጻለች። እንዲሁም ፈረንሳዊው ማውስ (1966) በደረሰበት የጥናት ግኝት "አንድ ሰው ስጦታን የሚሰጠው ዝምድናውን ለሚፈልገው ብቻ ነው። እንዲሁም ስጦታ አለመቀበል ወይም አለመስጠት ግንኙነቱን ያለመቀበል ፍላጎት ነው።" ሲል ገልጿል። ስለዚህ ስጦታዎች የሰዎችን የውስጥ ፍላጎት በመግለጽ በሰጪ እና በተቀባይ መካከል ያለ ግንኙነት ምን መምሰል እንዳለበት የሚቀርጽ መሳሪያ እና በእነዚህ ሁሉ ክንውኖች ውስጥ በመካከላቸው ያለውን ግንኙነት ወደ መልካም የመቀየር አቅም ያለው ማህበራዊ እሴት እንደሆነ በዚህ ጥናት በተገኙ መረጃዎች ለመረጋገጥ ችሏል።

### 5.6.2 ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ

ስጦታ የሰዎችን ኢኮኖሚ ከማሻሻል አንጻር ያለውን ፋይዳ በተመለከተ የተለያዩ ኢኮኖሚስቶች በስፋት አጥንተውት እናገኛለን (Camerer; 1988, Cheal; 1988)። በዚህ ጥናትም በማህበረሰቡ

ዘንድ ስጦታ ኢኮኖሚን የመመስረት፣ የማሻሻል እና የማስቀጠል ሚናን ሲጫዎት እንመለከታለን። ለምሳሌ፦ በጥናቱ ትንተና ወቅት በማህበረሰቡ የስጦታ ልማድ መሰረት ወላጅ ለአዲስ ጎጆ ወጪዎች ወይም ሙሽሮች ራሳቸውን እንዲችሉ እና በኢኮኖሚያዊ ህይወታቸው የጎለበቱ እንዲሆኑ እንደ መሬት የቤት እቃዎች ከብት ጌጣጌጦች ያሉ የተለያዩ የጎጆ መውጫ ስጦታዎችን ከሁለቱም ወገን ቤተሰቦች ይቀበላሉ። አዲስ ህይወት ለመጀመር የሚያስፈልጋቸው መሰረታዊ ፍላጎቶች በትብብር ይሟሉላቸዋል። ይህ ደግሞ ለግለሰብ ብቻ ሳይሆን ማህበረሰብ እንደ ማህበረሰብ በመረዳዳት እና በጠንካራ ኢኮኖሚ መሰረት ላይ ለመቀመጥ ስጦታ ያለውን አስተዋጽኦ ከፍተኛ መሆኑን ያሳያል። በማህበረሰቡ ልማድ መሰረት የሚሰጡ የስጦታ ዓይነቶችም ስጦታ ተቀባዮች ኢኮኖሚያቸውን እንዲያሻሽሉ እና የነበረውን እንዲያስቀጥሉ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያለው ነው። ለምሳሌ፦ አንድ ሰው ከቤተሰብ የእርሻ መሬት አሊያም የከብት ስጦታ ቢሰጠው መተዳደሪያው ግብርና የመሆን እድሉ ሰፊ ነው። ስለዚህ ስጦታ የአንድን ማህበረሰብ የኢኮኖሚ መሰረት የማስቀጠል ሚናዉ ከፍተኛ ነው። ሌላው በጥናቱ ውስጥ ከተነሱ ጉዳዮች መካከል የተለያዩ ድግሶች በሚደረጉበት ወቅት ደጋሾችን ለማገዝ የሚደረጉ የአቆልቋይ ስጦታዎችን ተመልክተናል። ይህ የስጦታ ልማድም ችግሮችን በትብብር ለመዎጣት ካለው ማህበራዊ ፋይዳ ጋር ከድግሱ በኋላ የሚመጡ የኢኮኖሚ ቀውሶችን ለመቀነስ እንደ ድጋፍ ሆኖ ያገለግላል። በተጨማሪም በተጠኝው ማህበረሰብ የሙስሊም እምነት ተከታች ሰደቃ በመስጠት አማኞች ስራ እንዲጀምሩ እንዲሁም እንዲያሻሽሉ የማድረግ ልማድ እንዳላቸው ተመልክተናል። ይህም አማኙ ማህበረሰብ በኢኮኖሚው እንዲጠነክር የማድረግ አስተዋጽኦው ከፍተኛ እንደሆነ እንረዳለን። ስጦታ የመለዋወጥ ልማድ ስጦታውን መሰረት አድርገው ለሚንቀሳቀሱ የንግድ ተቋማት የገቢ ምንጭ ሆኖ ያገለግላል። ምክንያቱም ስጦታን መሰረት አድርገው ገቢ ለማግኘት የሚያነሳሳቸው ማህበረሰቡ ለስጦታ ልውውጥ ያለው ልማድ ነው።

በአጠቃላይ በስጦታ ምልልስ ወቅት ያለውን የማህበረሰብ ልምድ ስንመለከት ስጦታ ተቀባይ የተሰጠውን ስጦታ እንደ ውለታ የማስቀመጥ ልማድ አለው። ሰጪውም ውለታው አንድቀን እንደሚመልስለት ይጠብቃል። በጥናቱ ውስጥም በማህበረሰቡ የስጦታ ደንብ መሰረት አብዛኛው ስጦታ በአስፈላጊው ወቅት አንዱ ለሌላው የሚያደርገው እና በውስጡ ምልልስ ያለበት ሂደት መሆኑን መረጃዎች ያመላክታሉ። ይህ ደግሞ በተጠኝው ማህበረሰብ ውስጥ የመደጋገፍ እና የመተባበር ስሜትን ከማሳደግ በተጨማሪ አንዱ ለአንዱ ያለው የስጦታ ምልልስ  የተቀባይን

ኢኮኖሚያዊ ክፍተት ሰጭው እንዲሞላ እድል የሚሰጥ ማህበራዊ ልማድ እንደሆነ በጥናቱ ለማረጋገጥ ተችሏል።

### 5.6.3 ባህላዊ ፋይዳ

የስጦታ ልማድ ብዙ ነገሮችን ያካትታል ሰጪ፣ ተቀባይ፣ ስጦታ፣ እና አጋጣሚ ወይም ልዩ አውድ መኖር አለበት እንዲሁም ለማን መስጠት፣ ምን መስጠት፣ መቼ መስጠት፣ ለምን መስጠት እና ምላሽ መስጠት የሚሉ ጉዳዮች ሁሉ ከባህላዊ ዳራ ጋር የተያያዙ ናቸው። ስጦታ የአካባቢውን ባህል መሰረት አድርጎ ሲከወን ማህበራዊ ደንብን ወይም የማህበረሰብ ባህልን የማስጠበቅ እና የማስቀጠል ሚናን ይጫወታል። ለምሳሌ፣ በዚህ ጥናት ውስጥ ሰዎችን በማስተዛዘን ወቅት የእዝን እንጀራ ቁጥር ጎዶሎ መሆን ይጠበቅበታል፤ በደስታ ጊዜ ደግሞ ሙሉ ቁጥር ይጠበቃል። በጥሎሽ ወቅት አንድ ሙሽራ ጥቁር ልብስ ገዝቶ ወይም በሌላ ጌጣጌጦች ሚስት የምትሆነውን ልጅአገረድ ሊያገባ አይችልም። እንደ ልማዱ ነጭ ሽማ አልብሶ በወርቅ ሽልሞ ይወስዳል እንጅ። ምክንያቱም በባህሉ ውስጥ ነጭ ቀለም ደስታ እና ህይወትን ጥቁር ደግሞ ሀዘን እና ሞትን ወርቅም ክብርን ፣ተፈላጊነትን እንዲሁም ንጽህናን ወክሎ እናገኘዋለን።

ማህበረሰቡ በደስታው እና በሀዘኑ ወቅት ቤተሰቦቹን፣ ወዳጅ ዘመዶቹን የደስታውም የሀዘኑም ተከፋይ የማድረግ፣ ስጦታ የመስጠት እና የመቀበል እንዲሁም የመመለስ ልማዶችን በስፋት እናስተውላለን። ስጦታ ሲሰጡ ከዘወትራዊ ለየት አድርጎ የተሻለውን የመስጠት፣ ሰጥቻለሁ ብሎ በይፋ ያለማውራት፣ በመልካም ልቡና  መስጠት ወይም ከተቀባይ የተሻለ ጥቅም ለማግኘት ብሎ አለመስጠት በማህበረሰቡ ዘንድ የሚደገፉ የመስጠት ደንቦች ናቸው። የተሻለ መስጠት ሲባል ለምሳሌ፦ የምግብ ስጦታ ሲቀርብ በቀላሉ የሚገኝ ሳይሆን የፍስክ ምግቦችን መምረጥ የተሻለ እንደሆነ ያስባል፣ ከፍስክ ምግቦች  ስጋ ሲሰጥ ትልቁን (በግ ከሆነ መሀል አገዳ የሚባለውን ክፍል፣ ዶሮ ከሆነ ፈረሰኛውን) መርጦ ለአባወራ ወይም ለትልቅ እንግዳ ይሰጣል። ይህ እንደ ባህል የምንመለከተው የመስጠት ደንብ ነው፣ ስጦታን ከፈጸሙ በኋላ በሰጪ እና በተቀባይ መካከል የሚሰጥ ምስጢር እንጂ ይህን አደረግሁ ብሎ ማውራት በማህበረሰቡ ባህል የሚያስተች ነው። ለምሳሌ፦  ስጦታ ሲሰጥ ሸፈን ተደርጎ ሲሆን እህል ውሃ ካልሆነ በቀር አብዛኛውን ስጦታ ወዲያው መክፈት ጨዋነት የጎደለው እንደሆነ እና ተቀባይን ስስታም ሊያስብል የሚችል ድርጊት እንደሆነ ይታሰባል። ይህም ስጦታ ያለውን ምስጢራዊነት እና ተቀባይ የሰጪውን ሞራል የመጠበቅ እንዳለበት ኃላፊነት ያሳያል።

በምልከታ ለማረጋገጥ እንደተቻለው የስጦታ አቀባበል ሁኔታን በተመለከተ ማህበረሰቡ  የራሱ ደንብ አለው:: ለምሳሌ፦ ከአንገት ሰግዶ መቀበል፣ በቀኝ እጅ ወይም በሁለት እጆች መቀበል፣ በጎ ተመኝቶ (መርቆ) መቀበል፣ ይጠቀሳሉ:: በስጦታ ወዲያው መክፈት ጨዋነት የጎደለው እንደሆነም ተነግሮኛል:: ተጨማሪም ይህም የአቀባበል ሁኔታ ሰጪውን እንዲሁም ስጦታውን እንደማክበር ይቆጠራል::

በማህበረሰቡ የስጦታ ልማድ ወቅት ስጦታ መቀበል ብቻ ሳይሆን የመመለስ ልማድም በስፋት ይስተዋልበታል:: ይህም ልማድ ከዚህ በፊት በተለያዩ ምክንያቶች የተቀበላቸውን ስጦታዎችን ከተቻለ አብልጦ ካልሆነም ተቀራራቢ የሆነውን በመስጠት ውለታን መመለስ በባህሉ የሚደገፍ ሲሆን አለመመለስ ደግሞ ሲያስተቸው እንመለከታለን:: ስለዚህ በበዓል፣ በድግስ፣ በሀዘን ወቅቶች የተቀበላቸውን ስጦታዎች የሰጪውን የተለያዩ ክስተቶች ጠብቆ ይመልሳል:: "የሰውን ሁሉ ድግስ በልቼ አልቀርም" ብሎ ደግሶ ያበላል:: ሰዎች ለሰዎች ከሚያደርጓቸው ስጦታዎች በተጨማሪ ስጦታ የመመለስ ግዴታን በስዕለት ውስጥ እንመለታለን:: ለምሳሌ፦ በማህበረሰቡ ልማድ ውስጥ አንዲት ኦርቶዶክሳዊት ሴት መውለድ እንቢ ሲላት ነብዩ ኤልያስ ቤተክርስቲያን ገብታ ጥቁሯን የሙሽራ ድንጋይ ተሸክማ ልጅ እንድትወልድ ስዕለት ትሳላለች እና ልጅን ብትወድ ስጦታዋን እንዲሁም ለውለታ ምላሽ አድርጋ ያሰበችውን ነገር ሁሉ የመስጠት ግዴታ አለባት:: ይህ ሳይሆን ቢቀር ግን ፈጣሪን እንደመካድ ይቆጠርባታል፡፡ በተጨማሪም የተወለደው ልጅ ዕጣፋንታ በህመም ወይም በሌላ ችግሮች እንደሚሰናከል ታስባለች፡፡ ስለዚህ ታማኝነቷን ለማሳየት የስጦታ ምላሽ ታደርጋለች፡፡ በአጠቃላይ ስጦታ በመስጠት፣ በመቀበል እና በመመለስ ዙሪያ ያሉ ደንቦች ሲከወኑ ማህበረሰቡ ሲደግፋቸው እና እንደ ደንቡ ሳይከወኑ ሲቀሩ ደግሞ በነቀፋቸው ቁጥር ስጦታን በተመለከተ ያለው ባህል እየተጠበቀ እንዲሁም እየተጠናከረ፣ የመሄድ ሚናን ይጫዎታል::

### 5.6.4 ሃይማኖታዊ ፋይዳ

የተጠኚው ማህበረሰብ  የሚከተላቸው የክርስትና እና የእስልምና ሃይማኖት የእምነት ህግጋቶች ስጦታ መስጠትን የሚደግፉ እና በወዲያኛው ዓለም ላለው ሰላማዊ ህይወት እንደ መዝገብ የሚቀመጡ በጎ ስራዎች ናቸው:: ስለዚህ የሃይማኖት ተከታዮቹ ስጦታ በመስጠት እና በመቀበል የእምነቱን ህግጋቶች ይፈጽማሉ ማለት ነው:: ለምሳሌ፦ ክርስቲያኑ ፈጣሪ ለሰው ልጅ የሰጠው ትልቅ ስጦታ የራሱን ስጋ እና ደም እንደሆነ ያምናል፤ ስጦታውንም ህጉን ጠብቆ ይቀበላል:: በዚህም የሃይማኖቱን ህግ ይፈጽማል፣ በተጨማሪም መባውን፣ አስራት በኩራቱን

ለቤተክርስቲያን ይሰጣል፣ በጻድቃን በመላእክት ስም ይደግሳል፣ ድሆችን በገንዘብ፣ በምግብ፣ በአልባሳት ይደግፋል። ምፅመኑ ስጦታ በመስጠት ቤተ እምነቱን ያሳንጻል። ቤተ እምነቶች በየአካባቢው ከመስፋፋታቸው ጋር ተያይዞ አማኙ በአቅም የመጠናከር እና በቁጥር የመብዛት እድሉ ከፍተኛ ነው። ከሞት በኋላ ለሚመጣው ህይወት ሰላም ለሙታን ጸልዮ ዝክር ያደርጋል። በዚህም አማኙ ከሞት በኋላ ባለው ነገር ተስፋ እንዳይቆርጥ እና ህይወቱን በተስፋ እንዲመራ ያግዘዋል። ወዘተ. ሙስሊሙም እንዲሁ በጾም፣ በፍስክ ወቅት ሰደቃ ይሰጣል። እርዳታ ለሚያስፈልገው ሁሉ በአላህ ስም መልካም ያደርጋል። በዚህም ሃይማኖቱ የሚያዘውን ህግ ይፈጽማል። በአጠቃላይ ስጦታ የማህበረሰቡን ሃይማኖት ህጋጋት ከመፈጸም አንጻር ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው እንረዳለን።

### 5.6.5 ስነ ልቡናዊ ፋይዳ

ስጦታ የማህበረሰቡን አስተሳሰብ ከማሳወቅ በተጨማሪ ስነልቡናውን የመቅረጽ ሚና ይጫወታል። በስጦታ ውስጥ ሰጪው ስለ ተቀባዩ ፣ ስጦታ ስለ ሰጠበት አጋጣሚው ወይም በመካከላቸው ስላለው ግንኙነት ያለውን ስሜት በተምሳሌትነት አካቶ ይዟል። ስጦታ የመስጠት አጋጣሚዎችን ተጠቅሞ ለአንድ ሰው መልካም እድል ለመመኘት፣ አመሰግናለሁ ወይም ይቅርታ ለማለት፣ በአጠቃላይ ከፍቅር፣ ከመተሳሰብ፣ ከመውደድ፣ ከመከባበር፣ ከአድናቆት ወይም ግንኙነቶችን ለማደስ እና ግንኙነቶችን ለመገንባት ካለው ፍላጎት የመነጨ ሊሆን ይችላል። ስጦታን መስጠት በተወሰነ ደረጃ ለሰጪው አስፈላጊ ለሆኑ ሰዎች አድናቆቱን የሚገልጽበት ወይም በጥልቀት ለሚያስባቸው ሰዎች ፍቅር እና ከልብ የመነጨ ስሜቱን የሚገልጽበት መንገድ ነው።

ተቀባዩ የቤተሰብ አባል፣ የትዳር ጓደኛ፣ የስራ ባልደረባ ወይም አዲስ ጎረቤት ሊሆን ይችላል። ግንኙነቱ ምንም ይሁን ምን ስጦታ መስጠት ለአንድ የተወሰነ ሰው ያለን አክብሮት እና ግንኙነት የመመስረት ወይም የማስቀጠል ስሜት ለማሳየት ሁልጊዜ ቀልፍ መንገድ ነው። በዚህም ስጦታ መስጠት ብዙውን ጊዜ በሰጪ እና በተቀባይ መካከል አዎንታዊ ስሜቶችን የማምጣት እድሉ ከፍ ያለ ነው። በተጨማሪም ስጦታ ምርጫን እና ውዴታን መጠቆሚያ ሆኖ በሰጪው ህይወት ውስጥ ካሉ ሰዎች ጋር የጠበቀ ግንኙነት በመፍጠር ከተወሰኑ ሰዎች ጋር ያለን ትስስር ለማጠናከር እና እርስ በእርስ ያለን ቀረቤታ ለማሳየት ያገለግላል።

በዚህ ጥናት ውስጥ ከተጠቀሱት የስጦታ ልምዶች መካከል የደም ግብር ማድረግ ለሚያረቧቸው ከብቶች እና ለአካባቢው ምንጭ ውሃ ጤና እና ደህንነት ፣ በጉችማ ቂቤ

እንዲሁም በጋን ድፍድፍ ለአዋይ እያሉ ማስቀመጥ ደግሞ ለራስ ጤንነት  ከረቂቅ መናፍስት ጋር  ሰላም ለመሆን  ይበጃል ተብሎ ይታሰባል፡፡ ስለዚህ ስጦታውን ሳያደርጉ ሲቀር ችግር ሊደርስብኝ ይችላል በሚል ስጋት እና ረፍት የማጣት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡ ስለዚህ ስጦታውን መከወን የአእምሮ ረፍት እንዲኖራቸው እና ደህንነቴ የተጠበቀ ነው ብለው እንዲያስቡ ይረዳቸዋል፡፡

ስጦታ መስጠት ካሉት ግላዊ ጠቀሜታዎች ውስጥ ደስታን የመፍጠር ሚና እንደሆነ እና ሰዎች ለሚወዱት ሰው ልዩ ነገር መስጠት ሲችሉ የአእምሮ ጤናን በማሻሻል እንዲሁም ስለራሳቸው ሕይወት የበለጠ ደስታ እንደሚሰማቸው ከስጦታ ጋር በተያያዘ የተጠኑ ምርምሮች ያስረዳሉ፡፡ ጆርጅ (2006) ባደረገው ጥናት ሰዎች ለበጎ አድራጎት ድርጅቶች እርዳታ በሚሰጡበት ጊዜ ከደስታ ፣ ከማህበራዊ ትስስር እና ከእምነት ጋር የተቆራኙ የአንጎል ክልሎችን ያነቃቃል ፣ ይህም በአእምሮ ውስጥ "ሞቅ ያለ ብርሃን" ይፈጥራል ፡፡ የሚል ግኝት አስቀምጧል፡፡ መስጠት ትብብርን እና ማህበራዊ ትስስርን ያበረታታል፡፡ ስጦታ ስንሰጥ፣ የመመለስ ዕድሉ ከፍ ያለ ነው፡፡ አንድ ሰው ለሌሎች ሲሰጥ ለጋስነቱ በሰጠው ሰው እና በሌሎች ሰዎች ዘንድ ምስጋና እና በጎ ምላሾችን ያስገኝለታል፡፡ በተጨማሪም እነዚህ ልውውጦች የመተማመን እና የመተባበር ስሜትን ያበረታታሉ፣ በሰጪው ዙሪያ ያለው ሰላምም ይጠበቃል፡፡ አዎንታዊ ማህበራዊ መስተጋብር ለጥሩ የአእምሮ እና የአካል ጤንነት ዋና ነገር ነው፡፡

በአጠቃላይ የመስጠት ባህሉ ቢለያይም ሰዎች ስጦታን የሚሰጡበት ምክንያት ተቀራራቢ ነው፡፡ ስጦታ ለመለዋወጥ ከሚነሱ ምክንያቶች ውስጥ ለራስ ደስታን መፍጠር እንዳለ ሆኖ  ከራስ አልፎ ለሌሎች በማሰብ ስሜት የሚደረግ መሆኑ ይጠቀሳል፡፡ ስጦታ በተፈጥሮ የሚገኝ ጉዳይ ነው ወይስ ከማህበረሰብ ኑሮ የሚለመድ? የሚለው ጉዳይ ብዙ የሚያከራክር ቢሆንም በለጋሽ ቤተሰብ መሀል ያደገ ህፃን ሰጪ በንፉግ ዘንድ ያደገ ደግሞ ንፉግ የመሆን እድሉም ከፍ እንደሚል ይጠበቃል፡፡ ስለዚህ ስጦታ ስነልቡናው የተስተካከለ እና አዎንታዊ ነገሮችን የሚያስብ ማህበረሰብ ለመፍጠር ያለው አስተዋጽኦ ከፍተኛ እንደሆነ እንረዳለን፡፡

# ምዕራፍ ስድስት:- ማጠቃለያ እና የይሁንታ ሀሳብ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ይህ ጥናት የተነሳባቸው ሃሳቦች ምንድን ናቸው? በምን ዓይነት መንገድ ተጠኑ እንዲሁም በጥናቱ የተገኙ ውጤቶችስ ምንድን ናቸው የሚሉ ሃሳቦችን አካቷል። በአጠቃላይ ጥናቱ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ የተጓዛቸውን መንገዶች፣ የጥናቱ ዋና ዋና ግኝቶችና ጠቃሚ ሃሳቦች ተመርጠው የቀረቡበት እንዲሁም በጥናቱ የተካተቱት ውጤቶች ተጠቃለው የቀረቡበት ሲሆን ከጥናቱ ውጤት በመነሳትም የይሁንታ ሀሳቦች የተተጠቆሙበት የጥናት ክፍል ነው።

## 6.1. ማጠቃለያ

ይህ ጥናት "ስጦታ ለማኅበራዊ ደንብ እንደመታዘዝ መገለጫነት በደብረ ኤልያስ ከተማ ተተኳሪነት" በሚል ርዕስ የቀረበ ነው። ጥናቱን ለማካሄድ የተነሳሁበት ምክንያት በኢትዮጵያውያን የአኗኗር ልምድ በማህበራዊ፣ ሃይማኖታዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ወዘተ.ጉዳዮች ውስጥ ስጦታ የመለዋወጥ ልምዶች በስፋት እናገኛለን። ከኢትዮጵያውያን በርካታ እሴቶች መካከልም አንዱ ለአንዱ የሚያደርገው በጎነት እና የመረዳዳት የመተጋገዝ ተግባር በስፋት ይታወቃል። ይህ ሁሉ እንዳለ ሆኖ ከዚህ በፊት ጉዳዩ እንደ ፎክሎር የከዋኞቹን ማንነት በመግለጽ በኩል ያለው ሚና የተለያዩ ማህበረሰቦች ልዩ ልዩ ክዋኔዎች በሚጠኑበት ጊዜ አብሮ ይነሳል እንጂ እንደ ዋና ርዕሰ ጉዳይ ለብቻው ተነጥሎ፤ ወይም እንደ ፎክሎር አንድ ቅንጣት ትኩረት ተሰጥቶት ስላልተመረመረ ጉዳዩ ከግለሰብ አልፎ በማህበረሰብ ባህልም ውስጥ እንዳለ ለማሳየት በሚል ነበር።

ጥናቱ ዋና ዓላማ አድርጎ የተነሳው፤ በተጠኘው ማህበረሰብ ውስጥ ስጦታ የአካባቢውን ልማድ ጠብቆ እንዴት ይከወናል የሚለውን መሪ ጥያቄ በማንሳት ማህበረሰቦቹ ስጦታ ለመለዋወጥ አነሳሽ የሆናቸውን ነገር በመለየት፣ በስጦታው አማካኝነት የሚያገኙትን ፋይዳ እና ትዕምርት ለመግለጽ ነበር። ጥናቱም ማህበረሰቡ ስጦታን እንዴት ይረዳዋል ፣ እንዴትስ ያስተናግደዋል ወይም ለምን ይጠቀምበታል፣ ስጦታ ብሎ የሚያቀርበው ነገር በዓይነት እና በመጠን እንዴት ያስቀምጠዋል፣ የስጦታ ጠቀሜታውስ እስከምን ድረስ ነው፣ በስጦታው ውስጥ የሚያስተላልፋቸው መልዕክቶች ምንድን ናቸው?፣ ወዘተ. የሚሉትን ጉዳዮች አካቷል። የጥናቱን ዓለማ ከግብ ለማድረስ በዋናነት ቃለመጠይቅ፣ ምልከታ እና የቡድን ተኮር ውይይትን ለመረጃ መሰብሰቢያነት ጥቅም ላይ አውሏል። መረጃ ሰጭዎችን አመች እና ዓላማ ተኮር

የንሞና ዘዴን በመጠቀም የተመረጡ ሲሆን በወሳኝ የምርምር ዘዴ፤ ገላጭ የመተንተኛ ስልትን በመጠቀም ተተንትኖ ቀርቧል። በማህበረሰቡ ደንብ መሰረት ስጦታ መለዋወጥ የዕለት ተዕለት ክንውን ሲሆን ሁሉንም ዓነቶች ለማካተት አመቺ ሆኖ አልተገኘም። ሆኖም ቤል (1994፣94) የከበራ ዓይነቶችን በከፋፈለችባቸው ዘርፎች ውስጥ ርዕሰ ጉዳዩን በመወሰን በእነዚህ ሪቹዋሎችን ተከትሎ የሚሰጡ ስጦታዎች ላይ አተኩሯል። እነርሱም የህይወት አውራ ጎዳና ስርዓቶችን ተከትሎ መወለድ፣ ማደግ እና መሞትን ተከትሎ፤ ለወለደች እናት እና ለአራስ ልጅ የሚሰጡ የአራስ ቤት ስጦታዎች፣ የክርስትና እና የሀቂቃ ስጦታዎች፣ የሰርግ ስጦታዎች እንዲሁም በሞት ጊዜ ያሉትን የማስተዛዘኛ እና የመታሰቢያ ጊዜ ስጦታዎች አካቷል። የጊዜ ሰሌዳዊ እና የመታሰቢያ ስርዓቶች ውስጥ በጊዜ ሽክርክሪት ሂደት በተደጋጋሚ የሚመጡ ቀናቶችን ተከትሎ ለሰው እና ለአማልእክት የሚሰጡ የአዲስ ዓመት፣የደብረ ታቦር፣ የቅዳም ስዑር፣ የንግስ በዓላት፣ የአባ ፊቂህ ክብረ በዓል ወዘተ. ስጦታዎች እና ምርት ከማምረት ጋር ተያይዞ የሚሰጡ የማርያም ባርኪ፣ እሸት ቅመሱ ወዘተ. የስጦታ ልማዶችን አካቷል። የመከራ ስርዓቶችን ተከትሎ  የደም ግብር፣ ጉችማ ማዘጋጀት እና በሶ መርጨት ያሉ የስጦታ ዓይነቶች አካቷል። በተጨማሪም በልውውጥ እና ቁርባን ስርዓቶች ውስጥ የቁርባን እና ስዕለት ስጦታዎችን እና በጾም መፈሰክ እንዲሁም በክብረ በዓላት ስርዓቶች ወቅት ያሉ የጾም ማግደፊያ ስጦታዎች ላይ በማተኮር ተመርምሯል። የትንታኔው ውጤትም እንደሚያሳየው በዋናነት ማህበረሰቡ ስጦታን ከሚከውንባቸው አውዶች መካከል ከበራዎችን ለጥናቱ አውድ በመምረጥ በእነዚህ አውዶች ምክንያት የደብረ ኤልያስ ማህበረሰብ  እርስ በእርስ ያላቸውን የመረዳዳት እና የመተሳሰብ ስሜት ስጦታ ሰጥቶ የመግለጽ፣ ከዚህ በፊት የተደረገን ውለታ ለመመለስ እና ምስጋና ለማቅረብ በስጦታው አማካኝነት ምላሽ የመስጠት እንዲሁም ለወደፊት ህይወት መንገድ ቀና መሆን፣ መልካም ጤና እና በረከት ለማግኘት በስጦታው የመማጸን ልማዶች እንዳሉት ተስተውሏል። ማህበረሰቡ የወቅቶችን መፈራረቅ፣ የተለያዩ የህይወት አጋጣሚዎችን ክስተቶች እንዲሁም የልዩ ልዩ ክብረ በዓላትን መምጣት ተከትሎ እርስ በእርስ ያለውን መተሳሰብ ለመግለጽ፣ ቀረቤታን ለማሳየት፣ ደስታን ለመፍጠር እና የሌሎችን ደስታ ለመካፈል፣ ሀዘንን ለመግለጽ፣ ምርጫን እና ውዴታን ለመጠቆም፣ ለወዳጅ ያለ አክብሮትን ለማሳየት፣ መልካም ምኞትን ለመግለጽ፣ አዲስ ሰውን ለማላመድ፣  ይቅርታን ለማግኘት፣ ምስራችን ለማብሰር፣ ውለታን ለመመለስ፣ ከአደጋ ለመጠበቅ ወዘተ. በሚሉ ምክንያቶች ውስጥ ስጦታ የመለዋወጥ ልማድ እንዳለው ያሳያል። በዚህ ጥናት ውስጥ ማህበረሰቡ የሚያደርገው የስጦታ ልውውጥ ወይም የስጦታ ልውውጡን የሚያደርግበት መንገድ ያለውን ባህል እና

አስተሳሰብ ፣ ሃይማኖቱን ፣ መተዳደሪያ ስራውን ሲያንጸባርቅበት ተስተውሏል። በተጨማሪም ከስጦታ ደንቡ ሳያፈነግጥ ለሰዎች ፣ ለፈጣሪ እንዲሁም ለረቂቅ መናፍስት የሚከውናቸው ስጦታዎች በስጦታ ሰጪ እና ተቀባይ መካከል ግንኙነትን ለመፍጠር፣ ያለውን ግንኙነት ለማጠንከር፣ ለማለሳለስ እና ለማስቀጠል ያለው ሚና ከፍተኛ እንደሆነ ተረጋግጧል።

## 6.2 የይሁንታ ሀሳብ

ይህ ጥናት ስጦታን ከፎክሎር አንጻር እንደ አንድ ልማድ በመመርመር በተጠኘው ማህበረሰብ ዘንድ ያለውን የማህበረሰብ ደንብ በማሳየቱ በሌሎች የኢትዮጵያ አካባቢዎች ያሉ ልማዶች በብዛት እና በጥልቀት እንዲመረመሩ መንገድ እንደሚከፍት ይታመናል። ከዚህ ጥናት አካባቢ ልማድ አንጻር ስንመለከት ማህበረሰቡ ስጦታን ከሚከውንባቸው አነሳሽ ምክንያቶች አንዱ ከዚህ በፊት የተቀበላቸውን ስጦታዎች የተገኘውን አጋጣሚ ጠብቆ ምላሽ ለመስጠት ያለው ፍላጎት እንደሆነ በጥናቱ ተረጋግጧል። ይህ ሁኔታ የስጦታ ሽክርክሪቱን ለማስቀጠል እና በዚህ ሽክርክሪት ውስጥ ያለውን የስጦታ ልማድ ለማስጠበቅ ያለው አዎንታዊ ሚና ከፍተኛ ቢሆንም ማህበረሰቡ ውለታን እንደ ብድር የመቁጠር እና ውለታ ለመመለስ በሚደረግ ትግል ውስጥ ደግሞ ለተለያዩ የማህበራዊ ኑሮ ቀውሶች እንዳያጋልጠው እና የስጦታን ትርጉም እንዳይቀይረው ያሰጋል። ለዚህም ሀሳብ መነሻ የሆነኝ አቆልቋይ በሚሰጥበት ወቅት ዋና አላማው ድግስ ያለባቸውን ሌሎች ሰዎች መርዳት ሆኖ ሳለ አንዳንድ ተጠኝዎች ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የአቆልቋይ ስጦታ ያልመለሰ ሰው በእድር ሊከሰስ የሚችልበት አጋጣሚ እንዳለ አስረድተውኛል። ይህ ደግሞ አቆልቋይን ከስጦታ አንድ ቅንጣትነት ያወጣዋል። ስለሆነም የአካባቢው ባህል እና ቱሪዝም እንዲሁም ሌሎች ማህበረሰብ ተኮር መስሪያ ቤቶች እና የሃይማኖት ተቋማት የሚከተሉትን የይሁንታ ሀሳቦች እጠቁማለሁ።

- በተጨማሪም ማህበረሰቡን ግንዛቤ የማስጨበጥ እና ባህሉ በነበረበት ክዋኔ እንዲሁም ዓላማ እንዲቀጥል የማድረግ ስራ ላይ ቢያተኩሩ፣

የተለዋዋጭነት ባህርይ ከባህል ባህርያት አንዱ ነው። ነገር ግን ባህል እንደ ባህልነቱ እንዲቀጥል ማህበረሰቡ ልማዱ ያለውን እሴት ሳይለቅ የማስቀጠል ኃላፊነት አለበት። ኢትዮጵያውያን አንድ ከሚያደርጋቸው ልማድ ውስጥ የስጦታ ልውውጥ እና መረዳዳት አንዱ ነው። ይህ ጥናትም አንዱ ማሳያ ነው። ነገር ግን ይህን ባህል አጉልቶ ከማውጣት ይልቅ ሀገረኛውን ደምስሶ ስጦታ መለዋወጥ የምዕራባውያን ብቻ የማድረግ እሳቤ እያስተዋልን ነው። ስለዚህ በተጠኘው እና በሌላውም ማህበረሰብ ዘንድ ያለው የስጦታ ልማድ እንዲተዋወቅ

ለማድረግ እና ለሌሎችም በቀላሉ ለማድረስ ከመገናኛ ብዙሃን ጋር ግንኙነት ፈጥሮ መስራት ቢቻል ያለውን ቀርሶ ለማስቀመጥ እና ለትውልድ ለማስተላለፍ ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡

## ዋቢዎች

ሉባባ አህመድ (2012)፤ "በኢሉ አባቦር ዞን ዶረኒ ወረዳ በኦሮሞ ማህበረሰብ ድንግልናቸውን ጠብቀው ለትዳር ለበቁ ሴቶች የሚደረግ ሥርዓት ትንተና"። ለኢትዮጵያ ስነ ጽሁፍ እና ፎክሎር ሁለተኛ ድግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት። ያልታተመ።

ሐሰን ታጁ (ተርጓሚ) (2004)፤ <u>ኢማም አን ነወዊ ሪያዱ አስ ሷሊሒን</u> (ከሐዲስ ቁጥር 1-810)። አዲስ አበባ፣ ነጃሺ ማተሚያ ቤት።

መነን መጽሔት (መስከረም 1995) እትም።

ሙለቀን የኔሰው (2010)፤ "የለውጥ ሽግግር በባሶሊበን ማህበረሰብ ባህላዊ የሰርግ ሥርዓት" በፎክሎር የሁለተኛ ዲግሪ ለማግኘት የቀረበ ጥናት። ባህርዳር ዩኒቨርስቲ ። ያልታተመ።

ሰሎሞን ተሾመ (2007)፤ <u>ፎክሎር ምንነቱና የጥናቱ የትኩረት አቅጣጫ</u>። አዲስ አበባ

አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።

በልማት እቅድ ክትትል ግምገማ ቡድን በሶሽዮ ኢኮኖሚክስና እስታስቲክስ ባለሙያ የተዘጋጀ ብሮሸር (2013) ደብረ ኤልያስ (ያልታተመ)።

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር (1980)፤ <u>መጽሐፍ ቅዱስ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት</u>። አዲስ አበባ። ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት።

ያለዉ እንዳወቀ (2004)፤ <u>የምርምር መሰረታዊ መርሆች አተገባበር</u>። ንግድ ማተሚያ።

አማን በላይ (2012)፤ <u>የጥንታዊቷ ኢትዮጵያ ትንሳኤ ታሪክ፤</u> አዲስ አበባ፣ ኤቭዳ አሳታሚ።

አበራ ጀንበሬ (2006)፤ <u>የኢትዮጵያ ሕግና የፍትሕ አፈጻጸም ታሪክ ከ1426 እስከ 1966 ዓ.ም</u>፣ በሲኤምዋይኬ ሚዲያ ኃ.የተ.የግ.ማ.። አዲስ አበባ።

አያልነህ ሙላቱ እና ሌሎች (1996)፤ ደብረ ኤልያስ የጥበብ ማዕከል።

ኤርሚያስ ከበደ (1998)፤ <u>ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ክፍል 2</u>። አዲስአበባ። ኩራዝ ማተሚያ።

ኪዳነ ወልድ ክፍሌ (1948)፤ <u>መጽሐፈ ሰዋሰው ወግስ መዝገበ ቃላተ ሐዲስ</u>። አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።

ካሕሳይ ገብረ እግዚአብሔር (2010)፤ <u>ባህልና ክርስቲያናዊ ትዉፊት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃና መምሪያ ማህበረ ቅዱሳን</u>፡፡

ፊቃደ አዘዘ (1991)፤ <u>የስነ ቃል መምሪያ</u>፡፡ አዲስ አበባ፣ ቦሌ ማተሚያ፡፡

Aafke Komter and Wilma Vollebergh. (1997). Gift giving and the Emotional Significance of Family and Friends. Published by: National Council on Family Relations.

Amy Shuman. (2000). Food Gifts Ritual Exchange and the Production of Excess Meaning Source The Journal of American Folklore ,Published by: American Folklore Society.

Anik, L.(2009). Feeling good about giving. The benefits (and costs) of self-interested charitable behavior.Harvard Business School Marketing Unit Working Paper.

Barry Schwartz. (1967) The Social Psychology of the Gift, Published by The

Bell,catherine (1997). Ritual.perspectives and Dimensions.New york.oxford

Business Relationships in China,Published by Springer.

C.R.Kothari.(1985). Research methdololgy methods and techniques New Age International Publisher (P) Ltd Crossman, A. (2018).folkways-mores-taboos and-laws.

Carrier J.G (1990). Gifts, Commodities, and Social Relations: A Maussian View of Exchange Source Sociological Forum , Vol. 6, Published by Springer Stable.

Colin Camerer.(1988). Gifts as Economic Signals and Social Symbols Source. American Journal of Sociology ,Vol. 94, Supplement Organizations and Institutions Sociological and Economic Approaches to the Analysis of Social Structure, Published by The University of Chicago Press.

Cronk, Lee. (2000) . Reciprocity and the Power of Giving.Conformity & conflict.Allyn & Bacon, MA, Chicago press.

Culler, J. (2002). The pursuit of signs semiotics, literature, deconstruction. Cornell University Press.

Danesi, M. (2004). Messages, signs, and meanings: A basic textbook in semiotics and communication (Vol. 1). Canadian Scholars' Press.

David, Gray.E (2004). Doing Research in the Real World. London, SAGE

Dawson, catherine. (2007). A practical guide to research methods afriend manual for mastering research techniques and projects. British library cataloguing in publication, oxford united kingdom.

Dorson M. richard. (1972). Folklore and folklife:An Introduction. university of chicago press.

Dundes Alan.(1980). Interpreting folklore.Indiana University Press.

Elliot Oring.(1986). Folk Groups and Folklore Genres An Introduction. Utah State

Engert, Andreas. (2016). Norms, rationality and communication. A reputation theory of social norms; franz steiner verlag.

Falk, Armin, and Urs Fischbacher. (2006). A theory of reciprocity. Games and economic behavior.chicago press.

Getie Gelaye. (1998) semantic analysis of Amharic kinship terms in gojjam. an anthropological approach.

Goldstien S. Kennth. (1964). A Guide for field workers in folklore Penns.

Graycar Adam and Jancsics David. (2016) Gift Giving and Corruption, International Journal of Public Administration.

H. Lorne Carmichael and W. Bentley MacLeod. (1997). Gift Giving and the Evolution of Cooperation. Vol. 38, Published by Wiley for the Economics Department of the University of Pennsylvania and Institute of Social and Economic Research, Osaka University.

http://eotcmkidusan.org/site/index.php?option=com_content&task=view&id=331&Itemid=35

http://ethiopianorthodox.org/amharic/abeyetbealat/yebealatenaatsewamat.pdf

http://www.verywellmind.com

http://wwww.giftculture.com

Jane Allyn Piliavin and Hong-Wen Charng.(1990). Altruism A Review of Recent Theory and Research. Annual Review of Sociology, Published by: Annual Reviews.

Janice G. Raymond.(1990). Reproductive Gifts and Gift Giving the Altruistic Woman.Source The Hastings Center Report, Vol. 20. Published by The Hastings Center.

John F. Sherry.(1983). Gift Giving in Anthropological Perspective. Published by Oxford University Press.

Jonathan Parry (1986). The Gift and the 'Indian Gift' Source: Man, New Series, Published by: Royal Anthropological Institute of Great Britain and Ireland

Joy A. Obando et al.(2019). Conducting Research and Mentoring Students in Africa∶ Research Integrity and Ethics. Council for the Development of Social Science Research in Africa Avenue Cheikh Anta Diop, Angle Canal IV BP 3304 Dakar, 18524, Senegal.

Karen Hellekson, (2009). A Fannish Field of Value Online Fan Gift Culture. Cinema Journal Published by University of Texas.

Kat Whittingham. (2011) The history of gift giving.

Katarina Nordblom. (2007) Explaining Gift Behavior Altruism or Social Norms? published by University of Gothenburg.

Kenneth J. Arrow. (1972). Gifts and Exchanges, Published by Wiley.

Komter, Aafke and Wilma Vollebergh. (1997). Gift Giving and the Emotional Significance of Family and Friends.Published by National Council on Family Relations.

Komter, Aafke. (2007) .Gifts and social relations: The mechanisms of reciprocity.International Sociology, 22 (1), 93-10

Marcel Mauss (1966) The gift forms and functions of Exchange in Archaic

Margolis Howard. (1982). A thought experiment on demand-revealing mechanisms. Public Choice, Chicago press.

Mathews, M. (2017). Gift-giving, reciprocity and trust. published by Taylor & Francis in the Journal of Trust Research, 7, pp. 90-106.

Mayet, C. & Pine, K. J. (2010). The Psychology of Gift Exchange. Published by University of Hertfordsh Hertfords.

P. Steidlmeier.(1999). Gift Giving, Bribery and Corruption Ethical Management of Business Relationships in China, Journal of Business Ethics, Published by Springer. .

R. L. Stirrat and Heiko Henkel (1997). The Development of Gift, The Problem of Reciprocity in the NGO World . Published by Sage Publications, Inc. in association with the American Academy of Political and Social Science.

Russell Belk. (1993). Gift Giving as Agapic Love An Alternative to the Exchange Paradigm Based on Dating Experiences Article in Journal of Consumer Research, York University.

Russell W. Belk. (2011). Gift-Giving Behavior. Digitized by tine Internet Archive Publications

Ruth Walker. (2017). Altruism and Generosity .published by The University of Waikato.

Sahlins, Marshall (1972). Stone Age Economics. Chicago: Aldine-Atherton.

Societies.

Sweterlitsch, Richard. (1997). ‘Custom’. In Folklore: An Encyclopedia of Beliefs, Customs, Tales, Music, and Art, edited by Thomas A. Green, 168–72. Santa Barbara.

University of Chicago Press.

Van Zyl, L., & Walker, R. (2013). Beyond altruistic and commercial contract motherhood: The professional model.

Vehrer, A. (2017). Teaching popular culture 3D/VR technology. In 2017 8th IEEE International Conference on Cognitive Infocommunications (CogInfoCom).

Wilson, David T. (1975). An integrated model of buyer- seller relationships. Journal of the academy of marketing science. witii funding from University of Illinois Urbana-Champaign.

Wolfinbarger, M. F. (1990). Motivations and symbolism in gift-giving behavior.ACR North American Advances.

www.worldweb.internationaldictionary.com

www.oxforddictionary.com .

## አባሪ 1፡- የመረጃ ሰጪዎች መዘርዝራዊ ዳራ

| ተ.ቁ | የመረጃ አቀባዮች ስም ዝርዝር | ጾታ | እድሜ | ስራ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | እማሆይ ህብስቴ ቦጋለ | ሴት | 87 | ጡረተኛ |
| 2 | ቄስ ሳመስግን አግሚስ | ወንድ | 59 | ቅስና |
| 3 | ሼህ እስሚ ከማል | ወንድ | 56 | ሼህ እና ነጋዴ |
| 4 | ዲያቆን አምሀ በለጠ | ወንድ | 30 | ዲያቆን |
| 5 | አቶ ደፋሩ ሞኜ | ወንድ | 50 | አርሶአደር |
| 6 | አቶ ደፋሩ ሞኜ | ወንድ | 50 | አርሶአደር |
| 7 | ወይዘሮ ዝናሽ ታመነ | ሴት | 35 | የቤትእመቤት |
| 8 | አቶ አያሌው ዳምጤ | ወንድ | 68 | አርሶአደር |
| 9 | ወይዘሮ እማዋይ መኮንን | ሴት | 45 | ነጋዴ |
| 10 | አቶ መዝገቡ ወርቅነህ | ወንድ | 42 | አርሶአደር |
| 11 | ወይዘሮ ዝይን ካሳ | ሴት | 60 | የቤት እመቤት |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | | | |
| 12 | ወይዘሮ ጥሩዓለም | ሴት | 32 | ነጋዴ |
| 13 | አቶ ደምል ጥሩሰው | ወንድ | 70 | አርሶአደር |
| 14 | አቶ ፈቃዱ አየነው | ወንድ | 39 | አርሶአደር |
| 15 | አቶ አበበ ፈረደ | ወንድ | 40 | አርሶደር |
| 16 | አቶ ደጉ አየሁ | ወንድ | 35 | ነጋዴ |
| 17 | አቶ ዋለ ገበየሁ | ወንድ | 65 | አርሶ አደር |
| 18 | ወይዘሮ ንጹህ ምትኩ | ሴት | 50 | መምህርት |
| 19 | ወይዘሮ ሰዋለም ተመስገን | ሴት | 39 | የቀን ስራተኛ |
| 20 | አቶ ምትኩ መኮንን | ወንድ | 31 | አርሶ አደር |

## አባሪ 2፡- ፎቶግራፎች



ፎቶ በአጥኝዋ፦ ዘመዳችን ከገጠር ያመጡልን የበቆሎ እሸት ስጦታ ሐሙስ ጥቅምት 26/2013ዓ.ም፣ደ/ኤልያስ



ፎቶ በአጥኝዋ፦ የቡሄ ዳቦ ለክርስትና ልጅ ይዘው ሲገቡ የተነሳ ነሃሴ13/2013ዓ.ም፣ደ/ኤልያስ



ፎቶ፦ በቡድን ተኮር ውይይት ጊዜ የተነሳ ከግራ ወደቀኝ አቶጥበቡ፣ ቄስ ላመስግን፣ አቶ ደፋሩ፣ አቶ ምትኩ፣ አጥኝዋ፣ አቶ መዝገቡ፣ አቶ ፈቃዱ ፣ አቶ አበበ፣ አቶ ደጉ 01/09/2013 ዓ.ም፣ ደ/ኤልያስ



ፎቶ በአጥኝዋ፦ ለሙሽሪት ዳቦ እና እንጀራ የሚወሰድበት በሙሽሪት ወይም በወዳጆቿ የሚዘጋጅ መሶብ ወርቅ 08/08/2013ዓ.ም



ፎቶ በአጥኝዋ፦ ለሙሽሪት የሚሰጥ የሙሽራ ዋንጫ 08/08/2013ዓ.ም



ፎቶ በአጥኝዋ፦ የእጅ አንባር እና ክታብ የያዘ ሙዳይ ሙሽሪት ከእናቷ የሚሰጧት ስጦታዎችን የሚያሳይ 08/08/2013 ዓ.ም



ፎቶ በአጥኚዋ፦ ማርዳ 01/08/2013ዓ.ም



ፎቶ በአጥኚዋ፦ጫጫቴ 01/08/2013ዓ.ም





ፎቶ በአጥኝዋ፦ ለድሆች የተሰጠ የእህል ስጦታ 01/04/2013 ዓ.ም፣ደ/ኤልያስ



ፎቶ፦ ህጻናት ለአዲስ ዓመት እንግጫ ጉንጉን ይዘው የሚያሳይ 01/01/2013ዓ.ም፣ደ/ኤልያስ



ፎቶ በአጥኚዋ፦ ለቤተክርስቲያን የእንግጫ ስጦታ 02/01/2013 ዓ.ም፣ደ/ኤልያስ



ፎቶ በአጥኚዋ፤ በደብረ ገነት ነብዩ ኤልያስ ቤተክርስትያን የምትገኝ የሙሽራ ደንጋይ 08/11/2013ዓ.ም፣ደ/ኤልያስ

## አባሪ 3፡- የጥናቱ መንደርደሪያ/መነሻ ጥያቄዎች

1. ስጦታ ማለት ምን ማለት ነው?
2. ስጦታ መቼ መቼ ይሰጣል?
3. እነደ ባህሉ ስጦታ ሲለዋወጡ ምላሽ ይጠበቃል?
4. ስጦታ ተቀባይ ስጦታውን እንዴት መቀበል አለበት?
5. ስጦታ በመስጠት ሂደት ውስጥ የሚደገፈው  እንዲሁም ነውር የሆነው ምንድን ነዉ?
6. ስጦታ ምን ጥቅም አለው?